አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# የኮንሶ ብሄረሰብ ቃላዊ ተረኮች

በ
ኃይለሚካኤል አረጋኸኝ

2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# የኹንስ ብሄረሰብ ቃላዊ ተረኮች

በ

ኃይለሚካኤል አረጋኸኝ

2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የኹንሶ ብሂረሰብ ቃላዊ ተረኮች

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ባይለየኝ ጣሰው (ዶ/ር)

በ

ኃይለሚካኤል አረጋኸኝ

ግንቦት 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# የኾንሶ ብሄረሰብ ቃላዊ ታሪኮች

በ

ኃይለሚካኤል አረጋኸኝ

ግንቦት 2005 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ

ባዬለየኝ ጣሰው.......................... ..................................

አማካሪ ፊርማ

አንቀጽን ሸጋለ.......................... ..................................

የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

መስፍን መሰለ.......................... ..................................

የውጭ ፈታኝ ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
I.L.S
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

# ምስጋና

በትድሚያ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው በማማከር፣ ጽሁፌን በማቃናትና አጋዥ መጻሕፍትን በማዋስ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉልኝ አማካሪዬን ዶ/ር ባይለየኝ ባሰውን አመሰግናለሁ።

ትምህርቴን እንድማር ድጋፍ ላደረገልኝ መስሪያ ቤቴ እና የጥናት ወጪዬን ለሸፈነልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ምስጋናዬን አደርሳለሁ።

ቀጥዬ ሁልጊዜም ከጎኔ በመሆን ሞራልና ብርታት ለምትሰጡኝ ውድ ባለቤቴ ወ/ሮ ዝናሽ ሞዲና ትንሿ ልዕልት ሀሴት ኃ/ሚካኤልን እጅግ አመሰግናለሁ። የውድ ባለቤቴ ድጋፍ ባይኖር ይህ ጥናት ከዳር መድረሱን አጠራጣሪ ያደርገው ነበር። «ሚጣዬም» በጥናቱ ምክንያት በመጠኑም ቢሆን የጨዋታሽን ጊዜ ተጋፍቻለሁና የምስጋና ድርሻሽ ከፍ ያለ ነው። ሁለታችሁም ተስፋዎቼና ብርታቶቼ ናችሁና ዘውትር ከጎኔ አይለያችሁ እንጂ ምን እላለሁ?

መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ ከመሄዴ በፊትና በመስክ ቆይታዬም ከጎኔ ሳይለዩ ከቦታ ቦታ እብረውኝ በመንከራተት ለጥናቱ ስኬት ደፋ ቀና ያሉት ቁልፍ መረጃ ሰጪዬ፣ አስተርጓሚዬ፣ የተከበሩ ዶ/ር ገዋዶ አይለዶ አብዝቼ አመሰግንዎታለሁ። እግዚአብሄር ጨምሮ ጨማምሮ ይስጥዎ።

እንዲሁም ሌሎች ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት፣ አቶ ኮራ ጋሪ፣ አቶ መምሩ ቆይራንቶ እና አቶ ጊሌዴ ባደናን በጣም አመሰግናለሁ። የጊዶሌ ጓደኞቼ ልዑልሰገድ ጥላሁን፣ የሺዋስ ተሰማ፣ ደመቀ መንግስትና ረዳት ሳጅን ኢሳያስ ወልዱም የምስጋናው ተጋሪ ናችሁ። በመስክ ቆይታዬ ከጎኔ በመሆን በረዳት አጥኚነትና በአስተርጓሚነት ከፍተኛ ድጋፍህን ላደረገልኝ ለኡርማሌ ሎውሌ እና ዲጂታል ካሜራዬ በመበሬት መጥፋት ምንንያት አገልግሎት መስጠት ባቆመችበት ጊዜ የግል ጀነሬተሩን በማስነሳት ስራዬ እንዳይቋረጥ ያደረገው የፎቶ ጆሲ ባለቤት ወጣት ዮሴፍም ሊትመሰገን ይገባል።

እናቴ ወ/ሮ ጥማዬነሽ ኃ/ማርያም፣ ወንድሞቼ መኳንንት ገ/መስቀልና ጌታሁን አረጋኸኝ እንዲሁም እህቴ ገበያነሽ ገ/መስቀል ለዚህ ጥናት በቀጥታም ሆነ በተዘዋሪ ድጋፍ አድርጋችኋልና እናንተም ትመሰገናላችሁ።

# ማውጫ


ምስጋና ....... i

ማውጫ ....... ii

የቁልፍ ቃላት መፍቻ ....... vi

የኾንሶ ወረዳ ካርታ ....... vii

አጠቃሎ ....... viii

ምዕራፍ አንድ ....... 1

መግቢያ ....... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ....... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....... 2

1.3. የምርምር ጥያቄዎች ....... 3

1.4. የጥናቱ ዓላማ ....... 3

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ....... 3

1.6. የጥናቱ ወሰን ....... 4

1.7. የመረጃ አሰባሰብ ....... 4

1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ....... 4

1.7.1.1. ቃለ መጠይቅ ....... 5

1.7.1.2. የቡድን ውይይት ....... 5

1.7.1.3. ምልከታ ....... 6

1.8. የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ ዘዴ ....... 6

1.8.1. የጥናቱ አተናተን ዘዴ ....... 7

1.9. በጥናቱ ሂደት የተገኙ ልምዶች ....... 8

ምዕራፍ ሁለት ....... 14

ክለሳ ድርሳን ....... 14

2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ....... 14

2.1.1. ቃላዊ ተረክ ....... 14

2.1.2. የቃላዊ ተረኮች ምደባ ....... 16

2.1.2.1. የኮንሶ ተረኮች አካባቢያዊ ምደባ ....18
2.1.2.1.1. ቶራ ....16
2.1.2.1.2. ቶሮታ ....16
2.1.3. አውዳዊ ትንተና (contextual Analysis) ....16
2.1.3.1. ባህላዊ አውድ ....16
2.1.3.1.1. የባህላዊ የአውድ ትርጉም (context of Meaning)........ 18
2.1.3.1.2. ተቋማዊ አውድ (Institutional context).... 18
2.1.3.1.3. የተግባቦታዊ ስርአት አውድ .... 19
2.1.3.2. ማህበራዊ አውድ ....19
2.1.3.2.1. ማህበራዊ መሰረት ....19
2.1.3.2.2. ገለሰባዊ አውድ ....20
2.1.3.2.3. ሁኔታዊ አውድ ....20
2.1.3.2.4. ተፈጥሮአዊ አውድ ....20
2.2. የተዛማች ጥናቶች ቅኝት ....21
ምዕራፍ ሶስት ....28
3. የኮንሶ ብሄረሰብ ማህባራዊ ዳራ ....28
3.1. የኮንሶ ብሄረሰብ ጥንተ አመጣጥና ቋንቋ ....28
3.2. የብሄረሰቡ ስያሜ ....29
3.3. መልከዓ ምድር ....29
3.4. ትውፊታዊ አስተዳደር ....31
3.4.1. ኬላ ....32
3.4.2. ሰንኬሊታ ....33
3.4.3. የሽማግሌዎች ምክር ቤት ....33
3.4.4. አባ ቲምባ ....34
3.4.5. ዳውራ ....34
3.4.6. የወንድ አዛውንቶች ቡድን ....35
3.5. ዘመናዊ አስተዳደር ....35
3.6. እምነት ....35

3.7. የኢኮኖሚ ሁኔታ ....................36

ምዕራፍ አራት ....................39

የቃላዊ ታሪኮች ትንተና ....................38

4.1. የብሄረሰቡን ጥንተ አፈጣጠርና አመጣጥ የሚተርኩ ....................38

4.2. ኮንሶና ባህላዊ አስተዳደር ....................41

4.2.1. (ፖቻላ) ቱማ ....................41

4.2.1.1. ፖቻላዎች፡ የኮንሶ ምድር ይገባኛል ጥያቄ ....................45

4.2.2. ቲምባ ....................47

4.2.3. ጻውራ (መሳያ) ....................49

4.2.4. የአገር ሽማግሌዎች ....................50

4.3. የኮንሶ እርከንና እደ ጥበብ ....................52

4.3.1. ኮንሶና የእርከን ስራ ....................53

4.3.2. ኮንሶና ሞራ ....................53

4.3.3. ኮንሶና ዋካ ....................55

4.4. ኮንሶዎችና ምንጮቻቸው ....................57

4.4.1. ኮንሶዎችና የውሀ መናፍስት ....................57

4.5. ከቦታዎች፣ አካባቢያዊ ስያሜዎችና ከነገሮች አመጣጥ ጋር ተያይዘው የሚተረኩ ....................60

4.5.1. የ(የኒዮርክ) አፈጣጠር ....................60

4.5.2. የአለኮ ዛፍ ማጠርና የሴቶች የወር አበባ ....................61

4.5.3. ቢቃውሌ ....................63

4.6. ኮንሶና ጋብቻ ....................64

4.6.1. ያላቻ ጋብቻ በኮንሶ ተራዎች ....................66

4.7. ኮንሶ ጦርነት እና አደን ....................67

4.7.1. ኮንሶና ከምኒልክ ጦር ጋር የተረገ ጦርነት ....................67

4.7.2. ኮንሶና አደን ....................68

4.8. ግብረ ገብ ተራዎችና ተረታዎች ....................69

4.8.1. ሌብነትን የሚኮንኑ ....................69

4.8.2. ብልጠት በኽንሶ ቶራ ውስጥ .......... 71

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ .......... 73

5.1. ግኝት .......... 73

5.2. የግኝቱ አንደምታዊ ጠቀሜታ .......... 74

ዋቢ ጽሁፎች .......... 75

አባሪዎች .......... i

አባሪ አንድ፣ የቶራና ቶሮታዎች ስብስብ .......... i

አባሪ ሁለት፣ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር .......... ii

አባሪ ሦስት፣ የፎቶግራፎች ዝርዝር .......... iii

# የቁልፍ ቃላት መፍቻ

| | |
|---|---|
| ኻውዳ | የኾንሶ የእደ ጥበብ ባለሙያ |
| ኤታንታ | በግብርና ሙያ የሚተዳደር |
| ፖችላ | የኾንሶ ባህላዊ መሪ፣ መንፈስ እንዳለባቸው የሚታመን |
| ቲምባ | እንደ ህግ የሚታይ ከበሮ ሲሆን ለጭፈራና ባህላዊ መሪ ሲሞት ለለቅሶ ይውላል። |
| ቱማ | ባህላዊ መሪው በእጁ ላይ የሚያደርገው ከንጹህ ብር የሚሰራ ጠፍጣፋ አምባር ነው። |
| ሙሊጋ | ከመዳብ የሚሰራ ምክትል የጎሳ አለቆች የሚያደርጉት አምባር |
| ጨኪቃ | ከማሽላ፣ ከበቆሎና አልፎ አልፎ ከስንዴ ዱቄት የሚሰራ ባህላዊ መጠጥ (ቦርዴ) የሚመስል |
| ፖሳንታ | ከዘጠኙ የኾንሶ ጎሳዎች ውስጥ አንዱ ነው። |
| አባ ቲምባ | በማህበረሰቡ ውስጥ ተሰሚነት ያላቸው በከበሮው ማህበረሰቡን በየተራ የሚያስተዳድሩ ሰዎች |
| ሞራ | የህዝብ መሰብሰቢያና ማረፊያ ቦታ |
| ሳራ | የባህላዊው መሪ አማካሪ |
| ናማ ዱዋራ | በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ተሰሚነት ያላቸውና የሚፈሩ ሰዎች |
| ኢላ | የውሀ ውስጥ መናፍስት |
| ኒዮርከ | ጋስርጊዮ በሚባል አካባቢ የሚገኝ መልክዓ ምድር |
| አለኮ (ሽፈሬ) | ለምግብነት የሚውል የዛፍ ቅጠል |
| ኩርኩፋ | ከስንዴ፣ ከበቆሎና ከማሽላ ዱቄት የሚዘጋጅ ባህላዊ ምግብ |
| ዋካ | ከእንጨትና ከድንጋይ ተጠርቦ የሚሰራ የመቃብር ላይ ምልክት |
| ፎራ | ከብቶች የሚግጡት ጨዋማ በሀ አፈር |
| ሙከላ | ምክትል ባህላዊ መሪዎች የሚያደረጉት አምባር |
| ኪኬሻ | ድርብርብ ክዳን ያለው ሞራ |
| ካዎታ | በኾንሶ መንደሮች ዙሪያ የሚገኝ የድንጋይ ካብ |
| ካቢታ | የውሀ ምንጮች ዙሪያ የሚገኝ ካብ |
| ካላ | ለኪርቲታ ጎሳ መጠሪያነት የሚሰጥ የማዕረግ ስም |
| ብርጃ | ከኻውዳዎች መካከል ከብት በማረድና ስጋ በመሸጥ የሚተዳደር |

# የኮንሶ ወረዳ ካርታ




ምንጭ :- ከኮንሶ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የኾንሶ ብሄረሰብ ቃላዊ ተረኮች ላይ የተካሄደ ነው። ለጥናቱ አጋዥ መረጃዎችን ከቤተመፃህፍ እና ከመስክ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ተሰብስቧል። በመረጃ ሰጪነት 14 ሰዎች እንዲሳተፉ የተደረገ ሲሆን፣ ስምንቱ ቁልፍ እና ስድስቱ ደግሞ ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች ናቸው። በቁልፍ መረጃ አቀባይነት የተመረጡት የብሄረሰቡን ቃላዊ ተረኮች በሚገባ የሚያውቁ እንዲሁም ተሳትፎአቸውም ከፍ ያለውን ነው። ከእነዚህ ውስጥ የብሄረሰቡ ተወካይ፣ ብሄረሰቡን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በመጻፍ ለንባብ ያበቁና በወረዳው ከሚገኙ ዘጠኝ ጎሳዎች የእንዱ የጎሳ መሪ ይገኙበታል። ቁልፍ እና ቁልፍ ካልሆኑ መረጃ አቀባዮች በመምረጥ በቡድን ውይይት መረጃ ተሰብስቧል። መረጃዎችንም በመቅረፀ ድምጽና በፎቶ ግራፍ እንዲሁም በማስታወሻ ለመያዝ ተችሏል። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆነ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ተደርጓል፣ በተዛማጅ ስራዎ ቅኝትም ከጥናቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው አስራ ሦስት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ስራዎች ተቃኝተዋል። ከመስክ የተሰበሰቡት ቃላዊ ተረኮች በአካባቢያዊ ምደባቸው መሰረት በሁለት ተመድበዋል። ጥናቱ የተከተለው ገላጭ የምርምር ዘዴን ሲሆን መረጃዎቹንም አውዳዊ ትንተና (contextual Analysis) ንድፈ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ተንትኗል።

በጥናቱም ሰባ ቃላዊ ተረኮች የተሰበሰቡ ሲሆን፣ ተረኮቹ በዋናነት የሚያተኩሩት በብሄረሰቡ ጥንተ አፈጣጠርና አመጣጥ፣ ስያሜ፣ በባህላዊ አስተዳደሮችና በስራቸው በሚገኙ ተሰሚነት ያላቸው የብሄሰቡ አባላት ሚና፣ እምነት፣ ከምንጮች ጋር ስላላቸው ተሳስሮ፣ የጥበብ ስራ፣ ጋብቻ፣ ርግማን፣ በስናይና በእኩይ ስነ ምግባሮች ላይ ነው። እነዚህን ተረኮች በየወገናቸው በማስቀመጥ በምን አውድ እንደሚነገሩና ያላቸውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማሳየት ተችሏል። በጥናቱ ውጤት መሰረት ቃላዊ ተረኮቹ ብሄረሰቡ እንዴት እንደመጣና እንደተፈጠረ፣ ስያሜውን ከየት እንዳገኘ፣ የባህላዊ መሪዎቹን ሚና፣ ከምንጮችና ኩሬዎች ጋር ያለው ትስስር፣ የእደ ጥበብ ስራ እና ተረኮቹ ያላቸው ተስተላፎ ምን እንደሚመስል አሳይተዋል። ቃላዊ ተረኮቹ የብሄረሰቡ አባላት አንድነታቸውን ሳይናጋ እንዴት እንዳስጠበቁና በአንድ አካባቢ እንዴት ጸንተው እንደኖሩ በመረዳት በታሪካቸው እንዲኩሩ፣ እነዚህን ቃላዊ ታረኮች በመጠበቅ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ እንደቻሉ ለማሳየት ተችሏል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ማንኛውም ማህበረሰብ «የራሴ» የሚለው ታሪክ፣ ባህል እና፣ ቋንቋ አለው። በዚህ ማህበራዊ እሴቱ አማካኝነትም ማንነቱን ይገልጽበታል፤ ህልውናውን ያስጠብቅበታል፤ አመለካከቱን እንዲሁም የህይወት ፍልስፍናውን ያንፀባርቃል። ይህ ጥናት የኾንሶ ብሄረሰብ ቃላዊ ተረኮች ከሚገቡበት ማህበራዊና ባህላዊ ዓውድ አኳያ በማጥናት ተረኮቹ ያላቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊያ ጠቀሜታ ማሳየት ነው። ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተደራጀ ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ ንድፈ ትልሙን፣ ምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳን ንድፈ ሀሳባዊና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በሚል በሁለት ክፍሎች ቀርቧል። በንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ስር የቃላዊ ተረኮች ብያኔ፣ ባህላዊ አከፋፈልና እና የአውዳዊ ትንተና (contextual Analysis) ምንነትና ተግባርን በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የተነሱ ልዩ ልዩ ንድፈ ሀሳቦች ቀርበዋል። የኾንሶ የቃላዊ ተረኮች በአካባቢያዊ ምደባ መሰረት በሁለት በመመደብ ቀርቧል። የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር የሚቀራረቡ ጥናቶች ዳሰሳን የሚገልጽ ነው። ሶስተኛው ምዕራፍ የማህበረሰቡን ጥንተ አመጣጥ ታሪክ፣ መልካምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንበረት፣ ስለ ባህላዊ አስተዳደሮችና መሪዎች እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን አካቷል። በምዕራፍ አራት የኾንሶ ብሄረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን አውዳዊ ትንተና (contextual Analysis)ን መሰረት በማድረግ በመተንተን ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ፣ ተረኮቹ የቀረቡበትን አውድ እና በብሄረሰቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ትርጉም የታየበት ነው። በመጨረሻው ምዕራፍ አምስት ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያ ውስጥ ግኝቶች፣ የግኝቱ አንደምታዊ ጠቀሜታ፣ የዋቢ ፅሁፎች ዝርዝር እና አባሪዎች የሰፈሩበት ነው።

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቃላዊ ዝርው ተረኮች የአንድን ማህበረሰብ ህይወት ከማንፀባረቃቸው ባሻገርም ልዩ ልዩ ማህበራዊ ፋይዳዎች አላቸው። ከእነዚህም ውስጥ ማስተማር፣ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ተቋማትን ምንነትና የሚገኙበትን ይዞታ መግለፅ፣ የማህበራዊ ልማዶች አመጣጥ ታሪክ መግለፅና ሌሎችም ተግባራት እንዳሏቸው ፊኔጋን (1970)፣ oring (1985) እና ፈቃደ (1991) ይገልፃሉ። በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የሚተረኩ ተረኮች የሚነገሩባቸው ዓላማዎችና የሚሰጧቸው ግልጋሎቶች እንዳሉም ይጠቁማሉ።

እነዚህ የማህበረሰቡ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በአንድ ማህበረሰብ አባላት መካከል የእርስ በርስ ትስስር እንዲኖር የሚያደርጉ ወይም የማህበረሰቡ አባላት በአንድ ገዥ በሆነ አስተሳሰብ ጥላ ስር እንዲገኙ የሚያስችሉ ናቸው ማለት ይቻላል። የኹንሶ ብሄረሰብም የራሱ ቃላዊ ተረኮች አሉት። በዚህ ጥናት እነዚህ ተረኮች ከሚገቡበት ባህላዊና ማህበራዊ ዓውድ አንጻር በመመርመር ምን አይነት ትርጉም እንዳላቸው እና ለማህበረሰቡ የሚኖራቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ማሳየት ይሆናል።

## 1.2. የጥናቱ እነሳሽ ምክንያት

የኹንሶ ብሄረሰብ ባለው የመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ በእርከን ስራ፣ በባህላዊ አምባ መንደራት፣ በካብ አጥር አሰራሩና በስነሰብዕ መካነ ጥናት መገኛነት እንዲሁም በልዩ ልዩ የጥበብ ስራዎች በአገር አቀፍም ሆነ በአለም ዘንድ የታወቀ ነው። በቅርቡም ብሄረሰቡ ለረዥም አመታት ባከናወነው የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠባበቅ ስራ በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ እውቅና በማግኘቱ አገራችን በዩኔስኮ ዘጠነኛውን ቅርስ አስመዝግባለች። የብሄረሰቡ አባላት በጣም ታታሪዎች፣ ለአካባቢያቸውና ለባህላቸው ተቆርቋሪና ከፍተኛ ግምት የሚሰጡ ናቸው። ይህንንም በኹንሶ አጎራባች በሆነችው ዲራሼ ወረዳ ረዘም ላሉ ጊዜያት በመምህርነት ስሰራ በነበረበት ወቅት ለመረዳት ከመቻሌም በላይ በእጅጉ እደነቅ ነበር። ስለ ብሄረሰቡ የሚነገሩ ቃላዊ ተረኮችንም እሰማ ነበር።

ሁልጊዜም እነዚህ ቃላዊ ተረኮች ለብሄረሰቡ ጥንካሬ፣ ለባህልና ቅርሶቹ ጥበቃ እንዲሁም ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወቱ ምን አይነት አስተዋጽኦ አበርክተው ይሆን፣ የሚል ጥያቄ በውስጤ ይመላለስ ነበር። ከአካባቢው ብርቅም ስለአካባቢው አልፎ አልፎም ማሰላሰሌ አልቀረም ነበር። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ማሟያ የሚሆን ርዕስ እንዳዘጋጅ ስጠየቅ ትውስታው ከውስጤ አልጠፋምና በዚህ ርዕስ ላይ እንድሰራ በውስጤ ሀሳብ አጫረብኝ። ይሁን እንጂ ባሰብኩት ርዕስ ላይ ከዚህ ቀደም የተሰራ ጥናት መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ነበረብኝ። በመሆኑም ብሄረሰቡን በሚመለከት በታሪክና በማህበረሰብ ጥናት የትምህርት ክፍሎች ስለ ማህበረሰቡ ባህላዊ አስተዳደር፣ መልክአ ምድር፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ላይ ከተረቡ ጥቂት ጥናቶች በስተቀር በመረጥኩት ርዕስ ላይ የተሰራ ጥናት ያላጋጠመኝ መሆኑና የመምህሬ የአቶ ዘሪሁን አስፋው ምክር በርዕሱ ላይ እንድሰራ ገፋፍቶኛል።

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

የጥናቱን ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ጥያቄዎች ይመለሳሉ።

- የኾንሶ ብሄረሰብ «የኔ ናቸው።» ብሎ የሚጠቅሳቸው ዝርው ቃላዊ ተረኮች የትኞቹ ናቸው?
- ቃላዊ ተረኮቹ በምን አይነት ማህበራዊና ባህላዊ አውድ ይነገራሉ? ከጥንተ አፈጣጠሩና ታሪካዊ አመጣጡ ጋር ምን አይነት ተዛምዶ አላቸው?
- ቃላዊ ተረኮቹ ከሚገቡበት አውድ አንፃር የብሄረሰቡን ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ህይወት እንዴት ተገልጿል?
- የቃላዊ ተረኮች መተረኪያ ዋነኛ ጉዳይ ምንድን ነው?
- ብሄረሰቡ ቃላዊ ተረኮቹን ለቀጣዩ ትውልድ ለምን ዓላማ ሲል ያስተላልፋቸዋል?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የኾንሶ ብሄረሰብ ቃላዊ ተረኮች ከሚገቡበት ማህበራዊና ባህላዊ አውድ አንጻር በመመርመር ያላቸውን ፋይዳ ማሳየት ሲሆን፣ ጥናቱ ከዚህ ዋና ዓላማ የተቀዱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችም ይኖሩታል።

- የኾንሶ ብሄረሰብ «የእኔ ናቸው፤ ይገልጹኛል።» ብሎ የሚጠቅሳቸውን ተረኮችን ማሳየት፣
- ቃላዊ ተረኮቹ ከሚገቡበት ማህበራዊና በባህላዊ አውድ መሰረት ያላቸውን ፍቺ እና
- ቃላዊ ተረኮቹ በምን አይነት መንገድ ሳይጠፉ ለቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ እንደቻሉ ማሳየት ነው።

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ እንዲመልሳቸው ከተቀመጡት ጥያቄዎችና ዓላማ አንጻር የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

- በማህበረሰቡ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ትኩረቱን አድርጎ ለሚያጠና የፎክሎር ተመራማሪ ቀጥተኛ የሆነ የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል።

- ለኸንሶ ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት፣ ለኸንሶ ባህላዊ ማዕከል እንዲሁም መንግስታዊ ለሆኑና ላልሆኑ አካላት የመረጃ ግብአት ሆኖ ያገለግላል።
- በመጨረሻም የማህበረሰቡን ማንነት፣ አመለካከትና እምነት ለማወቅ ለሚፈልግ አንባቢ ግንዛቤ ያስጨብጣል።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

በጥናቱ የተካተቱት ተረኮችም ማህበረሰቡ «እንዲህ ነን፤ እንዲህ ነበርን፤ እንዲህ ይደረጋል፤ እንዲህ ተብሎ ይታመናል።» ብሎ ያመነባቸውን ብቻ ናቸው።

ሌላው የኸንሶ ብሄረሰብ በ43 ቀበሌዎችና በአካባቢው ባሉ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖር ህዝብ ነው። ስለሆነም ባለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት ምክንያት በሁሉም ቀበሌዎች ተዟዙሮ መረጃ ለመሰብሰብ የሚቻል ባለመሆኑ መረጃ የተሰበሰበው ነባር ህዝቦች ይኖሩበታል ተብለው በተመረጡ በዱካቱ፣ በፋሻ፣ በኮልሜ፣ በዱራይቴ መንደሮችና እና በዋና ከተማዋ ካራት ብቻ ነው።

## 1.7. የመረጃ አሰባሰብ

ለዚህ ጥናት በግብአትነት የሚያገለግለው መረጃ ቃላዊ ተረኮች ናቸው። በዚሁ መሰረት በመስክ ቆይታ ወቅት 70 የኸንሶ ቃላዊ ተረኮችን ለማሰባሰብ ተችሏል።

### 1.7.1.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ጥናቱ ይዞ የተነሳውን ዓላማ ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን በአግባቡ ለመመለስ ያስችል ዘንድ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች በጥቅም ላይ ውለዋል። በካልዓይ የመረጃ ምንጮች ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናቶች፣ የታተሙና ያልታተሙ ፅሁፎች ከቤተመፃህፍት እንዲሁም ከኢንተርኔት ተሰብስበው ጥቅም ላይ ውለዋል።

ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ በቀጥታ ከመስክ የተሰበሰቡ ናቸው። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ እነዚህ መረጃዎች የተገኙት በዋናነት በቃለመጠይቅ (Interview) እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት (Focus Group Discussion) ነው። የመስክ ምልከታ (Observation) ተደርጓል።

### 1.7.1.1. ቃለመጠይቅ

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለው ዘዴ ቃለመጠይቅ ነው። ይህንን ዘዴ ለመጠቀም ያስፈለገበት ዋንኛ አላማ ሰዎች ያለምንም ገደብ በነጻነት ሀሳባቸውን እንዲገልጹና በዚህም ሂደት ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ሲባል ነው። በዚህ ዘዴ በወረዳው ልዩ ልዩ መንደሮች የሚኖሩና የማህበረሰቡን ቃላዊ ተረኮች በሚገባ ያውቃሉ የተባሉ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችን በመምረጥ፣ ቀጠሮ በማስያዝ እንዲሁም ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ቃለመጠይቅ ተካሂዷል። በቃለ መጠይቁ መካከልም ከጉዳዩ ጋር የሚያያዙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማንሳት መረጃውን ለማጠናከር ተችሏል። የተዘጋጁት ጥያቄዎች ሁለት አይነት ናቸው። የመጀመሪያው ክፍት (open-ended questions) ሲሆን፣ ሁለተኛው ዝግ (closed-ended questions) ናቸው።

በመጀመሪያው አይነት የጥያቄ አቀራረብ ስልት መረጃ አቀባዩ ያለምንም ገደብ በነፃነት መረጃውን እንዲሰጥ በማሰብ የተዘጋጀ ነው። በሁለተኛው የመጠይቅ አይነት ደግሞ መረጃ አቀባዩ ባልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይሄድ ተፈላጊውን መረጃ ብቻ እንዲሰጥ በማሰብ የተዘጋጀ ነው። በእነዚህም ስልቶች ከስምንት ቁልፍ እና ከስድስት ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥና ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ሲባልም ከመደበኛው ቃለ መጠይቅ በተጨማሪ ኢመደበኛ ቃለመጠይቅ በማድረግና የቡድን ውይይት በማካሄድ መረጃዎች ተጠናቅረዋል።

### 1.7.1.2. የቡድን ውይይት

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሳይነሱ የታለፉ አዳዲስ መረጃዎች ለማግኘት፣ በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ይበልጥ ለመረዳትና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ በሁለት የተለያዩ መንደሮች ላይ አምስትና አራት መረጃ ሰጪዎች ያሉበት የቡድን ውይይት ተካሂዷል። በቡድን ውይይቱ ከተሳተፉት ውስጥ ስድስቱ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ቁልፍ ያልሆኑ የመረጃ አቀባዮች ናቸው። በቡድን ውይይት የተገኙት ብዙዎቹ መረጃዎች ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ከሰጡኝ መረጃዎች ጋር የሚመሳሰሉና ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው። ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች ተገኝተውበታል። መረጃዎቹንም በመቅረጸ ድምጽ እና በዲጂታል ካሜራ በመቅረጽ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

#### 1.7.1.3. ምልከታ

በዚህ ጥናት የተወሰነ ምልከታ ለማድረግ ተሞክሯል። ምልከታውንም ያካሄድኩት በኢተሳትፎ (Non participant) ሲሆን፣ በምልከታውም የማህበረሰቡን የአኗኗር ስርአት፣ የማህበረሰቡን የስራ ባህል፣ የእርስ በእርስ ግንኙነትና ማህበራዊ መስተጋብሮችን ለመረዳት ጥረት ተደርጓል። ይህንንም በፎቶ ካሜራና በማስታወሻ በሚገባ አደራጅቶ ለመያዝ ተችሏል። በምልከታ የተገኙ ልምዶችም ለተረኮቹ ትንተና ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል።

ቃላዊ ዝርው ታሪኮቹ የሚነገሩት በሞራዎች (በህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች) በልዩ ልዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ማለትም በለቅሶ፣ በሰርግና መሰል ጉዳዮች ላይ ነው። ይሁን እንጂ በመስክ ቆይታ ወቅት ሁሉንም ማህበራዊ አጋጣሚዎች ማግኘት አልተቻለም። Goldstein (1974:80-90) እና ፈቃደ (1991፣122-124) በፎክሎር ጥናት መረጃዎችን ከመስክ ለመሰብሰብ ተፈጥሯዊ (Natural Setting)፣ ቅንብር ተፈጥሯዊ (Induced Natural Setting) እና አርቲፊሻል መቼቶች (Artificial Setting) በመጠቀም እንደሚቻል ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ ከአንድ ቦታ በስተቀር ተፈጥሮአዊ መቼት አልገጠመኝም። ስለሆነም አብዛኛዎቹ ቃላዊ ተረኮች የተሰበሰቡት በሁለቱ መቼቶች ነው።

## 1.8. የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ ዘዴ

ሁነኛ መረጃን ለማግኘት መረጃው የሚሰበሰብበትን ማህበረሰብ ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ቢቻል የማህበረሰቡ አባልና ለረጅም ዘመን በማህበረሰቡ ውስጥ የኖረ፣ እንዲሁም በቂ የህይወት ልምድ ያለው መረጃ ሰጪ ማግኘት ተመራጭ ነው። ስለሆነም ለዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ በቅድሚያ የተደረገው በወረዳው የቀድሞ የባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሀላፊ ከነበሩት ከአቶ ኡርማሌ ሎውሌ እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የማህበረሰቡ ተወካይ ከሁኑት ከዶ/ር ገዋዶ አይለዶ ጋር በመሆን ከማህበረሰቡ አባላት ውስጥ ስለማህበረሰቡ አጠቃላይ ሁኔታ በቂ እውቀት አላቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን ሰዎች ዝርዝር በመያዝ የመረጃ ሰጪ ናሙና አመራረጥ ስራው ሊከናወን ችሏል። በመረጃ አሰባሰብ ሂደት በቁልፍ መረጃ ሰጪነት ከተጠቆሙት ውስጥ አንዱ ሊገኙ ባለመቻላቸው፣ አንዱ ደግሞ ተሳትፏቸው በጣም አናሳ ሆኖ በመገኘቱ ከቁልፍ መረጃ ሰጪነት ወደ መረጃ ሰጪነት እንዲዘዋወሩ ተደርጓል። ዶ/ር ገዋዶ አይለዶን ጨምሮ አንድ መረጃ ሰጪ

በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ባደረጉት ከፍተኛ ተሳትፎ አማካኝነት ቁልፍ መረጃ ሰጪ ሆነዋል።

የተመረጡት ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በእድሜ፣ በትምህርት ደረጃ፣ በስራ፣ በኢኮኖሚ እንዲሁም ብሄረሰቡ ውስጥ ባላቸው ማህበራዊ ደረጃና ተቀባይነት መሰረት ሁሉንም አካላት እንዲያካትት ተደርጎ ነው። ከቁልፍ መረጃ ሰጪዎቹ አንዱ ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት በብሄረሰቡ ካሉት ዘጠኝ ጎሳዎች ውስጥ የኬርቲታ ጎሳ ባህላዊ መሪ (ፖትላ) ሲሆኑ፣ ሁለተኛው ቁልፍ መረጃ አቀባይ በብሄረሰቡ ላይ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በእንግሊዝኛ፣ በአማርኛና በአፋ ኾንሶ ለህትመት ያበቁ በቂ ትምህርት እና ልምድ ያላቸው ናቸው። ሶስተኛው ቁልፍ መረጃ አቀባይ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የማህበረሰቡ ተወካይ ናቸው። እነዚህ መረጃ አቀባዮች በብሄረሰቡ ውስጥ በሚገባ የሚታወቁና ትልቅ ክበሬታ የሚሰጣቸው፣ የትምህርት ዝግጅታቸውም ከዲፕሎማ እስከ ሁለተኛ ዲግሪ መሆኑን በመስክ ምልከታ ወቅት አረጋግጫለሁ። ቀሪዎቹ 5 ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ደግሞ ከየመንደሩ የተመረጡና በብሄረሰቡ ዘንድ በአገር ሽማግሌነት የሚታወቁ ናቸው።

ሌሎቹ ቁልፍና ቁልፍ ያልሆኑ የመረጃ አቀባዮች በእድሜ ደረጃቸው ሲታዩ አዛውንት እና በጎልማሳ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን፣ የትምህርት ደረጃቸው ደግሞ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ፣ ምንም ትምህርት የሌላቸው በማለት ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው። ባላቸው ማህበራዊ ደረጃ ሲታዩ ደግሞ ማህበረሰቡ ውስጥ በሚከሰቱ ግጭቶችም ይሁን በሚፈጠሩ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በሽምግልና የሚያገለግሉና ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው አዛውንቶች የተካተቱበት ነው። የአብዛኞቹ መተዳደሪያ ግብርናና አልፎ አልፎም ንግድ ነው። ያለምንም ስራ በልጆቻቸውና በቤተሰቦቻቸው የሚጦሩ መረጃ አቀባዮች በርከት ይላሉ።

በኾንሶ ባህል መሰረት ብሄረሰቡን የሚመለከቱ ትረካዎች የሚቀርቡት በአዛውንቶች ነው። በዚህ ምክንያትም ከአንድ ሰው በስተቀር ሴት መረጃ ሰጪዎችን ለማግኘት አልተቻለም።

1.8.1.የጥናቱ አተናተን ዘዴ

በቅድሚያ ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከመስክ የተሰበሰቡት 70 ተረኮች ከመቅረጸ ድምጽ እና ከማስታወሻ ወደ ጽሁፍ እንዲሰፍሩ ተደርጓል። ከዚያም ተረኮቹ በብሄረሰቡ ባህላዊ እከፋፈል መሰረት በሁለት ክፍሎች ተመድበዋል።

ለጥናቱ የተመረጠው ዘዴ ገላጭ የምርምር ስልት ሲሆን፣ መረጃዎቹን ለመተንተን አውዳዊ ትንተና (contextual Analysis) ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። ንድፈ ሀሳቡ የተመረጠበት ምክንያት የቃላዊ ተረኮች ትክክለኛ ፍቺና አገልግሎት የሚታወቀው ተረኮቹ ከሚቀርቡበት ማህበራዊ እና ባህላዊ አውድ መሰረት በመሆኑ ነው። በዚህም መሰረት ከተሰበሰቡት ቃላዊ ተረኮች ውስጥ 29 ባህላዊ አመዳደባቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በብሄረሰቡ ማንነት ላይ ተመስርተው በቀረቡ ዋና ዋና ርዕስ ጉዳዮች በመመደብ ተረኮቹ ከገቡበት ማህበራዊ እና ባህላዊ አውድ መሰረት ትንተና ማድረግ ነው።

## 1.9. በጥናቱ ሂደት የተገኙ ልምዶች

በኾንሶ ባደረግሁት የመስክ ምርምር በጣም የተደሰትኩበትና ትልቅ ልምድ ያገኘሁበት ነው። ከመስክ ጉዞ በፊት በመስክ ምን ምን ተግባራት እንደሚከናወኑ፣ የሚያጋጥሙ ችግሮን እና ለእነዚህ ችግሮች ምን አይነት መፍትሄ መከተል እንደሚጠቅም ቀደም ብሎ በማቀድና ስልት ተቀይሷል። ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ስለ ኾንሶ ብሄረሰብ ማንነት፣ ታሪክ፣ ባህልና መሰል ጉዳዮችን ከካልዓይ ምንጮች ማለትም ከቤተ መጽሀፍ እና ከኢንተርኔት ሰብስቢአለሁ። ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ቃለ መጠይቆችም ተዘጋጅተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ከአንዳንድ የብሄረሰቡ አባላት ጋር በመወያየት ጥሩ የሆነ ቅድመ መረጃ ለማግኘት ጥረት ተደርጓል። ሌላው የመስክ ስራውን በአግባቡ ለማከናይድ እንዲያመች አስፈላጊ የሆኑ እንደ ፎቶ ካሜራ፣ መቅረጸ ድምጽ እና የጽህፈት መሳሪያዎች ቀደም ብሎ ተዘጋጅተው ነበር።

ይህም ሆኖ አልፎ አልፎ ችግሮች ማጋጠማቸው አልቀረም። አጠቃላይ ሂደቱ ምን እንደሚመስል ማሳየቱ ጠቃሚ ስለሚሆን የመስክ ሂደቱን እንደሚከተለው በዝርዝር አቀርባለሁ።

ቅድመ መስክ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ መስከረም 10 ቀን 2005 ዓ.ም ጉዞዬን ከአዲስ አበባ ስጀምር ወቅቱ የመስቀል በዓል መዳረሻ ስለነበር በተለይ ወደ ጨንቻና አርባምንጭ በአልን ለማክበር የሚጓዘው የአገሬው ተወላጅ እጅግ በርካታ ነበር። በዚህ ምክንያት ከአዲስ አበባ ወደ አርባምንጭ ቀጥታ ትራንስፖርት ለማግኘት አልተቻለም ነበር። ከብዙ ጥረት በኋላ ከአዲስ አበባ-ሆሳዕና፣ ከሆሳዕና-ወላይታ ሶዶ፣ ከወላይታ ሶዶ- አርባ ምንጭ በማቆራረጥ አርባ ምንጭ ከተማ ደረስኩ። በማግስቱ መስከረም 11

ቀን 2005 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12:00 ሰዓት በመነሳት ቀድሞ እሰራባት ወደ ነበረችው እና ጥናቱን ወደሚካሄድባት አጎራባች ወረዳ ወደ ዲራሼ አቀናሁ። እለቱን ከቀድሞ ጓደኞቼ ጋር ስጫወት አድሬ በማግስቱ መስከረም 12 ቀን 2005 ዓ.ም. በጓደኞቼ በአቶ ደመቀ መንግስት፣ በአቶ ልዑልሰገድ ጥላሁን፣ በአቶ የሺዋስ ተሰማ እና በረዳት ሳጅን ኢሳያስ ወልዱ ሽኝነት ወደ ኾንሶ ተጓዝኩ። ከቀኑ 07:20 ገደማም ከአዲስ አበባ በ595 ኪ.ሜ.፣ ከክልሉ ርዕሰ ከተማ አዋሳ ደግሞ 361 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ከምትገኘው የኾንሶ ወረዳ ዋና ከተማ ካራት ደረስኩ። ለስራዬ አመቺና ከጫጫታ ነጻ የሆነ መኝታ አፈላልጌ አገኘሁ። ይህንን ረጅም መንገድ ከላይ እንደገለጽኩት አቆራርጬ በመምጣቴ ምክንያት ከፍተኛ ድካም ይታይብኝ ስለነበር በዚህ እለት ከማረፍ በስተቀር ምንም አይነት ስራ አልሰራሁም።

መስከረም 13 ቀን 2005 ዓ.ም. ከአቶ ኡርማሌ ጮውሌና ከዶ/ር ገዋዶ አይላዶ ጋር በመገናኘት መረጃዎችን ከየት ቦታዎች እንደምሰበስብ፣ በቁልፍ መረጃ አቀባይነት የሚተባበሩኝን ሰዎች ዝርዝር እንዲሁም የስራ እቅድና መርሀ ግብር አዘጋጀን። በቀጣዩ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም. ከአቶ ኡርማሌ ጮውሌ ጋር በዱካቱ መንደር መረጃዎችን መሰብሰብ እንደምጀምር ተቀጣጥረን ተለያየን። ከሰዓት በኋላ ወደ ወረዳው የባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት በማምራት የጥናቱን አላማ በማስረዳት የትምህርት ክፍሌ የጻፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ ግልባጭ አስረከብኩ። የጽ/ቤቱ ሀላፊ አቶ ገረመው በወረዳዋ የተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወርኩ ያለ እንከን መረጃዎችን እንድሰበስብ ለምሄድባቸው አካባቢዎች የድጋፍ ደብዳቤ እንደሚጽፉልኝ ገለጹልኝ፤ እኔም አመስግኜ ወደ ማረፊያዬ ሄድኩ። ለቀጣዩ ቀን ስራ ዝግጅት ሳደርግ አመሸሁ።

መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም ጠዋት ከረዳቴ ከአቶ ኡርማሌ ጮውሌ ጋር በመሆን ወደ ዱካቱ አመራን። የመጀመሪያ የመረጃ መሰብሰብ ስራዬን በብሄረሰቡ ታሪክና ባህል ላይ ልዩ ልዩ የጽሁፍ ስራዎችን ካከናወኑት ከአቶ ኮራ ጋራ መኖሪያ ቤት በመሄድ ከእሳቸውና በአካባቢው ትልቅ ተቀባይነት ካላቸው ከአቶ ገልሲሞ ዱኖቴ በሁለት ቀናት ቆይታ በቃለ መጠይቅና በውይይት ልዩ መረጃዎችን ሰበሰብኩ፤ አቶ ኮራ ጋራ ተግባቢ እና ጥሩ የአማርኛ፣ እንግሊዝኛና ኾንስኛ ተናጋሪ ስለነበሩ ለመረጃ አሰባሰቡ ስራ ረዳትና አስተርጓሚ ባለሙያ ሳያስፈልገኝ መረጃዎችን ልሰበስብ ችያለሁ።

በመስከረም 16 ቀን 2005 ዓ.ም. መረጃ ከምሰበስብባቸው ፋሻና ኮልሜ ቦታዎች ከመሄዴ በፊት በምንቀሳቀስባቸው ቦታዎች ሁሉ ችግር እንዳይገጥመኝና ማህበረሰቡ

ተገቢውን ትብብር እንዲያደርግልኝ የወረዳው ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የትብብር ደብዳቤ እንደሚጽፍልኝ ቃል በገባልኝ መሰረት የትብብር ደብዳቤውን በእለቱ ወሰድኩ። ከዚያም ቦታዎቹ አሌጋ ከያዝኩባት ዋና ከተማ ካራት ከ9 እስከ 13 ኪ.ሜ. ይርቁ ነበርና የወረዳው አስተዳድር ወደ ቦታዎቹ የሚያደርሰኝ የሞተር ሳይክል ትትብር እንዲደረግልኝ ለመጠየቅ ወደ ካራት ማዘጋጃ ቤት አመራሁ፤ ይሁን እንጂ የወረዳው አስተዳደሪ ስብሰባ ላይ ስለነበሩ ለማግኘት አልቻልኩም። ከሰዓት በኋላ በድጋሚ ሄድኩ የወረዳው አስተዳደሪ የሆኑት አቶ በራቶ በላቸው እንደ አጋጣሚ በጊዶሌ 2ኛ እና መሰናዶ ት/ቤት ይሰሩ በነበሩበት ወቅት የስራ ባልደረባዬ ነበሩና አጋጣሚው ጥሩ ሆኖልኝ ነበር። የመጣሁበትን ዓላማ በማስረዳት መረጃ ወደምሰበስብባቸው ቦታዎች ለ3 ቀናት አድርሶ የሚመልሰኝ የትራንስፖርት አገልግሎት ትብብር ጠየቅሁ። እሳቸውም ከግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ ከነበሩት አቶ ካሳሁን ጋር በመነጋገር አንድ ቶዮታ ፒክ አፕ መኪና ለሁለት ቀናት የደርሶ መልስ አገልግሎት እንድትሰጠኝ ተፈቀደልኝ። በእለቱ ወደ ወረዳው የባህል ማዕከል በማምራት በማህበረሰቡ ላይ የተጻፉ መረጃዎች ለማየት ሞከሬአለሁ።

መስከረም 17 እና 18 ቀን 2005 ዓ.ም. የመስቀል በዓል ቢሆም ወረዳው በፈቀድልኝ ትራንስፖርት በመጠቀም ወደኾንሶ ነባር ከተማ ፋሻ ከረዳቴ ከአቶ ኡርማሌ ሎውሌ ጋር በመሄድ መረጃዎችን ስሰበስብ ውያለሁ። መስከረም 19 ቀን 2005 ዓ.ም እንደተለመደው ከረዳቴ ከአቶ ኡርማሌ ሎውሌ ጋር በመሆን በሌላ ትራንስፖርት ወደ ኮልሜ በመሄድ በረዳቴ አስተርጓሚነት የመረጃ መሰብሰብ ተግባሩ ተከናውኗል። ከመስከ በኋላ ረዳቴ አቶ ኡርማሌ ሎውሌ በቀጣዮቹ ቀናት መረጃ ወደምሰበስብባት ጋሞሌ ፋራህ ተራራ በመሄድ በኾንሶ ከሚገኙ ከዘጠኙ ጎሳዎች ውስጥ የኬርቲታ ጎሳ ባህላዊ መሪ (ፖቾላ) ወደሆኑት ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት ቤት በመሄድ ሁኔታዎቹን እንዲያመቻችልኝ በመስማማት እኔ ወደ ማረፊያዬ እሱ ደግሞ ወደተባለው ቦታ አቀና።

መስከረም 20 ቀን 2005 ዓ.ም. ጠዋት እኔና ረዳቴ ከካራት ከተማ ወደ ባህላዊው መሪ ቤት ሞተር ሳይክል በመከራየት ሄድን። ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት የተማሩ፣ በእድሜ ወጣትና ተግባቢ ስለበኑሩ ስራችንን በነጻነት እንድንሰራ ረዳቴ አገናኝቶኝ ተመለሰ። እውነትም በጣም ወዳጅነትና ቀረቤታ ባለው መንፈስ የመረጃ መሰብሰብ ስራውን ስሰራ ዋልኩ። በማግስቱ መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም. በተመሳሳይ መንፈስና ስሜት የመረጃ መሰብሰብ ተግባሬን ሳከናውን ውያለሁ።

መስከረም 22 ቀን 2005 ዓ.ም. የመስክ ስራ አልሰራሁም። ዲጂታል ካሜራዬን ብቻ በመያዝ በሞተር ሳይክልና በእግሬ እየተዘዋወርኩ ምልከታ ሳካሂድ ዋልኩ፣ በዚህም ጠቃሚ ናቸው ብዬ ያሰብኳቸውን ነገሮች በፎቶ ካሜራዬ እየያዝኩ አካባቢውን ስቃኝና ስዝናና ዋልኩ። ማታ ላይ ወደ ካራት ከተማ በመምጣት ከአካባቢው ተወላጅ ከዶ/ር ገዋዶ አይላዶ ጋር በቀጣዮቹ 3 ቀናት በዱካቱ መንደር መረጃ እንደምንሰበስብና የተመረጡት ናሙና መረጃ አቀባዮች በጠዋት እንዲጠብቁን፣ እሳቸውም በመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ ላይ በአስተርጓሚነት እንደሚረዱኝ ተነጋግረን ቀጠሮ በመያዝ ተለያየን። ማታ ወደ ማረፊያዬ በመሄድም ውሎዬን በማስታወሻ ሳሰፍርና ለቀጣዩ ቀን ስዘጋጅ አመሸሁ።

ከመስከረም 23-25 ቀን 2005 ዓ.ም. ድረስ ላሉት 3 ቀናት በዱራይቱ በመቆየት ማህበረሰቡ የሚበላውንና የሚጠጣውን በመጋራት መረጃ ስሰበስብ ቆይቻለሁ። በአስተርጓሚነት ያግዙኝ የነበሩት ዶ/ር ገዋዶ አይላዶ ከቁልፍ መረጃ ሰጪም ጭምር በመሆን ያልተናነሰ መረጃ ይሰጡ ስለነበር ድጋፋቸው በጣም ትልቅ ነበር። በየእለቱ ማታ ማታ በውሎዬ ያስተዋልኳቸውን ጉዳዮች በማስታወሻ ላይ አሰፍር ነበር።

መስከረም 26 እና 27 ቀን 2005 ዓ.ም. መረጃ ለመሰብሰብ የታሰበው ከዋናዋ ካራት ከተማ ነበር። ይሁን እንጂ ዶ/ር ገዋዶ አይላዶን ጨምሮ በእነዚህ ሁለት ቀናት በቁልፍ መረጃ ሰጪነት የተጠቆሙትን ሶስት ሰዎች ቢሆንም ሁለቱን ለማግኘት አልቻልኩም። ስለዚህም በእነዚህ ሁለት ቀናት ዶ/ር ገዋዶ አይላዶን እንደ ቁልፍ መረጃ ሰጪነት በመጠቀም መረጃ ልሰበስብ ችያለሁ።

መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም. በተለያዩ ጊዜትና ቦታዎች ላይ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በተናጠልና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ለማረጋገጥ ጥረት በተደረገበት ወቅት በተለይ ከፋሻ አካባቢ የተሰበሰቡት መረጃዎች መጣራት እንዳለባቸው ፍንጭ ሰጪ አስተያየት ቀርቦ ነበር። ስለሆንም ይህን ለማጣራት በድጋሚ ወደ ፋሻ መሄድ አስፈልጓል። ስለዚህም በዚሁ እለት ወደ ፋሻ በመሄድ ቀደም ብለው መረጃ የሰጡትና አንዳንድ አዳዲስ ሰዎች በመጨመር በተናጠልና በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች እንዲካሄዱ በማድረግ በድጋሚ መረጃ ልሰበስብ ችያለሁ።

መስከረም 30 ቀን 2005 ዓ.ም. እልጋ በያዝኩበት ቤት ውስጥ በመዋል ቀኑን ሙሉ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ሳጣራ፣ ክፍተት አለባቸው የምላቸውን ቦታዎች ስመረምር ዋልኩ። በመጨረሻም ይጎድሉኛል ብዬ በገመትኩባቸው ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ የተሻለ

ማብራሪያ ይሰጡኛል የምላቸውን ቁልፍ መረጃ ሰጪ ለየሁ። ወዲያውም ጥያቄዎችን አዘጋጀሁ። ምሽት አካባቢ ቁልፍ መረጃ ሰጪዬ ቤት በማምራት ለቀጣዩ ቀን ቀጠሮ በማስያዝ ተመለስኩ።

ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ.ም. ወደ ዱካቱ በመሄድ ከአቶ ኮራ ጋራ ጋር ውይይት ሳደርግና መረጃዎችን ሳጣራ፤ የማህበረሰቡን ምግብና መጠጥ በተለይ «ጨቃ» የሚባለውን ባህላዊ መጠጥ እየጠጣሁ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማቅረብ አዳዲስ መረጃዎችን ስሰበስብ ዋልኩ።

በማግስቱ ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ.ም. በተመሳይ ሁኔታ ለግማሽ ቀን ተጨማሪ መረጃዎችን ስሰበስብ ዋልኩ። ከሰአት በኋላ እቃዎቼን ሳስተካክል ዋልኩ። መስከረም 10 ቀን 2005 ዓ.ም. የተጀመረው የመስክ ጉዞ ጥቅምት 02 ቀን 2005 ዓ.ም. ፍጻሜ በማግኘቱ ከኾንሶ ቀና ከተማ ካራት ጥቅምት 03 ቀን 2005 ዓ.ም. በመነሳት አርባ ምንጭ ከተማ ደረስኩ። አርባ ምንጭ ካደርኩ በኋላ በማግስቱ ጥቅምት 04 ቀን 2005 ዓ.ም. ከአርባ ምንጭ ወደ አዲስ አበባ ተመልሻለሁ።

መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ በተንቀሳቀስኩበት ጊዜ በርከት ያሉ ችግሮች አጋጥመውኛ ነበር፤ ይሁን እንጂ ለገጠሙኝ ችግሮች አስቸኳይ የሆኑ የመፍትሄ እርምጃዎችና ውሳኔዎችን በመውሰድ ተልዕኮዬን ለመወጣት ችያለሁ። ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችም የሚከተሉት ነበሩ።
እነዚህም፦

- የመጀመሪያው ችግር መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ኾንሶ ለመሄድ በተነሳሁበት ጊዜ ወቅቱ የመስቀል በዓል መዳረሻ ስለነበር ከአዲስ አበባ ወደ የአርባ ምንጭ ከተማ በአሉን ለማክበር የሚሄደው ተሳፋሪ ቁጥር እጅግ የበዛ ስለነበር የትራንስፖርት ችግርና እና ለተጨማሪ ወጪ መዳረግ ነው።

- ሁለተኛው ከዚህ ጋር የተያያዘው ችግር ከብዙ ልፋትና ጥረት በኋላ አርባ ምንጭ ከተማ ለመድረስ ቢቻልም ከላይ በጠቀስኩት ምክንያት ወደ ጨንቻና ሌሎች አጎራባች ወረዳዎች በሚጓዙ መንገደኞች ምክንያት አልጋ ማግኘት ያለመቻሉ ነው።

- ሶስተኛው በችግርነት የሚነሳው ኾንሶ ከአዲስ አበባ በ565 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የምትገኝ እና በርካታ ቁረስቶች እና ተመራማሪዎች በየጊዜው የማይጠፉባት

ወረዳ ነች። በዚህም ምክንያት በከተማዋ ረዘም ላለ ጊዜ አልጋ ይዞ ለመቆየት የገንዘብ አቅምን የሚፈትን መሆኑ ነው።

- ሌላው ችግር የሆነው በባህሉ ክልከላ ምክንያት ሴት መረጃ ሰጪዎችን ያለማግኘት እና
- የመጨረሻው አጥኚው የአካባቢውን ቋንቋ ያለማወቁ መረጃዎቹን በሚፈለገው መንገድ ለማግኘት ማስቸገሩ ነበር።

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚከተሉትን መፍትሄዎች መከተል አስፈላጊ ነበር።

- የመጀመሪያው ከመደበኛው የመጓጓዣ ታሪፍ ውጪ እጥፍ እጥፍ ከፍሎ በአቆራራጭ በመሄድ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ማድረግ፣
- ለደላሎች በመክፈል አልጋ ለመያዝ መሞከር፣
- ለጥናቱ ከተፈቀደው ገንዘብ ውጪ ሌላ ተጨማሪ ገንዘብ ከግል በማውጣት ጥናቱ እንዳይቋረጥ ማድረግ፣
- የጥናቱን አላማ በማስረዳትና በማሳመን ሴት መረጃ ሰጪን ለማግኘት መጣር እና የመጨረሻው
- ከብሄረሰቡ አባል የሆነ ረዳት አጥኚና አስተርጓሚ በመጠቀም ችግሩን ማቃለል እና የመሳሰሉት ናቸው።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ ክፍል የቃላዊ ዝርው ተረኮች ምንነትን በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን ያነሷቸው ሀሳቦች ይሰፍራሉ። ቀጥሎም ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይ የሆኑን ጥናቶችን በመከለስ ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት ይቀርባል።

## 2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ፎክሎር ዘርፈ ብዙ በመሆኑ በተናጠል ከማናት ይልቅ በተለያዩ ክፍሎች በመከፋፈል ማጥናት የተሻለው አማራጭ እንደሆነና ፎክሎርን ቃላዊ፣ ቁሳዊ እና ልማዳዊ በማለት ይከፋፍላሉ እነ Sims (2005:12)። ቃላዊ ፎክሎር፣ ሃገረሰባዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባህል እንዲሁም ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ በማለት በአራት ምድቦች ይከፋፍሏቸዋል Dorson (1972:3)። ፈቃደ (1991:11) ይህን ሃሳብ መነሻ በማድረግ ቃላዊ ፎክሎር በቃላት አማካይነት በሚፈጠሩ ማለትም በተረት፣ በሌጀንድ፣ በሚት፣ በቃል ግጥም፣ በምሳሌያዊ ንግግር፣ እንቆቅልሽ፣ በእንካ ሰላንቲያ እና የመሳሰሉትን ስለሚያጠቃለል ስነ ቃል ሊባል እንደሚችል ይገልጻል። ቃላዊ ዝርው ተረክም አንዱ የስነ ቃል ዘርፍ ነው ማለት ይቻላል።

ይሁን እንጂ እነ Sims (2005:17) የፎክሎር ዘውጎች አንዱ በአንዱ ውስጥ ሊከሰት እንደሚችል ይናገራሉ። ከዚህ በመነሳትም ብዙ የዘርፉ ምሁራን ከፎክሎር አይነቶች መካከል አንዱን ብቻ በመምረጥ ማጥናት እንደሚሻል ይገልጻሉ።

ከዚህ በታች ስለ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ምንነት የተለያዩ ምሁራን የሰጧቸውን ብያኔዎች እና ጽንሰ ሃሳቦች ይቀርባሉ።

### 2.1.1. ቃላዊ ተረክ

ቃላዊ ዝርው ተረክ በሁነቶችና በድርጊቶች የተዋቀረ የአንድን ቡድን ወይም ማህበረሰብ ልማድ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚጠቅም ነው በማለት Oring (1986:122) ይገልፃሉ።

ከላይ ከቀረበው ብያኔ መረዳት የሚቻለው ቃላዊ ዝርው ተረክ (Oral Prose Narrative) የስነቃል አንዱ ክፍል ሲሆን፣ ተለጣጣቂነት ወይም ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶችና ሁነቶች የሚፈፀሙበት፤ በድርጊቶቹ ውስጥ የሚሳተፉ ባለታሪኮች የሚገኙበት፣ ድርጊቱ የሚፈፀምበት ጊዜና ቦታ የሚመለከትበት እና ተከታታይ ድርጊቶች ቃላዊነታቸውን ሳይለቁ በዝርው ቅርፅ የሚቀርብበት ነው። በአጠቃላይ ቃላዊ ዝርው ትረካ በውስጡ የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን አመለካከት፣ እምነት፣ ባህል የመሳሰሉት ማህበራዊ እሴቶች የሚያንፀባርቅበት መሆኑን ነው።

ቃላዊ ዝርው ተረክ ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለውና በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝና በማህበረሰቡ ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ በተለያየ መልክ የሚከወን መሆኑን ያስረዳል ፍቃደ (1991:52)። ቃላዊ ዝርው ተረክ የማያረጅ ወይም ዘላለማዊ፣ ሲተረክ የሚኖር ስሜትን መግዛት የሚችልና ከሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ጋር አብሮ የሚጓዝ፣ ራሱንም እንደዘመኑ ሁኔታ በመቀያየር የሚኖር ነው በማለት ይገልፃሉ Dégh (1972:54)። በተመሳሳይ Oring (1986:123) ቃላዊ ተረኮች ቋንቋ ከተፈጠረ ጀምሮ የነበሩ እና እስከአሁንም የሚገኙ እንዲሁም ሁሉም ማህበረሰብ በየትኛውም የስልጣኔ እርከን ውስጥ ቢሆን የሚጠቀምባቸው እንደሆነ ያስረዳሉ።

ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ገለጻዎች መረዳት የሚቻለው የቃላዊ ዝርው ተረክ አመጣጥ ከጥንት ታሪክ የሰው ልጆች ልማዶችና እምነቶች እንደሆነና በተፈጠረበት ማህበረሰብ ውስጥ ስረጅም ዘመን ሳይጠፋ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየ መሆኑን ነው። በተስተላለፎ ሂደቱም እንደ ዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታና ተረኩ እንደሚተረክበት ማህበረሰብ ባህላዊ እውድ ጋር ተስማምቶ የሚቀርብና የተወሰነ ለውጥ የሚያሳይ ነው።

ስለ ዝርው ቃላዊ ተረክ Degh (1972:58) በዝርው መልክ የሚቀርብ ማንኛውም የስነ-ቃል አይነት ቃላዊ ዝርው ተረክ እንለዋለን በማለት ይገልፃሉ።

### 2.1.2.የቃላዊ ተረኮች ምደባ

ተረኮችን በየዘርፋቸው በመመደቡ ረገድ ሲታይ የአፍሪካ ስነ ቃል አካባቢያዊ የምደባ ዘዴዎች ወጥነት ያላቸው አይደሉም። ስለዚህም የአካባቢያዊ ምደባ ዘዴን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ጥናቱን አውዳዊ (contextual) ማድረግ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም አውድን መሰረት ያደረገ የዝርው ተረክ ምደባ እንደየተረኮቹ የክዋኔ ጊዜ፣ የከዋኙ ማንነት፣ የትረካ ክሁሎት፣ ታዳሚውንና የተረኩን ጠቀሜታ የመሳሰሉትን

ነገሮችን መነሻ ለማድረግ ጠቃሚ እንደሆነ ትገልጻለች (Finnegan,1970:365)። በሌላ በኩል ቃላዊ ተረኮችን በየዘሮቻቸው ለመመደብ ጥቅም ላይ ከዋሉት ዘዴዎች መካከል አካባቢያዊና የትንተናዊ ምደባ ዘዴዎች እንደሚገኙ ያስረዳሉ Bena-Amos (1982) እና Okphewho (1992)።

### 2.1.2.1. የኹንሶ ተረኮች አካባቢያዊ ምደባ

የኹንሶ ብሄረሰብ ተረት ቶሬ፣ ድንቃድንቅና ተአምራት ተረቶች ደግሞ ቶሮታ በመባል ይጠራሉ። በእነዚህ ውስጥም አፈ ታሪኮች ይካተታሉ። አፈ ታሪኮች ስለ ልዩ ልዩ ባህላዊ ገጽታዎች፣ ስለ ዝርያዎቻቸው ወደ አካባቢው መፍለስ፣ ስላካሄዷቸው ጦርነቶች፣ ስለ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች፣ ስለ ታሪካቸው የሚያወድሱ መሆኑን ኹንሶዎች ያምናሉ። (ቅ/ጥ/ጥ/ባ/ 2001፣ 20)

#### 2.1.2.1.1. ቶሬ

በማህበረሰቡ «ቶሬ» በመባል በሚቀርቡ ተረኮች የሰው ልጆችን ልዩ ልዩ ባህሪያት የወከሉ ሰውን ጨምሮ እንስሳ፣ አዕዋፍ የመሳሰሉት ገጸ ባህሪያት አሏቸው። ተረኮቹም ቀልድ አዘል የሆኑና እምብዛም ውስብስብነት የሌላቸው ማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊረዳቸው እንደሚችል የብሄረሰቡ አባላት ይገልጻሉ።

#### 2.1.2.1.2. ቶሮታ

«ቶሮታ» በሚል የሚጠሩት የኹንሶ ተረኮች የብሄረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ፣ እጅግ አስደናቂ ክስተቶች፣ የማህበረሰቡን ትልልቅ ገድሎች፣ በማህበረሰቡ አባላት፣ በጎሳ መሪዎች እና በመናፍስት የተፈጸሙ ተአምራትን የሚተርኩ ናቸው። ብዙውን ጊዜ ገጸ ባህሪያቱ ታዋቂ ሰዎች፣ የጎሳ መሪዎች እና ሰናይና እኩይ መናፍስት ናቸው። ተረኮቹ የብሄረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ፣ ለትውልድ ለማስተላለፍ፣ ለማስተማር፣ ለመምከር፣ የማህበረሰቡን የስራ ጥንካሬ፣ ታታሪነት አጉልቶ ለማሳየት አገልግሎት ላይ ይውላሉ። ተረኮቹ በሚሰብኩት ስነ ምግባር በመልካምነት የሚቆጠሩት ሚዛን ሲደፉ፣ መጥፎ የሚባሉት ደግሞ ተቀባይነት ሲያጡ ያሳያሉ። ብሄረሰቡ ከ«ቶሬ» ይልቅ «ቶሮታ» እውነታነት ያላቸው ተረኮች ናቸው ብሎ ያምናል።

### 2.1.3. አውዳዊ ትንተና (contextual Analysis)

በፎክሎር ጥናት መስክ በተሰበሰቡ ቴክስቶች ላይ ትኩረት ይሰጥ የነበረው የፎክሎር ጥናት የትኩረት አቅጣጫውን ቀይሮ ትኩረቱን ከቴክስት ወደ አውድ መመለስ

የጀመረው በፎክሎር ባለሙያዎች በእነ Roger Abrahams, Dan Ben-Amos, Alen Dundes...ነው። እነዚህ አጥኚዎች በ1960ዎቹ ሲነሱ፣ በአንድ የፎክሎር ቅርጽ ውስጥ የሚነሳ መልዕክት ወይም ሀሳብ በተግባር የሚታየው በቴክስቱ ውስጥ ሳይሆን በፎክሎራዊ ሁነቱ በሚከወንበት ወይም በተግባቦታዊ ሂደቱ ውስጥ ነው። የሚለውን ሀሳብ ማራመድ እንደጀመሩ ይጠቀሳሉ Dorson (2003:251)።

ሌላው ይህ ዝርው ቃላዊ ተረክ ተራኪ፣ አድማጭና ተረኩ የሚቀርብበት ተስማሚ አውድ የሚያስፈልገው መሆኑን ምሁራን ያስረዳሉ። ቃላዊ ተረክን በምናጠናበት ወቅት የተራኪውን እና የታዳሚውን ሚና ግምት ውስጥ ማስገባት እንዲሁም ተረኩ የሚነገርበትን አውድ ማስተዋል ጠቃሚ ይሆናል። ይህንን በተመለከተም Sims (2005: 137-139) አውድ የአንድ ቡድን ወይም ማህበረሰብ አባላት በፎክሎራቸው የሚጋሩበት መቼት (setting) እና ማህበራዊ ሁኔታ (social situation) ነው። በታዳሚዎች መካከል ያለው ግንኙነትም በአውዱ ውስጥ ይጠቃለላል። ስለዚህ የአንድን ተረክ ትርጉም በምንተነትንበት ወቅት ከከዋኙው አካባቢያዊ ገጽታ በተጨማሪ በከዋኙው ስፍራ እና ወቅት ያለውን ሁኔታ በአጠቃላይ በትኩረት ማጤን ይገባናል። ከዚህ በተጨማሪ ከዋኙው በሚኖርበት አካባቢ ያለውን ማህበራዊ ሁኔታ ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት አንድ ተረክ በተለያየ አውድ ውስጥ በተለያየ መልኩ ሊቀርብ ስለሚችል እና ተረኩ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ትርጉም የሚታወቀው በአውድ ውስጥ በመሆኑ ነው።

ከዚህም ባሻገር ቃላዊ ዝርው ተረክ ሲጠና የተረኩ መልእክት ምንድነው? ትረካዎቹ እንዲፈጠሩ፣ እንዲተረኩ እና እንዲከወኑ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው? እንዲሁም ተረኮቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ትርጉም ምንድን ነው? የሚሉት ነጥቦች ላይ ማተኮር እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ Degh (1972: 54)።

በሌላ በኩል በፎክሎር አውዳዊ ጥናት አውድ የሚባለው የቱ ነው? በሚለው ሀሳብ ዙሪያ የዘርፉ ባለሙያዎች ልዩ ልዩ ውይይቶችን አካሂደዋል። Young (1985: 115-122) ፎክሎር የሚከወንበት አካባቢ በጥቅሉ አውድ አድርጎ መውሰድ ስህተት ነው። አውድን አውድ፣ የሚያስብለው ፎክሎሩ በሚከወንበት አካባቢ ያለው የቦታ ቀረቤታ ሳይሆን የተግቢነት ደረጃ ነው ይላሉ።

### 2.1.3.1. ባህላዊ አውድ (Cultural context)

ባህላዊ አውድ ሶስት ገጽታዎች እንዳሉት ይገልጻሉ Buman (1983:363- 364)። እነሱም እንደሚከተለው በአጭሩ ይቀርባሉ።

#### 2.1.3.1.1. የባህላዊ የአውድ ትርጉም (context of Meaning)

ከፎክሎር ጥናት ጋር በተያያዘ በባህላዊ አውድ ላይ በብዙዎች ዘንድ የግንዛቤ ችግር እንደ መሰረታዊ ነጥብ ይነሳል። የአንድን የፎክሎር ይዘት፣ ትርጉምና ዋነኛ ነጥብ ለመገንዘብ ስለ ባህሉና ማህበረሰቡ በመረዳት በቂ መረጃ ሊኖር ይገባል። ባህላዊ አውድ ለፎክሎር የሚሰጠው ትርጉም በባህሉ ትንብር ውስጥ የሚወሰን ነው። በፎክሎሩ ምን ዓይነት የህዝብ አኗኗርና ዘይቤ ተገልጾበታል ኅልቶበታል? ተሳልፎበታል? የአምልኮት ስርአቶችና እሴቶች ያላቸው ግንኙነት የምክንያትና የውጤት ትስስር ምን ይመስላል? ያላቸው አነሳሽነትና ምርጫ፣ የአተገባበር ስልታቸው፣ ተምሳሌታዊነታቸውና ዘይቤአዊ ግንኙነታቸው፣ ፍቺዎች የፎክሎር አገላለጹን ምን ቅርጽ አስያዙት? ከውጤትና ትርጓሜ አንፃር ምን አይነት የአከፋፈል ቅርጽ አለው? የሚሉትን ማየት ያስፈልጋል። ማህበረሰቡን በውጭ የሚያውቅ አንድ አጥኚ የፎክሎር አውዳዊ ሁኔታዎችን በቀላሉ ለመረዳት በአውዱ ውስጥ መገኘትና ለባህሉ እውቅና መስጠት አስፈላጊ ነው። ማህበረሰቡንና ባህሉን ለማያውቅ አጥኚ የማህበረሰቡን ተቋም፣ ብዝሀነት የመለየት ችግር ሊገጥመው ይችላል።

አብዛኛው የፎክሎር ትርጉም በአውዳዊ ሁነቶች ተጽእኖ ስር የሚወድቅ ቢሆንም አንዳንድ የአተረጓጎም ልዩነቶች በሰዎች እውቀት፣ ግንዛቤና ልምድ እንደሚፈጠሩ ይታመናል። ይህ ማለት የፎክሎር ትርጉም አጥኚው እንዳሻው እንዳይተረጉም ህዝቡ ዋና ዋናውን ነጥብና ትርጉም እንዲገልጹለት ማድረግና ባህሉ ውስጥ ያልተጠናና አስፈላጊ የሆኑ አትጣጫዎችን ገልጾ ማውጣት አለበት።

#### 2.1.3.1.2. ተቋማዊ አውድ (Institutional context)

ተቋማዊ አውድ በጣም ሰፊ ከስነሰብዕ ጥናት ጋር ተቀራራቢ የሆነ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ከሚፃመዱ ሁነቦች የተገነባና ባህላዊና ማህበራዊ ነገሮችን ያካተተ ነው። ተቋሙ እንደ ፖለቲካ፣ ሀይማኖት፣ የዝምድና ግንኙነት ወይም ኢኮኖሚ፣ ጉርብትና፣ ተነሳሽነት እንዲሁም የበዓል ክበራ ሊሆን ይችላል።

የተቋማዊ አውድ ዋና እሴት ባህላዊ እሳቤዎች እንዴት እርስ በርስ እንደሚጣጣሙ እና ከምን ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ትኩረት በማድረግ ጽንሰ ሀሳባዊ ትንተና መስጠት ነው። በተመራማሪው አተያይ የፎክሎር ዓይነት ወይም አከፋፋል ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ እና እርስ በርስ በመተሳሰር ትልቁን ተቀቋም እንዴት እንደሚመሰርት፣ ከየትኛው ባህል ጋር እንደሚጣጣም እና እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውል ማሳየት ነው።

#### 2.1.3.1.3. የተግባቦታዊ አውድ ስርአት (Context of communicative system)

ፍክሎርን እንደ ዋና ተቋም በመውሰድ ከራሱ ህዝባዊ አተያይ አንጻር የፎክሎርን የአከፋፈል ደረጃዎች በአይነታቸው እና በአነጋገር ስልቶቻቸው እንዴት እንደሚደራጁ መገንዘብን ይጠይቃል። እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው ባህላዊ ክዋኔው የሚመነጭበትን የአገላለጽ ደረጃ እንደተወላጁ ትርጉም የሚሰጡ የአገላለፅ ስብስቦች እና ሀሳቡ አንዱን ከሌላው የሚለይባቸውን መለያዎች የሚያሳዩ መሆናቸውን ነው። እንደ አጠቃላይ ተግባቦታዊ አውድ የአንድ ማህበረሰብ ፍክሎር በባህሉ ውስጥ ካለው አጠቃላይ ተግባቦት እንዴት እንደሚገናኝ፣ እነዚህ እርስ በርስ የተሳሰሩ ትልልቅ አገላለፆች፣ ስርአቶች፣ ለእያንዳንዱ የተለየ ቅርጽና ከባህሉ ልማድ፣ ይዘት፣ አጠቃቀምና ምዘና አንጻር ትርጉም ይሰጣሉ።

### 2.1.3.2. ማህበራዊ አውድ (Social context)

#### 2.1.3.2.1. ማህበራዊ መሰረት (social base)

ፎክሎር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የህዝብ አገላለጽ ወይም ንብረት እንደሆነ መሰረታዊ ፎክሎራዊ እሳቤ ሆኖ ከ200 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል፤ አሁንም ከፍተኛ ተጽእኖ እያደረገ ይገኛል። የፎክሎር ማህበራዊ መሰረት በሚገኝበት ቡድኑ ፍክሎሩ የሚያንጸባርቀውን ጠቃሚ አተያይ ላይ ያተኩራል። እዚህ ላይ የትኞቹ የፎክሎር አገላለፆች ከማህበራዊ ማንነት ጋር ይያያዛሉ? የሚል ጥያቄ ይነሳል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፎክሎሪስቶች ትልቅ የውይይት አጀንዳ የሆነው «የፎክሎር ህዝባዊ መሰረት ማነው?» የሚለው ነው። የ19ኛ ክፍለ ዘመን ተመራማሪዎች "አርሶ አደሮች" ሲሉ የአሁን ፎክሎሪስቶች ደግሞ ቢያንስ አንድ የጋራ ነገር ያለው የህዝብ ቡድን ነው ወደሚለው አመለካከት አስፍተውታል። ለፎክሎር ጥናት ሁለተኛውን አመለካከት መከተሉ ተቀባይነት ነው።

### 2.1.3.2.2. ግለሰባዊ አውድ (Individual context)

ማህበራዊ ቡድኖችና ማህበራዊ ህይወት ከግለሰቦች ፍላጎትና ከፎክሎር አጠቃቀም ይመነጫል። ግለሰባዊ ታሪክና መቸት እንዲሁም በግለሰብ የሚደረግ ከዋኔ ደግሞ በአውድ ውስጥ የሚታይ ይሆናል። ግለሰባዊ አውድ ከግለሰብ ማህበራዊ ተሳትፎ ጋር የሚያያዝ በመሆኑ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ፎክሎር ያለውን ቦታ ለመገንዘብ ይረዳል።

### 2.1.3.2.3. ሁኔታዊ አውድ (Situational context)

እጅግ በጣም የቅርብ ጊዜ የሆነና የሚቀርበውን ፎክሎር ከሚገባበት ሁኔታ አንፃር የሚመለከት ነው። መሰረታዊ መነሻው የአገላለጽ መለኪያ፣ ትንታኔና እንጻራዊ ሁነት ነው። ሁነቱ በባህልና በልምድ ፍሰት የተቀነበበ አውዳዊ እንቅስቃሴን የሚገነባ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህ አውድ በሚደረጉ በርካታ ማህበራዊ ክንውኖች ላይ የሚመሰረትና የሚቀርብ ነው።

### 2.1.3.2.4. ተፈጥሮአዊ አውድ (Natural context)

ይህ አውድ የማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ገጽታዎች የሚከወኑበት ተፈጥሮአዊ አውድ ነው። አጥኚው አውዱን ለማየት የሚያስቸግረውና አውዱም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበረዘና ተፈጥሮአዊነቱን እይለቀቀ በመሄዱ ውጤታማ ወዳለመሆን የመጣ ነው። በአጠቃላይ ፎክሎርን ከአውድ አንጻር የማጥናት ተግባር በውስጡ ውስብስብ ነገሮችን የያዘ ሂደት ነው፣ ይሁን እንጂ በውጤታማነት ለማከናወን አውዳዊ አቀጣጫውን በቀጥታ መከተል የግድ ይላል። የመስክ ተመራማሪው በመጀመሪያ ማተኮር ያለበት ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን ወይም ሁለተኛ ደረጃ ማጊያ መረጃዎች ላይ ሳይሆን ከፎክሎር ቁሶች ጋር ግንኙነት ባለቸውና እርስ በርስ በተሳሰሩ ያውም አስፈላጊነቱን በሚያጎሉ መረጃዎች ላይ መሆን አለበት። ይህን ለመበየን መረጃዎችን በሚከተሉት ስድስት ነጥቦች ላይ ማደረጃት አስፈላጊ ነው። እነሱም:-

(1) አወዳዊ ፍቺ (መረጃው ምን ማለት ነው?) (2) ተቋማዊ አውድ (በባህሉ ውስጥ የቱጋ ይጣጣማል?) (3) ተግባቦታዊ አውድ (ከሌሎች የፎክሎር አውዶች ጋር እንዴት ይጣመዳል?) (4) ማህበራዊ መሰረት (ፎክሎሩ የየትኛው ህዝብ ነው?) (5) ግለሰባዊ አውድ (ፎክሎራዊ አውዱ ከግለሰባዊ ህይወት ጋር እንዴት ይጣጣማል?) (6) ሁኔታዊ አውድ (በማህበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት ጥቅም ላይ ይውላል?) የሚሉትን

የሚመለሱ ናቸው፤ ይሁን እንጂ እነዚህን ነጥቦች አንድ በአንድ በመውሰድ ለፎክሎር ጥናት እንደ ማረጋገጫ ዝርዝር ዓይነት መጠቀም ተገቢነት እንደሌለው Bauman (1983: 366-367) ይገልፃሉ። ይህ ጥናትም የብሄረሰቡን ተረኮች አውዳዊ ትንተናን መሰረት በማድረግ የሚተነትን ይሆናል።

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በኾንሶ ማህበረሰብ ላይ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ባለሙያዎች የተለያዩ ጥናታዊ ስራዎች ተሰርተዋል፤ ይሁን እንጂ እኔ በመረጥኩት ርዕስ ላይ የተሰራ አንድም ጥናት አላገጠመኝም። ነገር ግን ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር፣ በውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ፣ በማህበረሰብ ጥናት የትምህርት ክፍሎች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶችን እንደሚከተለው ከልሻለሁ።

ከእነዚህም ውስጥ አራቱ በብሄረሰቡ ላይ የተሰሩ ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ አስራ አንዱ ደግሞ ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው።

በኾንሶ ማህበረሰብ ላይ የተሰሩ አፀደ ያረጋል (2003) ዓ.ም.፣ Watson (2001) Kansite Gellebo (2011)፣ Mamitu Yilma (2002)፣ Lakew Regassa (1998) የተሰሩ ጥናቶች ናቸው። እነዚህ ጥናቶች ቃላዊ ተረኮችን የሚያነሱ ባለመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያለያያቸው፣ በአንድ ብሄረሰብ ላይ የተሰሩ በመሆናቸው ያመሳስላቸዋል።

ቀሪዎቹ አስራ አንድ የጥናት ጽሑፎች ደግሞ በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ትኩረት አድርገው የተሰሩ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት አላቸው። እነዚህን ጥናቶች በቃላዊ ዝርው ተረኮች ጭብጥ ላይ የተመሰረቱ፣ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በአውዳዊ አተባባቸውና በዘውግ ከፋፍለው ያቀረቡ እና ከባህላዊ ስርአቶች ጋር አጣምረው ያጠኑ ብሎ በሦስት ክፍሎች መመደብ ይቻላል። በመጀመሪያ የማቀርበው ዝርው ቃላዊ ተረኮች ባላቸው ጭብጥ ላይ ተመስርተው የቀረቡ ጥናቶችን በአጥኚዎቹ ስም ቅደም ተከተል መሰረት ነው።

Melakneh Mengistu. (1990) "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ የደቡባዊ አገውን ሀገረሰባዊ ተረቶች በመሰብሰብ በጭብጥና በሞቲፍ ላይ የተመሰረተ ትንተና በማድረግ የተረቶቹን

የሚመልሱ ናቸው፤ ይሁን እንጂ እነዚህን ነጥቦች አንድ በአንድ በመውሰድ ለፎክሎር ጥናት እንደ ማረጋገጫ ዝርዝር ዓይነት መጠቀም ተገቢነት እንደሌለው Bauman (1983: 366-367) ይገልጻሉ። ይህ ጥናትም የብሄረሰቡን ተረኮች አውዳዊ ትንተናን መሰረት በማድረግ የሚተንትን ይሆናል።

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በኹንሶ ማህበረሰብ ላይ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ባለሙያዎች የተለያዩ ጥናታዊ ስራዎች ተሰርተዋል፤ ይሁን እንጂ እኔ በመረጥኩት ርዕስ ላይ የተሰራ አንድም ጥናት አላገጠመኝም። ነገር ግን ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር፤ በውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ፤ በማህበረሰብ ጥናት የትምህርት ክፍሎች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶችን እንደሚከተለው ከልሻለሁ።

ከእነዚህም ውስጥ አራቱ በብሄረሰቡ ላይ የተሰሩ ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ አስራ አንዱ ደግሞ ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው።

በኹንሶ ማህበረሰብ ላይ የተሰሩ አፀደ ያረጋል (2003) ዓ.ም.፣ Watson (2001) Kansite Gellebo (2011)፣ Mamitu Yilma (2002)፣ Lakew Regassa (1998) የተሰሩ ጥናቶች ናቸው። እነዚህ ጥናቶች ቃላዊ ተረኮችን የሚያነሱ ባለመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያለያያቸው፤ በአንድ ብሄረሰብ ላይ የተሰሩ በመሆናቸው ያመሳስላቸዋል።

ቀሪዎቹ አስራ አንድ የጥናት ጽሑፎች ደግሞ በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ትኩረት አድርገው የተሰሩ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት አላቸው። እነዚህን ጥናቶች በቃላዊ ዝርው ተረኮች ጭብጥ ላይ የተመሰረቱ፤ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በአውዳዊ አገባባቸውና በዘውግ ከፋፍለው ያቀረቡ እና ከባህላዊ ስርአቶች ጋር አጣምረው ያጠኑ ብሎ በሦስት ክፍሎች መመደብ ይቻላል። በመጀመሪያ የማቀርበው ዝርው ቃላዊ ተረኮች ባላቸው ጭብጥ ላይ ተመስርተው የቀረቡ ጥናቶችን በአጥኚዎቹ ስም ቅደም ተከተል መሰረት ነው።

Melakneh Mengistu. (1990) "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፤ የጥናቱ ዓላማ የደቡባዊ አገውን ሀገረሰባዊ ተረቶች በመሰብሰብ በጭብጥና በሞቲፍ ላይ የተመሰረተ ትንተና በማድረግ የተረቶቹን

ስነፅሁፋዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ መመርመር፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ጠቀሜታ እና የህዝቡን ስነልቦናዊና ስነምግባራዊ አመለካከት ማሳየት የሚል ነው። መላክነህ የሰበሰባቸውን ስልሳ ተረቶች እምባገነንነት፣ ተስፈኝነት፣ ትእግስት ወይንም አለመታገስ፣ ሞኝነት፣ ስስት እና ማስመሰል በሚሉ ጭብጦች ከፋፍሎ አሳይቷል። በጥናቱም ተረቶች ተደጋጋሚ ጭብጦች እንዳሏቸው የተመለከተ ሲሆን፣ የማህበረሰቡን መልካም እሴቶች ለማስተማር፣ የወጣቶችን ስብዕና በመልካም ስነምግባር ለመቅረፅ እንደሚያገለግሉ ገልጿል።

Abdul Kadir, Haji Jama. "Some Cultural Elements as Reflected in Somali Folktales" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል እ.ኤ.አ በ1982 ዓ.ም. የቀረበ ጥናት ነው። የአጥኚው አላማ ተረቶቹን ሰብስቦ በማጥናት የሶማሌን ብሔረሰብ ባህላዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታ ማሳየት እንደሆነ ገልጿል። ስማንያ ሁለት ተረቶችን ሰብስቦ ጭብጣቸውን መሰረት በማድረግ በስምንት ክፍል መድቦ አቅርቧል። የተረቶቹ ጭብጦችም ብልሃት ወይንም ጥበበኝነት፣ ፍትህ፣ የማኖተኝነት፣ ጋብቻን እና ቅናትን የሚመለከቱ በማለት ከፋፍሎ አስቀምጧል። አጥኚው በጥናቱ ተረቶቹን ጭብጥ በመተንተን ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ስነ ልቦናዊ ጠቀሜታ ለማሳየት ሞክሯል።

አጥኚው መረጃዎቹን የሰበሰበው ጅጅጋ ስደተኞች ካምፕ ውስጥ ብቻ መሆኑ በጥናቱ ገጽ 23 ላይ ይጠቅሳል። ስለዚህም በአንድ ቦታ ብቻ የተሰበሰቡ መረጃዎች መላውን የሱማሌ ማህበረሰብ ይወክላሉ ለማለት የሚያስቸግር በመሆኑ በመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ ላይ ክፍተት ታይቶበታል።

ሌላው በጭብጥ ላይ ተመስርቶ የተሰራ ጥናት በTesfaye Gebre Mariyam. (1990) "A Study of Major Themes in Jabalwi Folktales" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበው ነው። የጥናቱ ዓላማ ለጥናቱ የተመረጡትን ተረቶች ጭብጥ በመተንተን የማህበረሰቡን እምነት፣ ማህበራዊ እሴት እና ለአለም ያላቸውን አመለካከት ማሳየት የሚል ነው። አጥኚው በጥናቱ ሰባ ሁለት ተረቶችን በሃያ አምስት ጭብጦች በመመደብ ለማሳየት ሞክሯል፤ ጭብጦቹም ብቀላን፣ ቅናትን፣ ስስታምነትን፣ ምቀኝነትን፣ ሞኝነትን፣ ደደብነትን፣ ስንፍናን፣ ትዕግስትን፣ ጨካኝነትን፣ አንድነትን፣ ፍትህን እና እውነትን በሚገልጹ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ያተኩሩ እንደሆኑ በጥናቱ አመልክቷል።

አጥኚው ለጥናቱ ከመረጃ አቀባዮች ፈቃድ ውጭ በድብቅ መረጃ ለመሰብሰብ መሞከሩን በጥናቱ ገጽ 12 ላይ ይገልጻል። ድርጊቱ ተገቢውን መረጃ ለማግኘት ካለ ከፍተኛ ጉጉት የመነጨ ሊሆን ቢችልም ከሙያው ስነ ምግባር አኳያ ሲታይ የተከተለው አካሄድ በመረጃ አሰባሰቡ ላይ ክፍተት መኖሩን ያሳያል።

ከላይ የቀረቡት ሦስት የጥናት ሥራዎች በዝርው ቃላዊ ተረኮች ጭብጥ ወይም ይዘታዊ ትንታኔ (thematic analysis) ላይ በማተኮር እና በመመርመር ታሪኮቹ በየማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ ማሳየት የቻሉ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላሉ፤ ነገር ግን ይህ ጥናት ተረኮቹን በማኅበረሰቡ ባህላዊ የአከፋፈል ስልት ተጠቅሞ ያጠና በመሆኑ ያለያየዋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚቀርቡት ጥናቶች ቃላዊ ዝርው ተረኮች በአውዳዊ አገባባቸውና በዘውግ ተከፋፍለው የቀረቡባቸው ናቸው። በአጥኚዎች ስም ቅደም ተከተል መሰረት የመጀመሪያው የማንያለው አባተ (1999) «የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው» በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው። የጥናቱ ዓላማ በቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ገላጭ ትንተና ማድረግና የማህበረሰቡ አባላት የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች ናቸው ብለው የሚጠቅሷቸውን ለይቶ ማመልከት መሆኑን ይገልፃል።

አጥኚው በስራው የቤንች ዝርው ተረኮች ከክወና አውዳቸው (ጊዜ)፣ ከፈጠራነታቸው፣ ከታሪኩ እውነተኛነትና ከትረካው ዓላማ አንፃር «ቤንችቶስ» እና «ኤሽኤሽ» ተብለው እንደሚከፈሉ ገልፆ፤ «ቤንችቶስ» የሚተረከው በቀን ሆኖ በአካባቢው የተነሱትን (ታሪካዊ) ሰዎችን የሚመለከቱ አፈታሪኮችና የብሄረሰቡን ባህላዊ እምነት፣ የአምልኮ ስርዓትና አሰራሮችን የሚመለከት መሆኑን በጥናቱ አሳይቷል። «ኤሽኤሽ» ደግሞ ታሪኩ የፈጠራ ሆኖ ከወናውም በምሽት ጊዜ በአዋቂዎች አማካይነት ለሕፃናት የሚቀርብ እንደሆነ ለማሳየት ሞክሯል። ጥናቱ የቃላዊ ዝርው ተረኮችን ማህበራዊ ፋይዳ ለማየት የሞከረና የማህበረሰቡን የአከፋፈል ስልት ተከትሎ የተጠና የክወና አውድን ማየቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። የእኔ ጥናት ሙሉ በሙሉ አውዳዊ ትንተና (contextual Analysis) ተከትሎ የተሰራ መሆኑ ይለየዋል።

Sahilu Kidane. "Borena Oromo Oral Prose Narrative: A Contextual Study" የሚል ርዕስ አ.አ.ዩ. በ1996 ዓ.ም. ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ጥናቱን ያቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዋና አላማ በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ

ተረቶችን በመሰብሰብ አይነታቸውን ማሳየት ነው። አጥኚው ሰባ አራት ተረቶችን ሰብስቦ ማህበረሰቡ በሚጠራው መጠሪያ መሰረት «ዱሪዱሪ» (የልጆች ተረቶች)፣ «ማግኩሳ» (የጎልማሶች ተረቶ) እና «አር.ጋጌቴ» (ሚቶችና አፈ.ታሪኮች) በማለት በሶስት ክፍሎ አትርቧቸዋል።

አጥኚው በመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች ውስጥ ቃለ መጠይቅ ስለመጠቀሙ አልገለጸም። ቃለ መጠይቅ በፎክሎር ጥናት አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ነው። (Dorson,1972: 407) ከዚህ ረገድ ሲታይ በመረጃ አሰባሰቡ ላይ የተወሰነ ክፍተት ታይቶበታል።

Bayileyegn Tasew. "Anyuaa, Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions" በሚል ርዕስ አ.ኤ.አ. በ1999 ዓ.ም. ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናት ነው። የባይለየኝ ጥናት አላማ ቃላዊ ተረኮችን ባህላዊ የአመዳደብ በመጠቀም ተረኮቹ ያላቸውን ተግባር መመርመር ነው። አጥኚው ለጥናቱ አንድ መቶ አስራ ስምንት ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ሰብስቦ «ሌሪ» (the lerree)፣ «ዊ» (the wae) እና «አንጋዴ» (the angade) በማለት መድቦ አቅርቧል። «ሌሪ» በሞት ስለተለዩ ጀግኖችና ታሪካዊ ክንውኖች፣ «ዊ» ደግሞ ስለ ሰው ልዩ ልዩ ባህሪያትና «አንጋዴ» ስለ እምነቶች፣ ማህበረሰቡ ለአለም ስላለው አመለካከትና የእምነት ስርዓቶች የሚገልጹ መሆኑን በጥናቱ አሳይቷል። ተረኮቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ልዩ ልዩ ማህበራዊ ፋይዳዎች ማመላከት መቻሉና ባህላዊ የአከፋፈል ስልትን መከተሉ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል።

አማረ ሞላ (1999) «የሸካቾ ብሄረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና» በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ የሸኮችን ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ ተረቶችን በመሰብሰብ መድቦ ከአከዋወን ስልትና ከይዘት አንፃር መተንተንና ተረቶቹን ሰንዶ ለመጭው ትውልድ ቅርስ ማቆየት እንደሆነ በጥናቱ ላይ አስቀምጧል። አጥኚው ተረቶቹን አካባቢያዊ ምደባን ተከትሎ የመደበ ሲሆን፣ ከይዘትም አንፃር ተረቶቹ ብልሀትን፣ መጥፎ ባህሪያትን፣ ፍትሃዊነትን፣ ጓደኝነትን፣ ትዕግስትን እና ጣውንትነትን እንደሚያሳዩ ገልጿል። የዚህ ጥናት ትኩረቱ በተረቶች ላይ መሆኑ፣ አከዋወናቸውን ማየቱና ተረቶችን በአካባቢያዊ ምድባቸው መለየቱ ከእኔ ጥናት የተለየ ሲያደርገው የይዘት ትንተና በማድረጉና ተረኮቹ ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ ማሳየት መቻሉ ግን ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል።

Aberaham, Alemu."Jimma Oromo oral prose Narrative: A Preliminary Descriptive Analysis" በሚል በ2000 እ.ኤ.አ. ለውጭ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የኤም.ኤ ጥናት ነው። ጥናቱ ማህበራዊ እና ባህላዊ እውዶችን መሰረት በማድረግ ተረኮችን መለየትና መበየን፣ የጥናቱ አላማዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ቃላዊ ዝርው ተረኮችን መለየት፣ ተጠኚው ማህበረሰብ ተረኮችን እንዴት እንደሚመድባቸው ማሳየት፣ ተረኮቹ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች መመርመር እና የተረኮቹን ባህሪያት ማጥናት የሚሉ ናቸው። ተረኮቹ «ሴና» (Seenaa) «ኦዱ ዱሪ» (oduu duri) «ቆሳ» (qoosaa) በማለት በሶስት ክፍሎ አቅርቧል። ምደባውም የማህበረሰቡን የአመዳደብ ስልት እና እውድን መሰረት አድርጎ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል።

Yihenew Jembere. (1996) "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ ለጥናቱ በተመረጠው አካባቢ የሚገኙትን ቃላዊ ዝርው ተረኮች መሰበሰብና መመደብ የሚል ነው። የአመዳደብ ስልቱ ለተረኮቹ ያላቸውን አመለካከት፣ የአተራረክ ዘዴያቸውን፣ የገፀባህሪያቱን አሳሳል መሰረት በማድረግ እንደሆነ ጠቁሟል። አጥኚው አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ሀገረሰባዊ ተረቶች፣ የሰበሰበ ሲሆን፣ እነሱንም አፈታሪኮች እና ዘር ቆጠራዎች (genealogy) በማለት በሦስት ምድብ ከፍሏቸዋል። ሀገረሰብ ተረቶች በየትኛውም የዕድሜ ክልል በሚገኙ የማህበረሰቡ አባላት የሚነገሩ ሲሆኑ፣ አፈታሪኮችና ዘር ቆጠራዎች ግን በእድሜ ባለፀጎች እንደሚቀርቡም ጠቅሷል። የይሄነው ጥናት ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በየመደባቸው በመከፋፈል ላይ ማተኮሩ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያለያያቸው ቢሆንም፣ ተረኮቹ ላይ የይዘት ትንተና መደረጉ የሚያመሳስላቸው ባህሪ ነው።

ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ቃላዊ ተረኮች ላይ ይዘታዊ ትንተና በማድረግ ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ ለማሳየት መቻላቸውና ተረኮቹ በማህበረሰቡ ባህላዊ የአመዳደብ ስልት ተከትለው መመደባቸው ከእኔ ጥናት ጋርና እርስ በእርስ ያመሳስላቸዋል።

በመጨረሻም የታዩት ጥናቶች ዝርው ቃላዊ ተረኮች ከባህላዊ ስርአቶች ጋር ተጣምረው የተጠኑባቸው ናቸው። እነዚህም በቁጥር ሁለት ሲሆኑ በአጥኚዎች ስም ዝርዝር መሰረት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ምንዳ ገብሬ «የጌዲኦ ልማዳዊ ስርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው» በሚል ርዕስ ጥናቱን ለኢትዮጵያ ስነ ፅሁና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በ2000 ዓ.ም. የቀረበ የኤም.ኤ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው። በጥናቱ አላማ ያደረገው በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው ውስጥ ምን ምን ግንኙነቶች እንዳሉ መመርመር፣ የተረኮቹ ይዘት ምን ምን እንደሆነ ማሳየት የተረኮቹን ጎሳዊ ምደባና አካባቢያዊ ስያሜዎችን ለይቶ ማውጣት የሚሉ ናቸው። በጥናቱ ዝርው ተረኮቹን «ጢንጎ» እና «መግነ» በሚል በሁለት ለይቶ አቅርቧል።

ምንዳ በጥናቱ የጌዲኦ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ የአምልኮ፣ የሀዘን እና ሰርግ ስርዓት እንዳለው አስቀምጧል። ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የማህበረሰቡን ስያሜ አመጣጥ፣ የስራ ባህል፣ የእምነት ፅናት እና በዝቅተኛ ኑሮ ያሉት የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም የተረኮቹን እና ልማዳዊ ስርዓቶቹን ግንኙነት አሳይቷል። ተረኮቹ ልማዳዊ ስርዓቶች ለማጠናከር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው በጥናቱ ላይ አስቀምጧል።

ሁለተኛው ከሁሉም በላይ «የንገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት» በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ስነጽሁና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በ2004 ዓ.ም ለኤም.ኤ ዲግሪ ሂሂያ የቀረበ ጥናት ነው። አጥኚዋ እንደ ምንዳ ጥናት ሁሉ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ከባህላዊ ስርዓቶች ጋር በማጣመር ያቀረበች ሲሆን፣ የጥናቷ አላማ የተጠኚ ማህበረሰብ ዝርው ተረኮችና እና ባህላዊ ስርዓቶች ለአዲስ ትውልድ የሚተላለፍበትን ምክንያት መመርመር፣ በቃላዊ ዝርው ተረኮችና በባህላዊ ስርዓቶች የሚተላለፉ ጉዳዮችን መተንተን፣ ማህበረሰቡ በባህላዊ ስርዓቶች ላይ ያላቸውን አመለካከት መፈተሸ እና ተረኮቹ የማህበረሰቡን ስያሜ፣ አመጣጥ፣ የስራ ባህል እና አምልኮ እንዴት እንደሚገልጹ ማሳየት እንደሆነ ገልጻለች። በማጠቃለያዋ ላይም ከቃላዊ ዝርው ተረኮች መካከል የተወሰኑት የማህበረሰቡ ስያሜ፣ ከአመጋገብ ስርዓታቸው፣ ከንገዱ ስም፣ ከስራ ባህላቸውና በአካባቢው ካለ የእህል ፍሬ መጠሪያ ጋር የተያያዘ እንደሆነ በጥናቷ አሳይታለች። ከዚህ በተጨማሪም የማህበረሰቡን ባህላዊ ስርአቶች በዳሰሰችበት የጥናቷ ክፍል ማህበረሰቡ ከሌላው ማህበረሰብ በተለየ ሁኔታ የአምልኮ፣ የግርዛትና የሰርግ ስነ ስርዓት እንዳለው ገልፃለች።

የምንዳም ሆነ የከሁሉ በላይ ጥናቶች ዝርው ቃላዊ ተረኮቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ፋይዳ መግለፅ መቻላቸው ከእኔ ጥናት ጋር ሲያመሳስላቸው ተረኮቹ ከማህበራዊ ስርአቶች ጋር በማቆራኘት ማጥናት መቻላቸውና የእኔ ጥናት ባህላዊ የአመዳደብ ስልትን በመጠቀም መተንተን ልዩነቱ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡ ጥናቶች በእንዳንዶቹ ላይ መረጃን ከአንድ ቦታ ብቻ መሰብሰብ፣ መረጃን ከመረጃ ሰጪው ፈቃድ ውጪ በድብቅ ለማግኘት መሞከር እና የቃለ መጠይቅ ዘዴም ለመረጃ መሰብሰቢያነት መጠቀምን አለመግለጽ ከመሳሰሉት ጥቃቅን ችግሮች በስተቀር ጠንካራ ጥናቶች ናቸው።

ጥናቶቹ በቃላዊ ዝርው ተረኮች ጭብጥ ላይ የተመሰረቱ፣ በአውዳዊ አገባባቸውና በዘውግ ተከፋፍለው መትረባቸው እና ከባህላዊ ስርአቶች ጋር ተጣምረው የተጠኑ በመሆናቸው እርስ በርስ የሚያለያያቸው ቢሆንም ሁሉም በቃላዊ ተረኮች ትንተና ላይ ማተኮራቸው ያመሳስላቸዋል።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.የኾንሶ ብሄረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ

የኾንሶ ብሄረሰብ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልላዊ መንግስት በሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞን ውስጥ ይገኛል። ይህ ማህበረሰብ የበርካታ ባህላዊና ቁሳዊ ቅርሶች ባለቤት መሆኑ አገራችን በአለም አቀፍ ዘንድ ጭምር እንድትታወቅ አስችሏታል። ለአብነት ያህልም በዩኔስኮ በቅርስነት የተመዘገበውን የእርከን ስራና ባህላዊ መንደሮች፣ እንዲሁም ልዩ የዕደ ጥበብ ስራዎቹን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። በዚህ ምዕራፍ ስለ ኾንሶ ብሄረሰብ ጥንተ አመጣጥ፣ ቋንቋና ማንነት፣ መልክዓ ምድራዊ ገጽታ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በዝርዝር የሚቀርቡ ይሆናል።

### 3.1. የኾንሶ ብሄረሰብ ጥንተ አመጣጥና ቋንቋ

የኾንሶ ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥን በሚመለከት ሁለት አይነት የአፈ-ታሪክ መነሻ ሁነቦች አሉ። አንደኛው ከመረጃ ሰጪዬ ከዶ/ር ገዋዶ አይላዶ1 ያገኘሁትና በጥናቱ በተረከ አስራ ስምንት ላይ የተቀመጠው ብሄረሰቡ ኤታንታ እና ኻውዳ ከሚባሉ የብሄረሰቡ አባላት እንደተገኙ የሚተርከው አፈ ታሪክ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በጥናቱ በተረክ ሀያ አንድ፣ ሀያ ሁለት እና ሀያ ሶስት ላይ ማህበረሰቡ ከኦሮሚያ ክልል ከቦረና አካባቢ ተነስቶ ወደ ኾንሶ መምጣቱን ከአቶ ኩሲያ በየነ2 እና ከሌሎች መረጃ ሰጪዎች የተገኙ ተረኮች የሚተርኩ ናቸው።

ስለ ኾንሶ ብሄረሰብ ጥንተ አመጣጥ ከአያት ቅድመ አያት ሲተረክ የቆየውና በጣም የተሰራጨው ብሄረሰቡ ከሊበን፣ ከቦረና፣ ከገዋዳ፣ ከአሌና ለሎታ አካባቢ ፈልሶ የመጣ መሆኑን ነው (Hallpike, 1972:4)።

የኾንሶ ቋንቋ ብሄረሰቡ መጣበት ተብሎ ከሚታሰበው መነሻ ቦታ ከሚነገረው የኦሮምኛ ቋንቋ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። ኾንስኛ ቋንቋ በብሄረሰቡ «አፋ ኾንሶ» ሲባል እንደ ኦሮምኛ ከምስራቅ ኩሽቲክ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ነው በማለት አቶ ኩራ

---

[1] ዶ/ር ገዋዶ አይላዶ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ናቸው። የብሄረሰቡ ተወላጅና በአሁኑ ሰዓት በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የብሄረሰቡ ተወካይ በመሆን መቀመጫ አላቸው።

[2] አቶ ኩሲያ በየነ የብሄረሰቡ ተወካይ እና የአገር ሽማግሌ።

ጋራ[3] ይገልጻሉ። ቋንቋው ቦረና፣ አሌ፣ ገዋዳ እና ጊዶሌ ከሚነገሩ ቋንቋዎች ጋር ቤተሰብ የሚመደብ በመሆኑ እና ከእነዚህ ጋር የቋንቋና የባህል ተመሳሳይነት ይታይበታል (Hallpike, 1972:3)።

## 3.2. የብሄረሰቡ ስያሜ

እንደ ቁልፍ መረጃ ሰጪዬ ካላ ገዛኸኝ[4] ወ/ዳዊት ከሆነ የኾንሶ ህዝብም ሆነ መሬቱ «ካራታ» ተብለው ይጠራሉ። ቋንቋውም «አፋ ካራት» ይባላል። «ኾንሶ» የተባለው ብሄረሰቡ የሰፈረበት ቦታ ለሰው ልጅ መኖሪያ ተስማሚ፣ ተራራማ፣ ደጋማና ነፋሻማ አየር ያለበት ቦታ «ኾንሲታ» ስለሚባል ከዚያው ስም በመነሳት ብሄረሰቡም «ኾንሶ»፣ ቋንቋው ደግሞ «አፋ ኾንሶ» መባል ጀመረ። በተመሳሳይም (Watson, 1998) ኾንሶ የሚለው ቃል በኾንስኛ ቋንቋ ከፍተኛ ቦታን የሚያመለክት ነው በማለት ጽፈዋል።

## 3.3. መልክዓ ምድር

የኾንሶ ልዩ ወረዳ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ከተዋቀሩት 8 ልዩ ወረዳዎች መካከል አንዱ ነው። የልዩ ወረዳው ዋና ከተማ ካራት ስትሆን ስያሜውም «ካራታ» ከሚባለው የአካባቢው መጠሪያ የተገኘ ነው። ከተማዋ (ከአዲስ አበባ 595 ኪ.ሜ.) ከክልሉ ርዕሰ ከተማ አዋሳ 361 ኪ.ሜ. ላይ የምትገኝ ሲሆን፣ ከባህር ጠለል በላይ ያላት ከፍታ ደግሞ ከ1400-2000 ሜትር ይደርሳል (የደ/ብ/ብ/ሕ/ ፕሮፋይል 2001፣ 152)።

ወረዳዋ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ በተደረገው ውህደት ከልዩ ወረዳነት ወደ ወረዳነት ዝቅ ብላለች። በአዲሱ አደረጃጀት ኾንሶ፣ ዲራሼ፣ ቡርጂና አማሮ ልዩ ወረዳዎችና የአሌ ወረዳ በአንድነት የሰገን አካባቢ ህዝቦች በሚል ዞን መስርተዋል። ዋና ከተማዋ ሰገን ስትባል በቀድሞ አጠራር ጉማይዴ በሚል የምትታወቅ ናት። የኾንሶ ወረዳ በሰሜን

---

[3] አቶ ኮራ ጋራ በኾንሶ ማህበረሰብ ላይ በአማርኛ፣ኦሮምኛና ኾንስኛ ቋንቋዎች በርካታ የስነ ፅሁፍ ስራዎችን ሰርተዋል።

[4] ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት በኾንሶ ብሄረሰብ ውስጥ ካሉት ዘጠኝ ጎሳዎች መካከል የኬርቲታ ጎሳ ባህላዊ መሪ (ፖቅላ) ሲሆኑ፣ ካላ የሚለው መጠሪያ ለዚሁ ባህላዊ መሪ የሚሰጥ የማዕረግ ስም ነው። ስልጣኑንም ከአባታቸው ከካላ ወ/ዳዊት ዳዮቴ የዛሬ9 ዓመት ገደማ ተረክበዋል።

[5] በአሁኑ ሰዓት ኾንሶ ከልዩ ወረዳነቷ ቀርቶ በሰገን ህዝቦች ዞን ተጠቃላ ወረዳ ሆናለች።

ከዲራሼ፣ በደቡብ ከኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ ከቡርጂና አማሮ ወረዳ፣ በስተምስራቅ ከደቡብ ኦሞ እና በሰሜን ምዕራብ ከአሌ ወረዳ ጋር ትዋሰናለች።

ከወረዳው ግብርና ጽ/ቤት በ2004 ዓ.ም. የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የወረዳው የቆዳ ስፋት 200, 000 ሄክታር (2000 ስ. ኪ.ሜ.) ነው። የወረዳዋ አጠቃላይ ህዝብ ብዛት ደግሞ 235,087 ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 113,412 ወንዶች እና 121,675 ሴቶች ናቸው። (CSA. 2007)። የወረዳዋ የአየር ንብረት 30% ወይና ደጋ፣ 70% ቆላ ነው። የሙቀት መጠን ከፍተኛው 34 $^{0}$c ፣ መካከለኛው 28 $^{0}$c ዝቅተኛው ደግሞ 22 $^{0}$c ይደርሳል። (ከወረዳው ግብርና ጽ/ቤት የተገኘ 2005) የዝናብ መጠን በበልግ ከፍተኛው 850 ሚ.ሜ.፣ ዝቅተኛው 550 ሚ.ሜ. እና አማካይ 700 ሚ.ሜ. ሲሆን፣ በመኸር ከፍተኛው 700 ሚ.ሜ.፣ ዝቅተኛው 500 ሚ.ሜ. እና አማካይ 600 ሚ.ሜ. ነው። በኾንሶ ሁለት የሚታወቁ የዝናብ ወቅቶች አሉ። ከየካቲት አጋማሽ እስከ ሚያዚያ ያለው በማህበረሰቡ አጠራር «ሮባ ሀጋያ» ሲባል፣ ሁለተኛው የዝናብ ወቅት ደግሞ ከነሀሴ እስከ ጥቅምት አጋማሽ ድረስ ያለው «ሮባ ካዳና» ይባላል። ከእነዚህ ወራቶች ውጪ ያሉት ደረቃማ ወራቶች ናቸው (Mamitu, 2002)።



የኾንሶ ባህላዊ የእርከን ስራ

የኾንሶ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ በአብዛኛው ተራራማ፣ ገደላማና ወጣ ገባ ሲሆን በከፍተኛ ደረጃ የተሸረሸሩና የተቆራረጡ ሸለቆዎች እንዲሁም መጠነኛ ሜዳዎች ይገኙበታል። (የደ/ብ/ብ/ሕ/ ፕሮፋይል 2001, 152) የኾንሶ ስነ ምህዳር በአብዛኛው ድንጋይ የበዛበት አፈር፣ ለእርሻ አስቸጋሪ፣ ዝናብ አጠር፣ በከፍተኛ ደረጃ ተጠጋግቶ

የሰፈረ ህዝብ የሚኖር እና ሞቃታማ በመሆኑ መሬቱ ለምነት፣ በቂ የግጦሽ መሬት የሌለው፣ ዝናብ አጠርና የሀብት ውስንነት ያለበት ሆኗል፤ ይሁን እንጂ ኾንሶዎች ያሉትን ሀብቶች በአግባቡ በመጠቀም ህይወትን የተመቻቸች ለማድረግ ችለዋል። ብሄረሰቡ ተራራማ መሬቶችን በእጅ መሳሪያዎች በማረስ፣ ንብ በማነብ፣ በንግድና በእደ ጥበብ ስራ ራሱን በማስማራት ታዋቂ ሆኗል (Teferi, 1992:23)።

የኾንሶ መንደሮች እርስ በርስ በተጠጋጉ ቤቶች የተሞሉ፣ መንደሮቹም ዙሪያውን እንደ ምሽግ በድንጋይ ካብ የታጠሩ ናቸው። መንደሮቹም አንድ ወይም ከዚያ በላይ መግቢያ በሮች አሉት። (Shinohara, 1993) ኾንሶን ከሌላው ገጽታው ልዩ የሚያደርገው ከተማው በድንጋይ ካብ (ካዋታ) የታጠረ ከተማ መሆኑ እና ሁሉም ተራራ በእርከን (ካባታ) የተሸፈነ መሆኑ ነው (Shinohara, 1993, Hallpike, 1972)።

የኾንሶ ምድር ጥንታዊ የሰው ልጅ አመጣጥ ጥናት የሚደረግበት ቦታ ነው። በስነሰብ ጥናት ከ1.4 እስከ 1.5 ሚሊየን አመት እድሜ ያስቆጠረ እንደሆሞ ኢሬክተስ፣ አስትራሎፒቴከስ እና የድንጋይ መገልገያ መሳሪያዎች በኢትዮጵያውያን፣ በጃፓናውያን እንዲሁም በአሜሪካዊያን ተመራማሪዎች ጥምረት መገኘቱን (Mamitu, 2002) ዮናስን ጠቅሳ ገልጻለች።

## 3.4. ትውፊታዊ የአስተዳደር ሁኔታ

በኾንሲታ ብሄረሰብ ውስጥ የሚገኙ ዘጠኙ ባህላዊ የጎሳ መሪዎች የአመራርና የዳኝነት ስልጣን አላቸው። በኾንሶ ኬርቴታ፣ ፓሳንታ፣ ቶከማሌታ፣ ኤላይታ፣ ማህሌታ፣ ሳውዳታ፣ እኛላይታ፣ አርካማይታ እና ቴክሳይታ የሚባሉ ዘጠኝ ጎሳዎች ሲኖሩ፣ እያንዳንዱም ጎሳ የጎሳ መሪዎች አሉ። ይህም በጎሳው ዘንድ ከፍተኛ ማዕረግና ክብር መሆኑን የሚያሳይ ነው። የጎሳ መሪዎች «ፖቅላ ቱማ» ወይም «ፖቅላ» ሲባሉ፣ «ቱማ» የሚባለው «ፖቅላው» በቀኝ እጁ የሚያስረው ክብር የተሰራ ክብ አምባር ነው። ስልጣኑም በዘር ለመጀመሪያ ልጅ የሚወረስ ነው። «የፖቅላው» የመጀመሪያ ልጅ የጎሳ መሪነቱን እስኪለያዘ ድረስ እንደማንኛውም ሰው የጎሳው አባል ነው፤ ነገር ግን የስልጣን ሽግግር በሚደረግበት ስርአት ስልጣኑን ከያዘ በኋላ በስርአት እንዲንቀሳቀስ እንደሚገደድ፣ የሚመገበውም ምግብ በጎሳው ሴት ልጃገረድ ብቻ የተዘጋጀ ነው። ከሚኒሊክ II መንግስት በኋላ አንዳንድ የጎሳ መሪዎች ግራዝማች ወይም ቀኝአዝማች የሚል ማዕረግ ተሰጥቷቸው ነበር። የጎሳ መሪዎች ተግባርም ማስተዳደር፣ ፍትህን

ማስፈር፣ የተጋጩ ቡድኖችን ማስማማት፣ አጥፊዎችን መገሰጽ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ መሪ በመሆናቸው መባረክ መሆኑን (shako, 1994:81-85) ይገልጻል።

በጎሳ መሪዎቹ ስር «ቱራይታ» (ፖቺላ ሙኩላ) እና «ግራ» የተሰኙ የማዕረግ መጠሪያ ያላቸው ሹማምንት ይገኛሉ። «ቱራይታ» የፖቺላ ቱማ ምትክ ሆኖ የሚሰራ ሲሆን «ግራ» የጎሳ መሪውን ትዕዛዝና መልዕክት ወደ ተራው ህዝብ የሚያደርስ መልዕክተኛ ነው። ከእነዚህ የተለያዩ የስልጣን ደረጃ ካላቸው የጎሳ መሪዎች ቀጥሎ የታችኛውን የህብረተሰብ ክፍል ችግሮችን በቅርብ ሆነው የሚፈቱ ሶስት ሽንጎዎች ይገኛሉ። እነሱም «ቶላ» (የቤተሰብን)፣ «ካንታ» (የጎረቤት)፣ እና «ፖሊታ» (አጠቃላዩን የህብረተሰብ ጉዳይ የሚመለከቱ) ናቸው።

መንደር ከመንደር ጋር የሚጋጭበት መጥፎ አጋጣሚ ሲፈጠር «መሳያ» ወይም «ዳውራ» በሚል የማዕረግ መጠሪያ የሚታወቁ የብሄረሰቡ መንፈሳዊ አባቶች መልካም መዓዛ ያለው «ሕንሳ» (የዳማከሴ እበባ በእጃቸው በመያዝ በሁለቱ ጠበኛ መንደሮች መካከል ይቆማሉ። በዚህ ጊዜ በግራም በቀኝም ያሉ ተፋላሚዎች ድንጋይ የያዘ ድንጋዩን፣ ጦር የያዘ ጦሩን በመጣል ወደ ውይይትና ድርድር ይገባሉ። ከድርድር ያለፉና አወዛጋቢ የሆኑ ጉዳዮች መሀላ ወደሚፈጸምበት ስርዓት ያመራሉ። ማንም የብሄረሰቡ አባል በመሀላው ስነ ስርአት በሀሰት ቢምል ይቀሰፋል ተብሎ ስለሚታመን አይዋሽም። በመሆኑም ግጭቱ ብዙ ጊዜ በመተማመን ይቋጫል።

በብሄረሰቡ መካከል በሚከሰቱ የዕለት ግጭቶች አጋጣሚ የሰው ህይወት ቢጠፋ «መሳያዎች» «ዳውሮዎች» ጉዳዩ ወደ ቂም በቀል፣ ወደ ከፋ ግጭትና ደም መፋሰስ እንዳያመራ በባህላዊ ስርዓት እርቅ ያወርዳሉ። (የደ/ብ/ብ/ሕ/ ፕሮፋይል 2001, 152)።

ኾንሶዎች ለባህላዊ የአስተዳደር ስልጣን ክብደት የሚሰጡና በእድሜ የተከፋፈለ ስርአት (Age grade system) ልምድ ያላቸው ናቸው። ይህ አይነቱ ባህላዊ የአስተዳደር ስልጣን ለብሄረሰቡ አስፈላጊ እንደሆነና በሚከተሉት መንገዶች እንደሚከፈሉ (Mamitu, 2002) ትገልጻለች።

### 3.4.1. ኼላ (Hella)

ኼላ የመንደሮችን ካቦች (ካዋታ) የመጠገን፣ የውሀ ምንጮችን (ሂርዳታ) የማጽዳት፣ መንደሮችን ከጠላት የመጠበቅና የመከላከል እንዲሁም የህዝብ መሰብሰቢያዎች

(ሞራዎችን) ደህንነት የማስጠበቅ ሀላፊነት አለባቸው። በዚህ ቡድን ውስጥ ዋና ተዋንያን ወንዶች ሲሆኑ «ሂርባ» እና «ካልኩሳ» የሚባሉ ሁለት ዋና ዋና ቡድኖች አሉ።

እያንዳንዱ ሄላ በሁለት ንዑስ ሄላ ተከፍሎ በስምንት ወይም በአስራ አንድ አመት በሚከበረው «ካራ» በሚባለው የስልጣን ሽግግር ክብረ በዓል ላይ በዕድሜ የገፉ ዋና ዋና ኬላዎች ለሌላው ኬላ ስልጣኑን ያስረክባሉ። በዕድሜ ገፋ ያሉ ንዑስ ኬላዎች ለመጀመሪያ ሰባት ዓመታት በስልጣን ላይ የሚቆዩ ሲሆን ተከታዮቹ ኬላዎች ደግሞ እስከ አስራ አንድ ዓመት የስልጣን ቆይታ አላቸው። (Mamitu, 2002) መታሰቢያን በመጥቀስ እንዳስፈረችው።

### 3.4.2. ሰንኬሌታ (Senkeleta)

እያንዳንዱ ንዑስ ኬላ «ሰንኬሌታ» በሚል መጠሪያ የሚታወቅ የተመረጠ መሪ አለው። ምንም እንኳ «ሰንኬሌታ» በኬላ አባላት የሚመረጥ ቢሆንም የምርጫው መስፈርትና ምርጫው በሽማግሌዎች ም/ቤት በሚወሰነው መሰረት የሚከናወን ይሆናል። የምርጫ መስፈርቱም መልካም ስነ ምግባርና ኃላፊነትን የመሸከም አቅምን እንዲሁም ስለ ኾንሶ ብሄረሰብ ባህልና ልማድ ማወቅ ከመስፈርቱ አንዱ ነው። «ሰንኬሌታ» በጣም ጠቃሚ የሆነ ተቋማዊ ሚና ያለው ነው። ሚናውም የሄላ ኃላፊነትን በበላይነት ማስተባበር ነው። (Mamitu, 2002)

### 3.4.3. የሽማግሌዎች ምክር ቤት (Council of elders)

በእድሜ አንጋፋ የሆኑ ሰዎች በባህላዊ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በኾንሶ ቀበሌያት ሁለት ዓይነት ባህላዊ ምክር ቤቶች አሉ። እነሱም የክፍል (ward) እና የቀበሌ ምክር ቤቶች ናቸው። የክፍል ምክር ቤት (ከአስር እስከ አስራ አምስት) የሚሆኑ የጎረቤት ቤተሰቦችን የሚይዝና ተመሳሳይ የሆኑ «ሞራዎችን» የሚያቅፍ ነው። የቀበሌ ምክር ቤቱ ደግሞ በብሄረሰቡ አንጋፋ የሆኑ የሽማግሌዎች ምክር ቤት ሲሆን ከተለያዩ ክፍል (ward) የተውጣጡ አባላትን የሚይዝ ነው። ምክር ቤቱ የቀበሌውን አስተዳደር በበላይነት የመቆጣጠር ኃላፊነት አለው።

የምክር ቤቱ አባላትም የየራሳቸውን ከተማ የዕለት ከለዕለት እንቅስቃሴ የመቆጣጠርና የመምራት ኃላፊነት አላቸው። ከዚህ በተጨማሪም አባላቱ «ኬላው» ወደ ቀጣይ ደረጃ

ማደጉን የሚያረጋግጡና በአካባቢው ልምድ መሰረት በጡረታ የተገለሉ አባላት ስልጣናቸውን ለተጣዩ የዕድሜ ቡድን የማስተላለፍ ኃላፊነት አለባቸው።

### 3.4.4. አባ ቲምባ (Apa Timba)

በባህላዊ አገላለጽ አባ ቲምባ ማለት የከበሮ አባት ሲባል «ቲምባ» (drum) የስልጣን ምልክት ነው። የስልጣን ምልክት መሆኑ በቀደምት የአካባቢው ነዋሪዎች ውሳኔ የተላለፈ ነው። ስለዚህ «ቲምባ» የባህላዊ አስተዳደር (ስልጣን) ምልክት ነው።

አንድ ሰው የ«ቲምባ» ምልክቱን ከያዘ የአባ ቲምባ ኃላፊነቱን በመረከብ ይመራል። እና «ቲምባ» እያንዳንዱን የኾንሶ መንደር እንደ የቅደም ተከተሉ አስተዳድሯል። ስርአቱም ለረጅም ጊዜ ህግ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል። ቲምባ የጎሳ መሰረት የለውም። ከተለያዩ ጎሳዎች የመጡ ሰዎች አባ ቲምባ በመሆን አገልግሎት ሰጥተዋል፤ ነገር ግን የአባቲምባ ስርአት ከአንዱ ቤተሰብ ወደ ሌላው ቤተሰብ ሲተላለፍ የነበረው በልምድ ብቻ ነበር።

የአባቲምባ የምርጫ መስፈርት መልካም ስነ ምግባር፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ማገኘት፣ የህብረተሰቡን ጉዳይ በብቃት መረዳትና ስለ ኾንሶ ማህበረሰብ ልማድና ባህል በቂ እውቀት ያለው መሆንን የሚጠይቅ ነው። አንድ ሰው አባቲምባ ሆኖ ከተመረጠ የሚኖረው የአገልግሎት ዘመን አንድ አመት ይሆናል፤ ይሁን እንጂ በሽማግሌዎች ምክር ቤት ስምምነት መሰረት እንደ የሁኔታው የስራ ዘመኑ ለተወሰኑ አመታት ሊራዘም ይችላል። «ኻውዳ» በመባል የሚታወቁ የዕደ ጥበብ አባላት የአባቲምባ ማዕረግ የማይሰጣቸው ሲሆን ስልጣኑ የሚሰጠው ለአራሾች «ኢቴንታ» ብቻ ነው። ቃለ መጠይቅ (አቶ ጊሊዶ ባደና መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### 3.4.5. ዳውራ (Dawra)

ዳውራዎች በኾንሶ ባህላዊና ልማዳዊ አስተዳደር ውስጥ የሽምግልና እና የአስታራቂነት ሚና ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው። ዳውራዎች ለህዝቦቻቸው ጸሎትና ምህረት የሚያደርጉ ናቸው። ሰዎቹ በብሄረሰቡ ውስጥ ታማኝ፣ ንጹህና መንፈሳዊ ስልጣን እንዳላቸው እንዲሁም ታማኞችና የማስታረቅ ተግባራቸውም ውጤታማ በመሆኑ በማህበረሰቡ ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው፣ የሚከበሩና የሚፈሩ ናቸው።

እነዚህ ሰዎች የማህበረሰቡ የሰላም ጠባቂ እንደሆኑ የሚቆጠር ሲሆን በእጃቸው የሚይዟቸው ረዣዥም በትሮች የሰላም ምልክቶች እንደሆኑ ይታመናል። በጎሳዎች መካከል ግጭቶች ሲነሱ በግጭቱ መሀል በመግባት በትሮቻቸውን ያስቀምጣሉ። ድርጊቱ የበላይ ኃላፊዎችን ትዕዛዝ የሚያሳይ በመሆኑ በግጭቱ ላይ ተሳታፊ የሆኑ ሁለቱ ወገኖች ግጭታቸውን በማቆም ዳኞራዎች የሚያስተላልፉትን የእርቅ መንገድ ይከተላሉ። (Hallpike, 1972)

### 3.4.6. የወንድ አዛውንቶች ቡድን (The old men group)

በኾንሶዎች የእድሜ ምደባ ስርዓት የመጨረሻውን ደረጃ የሚይዩት ከመደበኛ ስራቸው ጡረታ የወጡ ወንዶች ናቸው። እነዚህ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት «ጨቃ» የተባለውን ባህላዊ መጠጥ በመጠጣት፣ «ሞራ» ውስጥ በመቀመጥ ጥጥ በመፍተልና ፀሀይ በመሞቅ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከጓደኞቻቸው ጋር ገበጣ በመጫወትም ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ። ሰዎቹ በማህበረሰቡ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ሚና የላቸውም።

ከላይ እንደቀረበው ኾንሶዎች በዕድሜ የተከፋፈለ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ቡድኖች ሲኖሯቸው እነዚህ ቡድኖችም የየራሳቸው የስራ ድርሻና ሀላፊነት አሏቸው።

## 3.5. ዘመናዊ አስተዳደር

የኾንሶ ወረዳ ወደ በ43 የከተማና የገጠር ቀበሌዎች የተከፋፈለች ናት። 41ዱ የገጠር ቀበሌያት ሲሆኑ፣ ሁለቱ ደግሞ የከተማ ቀበሌያት ናቸው። ይህ የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች አስተዳደር ዝቅተኛው የፖለቲካዊ አስተዳደር አካል ነው። እያንዳንዱ ቀበሌ ብዛት ባላቸው ንዑሳን መንደሮችን ወይም «ካንታዎች» የተከፋፈሉ ናቸው። እነዚህ ቀበሌዎች ተጠሪነታቸው ለወረዳው ም/ቤት መሆኑን አስፍራለች (Mamitu, 2002)።

## 3.6. እምነት

በኾንሶ ሶስት ዋና ዋና የሀይማኖት አይነቶች ይገኛሉ። እነሱም ባህላዊ እምነት፣ የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት ክርስትና እምነቶች ናቸው። 34.62% ባህላዊ እምነትን የሚከተል ሲሆን፣ የክርስትና እምነት ተከታይ ነው። ከዚህ ውስጥ 50.34%

ፕሮቴስታንት ሲሆን፣ ቀሪው 13.81% ደግሞ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ነው። (CSA, 2007)

## 3.7. የኢኮኖሚ ሁኔታ

የኾንሶዎች ኢኮኖሚ በዋናነት የተመሰረተው በግብርና ስራ ላይ ነው። ኾንሶዎች በብዛት የሚያመርቷቸው የግብርና ምርቶች ገብስ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ አደንጓሬ፣ ምስር፣ ባቄላ እና አተር ናቸው። (Watson, 2009) የሽፋን መጠኑም ማሽላ 28.85%፣ በቆሎ 25.96%፣ ጤፍ 12.94%፣ ስንዴ 2.75%፣ ገብስ 2.57%፣ ዳጉሳ 6.24%፣ አደንጓሬ 17.49%፣ እና የፈረንጅ ሱፍ 3.15% ናቸው። (ከወረዳው ግብርና ቢሮ የተገኘ፣ 2005)

በተመሳሳይም ተልባ፣ የጉሎ ፍሬ፣ ዱባ፣ ድንች፣ ስኳር ድንች እና ቲማቲም በወረዳዋ የሚበቅሉና ለምግብነት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ናቸው። (Kansite, 2011) ከዚህም በተጨማሪ ቡና፣ ጥጥ፣ ጫትና ካሳቫ በወረዳዋ የሚበቅሉና ለሽያጭ የሚውሉ ናቸው። ከፍራፍሬ ፓፓያ፣ ማንጎ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ አቡካቶና ሌሎች የፍራፍሬ አይነቶች እንዲሁም በሳይንሳዊ ስያሜው (Moringa stenopetalla) በአገርኛ ስሙ ደግሞ ሽፈራ ይበቅላል።



(ጄዮርክ) ጋዕርጊዮ አካባቢ የሚገኝ የቱሪስት መስህብ ስፍራ

ኾንሶዎች ከእርሻ ስራ በማምራትነት የከብት እርባታ ስራ ያካሂዳሉ። እንዲሁም አልፎ አልፎ በንግድ ስራም የሚተዳደሩ የብሄረሰቡ አባላት አሉ። በተለይ ባህላዊ ልብሶችን ለሌሎች ማህበረሰቦችና ቱሪስቶች በመሸጥ ተጨማሪ ገቢን ያገኛሉ። ወረዳዋ ከቱሪስት

መስህቦች ተጨማሪ ገቢን የምታገኝ ሲሆን፣ ከምትታወቅባቸው የቱሪስት መስኮች ውስጥ የገሰርጊዩ የመሬት ገጽታ (ኒው ዮርክ)፣ በዓለም አቀፍና በአገር አቀፍ ደረጃ የሽልማት ባለቤት የሆንበት የእርከን ስራ (ካዋታ)፣ ጥንታዊ ባህላዊ የአምባ መንደራት እና በዙሪያቸው ያሉ ካቦች (ካዋታ)፣ የህዝብ መሰብሰቢያና ማደሪያ ሸንጎዎች (ሞራዎች) የትውልድ መቁጠሪያ እንጨቶች ያሏቸው መሆኑን በመስክ ምልከታዬ አረጋግጫለሁ።

ኾንሶዎች ከላይ በአካባቢያዊ ዳራዎች ከተገለጹት ቁሳዊ ሀብቶች ሌላ ልዩ ልዩ ትውፊታዊ ሀብቶችም አሏቸው። ከእነዚህ ውስጥም ቃላዊ ተረክ ይገኝበታል። በእነዚህ ቃላዊ ተረኮችም ስለ ታሪካዊ አመጣጣቸው፣ ቋንቋቸው፣ ስያሜአቸው፣ ስለ ባህላዊ መሪዎቻቸው፣ በአካቢያቸው ስለሚገኙ የውሀ ኩሬዎችና ከእነሱ ጋር ስላላቸው ቁርኝት፣ ስለታሪካዊ ቦታዎች አፈጣጠርና ስያሜ ወዘተ ይተርካሉ። የብሂረሰቡ አባላትም እነዚህን ቃላዊ ተረኮች በሁለት ክፍሎች የሚመድባቸው ሲሆን እነሱም «ቶራ» እና «ቶርታ» በማለት መሆኑ በምዕራፍ ሁለት ላይ ቀርቧል። በቀጣዩ ምዕራፍ አውዳዊ ትንተናን (contextual Analysis) መሰረት በማድረግ ተረኮቹ ይተነተናሉ።

# ምዕራፍ አራት

## 4. የኾንሶ ቃላዊ ታሪኮች ትንተና

በዚህ ክፍል ከመስክ የተሰበሰቡ ሰባ ታሪኮች በብሄረሰቡ ባህላዊ አመዳደብ መሰረት የአውዳዊ ትንተና (contextual Analysis) ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግና እንደሚያንፀባቸው ርእስ ጉዳዮች በማደራጀት ትንተና ተሰጥቶባቸዋል።

### 4.1. የብሄረሰቡን ጥንተ አፈጣጠርና ታሪካዊ አመጣጥ በሚመለከት የሚተርኩ

ኾንሶዎች እንደማንኛውም ፍጥረት ሁሉ በእግዚያብሄር የተፈጠሩ መሆኑን ያምናሉ። የዘራቸው መነሻ ቅል መሆኑን በቶርታ አስራ ስምንት ላይ እንዲህ ይገልጻሉ።

> አምላክ በአንድ ወቅት ኾንሶ ይመጣል። እሱ ሲመጣ አንድ ቅል ነበር። ቅሉ ይከፈትና በውስጡ ኢታንታ የሚባል አርሶ አደር ከነእርሻ መሳሪያው ተፈጠረ፤ ቀጥሎም ኼውዳ የሚባል የእደጥበብ ባለሙያ ከነሸመና መሳሪያዎቹ በመፈጠሩ የኾንሶ ምድር በእነዚህ ሁለት ሰዎች ዘር እንደተሞላ በአፈታሪክ ይነገራል።
>
> (ዶ/ር ገዋዶ አይለዶ መስከረም 26 ቀን 2005 ዓ.ም.)

በዚህ ቶርታ የብሄረሰቡ ማህበራዊ መዋቅር ከሁለቱ ባለሙያ ህዝቦች ማለትም ከገብርናና ከእደ ጥበብ ባለሙያዎች መሆኑን ከእነዚህ ሁለቱ ፍጥረት ዘራቸው እንደተባዛ ይተርካል። ኾንሶዎች የአፈጣጠር መነሻቸውን ከቅል ጋር ሲያገናኙ ከቅሉ ሀረግ ጋር በማነጻፀር ነው። ይህም እንደ ቅል ሀረግ የዘራቸውን ስፋት እና በብሄረሰቡ ዘንድ ያለውን ከፍተኛ ማህበራዊ ትስስር ለማሳየት ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአገር ሽማግሌዎችም «ዘራችን እንደ ቅል ሀረግ ተባዝቶ ሰገን[5] ወንዝ ይድረስ።» በማለት ሲመርቁ በመስክ ምልከታ ወቅት ለመስማት ችያለሁ። ከዚህም ቅል በብሄረሰቡ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት እንዳለው ተረድቻለሁ። ከዚያም ባሻገር ብሄረሰቡ ዘውትር እንደ ምግብነት የሚገለገልበትን ባህላዊ መጠጥ «ጨቃ» የሚጠጣው በቅል ነው። ይህ ደግሞ ቅል ከማህበረሰቡ ጋር ያለውን ጥብቅ ተሳስሮ የሚያሳይ ነው። ሌላው በብሄረሰቡ የእርሻ ማሳ ውስጥና ዙሪያም የቅል ተክል መኖሩ፤ አርሶ አደሮችና እረኞች ወደየስራ መስኮቻቸው ሲሄዱና ሲመለሱ ስንቃቸውን[6] ከነያዙበት ቅል እንደሚታዩ አስተውያለሁ። ኪታች ከምንጮቻቸው እና ከኩሬዎቻቸው ጋር በማነሳቸው

[5] ሰገን በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ የሰገን ህዝቦች ዞን ውስጥ የሚገኝ ወንዝ ነው።

[6] ጨ.ቃ የሚባለው ባህላዊ መጠጥ በኾንሶዎች ዘንድ እንደ ስንቅ የሚያገለግል ነው።

ትረካዎች ላይ በስፋት የሚብራራ ቢሆንም ከእነዚሁ የውሀ አካላት በእንስራ ውሀ መቅዳት የሚከለከሉ ሲሆን በቅል መቅዳት ግን ይፈቀዳል። ስለዚህ ቅል ከብሄረሰቡ ጋር ከፍተኛ ትስስር ያለው መሆኑን የሚያጠናክር ነው።

ሌላው የብሄረሰቡን ጥንተ አመጣጥ የሚተርከው ቶርታ ቆየት ያለ ቢሆንም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቶርታ አላቸው።

ይህም በቶርታ አስራ ዘጠኝ (ለ) እንደሚከተለው ቀርቧል።

> ከዚህ በፊት በኾንሶ ባሂሞ የሚባል ቤተሰብ ነበር። ይህ ቤተሰብ ኪቶሌ የሚባል ማካ ውስጥ ቅል የሚያፈራ ተክል ተክሎ ቅሉ እያደገና እየወፈረ እየወፈረ ሄደ። በአካባቢው የሚገኘው ሰው «ይህ ተክል ለምን ከአቅም በላይ እየወፈረ ሄደ?» በማለት እየተከታተሉት ነበር። አንድ ቀን ቅሏ ፈንድታ ለሁለት ተከፈለች። ከዚያ ውስጥም ሁለት ህጻናት ወጡ። በሁለቱ ህጻናት እጅ ላይም የአምባር ምልዕክት ነበር። በአንዱ ህጻን ልጅ ላይ ያለው የአምባር ምልክት የአርሶ አደር ባህላዊ መሪ (ፖቾላ) ምልክት ሲሆን፣ ሁለተኛው የብርቻ ባህላዊ መሪ (ፖቾላ) ምልክት ያለው ነበር። የአርሶ አደር ባህላዊ መሪ ምልክት ያለው «ባሂሞ» ሲባል አሁን ያለው ፋሻ ነው። የብርቻ መሪን የሚወክለው ደግሞ «አባ ኩሜ» ሲባል ያለው ሰውጌሜ ነው።
>
> (መምሩ ቆራይንቶ መስከረም 17 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ይህን ቶርታ የነገሩኝ አቶ መምሩ ቆራይንቶ ሲሆኑ ፋሻ አንድ ጠጅ ቤት ቁጭ ብለን ጠጅ እየጠጣን ነው፤ አጠገቤ ረዳት አጥኚዬ አቶ ኡርማሌ ሎውሲ እያስተረጎመልኝ ነበር።

በምዕራፍ ሁለት ቃላዊ ተረኮች በተስተላልፎ ሂደት እንደ ዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታና ትረካው እንደሚተረክበት ማህበረሰብ ባህላዊ እውድ መሰረት ተስማምቶ የሚቀርብና የተወሰነ ለውጥ የሚያሳይ መሆኑ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልጿል። ይህ ቶርታ ከላይ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም ተረኩ በቅርብ ጊዜ የተፈጸመና በተረኩ የቀረቡት ሰዎችም በብሄረሰቡ ዘንድ የሚታወቁ ሆነው ቀርበዋል። ይህ ተረክ ከላይኛው ተረክ የተወሰነ ለውጥ ብቻ እንዲያሳይ ሆኖ መቅረቡ የንድፈ ሀሳቡን ትክክለኛነት የሚያጠናክር ነው።

በቶርታው ብሄረሰቡ ስላፈጣጠሩ የነበረውን ነባር ታሪክ «ልክ ነው።» ብሎ የተቀበለው መሆኑን ቢታረኩ መደገም አሳይቷል። የቅርቡ ቶርታ የተፈጠሩት የማህበረሰቡ አባላት በስምና በመኖሪያ ቦታ ጭምር እንዲታወቁ በማድረግ ቶርታው ማቅረቡ ተአማኒነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው። በዚህም የብሄረሰቡ ማህበራዊ መዋቅር ከሁለቱ ታላላቅ ባለሙያዎች የተመሰረተ መሆኑን አረጋግጦበታል። የብሄረሰቡ መሰረት የሆኑት ሁለቱ

ባለሙያዎች ያላቸውን የእርስ በርስ ትስስር ከፍተኛ መሆኑንና ሁለቱም በሙያቸው መስመር እንደተጠሉ ለማጽኛነት ተጠቅመውበታል።

የአርሶ አደር ተወካይ የሆነው የህብረተሰብ ክፍልም ኾንሶዎች በግብርና ሙያ በተለይ በእፈር ጥበቃ ላይ ከፍተኛ ስራን በመስራት በአለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂና ተሸላሚ እንዲሆኑም ቶርታዎቹ ብርታት ሆነዋል ማለት ይቻላል። የእደ ጥበብ ስራም እንዲሁ።

በሌላ በኩል ኾንሶዎች ነባር ህዝቦች እንደነበሩ ከላይ የቀረቡት ቶራዎች ቢያመለክቱም ከሌላ ቦታ የመጡ መሆኑን ሌሎች ቶርታዎች ይተርካሉ። ቶርታ ሀያ ሶስትም የሚገልጸው ይህንኑን ነው።

> የኾንሶ ብሄረሰብ ዘጠኝ ጎሳዎች ያሉት ሲሆን አብዛኛው ህዝብ የመጣው ከምስራቅ በኩል ከቦረና ዞን ሊበን ወረዳ፣ ከቡርጂ፣ የካላ ጎሳ ደግሞ በአሌ በኩል ወደ ተልተሌ አልፎ በደቡብ አቅጣጫ አድርጎ ወደ ኾንሶ ካራት ገባ። በመጀመሪያ የመጡት የጎሳ መሪዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ህዝቦች ከእነዚሁ ጎሳዎች ተዋልደው ሊበዙ ችለዋል።
>
> (አቶ ከሲያ በየን መስከረም 17 ቀን 2005 ዓ.ም.)

በሌላ በኩል በቶርታ ሀያ አንድና ሀያ ሁለትም የብሄረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥ ከቦረና አካባቢ መሆኑን ይጠቁማል። በቦታው ለመስፋፋታቸው መሰረት የሆኑት የጎሳ መሪዎች መሆናቸው በተደጋጋሚ ይነሳል። ይህም ምንም እንኳን የብሄረሰቡ አመጣጥ ከሌላ ቦታ ቢሆንም ማህበረሰቡ የተገነባው ከጠንካራ የጎሳ መሪዎች እንደሆነና ጠንካራ ባህላዊ መሰረት እንዳለው ማሳያ ሆኖ ቀርቧል። አሁንም ማንኛውም የኾንሶ ህዝብ ከ9ኙ ጎሳዎች የአንዱ ጎሳ አባል ነው። ይህም የብሄረሰቡ ባህላዊ መዋቅር በጎሳ መሪዎች ላይ የተመሰረተ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ኾንሶዎች በቦታው ነባር እንዳልነበሩና ከሌላ ቦታ መጥተው አሁን ባሉበት ቦታ መስፈራቸውን ቶርታ ሀያ ሶስት ያረጋግጣል።

ከዚህ ሌላ የብሄረሰቡ ቋንቋ[7] ጭምር ከኦሮምኛ ቋንቋ ጋር የሚመሳሰልና ብዙው የኾንሶ ተወላጅ እንደሚናገር በመስክ ምልከታዬ አረጋግጫለሁ። ይህም መጣበት ከተባለው በኦሮሚያ ክልል ከሚገኘው ከቦረና (ሊበን) ጋር መሰረታዊ መነሻ እንዳለው ይጠቁማል። የዘጠኙ የጎሳ አወቃቀርም በኦሮሚያ ከሚገኘው የገዳ ስርአት (Geda System) ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው።

---

[7] ቋንቋው ቦረና፣ አሌ፣ ፃማ እና ጊዶሌ ከሚገኙበት የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ በመሆኑ ከእነዚህ ጋር የቋንቋና የባህል ተመሳሳይነት ይታይበታል (Hallpike, 1972:3)

## 4.2. ኸንሶና ባህላዊ አስተዳደር

በኸንሶ ባህላዊ አስተዳደርና የስልጣን እርከኖች ልዩ ቦታ ይሰጣቸዋል። የጎሳ መሪዎች ብሄረሰቡን ለረጅም አመታት በመሪነት ሲያስተዳድሩ እንደነበር በቃሮታዎቻቸው ይነገራል። ከእነዚህ የጎሳ መሪዎች ሌላ በየደረጃው የሚገኙ ብሄረሰቡን የሚያስተዳድሩ እና ለብሄረሰቡ ህልውና መጠበቅ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ አካላት እንዳሉ ተረኮቻቸው ያስረዳሉ። በአሁኑ ዘመናዊ የአስተዳደር ወቅትም እነዚህ ባህላዊ የጎሳ መሪዎችና በየደረጃው የሚገኙ የባህላዊ አስተዳደር አካላት በብሄረሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት ከፍ ያለ ነው። እነዚህ አካላት መንግስት ለሚሰራቸው ስራዎች ሁሉ ህዝቡን በማስተባበርና በማሳመን ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ እንደሚገኙ በመስክ ቆይታዬ ለማረጋገጥ ችያለሁ። እነዚህን አካላት በሚመለከት በብሄረሰቡ ዘንድ የሚተረኩ ተረኮች እንደየስልጣን ተዋረዳቸውና ተቀባይነታቸው በማቅረብ ትንታኔ ይሰጥባቸዋል።

### 4.2.1. «ፖቻላ» ቱማ

ኸንሶዎች ባህላዊ መሪዎቻቸውን (ፖቻላ) በማለት ይጠሯቸዋል። የኸንሶ «ፖቻላዎች» ከመሪነት ሚናቸው ባሻገርም መንፈሳዊ እንደሆኑ ይታመናል። ባህላዊ መሪ የሚሆኑት የመጀመሪያ ወይም የበኩር ወንድ ልጆች ብቻ ናቸው። ትልቁ መለያቸው ከስልጣን ውርስ ጋር በእጃቸው ላይ የሚያጠልቁት ከንጹህ ብር የተሰራ የእጅ አምባር (ቱማ) ነው። (ቱማው) የስልጣን ምልክት ነው። አሁን አሁን በስልጣን ውርስ የሚገኝ ሲሆን በጥንት ጊዜ ግን ስልጣኑን የሚወርሰው የመጀመሪያ ልጅ ይዞት እንደሚወለድ በቃሮታቸው ይተረካል። ቀጥሎ ባለው ቃሮታ ሀያ አራት የተነገረው ይህን የሚያሳይ ነው።

> በድሮ ጊዜ የኸንሶ «ፖቻላ» ባህላዊ መሪ ወንድ ልጆች ከ«ቱማ» ጋር ይወለዱ ነበር ይባላል። ከረጅም አመታት በፊት የኸንሶ ብሄረሰብ «ፖቻላ»ዎችን ጨምሮ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ባለመፈጸማቸው ምክንያት የባህላዊ መሪ ልጆች ያለ «ቱማ» ይወለዱ ጀመር። ይህንን ምልክት ለመተካት ሲባል በኸንሶ ብሄረሰብ ዘንድ የእጅ አምባር ማድረግ አስፈላጊ እየሆነ መጣ።
>
> (አቶ ጊሊዶ ባደና መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ከላይ በቀረበው ቃሮታ ስልጣን የሚይዙት የብሄረሰቡ አባላት የስልጣን ምልክት ይዘው እንደሚወለዱ፤ ነገር ግን ባህላዊ መሪዎችን ጨምሮ የኸንሶ ህዝብ እግዚአብሄርን በመበደሉ ምክንያት ከስተቱ መቆሙን ይተርካል። ይሁን እንጂ እነዚህ ባህላዊ መሪዎች የስልጣን ምልክት የሆነውን አምባር እየሰሩ ማድረግ መቀጠላቸው ይነገራል።

ይህ ቶርታ ብሄረሰቡ ያለውን የስልጣን ስርአትንና ባህላዊ ተቋሙን እንዴት አጽንቶ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዳስተላለፈ ያሳያል። በቶሮታውም የጎሳ መሪዎች ስልጣን ከላይ (ከእግዚአብሄር) ይሰጥ እንደነበር ይተርካል። ቶሮታው የተነገረበትን አውድ ስንመለከት በአገራችን ስፁመ እግዚአብሄር በሚል ስልጣን በዘር ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚተላለፍበት ዘመን መሆኑን ያመለክታል። «ስልጣን በመንግስት ቢያስተውሉም ባያስተውሉም ባለስልጣናት ሁሉ ሹመታቸውን ከእግዚአብሄር ተቀብለዋልና ሰዎች ሁሉ ሊታዘዙላቸው ይገባል።» (ዮሐ.19፡11 ሮሜ።13፤ 1-7) ከላይ የተሰጠ ስልጣን የማይጣስ፤ የማይገሰስ ነው። ስለዚህም በቶሮታው ህብረተሰቡ የእነዚህን አካላት ስልጣን አሜን ብሎ እንዲቀበል፤ እንዲታዘዝ፤ መንፈሳዊ ቅባትም ያላቸው በመሆኑ እንዲፈራቸውና እንዲያከብራቸው እንዲሁም መንፈሳዊ አገልግሎት ጭምር እንዲሰጡት በማድረግ ባህላዊ መሪዎቹ መሰረታቸው ለዘመናት ሳይናጋ እንዲፀና ያደረጉ መሆኑን ያሳያል።



ኣቶ ገዛኸኝ ወላዊት መረጃ በመስጠት ላይ በቀኝ እጃቸው ላይ የጎሳው ባህላዊ መሪ መሆናቸውን የሚያመለክተውን የብር አምባር (ቱግ) አድርገው ይታያል።

ሰው በምድር ሲኖር ከቶውንም ከሀጢያት አይጸዳምና የማህበረሰቡ አባላትና እነዚህ የማይጣስና የማይገሰስ ስልጣን ያላቸው የጎሳ መሪዎች እግዚአብሄርን በማስቀየማቸው ምክንያት ከላይ ይሰጣቸው የነበረው ሹመት እንደተቋረጠ ታሪኩ ያስረዳል። በመጽሀፍ ቅዱስ ላይም እንደተጠቀሰው «ለእነዚህ ባለስልጣናት ህዝቡ ሊታዘዝ የሚችለው የባለስልጣኑ ትዕዛዝ ከእግዚአብሄር ጋር ሲስማማ ነው።» (የሐዋ. 4፡19፤ 5፡29)

በቶርታው ባህላዊ መሪውን ጨምሮ ብሄረሰቡ በሰራው ሀጢያት ምክንያት መሪዎች ከላይ የሚሰጠውን የስልጣን ጸጋ ቢነፈግም በራሳቸው መንገድ ስልጣናቸውን እንዳቆዩ ተገልጿል። ለዚህም ማሳያው ለስልጣን ተምሳሌትነት ሆኖ የቀረበውን የእጅ አምባር የበኩር ልጆች ይዘውት መወለዳቸውን ሲያቆሙ በራሳቸው ሰርተው መተካታቸው ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታም የኸንሶ «ፖቻላ»ዎች ከእግዚአብሄር ጋር ባላቸው ግንኙነት መሰረት ታላቅ መንፈስ እንዳላቸው በማህበረሰቡ ዘንድ ይታመናል። እነዚሁ መሪዎች በተለያዩ ጊዜአት ተአምራዊ ድርጊቶትን እንደፈፀሙም በቶርታዎች ይነገራል። ይህም በቶርታ 26፣27፣28 እና 29 ላይ ቀርቧል።

ቶርታ ሀያ ስምንትን የነገሩኝ በብሄረሰቡ ካሉት ዘጠኝ ጎሳዎች ውስጥ የኬርቴታ ጎሳ ባህላዊ መሪ (ፖቻላ) የሁኑት ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት ናቸው። እኚሁ ባህላዊ መሪ በኢፌዴሪ መከላከያ ሚ/ር በምህንድስና ሙያ ተሰማርተው እንደነበር ሆኖም ከአባታቸው ከካላ ወልደ ዳዊት ካሮቴ ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው ምክንያት የዛሬ ዘጠኝ አመት ባህላዊ ስልጣኑን መረከባቸውን አጫውተውኛል። የእሳቸውም ማህበራዊ ህይወት በቶርታው ከቀረበው ትረካ እውነታነት ጋር የሚመሳሰል ነው።

ካላ ከኸንስኛ ሌላ ጥሩ የእንግሊዝኛ እና የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆናቸው ከእሳቸው ለምወስደው መረጃ አስተርጓሚ አላስፈለገኝም ነበር። ስለብሄረሰቡ የሚያወራውን ቶርታ የነገሩኝ በእንግዳ መቀበያቸው ውስጥ ሲሆን፣ በጥሩ የመግባባት መንፈስና እርጋታ ነበር።

> ካላ ጥሩ ነገር እንጂ መጥፎ ነገር የሚያመጣ ድግምት አይወድም ነበር። አንድ ቀን ካላና ከተከታይ ልጁ ከሆነው ከሆሌ ጋር ከቡሶ ወደ መሙሎ በሚሄዱበት ጊዜ ሰዎች ለመሰኖ የሚሆነውን ውሀ በድንጋይ ስለከበቡት ከብቶችን ይዘው መሻገር አልቻሉም። ካላ መሻገር ፈልጎ በትሩን በውሀው ላይ በመጣል ውሀውን ለማቆም ቢሞክርም አልሆነለትም። በኋላ ለሆሌ በትሩን ይሰጥና «ውሀው ላይ ጣልበት።» ይለዋል። በዚህን ጊዜ ሆሌ በትሩን ውሃው ላይ ሲጥልበት ውሀው ለሁለት ይከፈላል። ይሻገሩና ካላ ሆሌን «አሁን ደግሞ በትሩን በተከፈለው ውሀ ላይ ጣለው።» ይለዋል። ሆሌም በትሩን ሲጥል ውሀው በቦታው ይመለሳል። በዚህን ጊዜ ካላ ሆሌን የሰራው ጥሩ ነገር በመሆኑ «ሆሌ ሆነህ ይሆን ውሀ ገድበህ እየተጠቀምክ የፓሳንታ ጎሳ አባል ሆነህ ኑር።» ብሎ መረቀው።
>
> (ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት መስከረም 20ቀን 2005 ዓ.ም.)

ለቶርታው ካላ ከልጁ ጋር ወደ መንገድ ሲሄድ ውሀ አላሻግር ሲላቸው ለመሻገር ካላ በበትሩ ውሀውን መከፈል ቢሞክርም እንዳልቻለ፣ ነገር ግን የበኩር ልጁ የሆነውን ሆሌን እንዲሞክር አዞት ልጁ እንደተሳካለትና ውሀውን እንደተሻገሩ ያቀርባል።

በዚህ ቶርታ አባት ያጣውን መንፈሳዊ ሀይል ልጅ በማግኘት ውሀውን በበትሩ ሲከፍለውና ሲያሻግራቸው ይተርካል። ቶርታው መንፈሳዊ ኃይል እንደስልጣን ሁሉ ከወላጅ ወደ ውላጅ መሸጋገሩን ይነግራል። ብሄረሰቡ ውሀ ህይወት ነው ብሎ እንደሚያምን በምልከታዬ አረጋግጫለሁ፤ ስለዚህ በዚች ቶርታ የተጠቀሰው ውሀም የህይወት ተምሳሌት ሆኖ የቀረበና የጎሳ መሪ ምንም እንኳን ፈተና ቢገጥመው በተከታዩ የራሱ ትውልድ አማካኝነት እንደሚሻገር ሆኖ ተስሏል። ቶርታው ሙሴ ቀይ ባህርን በበትሩ በመክፈል እስራኤላውያንን ካሻገረው ታሪክ ጋር እንዲመሳሰል ተደርጎ ቀርቧል።

ቶርታው ለምን ዓላማ ሲባል ተነገረ? የሚለውን ስናይ የባህላዊ መሪዎች ስልጣንም ሆነ መንፈሳዊ ሀይል ወደ ተወላጅ ልጆቻቸው እየተላለፈ የሚሄድና ቀጣይነት ያለው መሆኑን ለማስረገጫነት የቀረበ ነው። በሌላ በኩል የእነዚሁ ባህላዊ መሪዎች የስራ ድርሻ ውስጥ መመረቅ፣ ክፉድ ጥፋት አድርሶ የተገኘ ካለ እንዲያምን ማድረግ «እምቢ!» ካለ መርገምን ያጠቃልላል። በብሄረሰቡም ዘንድ ርግማናቸው ሆነ ምርቃቻቸው ይደርሳል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ ለእነሱ የማይታዘዝ የጎሳ አባል አይኖረም። ቶርታዎቹ የብሄረሰቡን ስነ ልቡና በመያዝ በእነዚሁ የ«ፖችላ»ዎችና ተተኪ ልጆች እንዲመሩ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል።

በሌላ በኩል ኙንሶዎች ዘንድ የባህላዊ መሪነት ምልክት ያላቸው የጎሳው አባላትና ሌሎችም ይህንኑ ምልክት ከያዙ እንደ ባህላዊ መሪ ይቆጠሩ እንደነበር ቶርታዎች ይነግራሉ። ስለዚህም የቤተሰቡ አባላት ሆኑ ሌሎች ከውጭ የመጡ ሰዎች በብልጠትም ሆነ በሌላ መንገድ የባህላዊ መሪውን የብር የእጅ አምባር በእጃቸው ለማስገባት ብዙ ሸኩታ ያደርጉ እንደነበር በተለያዩ ቶርታዎች ላይ ተተርኳል። ይህም በቶርታ ሀያ ስድስት፣ ሰላሳ አንድ እና ሰላሳ ሁለት ላይ የቀረበ ሲሆን ቀጥሎ በአቶ ጊሊዶ ባደና የቀረበውን ቶርታ እንመልከት።

> ዳህሾና ካልማሌ የሚባሉ የቶክመሊታ የአንድ ጎሳ አባላት ነበሩ። ዳህሾ ቱማ ነበረው። ካልማሌ ግን ቱማ አልነበረውም። ሁለቱም ለመታጠብ ወንዝ ሲሄዱ ካልማሌ ዳህሾን «ቱማክን አስቀምጥና እንታጠብ።» ይለዋል። ዳህሾ ያወልቅና ይታጠባል። ከዚያም ካልማሌ ቀደም ብሎ ከውሃው ይወጣና ቱናማውን ይወስድና አጥልቆ ወደ ጃርሶ ቀበሌ ይሄዳል። ካልማሌ ጃርሶ ሲደርስ ሼርቆ የሚባል የኬርቲታ የጎሳ መሪ ቤት ይገባል። በዚህን ጊዜ ሼርቆ ቱማ ስለነበረው እና ሁለት የጎሳ መሪ በአንድ ቦታ ላይ መኖር ስለማይችሉ ወደ ደራ ቀበሌ ሄዶ የጎሳ መሪ ሆኖ በዚያ መኖር ጀመር። ካልማሌም በጃርሶ መኖር ጀመረ።

(አቶ ጊዶና ባደና መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ.ም.)

አቶ ጊሌዶ ይህንን ቶርታ ሲነግሩን ከአስተርጓሚዬ ከአቶ ኡርማሌ ጮውሌ ጋር ነበረኩ። ቶርታው እንደሚተርከው ዳሀሾና ካልማሌ የአንድ ጎሳ አባላት ቢሆኑም ዳሀሾ ቱማ አልነበረውም። ስለዚህ ወንዝ ሲሻገሩ ካልማሌን «አምባርህን አውልቅና እንታጠብ» በማለት በእጁ ካስገባ በኋላ ባህላዊ መሪ መሆን እንደቻለ ይተርካል። እዚህ ላይ መረዳት የሚቻለው በለየያዩ ምክንያቶች የመሪነት ምልክቱን የያዘ ሰው የበኩር ልጅ ባይሆንም ባህላዊ መሪ መሆን እንደሚችል የብሄረሰቡ አባላት በጋራ የሚግባቡበት መሆኑን ነው።

#### 4.2.1.1. «ፖችላዎች» የኾንሶ ምድር ይገባኛል ጥያቄ

በኾንሶዎች ዘንድ በተደጋጋሚ ከሚቀርቡት ትረካዎች ውስጥ አንዱ በባህላዊ መሪዎች ዘንድ ተነስቶ የነበረው የኾንሶ ምድር ይገባኛል ጥያቄ ነው። ይህን አስመልክቶ ከካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊትና ከአቶ ኮራ ጋራ ሁለት ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ቶርታዎች ሰብስቤአለሁ። እነሱም ቶርታ ሰላሳ እና ሰላሳ አንድ ናቸው።



አቶ ኮራ ጋራ ቶርታዎችን በመተረክ ላይ

አቶ ኮራ ጋራ ቶርታ ሰላሳ አንድን ሲነግሩኝ አቶ ጊሌዶ ባደናም አብረውኝ ነበሩ። ቶርታውን ሲተርኩልኝ ልክ እንደ ገጸ ባህሪያቱ ድምጻቸውን ከፍና ዝቅ፣ ጎርነንና ቀጠን እያደረጉ ነው። በዚህም አቀራረባቸው እኔና ለረጅም አመት አብረዋቸው የኖሩት ጓደኛቸው አቶ ጊሌዶ ባደናም ጭምር በተመስጦ እንሰማቸው ነበር። እኚሁ ግለሰብ በኾንስኛ፣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ቶራዎችን ጨምሮ ብሄረሰቡን የሚመለከቱ በርካታ መጻሕፍትን በመጻፍ ለንባብ ያበቁ ናቸው። በግብርና ጽ/ቤት

በባለሙያነት ተቀጥረው በክልሉ የተለያዩ ቦታዎች ላይ በመዘዋወር ለበርካታ አመታት የሰሩ በመሆናቸው መረጃዎችን የሰጡኝ ያለምንም እስተርጓሚ ነበር። ከዚህም ሌላ እጅግ ተግባቢና ታሪክና ጨዋታ አዋቂ ስለነበሩ በመስክ ቆይታዬ ደስተኛ እንድሆን አድርገውኛል። የግባት ጥያቄ በቶርታ ሰላሳ አንድ እንደሚከተለው ተተርኳል።

> የካላ ጎሳ ወደ ኾንሶ ሲመጣ በየቦታው እያረፈ ኾንሶ ካራት አካባቢ ኩተሌ በሚባል ስፍራ ተቀምጦ እያለ ካላ በአካባቢው በ(ፖችላንት) የተቀመጠውን ቲቲባን ሄዶ «እባክህ እኔ እንግዳ ስለሆንኩ እንወዳጅ።» ብሎ ይጠይቀዋል። ቲቲባም ይቀበለውና አብረው ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ ካላ ዘዴ ይፈልግና «አንተ ትልቅ መሪ ነህ እኛ እዚህ ስንተኛ ጠላት መጥቶ አንድ ነገር ቢያደርገንስ? ስለዚህ አንድ ነገር ማድረግ አለብን።» ይለዋል። ቲቲባም «እሺ!» ይላል። ካላ «በአንተ ቤት ዙሪያ መሬቱ ላይ አመድ ነስንሰን እንደርና ሌሊት ጠላት መጥቶ የሚሰልለን ከሆነ እናውቃለን።» አለው። ከዚያም ካላ የተነሰነሰውን አመድ ሌሊት የሚረጋግጡ ሰዎች አዘጋጀ። ጠዋት ሲፈተሽ አመድ የተነሰነሰበት መሬት በእግር ተረጋግጧል። ካላም «ይኸው አላልኩህም እንዴ? ጠላት እየፈተሸን ነው።» አለው። ቲቲባም «እውነትም ይህ ሰውዬ አዋቂ ነው፤ በቃ እኖረዋለሁ።» ይላል። ቆይቶ ካላ «መሬቱ የኔ ነው።» ይላል። ቲቲባም «እኔ በእንግድነት ስቀበልህ እንዴት መሬት የኔ ነው ለማለት ቻልህ?» በማለት ሲከራከሩ ካላ «መሬቷ ራሷ ትመስክር!» ብሎ ቃል አስገባው። ቲቲባም «ትመስክር፤ መሬቱ የኔ ነው፤ እንጂ ያንተ አይደለም።» ይላል። ካላ «እንግዲህ ነገ ሄደን መሬት ትናገራለች።» ይላል። ቲቲባም «አትናገርም፤ ከተናገረችም ጥሩ ነው።» ብለው ይወጣሉ።
>
> ካላ ሄዶ ጉድጓድ ፈጥሮ ውስጡ ሰው አኖረ። ከዚያ በኋላም ካላ ቲቲባን «በል ራስህ መሬትን ጠይቅ።» ይለዋል። ቲቲባም «ቲቲባያ!» «ቲቲባያ!» «ቲቲባያ!» እያለ ሲጠራ «አቤት!» አላለችም። «ይኸው ያንተ መሬት አይደለም፤ መልስ አልሰጠችም፤ በል አሁን ደግሞ እኔ ልናገር።» ይላል። ቲቲባም «ተናገር መቼ መሬት ይናገራል?» ይላል። ከዚያ ካላ «ካላይዲያ» «ካላይዲያ» «ካላይዲያ» ሲል «ኧ!» በማለት መሬት ድምጽ አሰማች። ካላ «መሬቱ የራሴ ነው። አላልኩህም?» ሲል እንግዲህ «መሬት ያልመሰከረለት መሬቱን ይለቃል።» ስለተባባሉ ቲቲባ መሬቱን ለመልቀቅ ግድ ስለሆነበት ወደ ዲራሼ ሄዶ ሰፈረ። እዚያ ሄዶ ቲቲባ የዲራሼ ጎሳ መሪ ሆነ።
>
> (አቶ ካራ ኩራ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ከላይ በቀረበው ቶርታ የቀረበው ካላና ቲቲባ አብረው ከኖሩ በኋላ «በመሬት ይገባኛል» ጥያቄ ከፍተኛ ክርክር ውስጥ ይገባሉ። በመጨረሻም መሬት እንድትፈርድ በማድረግ ተሰማምተው ካላ በብልጠት መሬትን የራሱ ሲያደርግ ቲቲባ ቦታውን ለመልቀቅ ግድ እንደሆነበት ተርኳል። በቶራውም በየትኛውም አይነት መንገድ የተገባ ቃል የሚከበር በመሆኑ ቲቲባ ቃሉን በማክበር ኾንፈቱን ተቀብሎ ወደ ዲራሼ ሲሄድ ያሳያል።

ወደ ትንታኔው ስንገባ ቶርታው ለምን ቀረበ? ብለን ስንመለከት ሁለት ነገሮችን ማንሳት ይቻላል። አንደኛው ከቦታ ጥበት አንጻር ሊታይ ይችላል። በተጨባጭ እንደሚታየው የኾንሶ መልክዓ ምድር ለእርሻ ስራ አስቸጋሪ ነው። ከእለት እለት የህዝቡ መጨመር ባለው የተፈጥሮ ሀብት ለመጠቀም እጥረትን ማስከተሉ አልቀረም። በቶርታው ላይም

ሁለቱ ባህላዊ መሪዎች የመሬት ይገባኛል ጥያቄ ማንሳታቸው ከመሬት ጥበትና ከሀብት ውስንነት የመነጨ መሆኑን ማየት ይቻላል። ስለዚህ ባለው ሀብት ለመጠቀም አንዱ የጎሳ መሪ ከስቤተሰቡ ቦታውን መልቀቅ ግድ ይሆናል። ቶርታም የመሬትና የመኖር ጥያቄ የህልውና ጉዳይ መሆኑንን አሳይቷል።

ሁለተኛው ነጥብ መሬትን ያለግጭትና የደም መፋሰስ የራስ አድርጎ ለማስቀረት ባህላዊ መሪዎች ዘንድ የተደረገው የመፍትሄ ሀሳብና ጥበብ እንዳለ ማሳየት ነው። «ፖችላ»ዎች የህዝብ አስተዳዳሪ እንደመሆናቸው መጠን በሆነው ባልሆነው የደም መፋሰስ እንዳይኖር በጣም የሚጠነቀቁ ናቸው። ይህም ማህበራዊ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ በመሆኑ ነገሮችን የሚያዩት በጥንቃቄ፣ ለችግሮችም መፍትሄ የሚሰጡት በዘዴ መሆኑን ቶርታው አሳይቷል። ካላ ገባኸንም በቶርታ ሰላሳ ላይ የንገሩኝ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው።

### 4.2.2. ቲምባ

ቲምባ በብሄረሰቡ ዘንድ እንደ በትረ ስልጣን የሚቆጠር ክበር ነው። ይህንን አስመልክቶ ቶርታ ሰላሳ አራትን የነገሩን አቶ ቱሬ ካምብር ናቸው።

> ኩበው አመታት በፊት የኾንሶ መኖሪያ ቤቶች ተበታትነው ይሰሩ ነበር። በኋላ ህዝቦች ተሰባስበና «አንድ ላይ ተሰባስበን ብንኖር ጥሩ ነው።» ተባባሉ። ከዚያም ባፍ ቆረጡና ቲምባ (ክበር) ሰርተው እንዲህ ተባባሉ «የክበሮው ባለቤት (አባ ቲምባ) የማስተዳደር ስልጣን አለው፤ ግጭት የፈጠረ ቀበሌም ሆነ ግለሰብ ለአባ ቲምባው ግብር ይከፍላል።» በማለት ክበሮውንም ልክ እንደሰው የሚሰማና የሚናገር እንደሆነ ህዝቡ ተስማምቶ ነበር ይባላል።
>
> በዚህ ሁኔታ ግጭት ሲፈጠር ሁሉም ወደ ክበሮው ዘንድ ሄዶ ሀሳቡን በክርክር ይገልጽ ነበር። በአንድ ወቅት አንድ ሰው ግጭት ፈጠረና አባ ቲምባው «ይህ ሰው ለከተማው ቅጣት ይክፈል አለ።» የአካባቢው ሰዎች ቅጣቱን እንዲከፍል ጠየቁት። ይሁን እንጂ ሰውዬው ቅጣቱን ላለመክፈል ተቃወመ። በዚህን ጊዜ ኾንሶዎች ይህንን ሰው ለማባረር ወሰኑ። ስለዚህም ሁሉም «እሳት አናስጭርህም፤ ውሀ አናስቀዳህም፤ ከአንተ ጋርም አብረን አንሰራም።» በማለት ሁሉም አገለሉት። ከዚያ በኋላ ሰውዬው ከተማውን ለቆ በመሄድ ከሌሎች ህዝቦች ጋር አብሮ መኖር ጀመረ።
>
> (አቶ ቱሬ ካምብር መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ይህ ቶርታ ኾንሶዎች ተበታትነው ከመኖር ይልቅ በአንድ ላይ ቢኖሩ የተሻለ እንደሚሆን መስማማታቸውን፣ በጋራ ሲኖሩ በመሀላቸው ችግር እንዳይፈጠር እንደ ህግ ሆኖ የሚያገለግል ክበር ከእንጨት እንደሰሩ ይተርካል። ይህ ቲምባም ሁሉንም የብሄረሰቡን አባላት እኩል እንዲያገለግል ልክ እንደ ሰው እንደሚሰማና በትክክልም እንደሚፈረድ መስማማታቸውን ይገልጻል። በቶርታው መሰረት ጥፋት ያጠፋ

የብሄረሰቡ አባል ቅጣት ይከፍላል። ጥፋተኛው የተጣለበትን ቅጣት «አልከፍልም።»ካለ ከብሄረሰቡ እንደሚገለል ጥምር ያስረዳል።

የቶርታውን እውድ ስንመለከት ብሄረሰቡ አንድ ጠንካራ ማህበረሰብን ለመፍጠር ያስቻለው መሆኑን የሚያሳይ ነው። ተብታትኖ ከመኖር ይልቅ አንድ ላይ መኖሩ እርስ በርስ ለመደጋገፍና ጠንካራ ማህበራዊ መሰረትን ለመፍጠር እንደሚጠቅም እንዲሁም «አንድነት ሀይል ነው።» የሚባለውን ብሂል የተረዳበት መሆኑን አሳይቷል። በተመሰረተው ማህበረሰብ ውስጥ በሚያጋጥሙ የእርስ በርስ አለመግባባቶች ምክንያት አንድነቱ እንዳይፈርስ ለማድረግና በጥንካሬው እንዲቀጥል ለማስቻል እንደ የጋራ መተዳደሪያ በመሆን ህግ እንዳበጀ ያሳያል። ቲምባው የህግ ውክልና እንዳለው በሁሉም ዘንገድ የጋራ መግባባትም አለ። ምናልባትም የዚህ አይነቱ ባህላዊ ህግ ለዘመናዊ ህግ መነሻ በመሆን አሻራውን አኑሮ ይሆን? የሚለውን ጥያቄ በውስጤ አጭሯል። መልሱን ሌሎች ተመራማሪዎች አጥንተው ቢመልሱት፣ በሚል ለእነሱ በመተው ኹንሰዎች ግን ጥንታዊነት ያለው የህግ መሰረት ያላቸው መሆኑን በቶርታቸው አሳይተዋል።

ቲምባውም በየተራ በየመንደሩ እየተሸከረከረ ለተወሰኑ አመታት እንደሚቆይ ከበሮው በእጁ ላይ የሚገባው የብሄረሰቡ አባል በትረ ስልጣን እንደጨበጠ ስለሚቆጠር አካባቢውን የማስተዳደር ስልጣን አለው። በተመሳሳይ መንገድ በቀረቡ ቶራ ሰላሳ አምስትና ሰላሳ ስድስት ላይ ቀርቧል። ቲምባው በእጁ ያለ የብሄረሰቡ አባል «አባ ቲምባ» ሲባል የክብር አባት የሚል ፍቺን ይሰጣል። ግለሰቡም የስልጣን ባለቤት ነውና የማስተዳደርና የመፍረድ ሚና ይኖረዋል።

ወደ ቶርታው ትንታኔ ስመለስ የብሄረሰቡ አባላት ቲምባው እንደሚሰማና ትክክለኛ ፍርድ እንሚሰጥ፣ እንዲሁም ብሄረሰቡ ካስቀመጠው ህግ ያፈነገጠ ቀረጥ እንደሚከፍል መስማማታቸው በቶርታው ተመልክቷል። ይህም የብሄረሰቡ ደንብ በቀላሉ እየተጣሰ አንዱ አንዱን እንዳይበድልና እርስ በርስ ተከባብሮና ተቻችሎ እንዲኖር ለማድረግ መሆኑን ያሳያል። የትኛውም የብሄረሰቡ አባል እንደ ልቡ እየተነሳ ማህበራዊ ስርአታቸውን እንዳያናጋ ከቀላል እስከ ከባድ የቅጣት ድንጋጌ ማስቀመጣቸውን ያሳያል። በቶርታው ላይም ለቲምባው እልገዛ ያለውን አባል በማንኛውም ማህበራዊ ተሳትፎ እንዳያደርግ በማገለል አካባቢውን እንዲለቅ ሲደረግ አሳይቷል። ይህም ሁለት አይነት አገልግሎት እንዳለው ያመለክታል። አንደኛው ቅጣቶችንና መገለልን በመፍራት ሰው ጥፋት እንዳይፈጽም በማድረግ የማህበረሰቡን ባህላዊ አንድነት እንዳያናጋ ብሎም እንዳይፈርስ ማድረግ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአጥፊው ላይ

የሚፈጸመው ቀላልም ሆነ ከባድ ቅጣት ለሌሎች መቀጣጫ እንዲሆን ለማድረግ ያገለግላል። ሁለተኛው፣ ጥፋት የፈጸመው ግለሰብ የሚቀጣው ለአካባቢው ባህላዊ አስተዳዳሪ ኢኮኖሚያዊ አቅም እንዲጠናከር ማድረግ ነው። ቶሮታው ብሄረሰቡ ከዘመናዊ የህግ ስርአት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ነባር የህግ ስርአት እንዳለው የሚጠቁም እና የቲምባ ህግ ይግባኝ የሌለው እንዲሁም የህግ የበላይነት መከበርን የሚያሳይ ነው።

### 4.2.3. «ዳውራ» ወይም «መሳያ»

በኾንሶ ባህላዊ አስተዳደርና የስልጣን እርከኖች ዳውራዎች ልዩ ቦታ ይሰጣቸዋል። አቶ ቱሬ ካምብሮ የተረኩልኝ ቶራ ሰላሳ ሰባት ይህን ይገልጻል።

> በዱሮ ጊዜ ኮንሶ ውስጥ ሁለት ቀበሌዎች ከፍተኛ ውጊያ ሲያደረጉ ሳራና የቲምባ ባለቤቶች ጦርነቱ እንዲቆም ሰዎች መልምለው ላኩ። ነገር ግን በሁለቱ ተዋጊ ወገኖች ሰላም እንዲሰፍን ማስገደድ አልተቻለም። በኋላ ሊሂታ ከምትባል ትንሽ መንደር «ናማ ዳውራ»[5] የሚባሉ አስታራቂዎች በሁለቱ ተዋጊ ወገኖች በኩል ማዕተብ በመጣል በረቀቀ ዘዴ ጦርነቱ እንዲቆም በማደረጋቸው ሁለቱ ተዋጊ ወገኖች በሰላምና በክብር ከጦርነት እንዲወጡ አደረጉ።
>
> (አቶ ቱሬ ካምብሮ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ከላይ በቀረበው ቶሮታ የጎሳ መሪዎችና አማካሪዎች ግጭቱ እንዲቆም ለማድረግ ቢሞክሩም እንዳልተሳካ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ሲመጡ ግን ጦርነቱ እንደቆመ ይተርካል።

በዚህ ቶራ የማህበረሰቡ ደህንነት በተለያዩ ምክንያቶች እንዳይናጋ ልዩ ልዩ ስልጣንና ኀላፊነት ያላቸው ሰዎች መኖራቸው አስፈላጊ መሆኑን ነው። በቶሮታው እነዚህ የማህበረሰቡ አባላት የሰላም አባት በመሆን ሲያገለግሉ ይታያል። ከዳውራዎቹ ሌላ ሌሎች ሰዎች ተልከው ጦርነቱን ማስቆም ያለመቻላቸው ያላቸውን ከፍተኛ ተቀባይነትና ተፈሪነት ያመለክታል። ዳውራዎች በኾንሶ ብሄረሰብ ዘንድ እጅግ የተፈሩና የተከበሩ ናቸው። መንደር ከመንደር በሚጋጭበት ጊዜ ግጭቱ መካከል

---

[5] (የዶ/ብ/ብ/አ/ ፕሮፋይል 2001፣ 152)። በወረዳው ውስጥ ግጭት በሚነሳበት ወቅት «ዳውራ» ወይም «መሳያ» በሚባል ማዕረግ የሚታወቁት የወረዳው አባላት «ሆንሳ» (የዳማክሌ አበባ) በመያዝ በሁለቱ ጠበኞች መንደር መካከል ይቆማሉ። በዚህ ጊዜ በጉራም በቀኝም ያሉ ተፋላሚዎች ድንጋይ የያዘ ድንጋዩን ጦር የያዘ ጦሩን በመጣል ወደ ውይይትና ድርድር ይገባሉ። ከድርድር ያለፉ አወዛጋቢ የሆኑ ጉዳዮች ካጋጠሙ መሃላ ወደሚፈፀምበት ቦታ በሕግ ሥርአት ያመራሉ። ማንም የወረዳው አባል በመሃላው ስነ ስርአት በሐሰት ቢምል ይቀሰፋል ተብሎ በጽኑ ስለሚታመን አይደፍሩም። በመሆኑም ግጭቱ ብዙ ጊዜ በመተማመን ይቋጫል።
በወረዳው መካከል በሚከሰቱ የሰላት ግጭቶች አጋጣሚ የሰው ህይወት ቢጠፋ «ዳውራዎች» ወይም «መሳያዎች» ጉዳዩ ወደ ቂም በቀልና ወደ ከፋ ግጭትና ደም መፋሰስ እንዳያመራ በባህላዊ ስነ ስርአት እርቅ ያወርዳሉ።

በመገኘት ፍልሚያውን በማስቆም የእርቅ ስነ ስርአት እንዲፈጸም ያደርጋሉ። የብሄረሰቡ አባላት እነሱን አልቀበል ያለን ይረግማሉ፤ እርግማናቸውም ቶሎ ይደርሳል ብለው ያምናሉ። ስለዚህ ይፈሯቸዋል፤ ያከብሩዋቸዋልም።

በቶርታው ኾንሶዎች እንደዚህ አይነት ሰዎችን ማስቀመጣቸው በእርስ በርሰ ግጭቶች አማካኝነት የማህበረሰባቸው አንድነት እንዳይናጋና እንዳይፈራርስ ለማድረግ ነው። ይህ ቶርታ የቀረበበትን ማህበራዊ አውድ ስንመለከት ሰዎቹ በትድሚያ በጦርነቱ መካከል ከመገኘት ውጪ ምንም ነገር አይተነፍሱም። በግጭቱ መካከልም «እንነዳለን።» የሚል ስጋት አይኖራቸውም። እነሱን የተመለከተ ማንኛውም ተዋጊ በቶፕታ ውጊያውን ግቶም መቻሉም ሰዎቹ በማህበረሰብ ውስጥ ምን አይነት ቦታ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። የሰዎቹ በጦርነቱ መካከል መገኘት ብቻ የትኛውም ወገን ጦርነቱን እንዲያቆም የሚያስገድድ መሆኑን እንደ ቋንቋ ሁሉ በተዋጊዎች መካከል በጋራ እንደሚያግባባቸው አሳይቷል።

### 4.2.4. የአገር ሽማገሌዎች

በኾንሶ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ከላይ በስልጣን ተዋረድ መሰረት ከተጠቀሱት የማህበረሰቡ አባላት ቀጥሎ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው የአገር ሽማገሌዎች ናቸው። እነዚህ የአገር ሽማገሌዎች አብዛኛውን በጡረታ ላይ የሚገኙ ናቸው። ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት በሞራዎችና በመንደር አካባቢ ገበጣ በመጫወትና «ጨቃ» በመጠጣት ነው። ከዚህም ሌላ በሽምግልናና እርቅ፣ ስለብሄራሰባቸው በመምከርና ታሪካቸውን ለትውልድ በማስተላለፍ ያገለግላሉ። በተለይ ብሄረሰቡን የሚመለከቱ ቶራ እና ቶርታዎችን ከእነሱ ሌላ ወጣቶችና ሴቶች መተረክ እንደማይፈቀድላቸው በመስክ ምልከታዬ ታዝቢአለሁ።

የአገር ሽማገሌዎቹ ምንም እንኳን በእድሜ ቢገፉም ጥበበኛና መፍትሄ አዋቂ መሆናቸው በብሄረሰቡ ዘንድ ይታመናል። በዚሁ ዙሪያ ከሚታወቁ ቶርታዎች ውስጥ አንዱን ቶርታ ሰሳሳ ስምንትን አቶ ጊሌዴ ባደና እኔ፣ ዶ/ር ገዋዶ አይለዶ፣ አቶ ዲዶ ገለቦ እና አቶ ቱሬ ካምብር ባለንበት በዱራይቱ ቀበሌ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ ነግረውኛል።

> በድሮ ጊዜ አንዲት ሴት በኾንሶ ምድር ላይ ነግሳ ነበር። ይህቺ ንግስት ባሎችን የመግደል ስልጣን ተሰጥቷት ስለነበር በአገሪቱ ላይ ያሉትን ባሎች ባጠቃላይ ማጥፋት ጀመረች። አንድ ልጅ ይህንን ሰምቶ ኖሮ ወደ አባቱ በመሄድ ንግስቲቱ ባሎችን በጠቅላላ እየገደለች መሆኑን ነገረው። አባትየውም እርሱ ከደበቀው እንደሚተርፍ አስረዳው። ልጁም አባቱን ደብቆ ከሞት አዳነው።

በአንድ ወቅት ንግስቲቱ በክር ጨርቅ ሰርተው ተራራውን እንዲያለብሱ የአገሩን ልጆች አዘዟቸው። ልጁም ተደብቆ ወደነበረው አባቱ በመሄድ የታዘዙትን ነገረው። አባትየውም «ተራራው ላይ ሄዳ ነው? ወይስ ከቤት ሆና ነው የምትመለከተው?» ሲል ጠየቀው። ልጁም ከቤት ሆና እንደምትመለከት መለሰለት። አባትም «ተራራውን በሙሉ አታጥልና ሊንጋ ሲል አጥፋው።» ሲል መከረው። ልጁም እንደመከረው አደረገ። በማግስቱ ንግስቲቱ ከቤት ሆና ተራራውን ስትመለከት የተቃጠለውን ቁጥቋጦ ተመልክታ ጥቁር ጨርቅ ስለመሰላት ልጁን አመሰገነች። በሁለተኛው ቀን በሁለት ጎኑ ወንር ባለው ቆዳ የተሰራ ጫማ እንዲያመጡ አዘዟቸው። ልጁም ሄዶ የታዘዙትን ለአባቱ ነገረው። አባትየውም «ሁለቱን የአህያ ጆሮ ቆርጠህ ይዘህላት ሂድ።» አለው። ልጁም አባቱ እንዳለው በማድረጉ ተመሰገነ። በሌላ ቀን ደግሞ ንግስቲቱ «ቁንጫ በስልቻ ሞልታችሁ አምጡልኝ።» ስትል አዘዟቸው። ልጁም ወደ አባቱ ሄዶ ምክር ጠየቀ። አባትም «የፍየል ፍግ በስልቻ ሞልተህ አስተምጥ። ቁንጫም ቀስ በቀስ እየገባ ይሞላዋል።» አለው። ልጁም በማዳበሪያ ቁንጫውን ሞልቶ ወደ ንግስቲቱ ሄደ። እርሷም «ጥሩ ነው!» ብላ ካመሰገነችው በኋላ ቀጣይ ትዕዛዟን ገለጸች። ትዕዛዟም «ጎጆ ቤት ትሰሩላችሁ፤ ቤቱ ግን ምሰሶውን ጨምሮ ሙሉ በሙሉ የሳር መሆን አለበት።» የሚል ነበር።

የአገሩ ልጆች በሙሉ በትዕዛዙ ክብደት ይጨነቁ ነበርና ልጁ ወደ አባቱ ሄዶ መፍትሄ እንዲጠይቅላቸው ጠየቁት። ልጁም ለአባቱ ትዕዛዙን ሲነግረው «ዛሬ የንግስቲቱ ሞት ይሆናል።» በማለት እንዲህ ሲል መከራቸው። «አንድ በቅሎ መርጣችሁ በደንብ ከገረፋችኋት በኋላ ለንግስቲቱ ስጧት። እሷም በቅሎዋን በምትጋልብበት ጊዜም ንግራውን ይዛችሁ ከበቅሎዋ ፊት ቁሙ።» አላቸው። ልጆቹም እንደተባሉት ሲያደርጉ በቅሎዋ አለንጋውን ስታይ ፈርታ እየተደናበረች ንግስቲቱን ይዛ ገደል ገባች። በዚህን ጊዜ ንግስቲቱ «ባሎችን ገድዬና ህዝቤን አስጨንቄ በራሴ ላይ ሰበብ አመጣሁ። ከእንግዲህ እኛ ሴቶች ለወንዶች እንገዛ።» አለች ይባላል።

(አቶ ጊሊዶ ባደና፣ መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ.ም.)

በቶርታው አንድ የአገር ሽማግሌ የአገሪቱ ንግስት የሆነች ወንዶችን ስታጠፋ በልጃቸው እርዳታ መደበቃቸውን ይተርካል፤ ሆኖም የአገር ሽማግሌው እጅግ አዋቂና ብልህ ነበሩና በንግሲቲቱ አማካኝነት ለልጃቸውና ለአካባቢው ወጣቶች የሚተላለፈውን አስቸጋሪ ትዕዛዝ ከጀርባ በመሆን ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ልጆቹ በዘዴ ትእዛዟን እንደፈጸሙ አድርጋ እንድታምን ማድረጋቸውን ይነግራል። ለልጆቹ የሚተላለፈው ትዕዛዝ እየከበደ ሲመጣ መጥፊያዋን በትእዛዟ አስታከው ያመቻቻሉ በመጨረሻም ይሳካና ንግስቲቱ የእጇን እንድታገኝ ያደርጋሉ።

ይህ ቶርታ ብዙውን ጊዜ የሚነገረው በአገር ሽማግሌዎች ነው። አገልግሎቱም ልጆችን ለመምከርና ለማሳወቅ ነው። ከዚህ አንጻር የቀረበበትን ማህበራዊ አውድ ስንመለከት የአገር ሽማግሌዎች እጅግ ብልህና መፍትሄ አዋቂ እንደሆኑ ለአዲሱ ትውልድ ለማሳወቅ ነው። የትረካው ማዕከላዊ ነጥብ የብሄረሰቡ ህልውና ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍ የእነዚሁ አካላት አስፈላጊነትን ማረጋገጥ ነው። በቶራው እንደቀረበው ሽማግሌ እንደሊሉች ወንዶች ቢገደሉ ኖሮ አዲስ ትውልድ አደጋ ላይ ይወድቅ እንደነበር አመልክቷል። ወጣቱ ትውልድም ያለእነዚህ አካላት የተሟላ እንዳልሆን

አሳይቷል። ለአዲስ ትውልድ ማሸነፍ የሚቻለው በጉልበት ብቻ ሳይሆን በጥበብ መሆኑን ለማስተማሪያነት አገልግሏል። የብሄረሰቡ ማንነት የተገነባው በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ማለትም በህጻናት፣ ወጣቶችና ሽማግሌዎች በመሆኑ አንዱ ለአንዱ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመስበክ እርስ በርስ በመከባበር የማህበረሰቡን ትስስር ለማጠናከር ጥቅም ላይ ውሏል።

እነዚህ የብሄረሰቡ አባል የሆኑ የአገር ሽማግሌዎች ከአካባቢያቸው ግጭት እንኳን ቢፈጠር ነገሩን በትዕግስት እንደሚያዩና የመጣውን ጦር አቅም ካስጠኑና ከገመገሙ በኋላ ወጣቶች እንዲዋጉ መርቀው እንደሚልኩ ወጣቶችም ያለእነሱ ፍቃድና ምርቃት ዘለው ወደ ውጊያ እንደማይገቡ ቁልፍ የሆኑት መረጃ አቀባዬ ዶ/ር ገዋዶ አይላዶ ካራት ከተማ በተከራየሁት ቤት አጫውተውኛል። በመስክ ምልከታዬም ብሄረሰቡን የሚመለከት ማንኛውንም መረጃ ሊሰጡ የሚችሉት እነዚሁ ሰዎች ናቸው። በተለይ ወጣቱ ስሜታዊ በመሆኑ የተዛባ መረጃ ይሰጣል ተብሎም ስለሚታመን መረጃ መስጠት ወቅት ነገሮችን ለሽማግሌዎች ከማስታወስ የዘለለ ሚና እንደሌለው አይቻለሁ።

### 4.3. የኾንሶዎች እርከንና እደ ጥበብ

ኾንሶዎች በእርከን እና በእደ ጥበብ ስራዎች ይታወቃሉ። በእርከን ስራቸውም ኢትዮጵያ ዘጠነኛ ቅርሷን በዩኔስኮ እንድታስመዘግብ አድርገዋታል።

#### 4.3.1. ኾንሶና የእርከን ስራ

ኢትዮጵያ በዩኔስኮ ቅርስነት ካስመዘገበችው አንዱ የሆነው ቅርስ በኾንሶ አፈርና ውሃን ለመጠበቅ የሚካሄደው የእርከን ስራ ነው። ኾንሶዎች ይህንን ስራ እንዴት ጀመሩት? ለሚለው በቃላቸው እንደሚከተለው ቀርቧል።

> ኾንሶዎች ወደ ኾንሶ ምድር ሲመጡ በየደረሱበት ቦታ እርከን እየሰሩ ነበር። ኾንሶዎች በመጡበት በስተምስራቅ ከሊበንና ሌሎች በመጡባቸው ቦታዎች ሁሉ በበሬ እየታረሰ እርከኑ እየጠፋ ቢሆንም የእርከን ፈለጎች ግን አሁንም አሉ። ስለዚህም ኾንሶዎች እርከን የመስራት ጥበቡን ቀድመው ይዘው የመጡ ናቸው። ኾንሶዎች «መሬት እናታችን ሆና ምግብ ትሰጠናለች፤ ስንሞትም እንቀበርባታለን፤ ስለዚህ በአግባቡ መያዝ አለብን።» የሚል ጠንካራ እምነት ስላላቸው ነው መሬት እንዳይጎዳ እርከን የሚሰሩት።
>
> (አቶ ኩሬ ካራ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቀርታ የነገሩኝ አቶ ኩራ ጋራ ሲሆኑ ታችኛው ዱካቱ በመኖሪያ ቤታቸው ግቢ ነበር። በቀርታ እርባ ኾንሶዎች በመጡበት ቦታ ሁሉ እርከን እየሰሩ መምጣታቸው፣

ምልክቱም ባለቀበት ቦታዎች ሁሉ መታየቱና እህል ስለምታበቅልለት እንደሚወዳት ተገልጿል።

የትረካውን ማህበራዊ አውድ ስናየው ብሄረሰቡ ሁለት አብይ ነጥቦችን ለማጽኛነት እንደተጠቀመበት አመልክቷል። አንደኛው አገሪቱም ሆነች ወረዳዋ በአለም አቀፍ ጭምር የታወቀችበት የእርከን ስራ የብሄረሰቡ ነባር ባህላዊ እውቀት መሆኑን ማሳየት ሲሆን፣ ሁለተኛው በማህበረሰቡና በመሬት መካከል ያለውን ከፍተኛ የህይወት ፍልስፍናና ትስስር ማሳየት ነው። ኾንሶዎች የእርሻ ማሳቸውን የቤት ያህል ይንከባከባሉ፤ ማሳዎቻቸው በሚገባ የተያዙና የሚያምሩ መሆኑን ተመልክቻለሁ። የእርሻ ማሳ እንክብካቤ ተግባራትንም በየጊዜው እንደሚከውኑና በዚህም ኩራት እንደሚሰማቸው ጭምር አጫውተውኛል።

በተመሳሳይም የኾንሶ ብሄረሰብ ምንጮቹንና መንደሮቹን ከአደጋ ለመጠበቅ የድንጋይ ካብ እንደሚሰራ በቶራ አንድ ላይ ተተርኳል። በቶራ አንድ ኾንሶዎች መንደራቸውን ከጠላት እና ከእሳት አደጋ ለመከላከል ዙሪያውን በካብ እንዳሚያጥሩ ይገልጻል። በዚህም ቶርታ የብሄረሰቡ መንደር ዙሪያውን መታጠሩ ምን አይነት አውደዊ ፍቺ አለው ብለን ስናይ የማህበረሰቡ ህይወቱን በአንድ ቀለበት በሚመስል አይነት ያለ ልዩነት በጋራ የሚኖር፣ ከፍተኛ የእርስ በርስ ትስስር ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው።

### 4.3.2. ኾንሶና ሞራ

ለኾንሶ ብሄረሰብ ሞራ እንደ መሰበሰቢያ ሸንጎ በመሆን ሲያገለግል በተለይ ለወጣቱ ማደሪያና ማረፊያ ነው። አሰራሩም ከመደበኛ ቤት ለየት ያለ ነው። ቀጥሎ የቀረበውን ቶራ የነገሩኝ አቶ ቱሬ ካምብር ናቸው። ግለሰቡ እርሶ አደርና በሞራ አሰራር ጭምር ጥሩ እውቀት እንዳላቸው ጥምር አጫውተውኛል።

> የኾንሶዎች ቤት ሲሰራ እንደማንኛውም አይነት ነበር። በኋላ ኬኬሻ የሚባል የሞራ አይነት የሳር አከላደን ያለው ጎጆ መስራት ተጀመረ። ይህ የተጀመረው በኮንሶ አልፎ አልፎ ድርቅ የሚከሰት ሲሆን በዚህም ምክንያት ብዙ ከብቶች በምግብ እጥረት ይሞቱ ነበር። ይህ ኬከሻ የሚባለው ባለሁለት ደረጃ ያለው የሳር ቤት ክዳን በብዙ ሳር የሚከደን ሲሆን በደህና ጊዜ ለቤቱ ውበትና ጥንካሬ በመስጠት ያገለግላል። ድርቅ ሲመጣ ደግሞ ከዚህ የሳር ክዳን ውስጥ ሳር እየተመዘዘ ለከብቶች በመስጠትና በመመገብ ክፉ ጊዜ እንዲያልፍ ይደረጋል። በደህና ጊዜ ደግሞ በሳር መልሶ ይከደናል።
>
> (አቶ ቱሬ ካምብር መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቶራው የኾንሶዎች ሞራ አሰራር በብዙ ሳር እንደሚከደን ይገልጻል። በችግር ጊዜም ተደራቢውን ሳር በመሞዘዝ ለከብቶች መኖነት እንደሚጠቀሙ በሰላም ጊዜ ደግሞ መልሰው በአዲስ ሳር እንደሚከድኑት ይተርካል።





የኾንሶ ባህላዊ የህዝብ መሰብሰቢያ (ሞራ) ውጪያዊ ገጽታ

ውስጣዊ ገጽታ

የጋራ የሆነው ይህ ሞራ በሰላሙ ቀን የማህበረሰቡ መምከሪያና ማረፊያ ነው። ግለሰባዊም ሆነ ማህበራዊ ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ በዚሁ ጠላ ስር ተሰባስቦ በመመካከር ችግሮቹን ይፈታበታል። ሞራ ሁሉንም የብሄረሰቡ አካል በእኩልነት ያገለግላል። በተረኩ እንደተረበው በድርቅ ጊዜ በሞራው ላይ ያለው ሳር ጥቅም ላይ የሚውለው ለሁሉም መሆኑ የብሄረሰቡን አርቆ አስተዋይነት ያመለክታል። ሌላው ሞራው አሰራር ክብ ቅርጽ የብሄረሰቡን አንድነት፣ በአንድ ማህበራዊና ባህላዊ የአኗኗር ጠላ ስር መኖሩን እንዲሁም የጋራ መገልገያ የሆነው ሞራ ለማህበረሰቡ አንድ ትልቅ ተቋም መሆኑን ትረካው ያሳያል።

### 4.3.3. የኾንሶ ዋካ

ኾንሶዎች ከሚታወቁባቸው የጥበብ ስራዎች ውስጥ አንዱ በሰው ቅርጽ የሚሰሯቸው የእንጨት ዋካዎች ናቸው። ስለ ዋካዎቹ ቁራውን የነገሩኝ አቶ መምሩ ቃይሬንቶ ናቸው። አቶ መምሩ ይህን ቁራ የነገሩኝ ፋሻ አንድ ጠጅ ቤት ቁጭ ብለን ነው።

> በኾንሶዎች ዋካ ለጀግኖችና ለማህበረሰቡ ታላላቅ ስራ ለሰሩ ሰዎች ይሰራላቸዋል። ይህ ዋካ የሚሰራው ከእንጨትና አንዳንድ ጊዜም ከሸጣጣ ድንጋይ ነው። ለዋካ የሚሆነው እንጨትም ቶሎ እንዳይበላ የጥድ እንጨት ነው። በዋካውም ላይ የሰውዬው ምስል፣ የገደላቸው የዱር እንስሳት፣ እንዲሁም ያለውን ማሳ ብዛት የሚያሳዩ ትንንሽ ድንጋዮች አብረው ይተከላሉ።
>
> (አቶ መምሩ ካይሬንቶ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ከላይ ከቀረበው ቁርቃ መረዳት የሚቻለው ትልልቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱ የብሄረሰቡ አባላት በሞት በሚለዩበት ጊዜ በቀላሉ እንዳይረሱ ቋሚ መታሰቢያ የሚሆን ሀውልት እንደሚያቆሙ ነው።

ቁርቃውን ስንመለከት በርካታ ነገሮችን የሚያሳይ ነው። አንደኛ በዋካዎቹ አሰራር ላይ ብሄረሰቡ ያለውን ጥበብ ነው። ሌላው ሟች የገደላቸውን እራዊት የመሬቱ ብዛት የሚያሳዩ ናቸው። ብሄረሰቡ በእነዚህ ምልክቶች አማካኝነት ያለውን ጥበብ እና የህይወት ፍልስፍና የሚያንጸባርቅበት መሆኑን ተረኩ አሳይቷል። ከዚህም ሌላ ዋካውን የተመለከተ ማንኛውም የብሄረሰቡ አባል ስለሰውዬው ማንነት በዋካውና በአካባቢው በሚተከሉ ልዩ ልዩ ነገሮች ሊረዳ የሚችል በመሆኑ እንደ ቋንቋ በጋራ የሚያግባባቸው ነው።

ስለ ኾንሶ እደ ጥበብ ስራ ስናነሳ በዚህ ሙያ የተሰማሩት ኻውዳ በመባል የሚጠሩት የብሄረሰቡ አባላት ናቸው። እነዚህ አባላት በሌሎችም ማህበረሰቦች በሙያ ስራ ለሚሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዝቅ ያለ ግምት ይሰጥ እንደነበር ሁሉ አይብዛ እንጂ እነዚህንም የህብረተሰብ ክፍሎች ዝቅ አድርገው የሚመለከቱ ትረካዎች ኢጋጥመውኛል። ለአብነት ያህል የሚከተለውን ቁራ እንመልከት። ይህን ቁራ የነገሩኝ አቶ ኩራ ጋራ ናቸው።

> ብዙ ጊዜ ኻውዳዎች ብልጣብልጥና ከቦታ ቦታ ሄደው የሚሰሩና ቋሚ መኖሪያ የሌላቸው ናቸው። በዚህም ምክንያት ብዙም እምነት የሚጣልባቸው አይደለም። አንድ ቀበሌ ከሌላ ቀበሌ ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ሚስጢርም የሚያባክኑ ናቸው። አንድ ቀበሌና ሌላ ቀበሌ እርስ በርስ በሚጋጩበት ጊዜ ከህዝብ ጋር ለጦርነት ይወጣሉ፤ ነገር ግን በጦርነቱ የአንድ ቀበሌ ሽማኔ ከሚዋጋው ቀበሌ ካለው ሽማኔ ጋር ድንጋይ

> የሚወረውሩ ይመስሌና ርሀብን ለመከላከል ቂጣ ይወረውራሉ፤ ወይም ለልብስ ማንጫኒት የሚውል ፍሬ ቢጤ ነገር ልክ ኑሮ ባልጨት እስመስሎ እዚያ ላለው ኻውዳ ይወረውርሊታል።
>
> ኻውዳዎች በውሸት «እኔ ሌሙት! ልጂ ይሙት!» ብለው የሚምሉ ቢሆንም ማላው ምንም ስለማያደርጋቸው «ፊሬ ኻውዳ ሊክሺ» ማላ የሀውዳ ሰዎችን ከመግደል ይልቅ ያበዛቸዋል። ይባላል።
>
> (አቶ ኮራ ካሬ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ከላይ በቀረበው ቀሬ በሙያ ስራ የሚተዳደሩት ሀውዳዎች[9] ቋሚ የመኖሪያ ስፍራ እንደሌላቸው የሚገልጽ ነው። ማህበረሰቡም እነዚህን ቋሚ መኖሪያ የሌላቸውን ህዝቦች ብዙም እምነት እንደማይጥልባቸው ይተርካል።

የዚህን ቀሬ አውዳዊ አገባብ ስንመለከት በብሄረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸውና የማይሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መኖራቸውን የሚያሳይ ነው። ከላይ በቀረበው በቀርታ እስራ ስምንት ላይ ከቅሉ ከተፈጠሩት ሁለት ህጻናት መካከል መጀመሪያ የመጣው ኢቁንታ ወይም አርሶ አደሩ ሲሆን ኻውዳው ከሱ ኋላ የተፈጠረ ነው።

ለእነዚህ ባለሙያዎች ማህበረሰቡ ለምን እኩል ቦታ አልሰጣቸውም? የሚለው ሲታይ በዋናነት በማህበረሰቡ ውስጥ በቋሚነት የሚኖሩ ባለመሆናቸውና ከቦታ ቦታ መዘዋወራቸው እንደ ምክንያት ቀርቧል። ከላይ ከቀረበው ብሄረሰቡ አንድ ቦታ ረግቶ ለዘመናት የኖረ ከመሆን አንጻር ሲታይ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ለሚኖር የህብረተሰቡ ክፍል ዝቅተኛ ግምት የሚሰጡ መሆኑን ያሳያል። በተመሳሳይ መንገድም አካባቢውን ለቆ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ የሚኖረውን የብሄረሰቡ አባላት ቋሚ ነዋሪው «የእኔ እገሌ ዘር ተሰዳጅ ነውና እንዳታገቡ!» ጨምር እንደሚባል አቶ ኮራ ጋራ ነግረውኛል። ይህም የብሄረሰቡ ማህበራዊ ተቋም እንዳይናጋና አካባቢውን እና ባህሉን ሳይለቅ ባለበት ረግቶ እንዲኖር ስለ ልቡናዊ ጫናን ለማሳደር የሚገለገሉበት ነው ለማለት ይቻላል።

---

[9] ኻውዳዎች ልክ እንደ ኢቁንታዎች ሁሉ በጸጠኛም ጎሳዎች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን እንደ ስራቸው አይነትም ሴዓ (ሴታ ሰፋኙ)፤ እያታ (ሸማ ሰሪ) ቂማ (በረታብረት ሰሪ) ኮላታ ቱካ (ቆዳ ሰሪ) እና አገዳ (ሸክላ ሰሪ)ብለን በአምስት ልንከፍላቸው እንችላለን። (Watson and lakew, 2001:48)

እነዚ# የማህበረሰብ ክፍሎች እ.ኤ.አ. ከ1897 ዓ.ም. በፊት በጣም የተገለሉና ምንም አይነት መሬት ያልነበራቸው እንዲሁም ከሌሎች ማለትም ከኢቁንታዎች ጋር መብላት፣ መጠጣትና ማንኛውንም ማህበራዊ ግንኙነት ማድረግ እይፈቀድላቸው እንደነበር ይገልጻሉ (Hallpike,1968።)

### 4.4. ኾንሶዎችና ምንጮቻቸው

የኾንሶ ወረዳ ዝናብ አጠር ከሚባሉ ቦታዎች የሚመደብ ነው። ስለዚህም ይህን ብሄረሰብ በተለይ በቢጋው ወቅት ለራሱም ይሁን ለከብቶቹ በብዛት የሚጠቀመው የኩሬና የምንጭ ውሀ ነው። እነዚህ የውሀ አካላት ለብሄረሰቡ ህልውና ያላቸው አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ ስለ አፈጣጠራቸው፣ በውስጣቸው ስላሉ የውሀ መናፍስት፣ መናፍስቱ ስለሚወዷቸውና ስለሚጠሏቸው ነገሮች፣ በምንጮችና ኩሬዎች ላይ ስለተፈጠሩ ድንቅ ተአምራት የመሳሰሉት በትረካዎቹ ይንጸባረቃሉ።

ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው ስለ እነዚሁ አካላት የተተረኩ ቶርታዎች በርካታ በመሆናቸው የተወሰኑ ማሳያዎችን በመውሰድ ቀሪዎቹ በአባሪ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል።

#### 4.4.1. ኾንሶዎችና የውሀ መናፍስት

በብሄረሰቡ ቶርታዎች በምንጮችና በኩሬዎች ውስጥ መንፈስ አለ ተብሎ ይታመናል። የውሃ መናፍስትም የውሀውን ደህንነት የሚጠብቁ ናቸው ተብሎ ይታመናል። የሚጠሉትና የሚወዱት ነገር አለ ተብሎ ስለሚታመን የብሄረሰቡ አባላትም ከእነዚህ አካላት ውሀ ለመቅዳት ሲመጣ እነዚህን ነገሮች ማክበር ይኖርበታል። የሚጠሏቸውን ነገሮች የሚፈጽም የብሄረሰቡ አባል እንዲቀሰፍ ማድረግ እንደሚችሉና እነሱም በድርጊቱ ተከፍተው እንደሚደርቁ በቶርታዎቹ ቀርቧል።

ከዚህ በታች የቀረበውን ቶርታ አርባ ሰስትን የነገሩኝ አቶ መምሩ ቆራይንቶ ናቸው። ስለ እነዚሁ የውሀ አካላት ከመስክ የሰበሰብኳቸውን ቶራዎች እንዲያረጋግጡልኝ ስጠይቃቸው ቶራዎቹ በትክክልም በብሄረሰቡ ዘንድ እንደሚተረኩና ታሪኮቹም እውነትነት አላቸው ተብሎ እንደሚታመን አረጋግጠውልኛል።

> በውሀ አካባቢ ያሉ መናፍስት ይከበራሉ። ሰዎች ደግሞ ህጉን ካላከበሩ ደግሞ ይቀጣሉ። እነዚህ መናፍስት ከላስቲክ የሚሰሩ ጫማዎችና እቃዎች ወደ ውሀው አካባቢ መጣልን፣ ከበሰላ የሚሰሩ እንስራዎችን፣ የወር አበባ ላይ ሆነው ውሀ የሚቀዱ ሴቶችን ይጠላሉ። አርምቺም ስለሚወሰዱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በሰርቦ ቀበሌ ገበሬ ማህበር በደባናና ሰገሌ መካከል ያለ ዘንዶ የሚባል ቆንጆ የውሀ ምንጭ አለ፤ ነገር ግን እነዚህ ደንቦች ደንቦቹ በሚጣሱበት ጊዜ በተደጋጋሚ ወደ ደምንትና ትል በትል ወደመሆንነት ተቀይሯል። አሁንም ደንቦቹ ሳይከበሩ ከቀሩ ወደ ደምነት ይለወጣል። ውሀውም ትል በትል ይሆናል። ውሀው ወደነበረበት ቦታ የሚመለሰው ፍየል ታርዶ ልመና ተደርጎ ነው።
>
> (አቶ መምሩ ካይሬንቶ መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ.ም.)

በተርታው እንደተመለከትነው በኩሬዎቹና በምንጮቹ ላይ መናፍስት እንዳሉ፣ እነዚህ መናፍስት ደግሞ ከላስቲክ የተሰራን ጫማ፣ እንስራን፣ ሴቶች የወር አበባ ላይ ሆነው ወደ ምንጩ መግባትን ይከለክላሉ። የሽጎዶ ምንጭም እነዚህ የተከለከሉ ነገሮች በምንጩ ላይ በመፈጸማቸው ምክንያት ምንጩ በተደጋጋሚ ወደ ደምነትና ትልነት እንደሚቀየር ተገልጿል። ውሀው ወደ ነበረበት ቦታ የሚመለሰውም መለማመኛ ከቀረበ ብቻ መሆኑን ነው።

ተርታውን ስንመለከት አውዱን ማየት ያስፈልጋል። ተርታው የቀረበበት አውድ ስናይ ብሄረሰቡ የጋራ የሆነውን ሀብት እንዴት መጠቀም እንዳለበት የሚያሳይ ነው። በተርታው የቀረቡት ክልከላዎች በሙሉ የጋራ የሆነው ሀብት ለመጠበቅ ሲባል የቀረቡ ናቸው። አንዲት ሴት ከነወር አበባዋ ውሀ ውስጥ ብትገባ ደም ነክታለችና ውሃው ይረክሳል። ወይም ለመጠቀም የሚያስቸግር ይሆናል። ሌሎቹ እንደ እንስራ ያሉት ደግሞ በቀላሉ ሊሰበሩ የሚችሉ ናቸው። እነዚህ ቁሶች በውሀ አካባቢ ቢሰበሩ በቶሎ አይበሰብሱም። ይህ ደግሞ እንደ ምንጭና ኩሬ ያሉ የሚፈልቁበት መሬት ላይ ካረፈ የሚፈልቀውን ውሀ የሚደፍን ነው። ከላስቲክ የተሰሩ ቁሶችም እንዲሁ። በሌላ በኩል ደግሞ ከምንጮቹ በትል ውሀ መትዳት ይፈተዳል። ይህ የሆነበት ምክንያት በላይኛው ትንተና ላይ እንደቀረበው አንድም ትል ከብሄረሰቡ ጥንተ አፈጣጠርና የእለት ከእለት ኑሮ ጋር የተያያዘ መሆኑን ለማሳየት ሲሆን፣ ሁለተኛው ትል በውሃው አካባቢ ቢሰበርና ቢወድቅ ለትል ማህበረሰቡ ከሚሰጠው ትርጉም አንጻር ውሀውን የማይበክልና የማያበላሽ ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው። ሌላው ትል ቶሎ የመበስበስ ባህሪ ስላለው በምንጩ ላይ ምንም አይነት የሚያስከትለው ጉዳት ያለመኖሩ ነው። ስለዚህ ከላይ በጠቀስኳቸው ማሳያዎች ክልከላዎቹ የውሀውን ደህንነት ለማስጠበቅ ሲባል ሆን ተብሎ የሚቀርቡ ናቸው ለማለት ያስደፍራል።

ከላይ ለቀረበው መንሻ ሀሳብ ማጠናከሪያ የሚሆኑ ሌሎች ተርታዎችን ቀጥለን እንመለከታለን። ተርታው የተተረከው በአቶ ኩራ ጋራ ነው።

> በቅርብ አመታት ውስጥ ከዱባሌ ቤተሰብ መካከል አንዲት ሴት ከጭቃ የተሰራ እንስራ ወደ ሂዎጆራ ምንጭ በመውርወሯ የምንጩን መናፍስት አስቆጣች። በዚህም ምክንያት የምንጩ ውሀ ወደ ቀይነት ተቀየረ። ሀይለኛ ንፋስ በሚነፍስበት ወቅት ውሀው የቀስተደመና መልክ በመያዙ የአካባቢው ማህበረሰብ ውሀውን መጠቀም በማቆም ምክር ለመቀበል ወደ ጠንቋይ ዘንድ በመሄድ ሁኔታውን አስረዱ። ጠንቋዩም የአካባቢውን ህዝብ «ጥቁር ሴት በግ መስዋዕት አረዱለትና እባክህ ከዚህ በፊት ላጠፋትና እኛም ላጠፋነው ጥፋት ሁሉ ይቅር በለን።» በሉ ብሎ የምንጩን ውሀ መናፍስት ይቅርታ እንዲጠይቁ መከራቸው። ማህበረሰቡም የታዘዘውን ጸሎት መፈጸም በመጀመሩ የሚጠይቀው ነገር በሙሉ ይፈፀምለት ጀመር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የዱባሌ ቤተሰቦችም ያለእንከን መወለድ ጀመሩ።

(አቶ ኮሪ ካሪ ጥቅምት 02 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቀደም ብለን ባየነው ቶርታ የውሀ መናፍስት የሚጠሏቸውን ነገሮች የብሄረሰቡ አባላት ከፈጸሙ እንደሚደርቁ ቀርቧል። በዚህ ቶርታ ደግሞ በጥፋት ምክንያት የደረቁ የውሀ አካላት እንዴት ወደነበሩበት እንደሚመለሱ ተጠቁሟል።

በቀረበው ቶርታ ከላይ የዱባሌ ቤተሰብ የሆነች አንድ ሴት የሚከለከለውን የእንስራ ስባሪ ሂምፓሪ ምንጭ ውስጥ በመጨመሩዋ ምክንያት ውሀው የቀድሞውን መልክ በመለቀቅ መቀየሩን ያስረዳል። ህብረተሰቡም ውሀውን መጠቀም በማቆሙ ምክንያት መቸገሩንና መፍትሄ ለመፈለግ መጣሩን ያሳያል። ጠንቋዩ በነገራቸው መሰረት ልመና በማድረግ እርግማን የወረደባቸው የዱባሌ ቤተሰቦች በሰላም መውለድና መኖር እንደጀመሩ ይተርካል።

ይህ ቶርታ የተነገረበትን አውድ ስንመለከት ከሁለት አንጻር ነው። አንድም ማህበረሰቡ የጋራ የሆነውን ሀብት እንዲጠብቅ ማድረግ፣ ካልጠበቀ ደግሞ መዓት እንደሚመጣበት ማስጠንቀቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው እንደ አጋጣሚም ሆኑ ተጥሶ ቢገኝ ፍየል ታርዶ እርቅ ከተካሄደ ውሀውም ሆነ እርግማኑ ወደነበረበት ይመለሳል መባሉ ነው። ይህም በውሀው መርከስና በደረሰበት መዓት ውስጡ ደስ ያላለው የብሄረሰቡ አባል «ከእንግዲህ እርቅ ተደርጓል፤ ውሀውም ከርኩሰትና ከእርግማን ነጽቷል።» ብሎ እንዲያስብና የአዕምሮ እረፍት እንዲያገኝ ለማድረግ ነው።

ኾንሶዎች ከውሀ መናፍስት ሌሎች በስም ጭምር የሚታወቁ መናፍስት መኖራቸውን በቶርታዎቻቸው ውስጥ በብዛት ይተረካሉ። በብሄረሰቡ ላይ ጉዳት የማያስከትሉ ቢሆንም አብዛኞዎቹ ግን መጥፎ መናፍስት እንደሆኑ በቶርታዎቹ ይገለጻል። ከእነዚህ መካከልም የኤላ፣ የአራታ እና አለባይቴታ መናፍስት ይጠቀሳሉ። ከዚህ በታች በአቶ ኮሪ ጋሪ ስለ አለባይቴታ የተነገረውን ቶሪ እንመለከታለን።

> በሌት ጾታ የምትጠራና እንደሴት ድምጽ ያላት «አለባይቴታ» የምትባል መንፈስ ነበረች። ይህቺ መንፈስ ወደፊት የሚመጣውን መጥፎ ክስተት በሙሉ እየጮኸች ወይም እያለቀሰች ትተነብያለች። እኔ በህይወቴ ከአንድም አራት ጊዜ ያጋጠመኝ ነገር አለ። ጨነኛ የሆኑ ሰዎች አለባይቴታ ቀድማ አልቅሳላቸው በኋላ ሰዎቹ ሞተዋል።
>
> ዱሮ በሚኒሊክ ጊዜ የልልሰገድ ጦር ወደ ኮንሶ ገብቶ የዱካቶን መንደር ከማቃጠሉ በፊት ይህቺው አለባይቴታ ሌሊት እየዞረች «ወይኔ! ወይኔ! ይህቺ ውብ ቀበሌያችን ወዬውላት ተቃጠለች። ወይኔ! ወይኔ! ይህቺ ውብ ቀበሌያችን ወዬውላት ተቃጠለች።» እያለች ትጮህ ነበር። በኋላ በልልሰገድ የሚመራው የሚኒሊክ ጦር መጥቶ እንደተባለው ዱካቶን አቃጠላት።

(አቶ ኮሪ ጋሪ መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቶሮታውን እቶ ኮሬ ከነገሩኝ በኋላ ይቺው መንፈስ ምንም ያልታመሙ የጎረቤታቸውን ስም በመጥራት እንደሚሞቱ መናገሯንና ሰውዬውም ወዲያው በማግስቱ እንደሞቱና መንፈሷ የምትተነብየው ነገር ከአንድም ሁለት ጊዜ በትክክል ሲፈጸም ማየታቸውን ነግረውኛል።

ወደ ትንታኔው ስንገባ በሴት ጾታ የምትጠራው መንፈስ በብሄረሰቡ ላይ የሚመጣውን አደጋ ቀደም ብላ እንደምትገልጽ ተረኩ ይገልጻል። በመጨረሻም አስቀድማ የተነበየችው ነገርም ይፈጸማል። ይህን መሰል ቶራ እና ቶሮታዎች ብሄረሰቡ ለምን ሲል ይተርካቸውል? የሚለውን ስንመለከት ብሄረሰቡ ማህበራዊ ህይወቱን በሚመራበት ጊዜ ከእሱ አስተሳሰብ ውጪ የሆኑ ጉዳዮችን ተግባራዊ እንዲያደርግ ሌሎች ኃይሎች ይረዱታል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ከላይ በቀረበው ቶራም የአለባይቴታ መንፈስ በብሄረሰቡ ላይ የሚከሰተውን ነገር ቀደም አድርጋ እንደጠቆመች የሚያሳይ ነው። በሌላ መንገድም በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ አሊታዘዝ ያለን የህብረተሰብ ክፍል መቅሰፍት በማውረድ አስቸጋሪውን አካል በመንቀል ማህበረሰቡ የተረጋጋ ህይወትን እንዲመራ የሚያግዝ መሆኑን ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 5.9.1 ላይ ከሚቀርበው ትንተና መረዳት ይቻላል።

## 4.5. ከቦታዎች፣ አካባቢያዊ ስያሜዎችና ከነገሮች አመጣጥ ጋር ተያይዘው የሚተረኩ

### 4.5.1. የ(ኒዮርኪ) አፈጣጠር

ኮንሶዎች ካላቸው የቱሪዝም መስዕቦች መካከል ጋስርጊዮ ውስጥ የሚገኘው የ(ኒውዮርክ) የመሬት ገጽታ አንዱ ነው። ይህ በውሃ የተበላ የሚመስለው የመሬት ገጽታ ከሩቅ ሲታይ በልዩ ልዩ ጥበብ የተሰራ ህንጻ ስለሚመስል ቱሪስቶች ኒዮርክ እንዳሉት በአካባቢው በስፋት ይነገራል። ስለ አፈጣጠሩም የተለያዩ ቶሮታዎች ይተረካሉ።

> ጋስርጊዮ አካባቢ ወይም በአሁኑ አጠራሩ ኒዮርክ ተብሎ የሚጠራው ቦታ የእልሞጌ ቤተሰብ ታናሽ ዘሀታ የሚባለው ሰው ከቤቱ ተነስቶ እቃ ይዞ ይወጣል። የወሰደው እቃ ቶማ (የእጅ አምባር) እና የአውራሪስ ቀንድ ነበር። እቃውን ይዞ ከቤቱ ወጥቶ ሲሄድ አሁን ኒዮርክ የሚባለው ቦታ ላይ ሲደርስ የእጅ አምባሩ ወደቀበት። ፈልጎ ፈልጎ ሲያጣው ተናዶ ጥሎት ሄደ። ካሬቴ የሚባል ተራራ ላይ ደርሶ ወደ ኋላ ዞሮ ሲያይ ቶማው ሲያብረቀርቅ ያያል። ተመልሶ እንደገና ቢፈልገው ሊያገኘው አልቻለም። እንደገናም ጉዞውን ወደ ፊት በመቀጠል እዚያ ቦታ ሲደርስ እንደገና ዞሮ ቢመለከት ቶማው አሁንም ሲያብረቀርቅ ይመለከተዋል። አሁንም ተመልሶ ቢፈልገው ሊያገኘው አልቻለም። በጣም ተናዶ በያዘው የአውራሪስ ቀንድ መሬቱን መቶ «አንቺ መሬት ገደል ይውጣብሽ» ብሎ ረገሞ ከያሌ ወደሚባል ሰፈር ሲያመራ ከፊት ለፊቱ ወንዝ

> ያገኛል። ወንዙንም በበትሩ በመምታት አቋርጦ ሄደ። ከዚያ በኋላ ያ አካባቢ በውሀ ተበልቶ አሁን ያለውን መልክ ሊይዝ ቻለ። ይህ ግለሰብ ይህን ነገር በማድረጉ ሰው ተደንቆ የሄደበት አካባቢ ነገሶ ኖረ ዘሩም እስከ አሁን ድረስ በዚያ አካባቢ ይገኛል።
>
> (አቶ መምሩ ቆይራንቶ መስከረም 17 ቀን 2005 ዓ.ም.)

በቶርታ አርባ ሰባት (የኢዮርኬ) የመሬት ገጽታ የተፈጠረው አንድ የባህላዊ መሪ ልጅ ከስቤተሰቡ የስልጣን ምልክት የሆነውን ቱማ እና የአውራሪስ ቀንድ ከቤት ወስዶ ሲሄድ በመንገድ ላይ የእጅ አምባሯ ትጠፋበታለች በሩቁ እያያት ሊያገኛት ባለመቻሉ በአውራሪስ ቀንድ መሬቱን በመምታቱ ምክንያት እንደተፈጠረ ተረኩ ያስረዳል።

በቶርታ አርባ ስምንት ሌቦች የስልጣን ምልክት የሆነችውን ቱማ ሰርቀው በቦታው ላይ እንደደበቁ ባለንብረት የሆነው ባህላዊ መሪም ከበርዋ ያለችበትን ቦታ ሲመታ ቦታው ነድጉዶ እንደቀረ ይገልጻል። ቶርታ አርባ ዘጠኝ ደግሞ ይህው የባህላዊ መሪ ንብረት የሆነው ከበሮ በሌቦች ተሰርቆ ባለቤቱ በፍላጋ ላይ እንዳለ የተቀመጠባት ፈረስ ቦታውን በመርገጥ እንዳሳረችና እንደተገኘ ይገልጻል። ሁለቱን ቶርታ የነገሩን ካላ ገዛኸኝ ወ/ላዊት ናቸው።

ሶስቱ ቶርታዎች የተወሰነ የሁነብ ለውጥ አሳይተዋል። ይህ ደግሞ የቃላዊ ታሪኮች አንዱ ባህሪ መሆኑ በክፍል ሁለት ላይ ቀርቧል። ይሁን እንጂ በሶስቱም ላይ የጋራ የሆነ ነጥብ አለ። እሱም ንብረቱ የተሰረቀው የባህላዊው መሪ መሆኑና ለቦታው መፈጠርም ምክንያት መሆኑ ነው።

እነዚህ ቶርታዎች ከነበሩበት ማህበራዊና ባህላዊ አውድ አንጻር ስንመለከታቸው ሁለት አገልግሎት እንዳላቸው እንረዳለን። አንደኛው የብሄረሰቡ አባል እንደዚህ አይነት ነገሮች እንዴትና በምን ምክንያት እንደተፈጠሩ ጊዜአዊ ምላሽን ይሰጣል። ሁለተኛው ለቦታዎች መፈጠር እነዚህ ባህላዊ መሪዎች ምን አይነት ሚና እና መንፈሳዊ ኃይል እንዳላቸው ለማሳየት ነው።

### 4.5.2. የእለኮ ቁፍ ማጠርና የሴቶች የወር አባባ

በሁብረተሰቡ ውስጥ ስለ ነገሮች አፈጣጠር የሚናገሩ ቶርታዎች በጣም በርከት ያሉ ናቸው። በቶርታ ሀምሳ አንድ ሰው እግዚአብሄርን እገድላለሁ ብሎ በመነሳቱ ምክንያት እግዚያብሄር ለቅጣቱ ምልክት እንዲሆነው አይኑን እንዳንሸዋረረው ይተርካል። በተመሳሳይ መንገድ ስለ ተለያዩ ነገሮች አስያያም በቶራ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት፣ በቶርታ ሀምሳ ሁለት ላይ ቀርበዋል። ቀጥሎ ለማሳያነት ሁለት ቶራዎች ይቀርባሉ።

ሰማይና ምድር ቅርብ ለቅርብ ነበሩ። ሰማይም በጣም ዝቅ ብሎ እስከ እጽዋት አናት ድረስ ይደርስ ነበር። የእለኮ (ሽፈራ) ዛፍ ቁመቱ ከሌሎች ዛፎች የበለጠ በጣም ረጅም ነበር። ዛፍ ላይ ወጥቶ ለምግብነት የእለኩን ቅጠል የመልቀም ግዴታ የሴቶች ብቻ ነበር። ወንዶች ስራቸው የተሰራውን እለኮ መብላት ብቻ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሴትዮ ለቤተሰብ እራት ለመስራት የእለኮ መልቀሚያ «ሸንቃራ» (የብረት መንጠቆ) ይዛ የእለኮ ዛፍ ላይ ትወጣለች። እለኮውን በብረት መንጠቆው ስትለቅም ሰማይ ቅርብ ነበርና በመንጠቆው ስለት አቆሰለች። በዚህ ጊዜ ሰማይ መድማት ጀምሮ እንደ ዝናብ ይወርድ ነበር፤ የሚደማው ግን በሷ ላይ ብቻ ነበር። በልብስ ውስጥ ብትደበቅም ሊብሶቹን እለፎ ደሙ በሷ ላይ ይወርድ ጀመር። ህዝቡ ሁኔታውን አይቶ መፍትሄ ለመፈለግ ይነጋገርና መፍትሄው እግዚአብሄርን መለመን ብቻ መሆኑን ይስማሙና ሽማገሌዎች ተመርጠው እግዚአብሄርን ለማነጋገር ይሄዳሉ። በኋላም «እግዚአብሄር ሆይ! ይህቺ ሴት አጥፍታለችና ይቅር በላትና የደም ዝናብህን በሷ ላይ ማውረድህ ቢቀር፤ ቅጣትም ከሆነ እንቀበላለን። የኛ ውሳኔ ዛፍ ላይ መውጣቱ የሴቶች ብቻ ሳይሆን የወንዶችም እንዲሆን፣ አንተም ሰማይ ቤትህ ነውና ሰው በመንጠቆው እንዳይነካበህ በጣም ከፍ እንዲል ብታደርግ፣ ሌላው ደሀ በጣም ከፍ ያለው የእለኮ ዛፍ ዝቅ እንዲል ወስነናል። ሌላው ሴቶች ከዚህ በፊት እንደ ሌሎች እንስሳ የነበረው የወር አበባ ቀርቶ በየወሩ እንዲሆንና እሷም እንድትታገስ እናደርጋለንና በዚህ እሺ ብትለን?» ብለው ይማፀናሉ። እግዚአብሄርም የእለኮ ዛፍ ዝቅ እንዲል፣ እለኮ መልቀም የወንዶችም ተግባር ሆኖ ዛፍ ላይ ወጥተው መልቀም እንዲጀምሩ፣ ሴቶችም በየወሩ የወር አበባ እንዲያዩ በመስማማቱ በሴትየዋ ላይ ይዘንብ የነበረው ደም ቆመ። ይባላል።

(አቶ ኮራ ጋራ ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ይህን ቁርጋ የነገሩኝ አቶ ኮራ ጋራ ናቸው። በቁርጋው እንዴት የሴት ስራ ብቻ የነበረው የእለኮ ለመልቀም ስትል ቅርብ የነበረውን ሰማይን በብረት መንጠቆ በመውጋቷ ምክንያት ሰማይ እንደራቀ፣ እሷም በሀጢያቷ ምክንያት ብዙ ደም እንደፈሰሰት ተጠቁሟል። በሴትየዋ ጥፋት ምክንያት በሽማግሌዎች ድርድር በማድረግ ሴትየዋ ቀለል ያለ ደም (የወር አበባ) እንድታይ መደረጉን፣ ሰማይም ቅርብ መሆኑ ቀርቶ ከፍ እንዲል እና የእለኮ ዛፍም ዝቅ እንዲል የመፍትሄ ሀሳብ ተቀምጧል።

ቁርጋው የቀረበበትን አውድ ስንመለከት ማህበረሰቡ ከየት እንደመጣ፣ ነገሮች እንዴት እንደተፈጠሩ መልስ ይፈልጋል። ስለዚህም በዚህ ቁርጋ ብሄረሰቡ በአቅራቢያው ለሚያውቃቸው ነገሮች ሶስት ነገሮች መልስ ሰጥቷል። አንደኛው ሴቶች ከወንዶች የተለየ የወር አባባ የሚያዩት ሴቷ በስራችው ጥፋት ምክንያት ነው የሚል ነው። ሁለተኛው ሰማይም ከፍ ያለው ይኸችው ሴት እለኮ ለማውረድ ብላ ስለወጋችው እንደሆነ ተገልጿል። ሶስተኛው በብሄረሰቡ ዘንድ ለምግብነት የሚገለገሉበት እለኮም ዝቅ ያለው ሰዎች ቁቁ ላይ እየወጡ ሰማይን እንዳይነኩ ለማድረግ ሲባል እንደሆነ ተጠቁሟል። ቁርጋው የተገለጸችው ሴት በመጽሀፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ላይ ከተረበው የሄዋን ሀጢያትን ከሚተርከው ጋር ተመሳስሎ የቀረበ ነው።

ቀርታው ለምን ዓላማ ሲባል ተተረከ የሚለውን ስናይ ሶስት ነገሮችን በዋናነት ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው ብሄረሰቡ በምግብነት የሚጠቀምበት አለኮ እንደ ልቡ በአትራቢያው በማግኘት እንዲጠቀምበት መቻሉን ለማሳየት ነው። ሁለተኛው አለኮውን የመልቀም ስራ ድሮ የሴቶች ብቻ እንደነበር አሁን ግን የወንዶች ጭምር እንዲሆን በማድረግ ፍትሀዊ የሆነ የስራ ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ እንደተቻለ ለማሳየት ነው። ሶስተኛው የአገር ሽማግሌዎችን የማስታረት ወይም የማሸማገል ሚና ትልቅ መሆኑን ለማመላከት ነው። በቀርታው የነገሮች መነሻ ምን እንደሆነ መልስ ለመስጠት ማገልገሉ ቀንኛው ዓላማው ሲሆን የአገር ሽማግሌዎች እንኳን በሰውና በሰው መካከል ቀርቶ በሰውና በአምላክ መካከልም የማሸማገል ሚና እንዳላቸውና ሚናቸውንም በትውልዱ ውስጥ መትከል እንዲሁም ማጽናት ነው።

4.5.3. ቢቃውሌ

በቾንሶዎች ባህል መሰረት በብሄረሰቡ ውስጥ ከሚፈጠሩ ክስተቶች ጋር እያያዙ ስም የማውጣት ልማድ የተለመደ ነው። በዚሁ መንገድ ስያሜአቸውን እንዳገኙ የሚተረክላቸው በርካታ ነገሮች እንዳሉ ከላይ ተገልጿል። በመቀጠልም ቀራ ስምንት ከአሁኗ ካራት በፊት የኮንሶ ወረዳ ዋና ከተማ በመሆን ያገለገለችው የቢቃውሌ ከተማ ስም ከምን እንደመጣ በቀራው እናያለን።

> ከካራት በፊት የኾንሶ ዋና ከተማ በመሆን ለረዥም አመታት ያገለገለችው ቢቃውሌ ነበረች። ይቺ ከተማ ስያሜዋን ያገኘችው በአጼ ሚኒሊክ እንደነበር ይነገራል። የሚኒሊክ ጦር ለማዕከላዊ መንግስት ለማስገበር ኾንሶ ድረስ ከመጣ በኋላ ሚኒሊክ «ከዚህ በኋላ ሌላ ግዛት አልፈልግም፤ ቢቃ ውሌ።» በማለታቸው ከተማዋን ቢቃውሌ ተባለች ይባላል።
>
> (አቶ ቁሬ ካምብሮ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቢቃውሌ ስሟን ያገኘችው የሚኒሊክ ጦር ግዛቱን ለማስፋፋት ኾንሶ ከደረሰ በኋላ ወደ ሌላ ላለመሄድ «ቢቃ ውሌ!» ብለው ሚኒሊክ ከተናገሩት ንግግር እንደመጣ ይገልጻል። ከዚህ ቀራ መረዳት የሚቻለው ብሄረሰቡ በአካባቢው የተፈጠሩ ታላላቅ ክስተቶችን በማስደገፍ ስም ማውጣቱን ነው። ብሄረሰቡ ይህን የሚያደርገው እነዚህ ታላላቅ ክስተቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ቶሎ እንዳይጠፉና ማስታወሻ ሆነው እንዲቆዩ ለማድረግ ነው። የብሄረሰቡ አባላትም በዚህ አይነት መንገድ በሚሰየሙት ስያሜዎችም ላይም በቀላሉ እርስ በርስ እንዲግባቡ ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም ስሙ በተነሳ ቁጥር ስለ ክስተቱ መልስ ብለው የሚያወጉበት አጋጣሚ ስለሚሰፋ ነው። ከዚሁ አሰያየም አዲስ

ትውልድም ስላለፈው የብሄረሰቡ አባል ታሪክ በቀላሉ እየተማረና እያወቀ እንዲሄድ ይረዳል።

### 4.6. ኹንሶና ጋብቻ

በብሄረሰብ ውስጥ ወደ ስድስት የሚጠጉ የጋብቻ አይነቶች አሉ። በይበልጥ የተለመደውና የሚፈጸመው የጋብቻ አይነት በቤተሰብ ምርጫ የሚደረግ የጋብቻ አይነት ነው። ቀጥሎ ጋብቻ በብሄረሰቡ ዘንድ ምን አይነት መልክ እንዳለው የሚነገሩት ተረቶችና ቀርታዎች ይቀርባሉ።

ከጋብቻ ውጪ ማመንዘር በብሄረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ መቅሰፍትን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል። ይህን በተመለከተ ፋሻ ላይ በተደረገው የቡድን ውይይት የተገኘው ቶራ ተጥለን እንመለከታለን።

> በኹንሶ ባህል ወንዶች ሴቶችን አይደፍሩም። ሴቶችም ወንዶችን አይደፍሩም። አንድ ወንድ ከሚስቱ ውጪ ሌላ ሴት ቤት ሄዶ ሌላ ሰው በተኛበት ቁርበት ላይ ሴት ከተገናኘ ለሰውየው የሚመች ነገር አይኖርም። ይኮነናል፤ በመጨረሻም ይሞታል። ሴትም እንዲሁ። በኹብሄረሰቡ ውስጥ ሙሉ ሲጋዊ ስሜት የለም ማለት ሳይሆን አንድ ሚስቱ የሞተችበት ሰው ሲጋዊ ፍላጎት ቢኖረው ይህን ስሜቱን የሚፈጽመው በተመሳሳይ መልኩ ባሏ የሞተባትን ሴት በማግባት ብቻ ይሆናል። በባልና በሚስት በኩል በትዳራቸው መካከል ማመንዘር እንዳይኖር በብሄረሰቡ በኩል ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣ መተዳደሪያ ደንብ የሚቆጠር ነገር አለ። ይህን ድርጊት መፈጸም በብሄረሰቡ «ኦሲማሌማ» ይባላል። ፍቺውም ማመንዘር የሚል ነው። ይህንን ፈጽሞ የሚገኝ ሰው ከፍተኛ ውግዘትና ቅጣት ይደርስበታል። የኹንሶዎች የቤቶች አሰራርም አንዱ ወደ ሌላው ቤት በመሄድ ለማመንዘር አመቺ እንዳይሆን የአንዱ ቤት በር በሌላው ቤት በር ፊት ለፊት ተደርጎ ነው።
>
> (ፋሻ በቡድን ውይይት የተገኘ መስከረም 18 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቶራ ዘጠኝ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በባሎቻቸው ወይም በሚስቶቻቻው ላይ ማመንዘር በጥብቅ እንደሚከለከል ይገልጻል። ይህን ማህበራዊ ደንብ ጥሰው በትዳራቸው ላይ ቢያመነዝሩ ሰዎች መቅሰፍት እንደሚወርድባቸው የሚታመን መሆኑ ተጠቁሟል። ይሁን እንጂ ባል ወይም ሚስት የሞተባት ወይም የሞተችበት ከቢጤው ጋር መጋባት እንደሚችል ይተረካል። ይህም ልክ እንደ ህግ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላላፈ ተፈጻሚ እንደሚሆንም ያስረዳል። የቤቶቻቸው አሰራርም አንዱ ከሌላው ቤት ተደብቆ እንዳይገባ ለመከላከል እንዲያስችል ተደርጎ የተሰራ ነው።

በዚህ ቀርታ መረዳት የሚቻለው ብሄረሰቡ ማመንዘርን የሚጸየፍ ከመሆኑ ባሻገር ለዚህ ተግባር በር የሚከፍቱ ቀዳዳዎችን አስቀድሞ ባህላዊ በሆነ የሚደፍን መሆኑን ያሳያል። ከዚህም ሌላ ይህንኑ ተግባር የሚከለክል ባህላዊ ህግ መሳይ ነገር እንዳለው፣ ይህን ጥሶ የተገኘ የብሄረሰቡ አባል መቅሰፍት ይደርስብኛል ብሎ ያምናል። ከአድራጎቱም

ይቀጠባል። የቀርታው የሚቀርብበት እውድ ብዙ ጊዜ በባልና ሚስት መካካል በሚፈጠር ግጭት ምክንያት በሚካሄድ ሽምግልናና የእርቅ ስነ ስርዓት ላይ ነው። ቀርታው የሚቀርብበት ምክንያትም በቅሬኔ ሰበብ ባልም ሆነ ሚስት ወደ አልተገባ አትግጫ እንዳይገቡ ከወዲሁ ለማረቅ ሲባል።

በሌላ በኩል ጥሩ ሀብት ያለው የብሄረሰቡ አባል ሁለት ሚስት ማግባት የሚችል ቢሆንም የጎሳ መሪዎች ግን ሁለት ሚስት እንዲያገቡ እንደማይፈቀድ የሚነግሩ ተረኮች መኖራቸውን ካሳ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት ነግረውኛል።

> በዥንሶ ማህበረሰብ ባህላዊ መሪ «ፖችላ» ሲሞት አይቀበርም ነበር። ባህላዊ መሪው ሲሞት እስከሬኑ ድንጋይ ላይ ይቀመጥና ደመና መጥቶ ይወስደዋል። ይህ የቀረው በሁለተኛ ሚስት ምክንያት ነው። ባህላዊ መሪው ህዝቡን በጥሩ መንፈስ እንዲያስተዳድር ማታ ማታ መላእክት መጥተው ያነጋግሩት ነበር። ይህ የሚሆነው ብቻውን ሲሆን ብቻ ስለሆነ ሚስቱ መኝታ ክፍሉ አትገባም ነበር። እንደተለመደው አንድ ቀን ባህላዊ መሪው ከመልአኩ ጋር ሲነጋገር ድምጽ ሲያሰማ ሚስት ከሁለተኛዋ ሚስት ጋር የሚነጋገርና ባህላዊ መሪው ያታለላት ይመስላትና ገረዱን ከማን ጋር እንደሚነጋገር እንድትነግራት ገብቱ ውስጥ ትደብቃታለች።
>
> እንደተለመደው ባህላዊ መሪውን መልአክ ሊያነጋግረው ሲመጣ መልአኩ አንድ ባእድ ነገር እንዳለ ለባህላዊ መሪው ይነግረዋል። መሪው ግን ምንም ስለማያውቅ ምንም ነገር እንደሌለ ይመልስለታል። መልአኩም «ከእንግዲህ ወዲህ በአካል መጥቼ አላነጋግርህም፤ የሚገለጽልህ ነገር በሙሉ በህልም ይሆናል። አንተን ግን መሬት ይጠሆርህ።» አለው። «ለዚህም ምልክት ከዚህ ገቡቱ ስር ነገ ሬሳ እንሳ።» ብሎት ጥሎት ሄደ። ጠዋት ገረዷ ስትፈለግ ትጠፋለች። በኋላ ንጉሱ ትዝ ሲለው ገቡቱው እንዲከፈት ሲያደርግ ሞታ ተገኘች።
>
> ከዚያ በኋላ ባህላዊ መሪው ሲሞት እንደተለመደው እሬሳውን ድንጋይ ላይ ተቀመጠ። ከሶስት ቀን በኋላ ትንሽ ዳመና የሚመስል ነገር መጥቶ አካባቢውን ጋረደውና ሬሳው ተሰወረ። ከ9 ቀን በኋላ እረኞች በሬ ደም ሲያይ የሚጨኸውን አይነት ድምጽ ሰምተው ወደ ቦታው ሲሄዱ የባህላዊ መሪውን ጣት ከነቀለበቱ አገኙ። ይህንን ለአካባቢው ሽማግሌዎች ወስደው ሰጡ። ከዚያ በኋላ ባህላዊ መሪው መቀበር ጀመረ።
>
> (ካሳ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት መስከረም 20 ቀን 2005 ዓ.ም.)

በዚህ ቀርታ ለባህላዊ መሪው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መገፈፍ ምክንያት ሁለተኛ ሚስት ናት። በእሷ ሰበብ ባህላዊ መሪው ከመልዓክት ጋር ያለው ግንኙነት ተቋርጧል፤ ሲሞት ያርግ የነበረውም እንደማንኛውም ሰው መቀበር እንዲጀምር ሆኗል።

በቀርታ ሀምሳ ሁለት የካሳ ቤተሰብ የቀድሞ መኖሪያውን ለቆ ወደ ሌላ ቦታ ቦታ እንዲሰደድ ያደረገች ሁለተኛ ሚስት መሆኗ፤ በቀርታ አምሳ አራት ደግሞ በሁለተኛ ሚስት ምክንያት የአንድ ቤተሰብ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት ይተረካሉ።

ከጋብቻ ውጪ ማመንዘርንና ሁለተኛ ሚስት ማግባትን የሚከለክሉ ትረካዎች እንዳሉ ሁሉ ከጋብቻ ውጪ መውለድንም የሚከለክሉ ቶሮታዎች በብሄረሰቡ ዘንድ ይተረካሉ። ተጥሎ ዱራይቴ በቡድን ውይይት የተገኘው ቶሮታ ይቀርባል።

> በዱሮ ጊዜ ነው አሉ አንዲት የኾንሶ ልጅ ከጋብቻ ውጪ ታረግዛለች። ከዚያ በኋላ በአካባቢው የተዘራው እህል ሙሉ በሙሉ በቁጫጭ ተሞላ፣ ሰብሉም ጠወለገ፤ መኖሪያ አካባቢም በቁንጫጭ ተወረረ። ከዚያ በኋላ ከጋብቻ ወጪ የምታረግዝ ልጃገረድ በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ አትወልድም። የምትወልደው ከመኖሪያ ቤቷ አካባቢ በመራቅ ነው።

(ከዱራይቴ በቡድን ውይይት የተገኘ መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ከቶሮታው መረዳት የሚቻለው ከጋብቻ ውጪ የምታረግዝ ሴት ማህበረሰቡ ቀደም ብሎ ካስቀመጠው ክልከላ ውጪ ልጅ ብትወልድ በአካባቢው ላይ ሌላ መዓት ይመጣል ተብሎ ይታመናል። ልጅቱም የብሄረሰቡን ደንብ ጥሳለችና ቤቷ በክብር ልትወልድ እንደማትችል ያሳያል።

ቶሮታው የሚቀርብበትን አውድ ስንመለከት ብዙውን ጊዜ ለደረሱ ወንዶችና ልጃገረዶች እንደሆነ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ገልጸውልኛል። ይህም የደረሱ ልጆች በስሜት ወደ አልተገባ ነገር እንዳይገቡና ራሳቸውን ሳይችሉ ልጅ እንዳይወልዱ ለማድረግ ነው። ከማህረተሰቡ ደንብ አፈንግጠው ከተገኙ የሚደርስባቸው መገለል ከፍተኛ መሆኑን በመጠቆምና ስነ ልቡናዊ ጫናን በመፍጠር የብሄረሰቡን ባህል ማስጠበቅ ነው።

4.6.1. ያለ እቻ ጋብቻ በኾንሶ ቶራዎች

ብሄረሰቡ እንደ ሁለተኛ ሚስትና ከጋብቻ ውጪ መውለድን እንደሚከለክል ሁሉ ያላቻ ጋብቻንም እንደማይቀበል በቶሮታዎቹ አማካኝነት ያንጸባርቃል። ይህንን በተመለከተ በቶሮታ ስድሳ ስምንትና በቶራ አስራ አንድ ላይ ቀርቧል። በቶሮታ ስድሳ ስምንት አንዲት የኾንሶ ልጃገረድ የሌላ መንፈስን ማፍቀሯንና በመንፈስና በስጋ ሰው መካከል የሚደረግ ጋብቻ የማይቻል በመሆኑ መጨረሻ ላይ ሲገድላት ይተርካል። ቀጥሎ ከዚሁ ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቶራ በአቶ ካልቱማ ተገኘ እንደሚከተለው ተተርኳል።

> በድሮ ጊዜ ጸለምተማተ ሚስቱ ሞታበት ከአንድ ልጁ ጋር አብሮ ይኖር ነበር። ልጁም አድጎ ለአቅመ አዳም ሲደርስ አባቱ እንዲያገባ ይጠይቀዋል። ልጁም ለአባቱ «አባቴ በእኔ ምርጫ እንጂ በአንተ ምርጫ አላገባም።» ሲል ይመልስለታል። ከጊዜ በኋላ ለአባቱ «አገባቻለሁ።» ለማለት ሚስቱን እስከትሎ ይመጣል። አባት «ሚስትህ የት አለች?» ሲል ጠየቀው። ልጅም «በመሬት እየተሳበች የምትመጣው ሚስቴ ናት።» በማለት በእቅራቢያው ያለችውን እባብ አመለከተ። አባትም «ምነው ልጄ! ዘራችንን ከጨረሱትና እናትህንም ከገደሉት መካከል ታገባለህ? በል ይልቅ ቶሎ ብለህ አባራት፣ ወይም ቅቤ እንዳለው ብለህ ጥለሃት ጥፋ።» ብሎ እንደመከረው ጥኒት ጠፋ ይባላል።

(አቶ ካሴቱማ ተገኘ መስከረም 18 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ከላይ የቀረበውን ቀራ ስንመለከተው ሸለምጥማጥ ያለ አባቱ ፍቃድ አባብን እንዳገባና አባትም ጋብቻው በእቃዎች መካከል የተፈጸመ ባለመሆኑ ልጅ ትዳሩን እንዲያፈርስ በመገፋፋቱ ምክንያት ጋብቻው ሳይሳካ መቅረቱን ይገልጻል።

የብሄረሰቡ አባላት ይህን ቀራ በብዛት የሚነግሩበትን እውድ ስንመለከት ለትዳር ለተቃረቡ ልጆችና ወጣቶች ነው። በቀራውም ሊተላለፍ የተፈለገው ቁም ነገር ጋብቻው ያላቻ ከተፈፀመ ሊዘልቅ እንደማይችል ለማስተማሪያነት ነው። በትረካውም ወጣቶች በስሜታዊነት ተገፋፍተው ከብሄረሰቡ ደንብ ውጪ ያለእቻቸው ትዳር እንዳይመሰርቱ እና በዚህም ምክንያት ያልሆነ ቦታ ላይ እንዳይወድቁ ለመምከሪያነት ይጠቀሙበታል፤ ምክንያቱም በቀረበው ቀራ አባቱ አባቦች ዘራቸውን እንዳጠፋና እናቱንም የገደሉት እነሱ መሆናቸውን ባይነግረው ኖሮ አንድ ቀን የሱም እጣ ፋንታ ይህው ይሆን ነበር።

ይህን ቀራ ለብሄረሰቡ አባላት የሚተርኩት የእድሜ ባለጸጎች ሲሆኑ የትረካው ዋና ዓላማም ትውልዱ የእነሱን መስመር ይዞ እንዲሄድና ከሌላ ጋር ሳይቀላቀል ማህበራዊ ተቋሙ ባለበት እንዲቀጥል ለማድረግ ነው።

## 4.7. ኾንሶ ጦርነት እና አደን

ኾንሶዎች ጦርነት እንደማይወዱ፤ ነገር ግን ሊያጠቃቸው የመጣ ካለ ወደ ኋላ የማይሉ ህዝቦች መሆናቸውን ቀርታዎቻቸው ያሳያሉ።

### 4.7.1. ኾንሶና ከምኒሊክ ጦር ጋር የተደረገ ጦርነት

ኾንሶዎች በአካባቢያቸው ከሚገኙ የተለያዩ ብሄረሰቦች ጋር እንደተዋጉ ስለ ጦርነት ሲወሳ በብዛት የሚተረከው ብሄረሰቡ በአፄ ሚኒሊክ መንግስት ዘመን ከማዕከላዊ መንግስት ሊያስገብር ከመጣው ከደጃዝማች ልዑልሰገድ ጦር ጋር የተደረገው ጦርነት ነው። ቀጥለን በቀርታ ስድሳ አንድ የቀረበውን ትረካ እንመልከት። ይህን ቶሮታ የነገሩኝ አቶ ጊሌዴ ባደና ናቸው።

> በአፄ ሚኒሊክ ዘመን የኾንሶ ማህበረሰብ ራሱን በራሱ በባህላዊ መንገድ ያስተዳድር ነበር። በኋላ የሚኒሊክ ጦር የኾንሶን ህዝብ ለማዕከላዊ መንግስት ለማስገበር በፊታውራሪ ሉልሰገድ የሚመራ ጦር በቡርጂ ወረዳ በኩል ወደ ኮንሶ ይገባል። በዶካቶ ቀበሌ የሚገኘው የኮንሶ ማህበረሰብ ወደ ጦርነቱ ላለመግባት አንድ በግ የባንዲራ ቀለም ያለው ልብስ በማልበስ ወደ ሉልሰገር ጦር ይልካል። በጃርሶ ቀበሌ የሚገኘው የኾንሶ ማህበረሰብ ደግሞ «እኛ ጀግኖች ነን፤ ለምን እንደ ሰነፍ ህዝብ በባህላዊ መንገድ እርቅ ይላካል?» በሚል ወደ ጦርነቱ ለመግባት ተዘጋጀ። ከዚያም ኩሲያ ሳሊቶ የሚባል በጃርሶ የሚገኝ አንድ ሰው ህዝቡን የሉልሰገድ ጦር ወደ መጣበት ጉማይዴ አካባቢ

በመውሰድ እስ ከፊት ህዝቡን ደግሞ ከኋላው አድርጎ ጭንቅላታቸውን ወደ መሬት፣ እግራቸውን ወደ ላይ በማድረግ ለጠላት ምልክት ያሳያሉ። ጠሩም አዲስ አይነት የውጊያ ስልት መስሎት በመፍራት ወደ ዶራሼና ሌሎች አካባቢዎች በመሄድ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ። ህዝቡም በዚህ ስልቱ ከሲያ ሳሊቶን በወቶቱ በቅኔ ያወድሱትና ያከብሩት ነበር።

በኋላም የፊተኛው የልዑልሰገድ ጦር ወደ ዶራሼ አካባቢ ሲያመራ ቀሪው ጦር ተጠናክሮ ወደ ኮንሶ ጃርሶ ቀበሌ በመምጣት ህዝቡን አጠቁት። የጃርሶ ቀበሌ ህዝብ ቢጎዳም ከፍተኛ ትንቅንቅ በማደረግ የተጎዳ ተጎድቶ ጦሩን ከአካባቢው ያባርራል። የሉልሰገድ ጦርም ወደ ዱካቶ ቀበሌ ያመራል። የዱካቶ ቀበሌ ህዝብም የጦሩን አመጣጥ በማየት በየጎጆው ተሸሽጎ ጦሩን ለመውጋት ስልት ይቀይሳል። የጎጆውም አሰራር በዙሪያው ዝቅ ያሉ በሮች ያሉት ነበር። የዱካቶ ህዝብም በየበሩ ትይዩ ጦር ይዞ ከላይ በቤቱ ጣራና ግድግዳ ላይ ተደብቆ ጦሩን ይጠብቅ ነበር። ውጭ ምንም ሰው ያላገኘው የሉልሰገድ ጦርም በየቤቱ የሚገኘውን የዱካቶ ህዝብ ለመውጋትና ለመማረክ ከነታጠቀው ዘመናዊ መሳሪያ በየጎጆዎቹ በሮች ሲገባ አድፍጦ የነበረው በዱካቶ አካባቢ የሚገኘው የኮንሶ ማህበረሰብ ጦሩን ከላይ ሆኖ በጦሩ እየወጋ ይገድለው ጀመር። ከውጭ የሚገኘው የሉልሰገድ ጦር ከጎጆው የሚወጣ አንድም የራሱን የጦር አባል ሲያጣና ይብሱንም የራሱን የጦር አባል ደም ከጎጆዎቹ እንደጎርፍ ሲወርድ ይመለከታል። በዚህን ጊዜ ይህ አይነቱ የውጊያ ስልት እንደማያዋጣ የተረዳውና በወገኖቹ ማለቅ በጣም የተናደደው የሉልሰገድ ጦር የዱካቶን ህዝብ ለመፍጀት በማሰብ በየጎጆዎቹ ላይ እሳት ለቀቀባቸው። ህዝቡም ከየጎጆው በመውጣት ዙሪያውን ከከበበው ጦር ጋር መፋለም ጀመረ። በዚህም የዱካቶ ቀበሌ በእሳት ብትጠፋም ያለቀው አልቆ የሉልሰገድ ጦርን እንዲዳከምና ከአካባቢው እንዲለቅ አድርጓል።

(አቶ ጊሊዶ ባደና መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቶርታው ኾንሶዎች በደጃዝማች ልዑልሰገድ የጦር መሪነት ሊያስገብር ከመጣው የሚኒሊክ ጦር ጋር ያደረጉትን ጦርነት የሚያወሳ ነው። በዚህም በተለያዩ የኾንሶ አካባቢ የሚገኙ ህዝቦች ራሳቸውን ለመከላከልና ለማጥቃት የተጠቀሙበትን ስልት ያሳያል።

ይህ ቶርታ የሚነገርበት አውድ ስንመለከት ብዙ ጊዜ በአካባቢው ካሉ ሌሎች ብሄረሰቦች ጋር ጦርነቶች ሲካሄዱ ነው። ቶርታው የሚነገርበት ዋነኛ ዓላማ ኾንሶዎች ነባር የሆነ የጦርነት ታሪክና የአወጋግ ስልት እንዳላቸው በመንገር ወደ ጦርነት የሚሄዱትን የማህበረሰቡን አባላት ለማጀገንና ለመቀስቀስ ነው። ወደ ጦርነት ለሚሄዱ ወጣቶች በቂ የስነ ልቦና ዝግጅት እንዲኖራቸው ለማድረግ ያገለግላል።

### 4.7.2. ኾንሶና አደን

በኾንሶዎች ዘንድ ከጦርነት ባሻገር ትልልቅ አውሬዎችን የገደለ ጀግና እንደሚባል ቶርታዎቻቸው ይገልጻሉ። ከአደን ጋር በተያያዘ በርካታ ግለ ትረካዎች ይገኛሉ። ከቶርታ ስድሳ ሶስት እስከ ስድሳ ስድስት የቀረበ ሲሆን ለማሳያነት በአቶ ገልሲሞ ዱኖቴ በቶርታ ስድሳ ስድስት የቀረበ ግለ ታሪክ እንደሚከተለው ይቀርባል።

> አንድ ቀን በዮ ፈርታ የሚባል በጣም ጨካኝ የሆነ የኮንሶ ሰው ነበረ። በዮ አንበሳ ካልገደልኩ ብሎ ጫካ ለጫካ ሂዶ አንበሳ ሲፈልግ ውሎ በመጨረሻም አንበሳውን አግኝቶ በእጁ ይዞ ተናንቶ፤ ነገር ግን በዚህን ጊዜ አንበሳው ተወርውሮ ይዞ ሰውዬውን ገደለው። ይሁን እንጂ በዮ ፈርዳ ቢሞትም ጀግና ነው። ጀግና በመሆኑ «ዋካ» ተሰርቶለታል።
>
> (አቶ ገለሲዋ ዱኖቴ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ከተርታው መረዳት የሚቻለው በኮንሶዎች ዘንድ ጀግና የሚባለው ሰውን የገደለ ብቻ ሳይሆን ትልልቅ አራዊትን የሚገድል ጭምር ነው። ከዚህም በተጨማሪም አንድ ሰው ከትልልቅ የዱር እንስሳት ጋር ተናንቆ ቢሞትም እንኳ ከጀግኖች ተርታ እንደሚሰለፍ በተርታው ቀርቧል።

ይህ ቶርታ የሚቀርብበት ማህበራዊ አውድ ማታ ማታ ሲሆን ቦታውም የብሄረሰቡ አባላት በአካባቢያቸው በሚገኙ ሞራዎች ተሰብስበው የብሄረሰቡን ታሪክ በሚያወጉበት ጊዜ ነው። ብሄረሰቡ ትልልቅ ተግባራትን የፈጸሙ ግለሰቦችን ስም በመጥራት ስለእነሱ ተጋድሎ እያነሳ በቦታው ለተገኙ ታዳሚዎች ያቀርባል። ቶርታው የሚቀርበበት ምክንያትም በብሄረሰቡ ዘንድ ተኪታይ ጀግናዎችን ከአዲሱ ትውልድ ለመመልመል በማሰብ ነው። በቶርታው እንደቀረበው አንድ ሰው ከአቅሙ በላይ ከሆነ ነገር ጋር ተጋፍጦ ቢሸነፍ እንኳ ግለሰቡ ጀግና እንደሚባል ይገልጻል። ይህን ስንመለከት ሰዎች ፈርተው ከዚህ አይነት የጀግንነት ተግባር ከወዲሁ እንዳይቀሩ ለማድረግ ነው። በተለይ ከትልልቅ አራዊት ጋር በሚደረገው ትልትንት በማሸነፍም ሆነ በመሸነፍ ጀግና መሆን እንደሚቻል ከወዲሁ ስለሚጠቁም በተለይ ወጣቱ በስነ ልቦና ዝግጅት እንዲያደርግና እንዲበረታታ የሚያግዝ ነው።

## 4.8. ግብረ ገብ ቶራዎችና ቶርታዎች

ኮንሶዎች በቶራዎቻቸውና በቶርታዎቻቸው አማካኝነት ለብሄረሰባቸው አባላት ልዩ ልዩ ስነ ምግባራዊና ሞራላዊ መልእክቶቻቸውን ያስተላልፋሉ። ስለ ደግነት፣ ክፋት፣ ታማኝነት፣ ሞኝነት፣ ብልጣ ብልጥነት፣ ብልህነት፣ ሌብነትን የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ይነሳሉ። በመስከ ቆይታዬ በብዛት ከሰማኋቸውና ከሰበሰብኳቸው ስነ ምግባራዊ ቶራዎችና ቶርታዎች መካከል የሌብነትን አጸያፊነት የሚያጎሉ በርከት ይላሉ።

### 4.8.1. ሌብነትን የሚኮንኑ

ሌብነትን የሚጠየቁ ቶርታዎች በቶርታ ቁጥር ስድሳ ዘጠኝ፣ ሰባ እና ሰባ አንድ ላይ የቀረቡ ሲሆን፣ ቀጥሎ በአቶ ኮራ የተተረከውን ቶርታ ቁጥር ስድሳ ዘጠኝን

እንደሚከተው ተርከውታል። አቶ ኮራ ይህን ቶርታ ሲነግሩኝ ልክ እንደ ገጸባህሪያቱ ድምጻቸውን ከፍና ዝቅ፣ ወፈርና ቀጠን እያደረጉ ነው። በዚህ አቀራረባቸው ሳላምጣቸው የነበረው በጣም ተመስጬ ነበር።

> ኮንሶዎች በመሰረቱ ማንኛውም እምነት አልነበራቸውም። የሚያምኑት «ሰው ከሞተ በኋላ መንፈስ ይኖራል።» በሚል ነው። ይህ መንፈስ «ከራያ» በዱሮ አካባቢ ደግሞ «ካራዋ» ይባላል። መንፈስ በህዝብ ዘንድም ሆነ በአስተዳደሩ ላይ ስህተት የሚፈጽም ከሆነ «እርምጃ ይወስዳል።» ስለሚባል ይፈራል።
>
> ከዚህ ቀደም ኮንሶ ውስጥ ዱሮ በሚባል አካባቢ የተወሰኑ ሰዎች ስርቆት በመፈፀም የሰውን እሁራ ፍየሎች እየሰረቁ በመቃብር ውስጥ እያረዱ ይበሉና ይመለሱ ነበር። ሌቦቹ መቃብር ቦታ ውስጥ ፍየሎችን ሰርቀው እያረዱ የሚበሉት ሰዎች «በመቃብር ውስጥ እሳት የሚያነዱት መናፍስ ይሆናሉ። ብለው ያስባሉ።» በሚል ነበር። በኋላ ህዝቡ አወቀባቸው። አንድ ቀን ፍየል ሰርቀው እሳት ሲያነዱ ሰዎችን መርጠው በአራቱም አቅጣጫ አስቀመጡ።
>
> አንድ ሰው ከሩቅ ሆኖ «አንተ እነዚህ እንማናቸው በሰው መካነ መቃብር ውስጥ ሆነው እሳት የሚያነዱ? ከሙታን መናፍስት ውስጥ አንዱ ጨካን መጥቶ አንዱን በጥፊ አይወለውለውም እንዴ?!» ብሎ ድምፅ ሲያሰማ ሌሎች የተደበቁ ሰዎች ደግሞ በየተራ «አዎ በቅርቡ ነው ያለነው፤ በቅርቡ ነው ያለነው፤ እረሳንም! እረሳንም! እረሳንም!» ሲሉ እነዚያ ሰዎች በርግገው እየወደቁ እየተነሱ ሸሹ። በመጨረሻም በተቅማጥ አለቁ ይባላል።
>
> (አቶ ኮራ ካራ መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ከላይ የቀረበው ቶርታ የሚተርከው ስለ ሌቦች ነው። ሌቦች የሰፈሩን ፍየሎች እየሰረቁ በመቃብር ስፍራ እያረዱ እንደሚበሉ፣ ህብረተሰቡም መንፈስ ይሆናሉ ብሎ ችላ እንዳላቸውና በመጨረሻም ሌቦች መሆናቸውን እንዳወቀ ነው።

ይህ ቶርታ የሚቀርብበት ማህበራዊ አውድ ማምሻ አካባቢ የብሂረሰቡ ተወላጆች በየሞራዎቻቸው ስር በሚሰባሰቡበት ጊዜ እንደሆነ አቶ ኮራ ነግረውኛል። በዚህ ማህበራዊ አውድም ማህበረሰቡን የሚመለከቱ በርካታ ጉዳዮች እንደሚነሱና ሌቦችን በሚመለከት የሚተረኩ ቶርታዎች እንደሚደጋገሙ አጫውተውኛል።

ይህን ቶርታ ስንመለከት በህብረተሰቡ ውስጥ ሌቦች እንደሚኖሩ፣ ነገር ግን እነዚህ ሌቦች የፈለገውን ያህል እየሰረቁ ቢደበቁም አንድ ቀን መጋለጣቸው እንደማይቀር ያሳየበት ነው። ይህንን ነገር በማጋለጥ በኩልም አጋዥ የሆኑ መናፍስት እንዳሉ በቶርታዎች ላይ በተደጋጋሚ ሲንጸባረቅ ይታያል። ይህ የሚሆነው ሆን ተብሎ ሲሆን ሌቦች «ስርቆታችንን ሰው ባያየውም ከእነዚህ መናፍስት ማምለጥ አይቻልምና እንጋለጣለን።» ብለው እንዲፈሩና ከስርቆት ተግባራቸው እንዲታቀቡ ስነ ልቦናዊ ጫናን ለመፍጠር ነው።

ይህ ስነ ልቡናዊ ጫና በትክክልም በብሄረሰቡ አባላት ላይ እንደሚንጸባረቅ ከላይ የቀረበው ቀርታ ያሳያል። ሊቦች ፍየሎችን እየሰረቁ እያረዱ የሚበሉት በመቃብር ውስጥ ነው። ለዚህም ምክንያታቸው ስጋውን ለመጥበስ የሚያነዱት እሳትና ጭስ ቢታይ እንኳ ተግባሩ የተፈጸመበት ቦታ መቃብር በመሆኑ ድርጊቱን ሰው ያደርገዋል ተብሎ እንደማይታመንና ቢታይም እንኳ መናፍስት ናቸው ተብሎ እንደሚታሰብ ሊቦቹ በመረዳታቸው ምክንያት ነው። ይሁን እንጂ እነዚሁ ሊቦች በየቦታው ተደብቀው እንደ መንፈስ የሌብነት ድርጊታቸውን የሚቃወሙ ድምፆችን ሲሰሙ የእውነት መንፈስ መስሏቸው ተደናግጠው ሲሮጡ መተረኩ ማሳያ ነው።

በቀርታው መጨረሻ ላይም እነዚህ ሊቦች በተቅማጥ ሲያልቁ ይቋጫል። ይህ መደምደሚያ ሁለት ነገሮችን ያሳያል። አንደኛው የራስ ያልሆነ ገንዘብን ቢበሉት ለጤና አይስማማም፤ ብሎም ይገድላል የሚል ማስጠንቀቂያ አዘል መልእክት መያዙ ሲሆን፣ ሁለተኛው ኾንሶ አካባቢ ያሉ መናፍስት ሊቦችን በመጠቆም እንደሚያጋልጡ መናገር ነው። ይህም የብሄረሰቡ ማህበራዊ ህይወት ላይ ጫናን በመፍጠር ስነ ምግባርን መቆጣጠሪያ ስልት እንዳለው አመላካች ነው።

### 4.8.2. ብልጠት በኾንሶ ቀራ ውስጥ

በብሄረሰቡ ዘንድ ተደጋግሞ ከሚቀርቡ ስነ ምግባራዊ ቀራዎችና ቀርታዎች ውስጥ ብልጣ ብልጥነትን የሚመለከቱ ይገኙበታል። በመቀጠልም በወ/ሮ ኩዬ የተተረከውን ቀርታ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

> በድሮ ጊዜ አንድ ብልጥ ሰው ነበር። ይህ ሰው የመንደሩን ሰዎች «ሂዱና ባሬ የተወለደች ቀጃ ወተት አምጡልኝ።» አላቸው። የሰፈሩም ሰዎች ተገርመው ለጥያቄው መልስ ለመፈለግ ወደ አንድ አማካሪ በመሄድ የተባሉትን ሁሉ በዝርዝር አስረዱት። አማካሪው በጥሞና ካዳመጠ በኋላ «እርሱ በሚያልፍበት መንገድ ሂዳችሁ ትልቅ ድንጋይ ከባችሁ ቆሙ። እርሱም ምን እንደምታደርጉ ቢጠይቃችሁ ድንጋይ እያዋለዳችሁ መሆኑን ንገሩት።» ብሎ መከራቸው። የመንደሩ ሰዎችም ብልጡ ሰው ወደሚያልፍበት መንገድ በመሄድ ድንጋይ ከበው ቆሙ። ብልጡም ሰው ሲያልፍ ሰዎቹን አስተውሏቸው ነበርና «ምን እያደረጋችሁ ነው?» ሲል ጠየቃቸው። እነሱም ድንጋይ እያዋለዱ መሆኑን ነገሩት። ብልጡም ሰው ፊቱ በተቀላቀለበት ድምጽ «የት አገር ነው ድንጋይ የሚወለደው?» ቢላቸው የመንደሩ ሰዎችም «የት አገር ነው ዛሬውኑ የተወለደች ቀጃ ወተት የምትሰጠው?» አሉት ይባላል።
>
> (ወ/ሮ ኩዬ አርጓይታ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ይህን ቀራ ወ/ሮ ኩዬ የነገሩኝ ፋኛ አንድ "ጨቃ" ቤት ይህንኑ መጠጥ እየጠጣን ነው። ካላይ እንደጠቀምኩት ብሄረሰቡን የሚመለከቱ ማንኛውም መረጃዎች መናገር የሚችሉት አባውንት እና ወንዶች በመሆናቸው ምክንያት ግለሰቧ ፎቶ ለመነሳት

ፍቅደኛ ባለመሆናቸው አልተቻለም። ተረኩቹንም የነገሩኝ ዓላማዬን በሚገባ ስላስረዳኋቸውና ተግባቢ ስለሆንም ጭምር ነው።

ወደ ተረታው ስንመለስ አንድ ብልጥ ሰው የመንደሩን ሰዎች ሰብስቦ ዛሬውኑ ከተወለደች ጥጃ የተገኘ ወተት አምጡ ይላቸዋል። የመንደሩም ሰዎች በትዕዛዙ ግራ በመጋባት ለአንድ አመካሪ ያማክሩታል እርሱም መፍትሄ ይሰጣቸዋል። በዚህ መፍትሄም በመጠቀም የብልጡን ሰው ያልተገባ ትዕዛዝ በብልጠት እንደተወጡ ያስረዳል።

ይህን ተረት ለምን አላማ ተነገረ? ብለን ስንመለከት ሁለት ነገሮችን እናገኛለን። አንደኛው ሰው በቸገረው ጊዜ ለችግሩ መፍትሄ ለማስተመጥ ሌሎች የተሻሉ ሰዎችን የማማከር አስፈላጊነትን ለማሳየት ሲሆን፣ ሁለተኛው ብልጦች ከራሳቸው በላይ ማንም ብልጥ የለም ብለው እንዳይኩፈሱና የብሄረሰቡን አባላት ያለአግባብ እንዳይበድሉ ለማሳሰብ ነው።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የኾንሶ ብሄረሰብ ቃላዊ ታሪኮች በማህበራዊ እና ባህላዊ አውድ ውስጥ ምን አይነት ፋይዳ፣ መልእክት እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳላቸው ማሳየትን ዋነኛ መነሻ አድርጎ የቀረበ ነው። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንም በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይት እና በምልከታ ከመስክ ተሰብስቧል። መረጃዎቹን ለመሰብሰብ እንዲያስችል ክፍት (open-ended questions) እና ዝግ (closed-ended questions) ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ለመረጃ ሰጪዎች ቀርበዋል። መረጃዎቹም በመቅረጸ ድምጽና በጽሁፍ ተይዘዋል። ታሪኮቹም በብሄረሰቡ ባህላዊ የአከፋፈል ስልት መሰረት ቶራ እና ቶርታ በማለት በሁለት ክፍሎች ለለመደብ ተችሏል። በጥናቱ የቀረቡትን የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ አውዳዊ ትንተና (contextual Analysis) ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ ትንተና ተካሂዷል።

### 5.1. ግኝቶች

ከመስክ የተሰበሰቡት የኾንሶ ቃላዊ ተረኮች ህብረተሰቡ «የእኔ ናቸው።» ብሎ የሚያምንባቸውና ባህላዊ አመዳደብ ጭምር እንዳላቸው ጥናቱ አረጋግጧል። እነዚህ ቶራ እና ቶርታ ተብለው የሚታወቁት ቃላዊ ታሪኮች የብሄረሰቡን ጥንተ አፈጣጠርና አመጣጥ፣ ማንነቱን፣ ለባህላዊ መሪዎቹ ያለው አተያይ፣ ከምንጮችና ከኩሬዎች ጋር ስላለው ዝምድና፣ የእደ ጥበብ ስራዎቹ፣ ለጋብቻ ያለውን አመለካከት፣ በአካባቢው ስለሚገኙ ነገሮች አፈጣጠር እንዲሁም የብሄረሰቡን ስነ ምግባርና ሞራል ምን እንደሚመስል አሳይተዋል። ታሪኮቹ በሚገኙበት ማህበራዊ እና ባህላዊ አውድ ውስጥ ለብሄረሰቡ አባላት ምን አይነት መልእክትና ፋይዳ እንዳላቸው ጥናቱ አሳይቷል።

ታሪኮቹም በብሄረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው፣ ዘወትር የሚተረኩ ብሄረሰቡ ስለማንነቱ፣ ባህሉ፣ ታሪኩ፣ ቅርሱን የመሳሰሉትን ከቀደመው ትውልድ የሚረዳበትና ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፊያነት የሚጠቀምበት ነው። ብሄረሰቡም በታሪኮቹ ውስጥ ከሚነሱት ማህበራዊ ክስተቶች ራሱን በማራቅ በጋራ ተስማምቶና ተሳስሮ ለመኖር እንዲሁም የማህበረሰቡን አንድነት አጽንቶ ለማቆየት እንደተጠቀመበት ጥናቱ አረጋግጧል።

## 5.3. የግኝቱ እንደምታዊ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በዋናነት የኸንስ ብረሰብን ማወቅ ለሚፈልግ ማንኛውም አካል በቂ መረጃ ይሰጣል። በተለይ ለፎክሎሪስቶች በብሄረሰቡ ላይ ጥናት እንዲያካሂዱ መነሻ ሀሳብ ያጭራል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በታሪክ፣ በስነ ሰብዕ እና በስነ ማህበረሰብ ጥናት መስክ ለሚሰማሩ አጥኚዎች በዚህ ጥናት የቀረቡትን የብሄረሰቡን ቃላዊ ታሪኮች እንደ መረጃ በመያዝ ሊገለገሉበት ይችላሉ ተብሎም ይታሰባል።

ጥናቱም የብሄረሰቡን ባህላዊ እውቀት፣ አስተሳሰብ፣ ልምድ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶች ላይ እውቀትን የሚያስጨብጥ በመሆን ለትምህርት አገልግሎትም ሊውል ይችላል። በመጨረሻም መንግስት በየአስተዳደር እርከኑ ለሚያካሂደው ልማት ስለ ብሄረሰቡ የቀረቡት መረጃዎች አቅጣጫ ሊያመላክቱ ይችላሉ ተብሎም ይገመታል።

## ዋቢ ጽሁፎች


ማንያለው አባተ። «የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው»። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999።

ምንዳ ንብሬ። «የጌዲኦ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው»። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000።

አግሬ ሞላ። «የሸኮቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና»። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 1999።

አወደ ያረጋል። «የኮንሶ ሀገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች ገላጭ ጥናት» በኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2003።

ከሁሉም በላይ። «የጎንደ ወይጦ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች»። በኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2003 ዓ.ም።

ኮራ ጋራ። የወንጌል እንቅስቃሴ በኮንሶ ከ1944-1999። ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ፤ ኮንሶ፣ 1999።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። መጽሐፍ ቅዱስ። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፤ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን። በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ከሚገኙ 20 ወረዳዎች ኢንቃንጀብል ባህላዊ ቅርሶች ላይ የተደረገ ኢንቬንቶሪ፤ አዲስ አበባ፤ ቅጽ 3፣ 2001።

የኮንሶ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት። አጠቃላይ የግብርና መረጃ፣ 2005።

የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ሕዝቦች ፕሮፋይል። ፍቅረ ሰላም ማተሚያ ቤት፤ አዋሳ፣ 2001።

ፈቃደ አዘዘ። የስነቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመጻሕፍት ማዕከል፣ 1991ዓ.ም።

Abdulkadir Haji Jima. "Some Cultural Elements As Reflected in Somali Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1982.

Abraham Alemu. "Jimma Oromo Oral Prose Narratives: A Preliminary Descriptive Analysis." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 2000.

Amborn, H. "History of the Events and Internal Development: The Example of the Burji Konso Cluster." In Tadesse Beyene (ed). *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*. 1988.

Anna, De Finna. *Identity in Narrative: a Study of Immigrant Discourse.* Amsterdam/Philadelphia, John Benjamins publishing, 2003.

Bascom, William R. "Four Functions of Folklore". The Journal of American Folklore, Vol.67, No.266 (Oct.-Dec., 1954), 333-349.

____ "The Forms of Folklore: Prose Narratives". In Segal, Robert A. (Ed.). *Anthropology, Folklore, and Myth*. New York and London: University of Lancaster, Garland Publishing,1969.

____ "The Forms of Folklore: Prose Narrative". *The Journal of American Folklore*. Vol.78, No.307 (Jan.-Mar., 1965), 3-20, American Folklore Society, http://www.jstor.org/stable/538099.

Bauman, Richard. *The Field Study of Folklore in Context* in Handbook of American Folklore, (ed.) Richard Dorson. Bloomington: Indiana University Press, 1983: 362-368.

____ *Story, performance, and Event: Contextual studies of Oral Narratives.* Cambridge University press, New York, 1986.

Bayileyegn Tasew. "Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethinc Genres and Social Functions." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1999.

Ben-Amos, Dan. *Folklore in context*. New Delhi, South Asian puplisher, 1982.

___."*Folktale*." In Bauman, Richard. (ed.) *Folklore, Cultural Performances, and popular Entertainments*. New York oxford, Oxforad University Press, 1992.

CSA "The Population and Housing Census of Ethiopia, Southern Nations and Nationalities and People's Regions." Central Statistical Authority. Addis Ababa, 2007.

Dégh, Linda. "Oral Folklore: Oral Narratives." In Dorson, Richard M. (Ed.) *Folklore and Folklife: An Introduction*. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972. 54-58

Dorson, Richard M. (Ed.) *Folklore and Folk Life: An Introduction*. Chicago: The Univeristy of Chicago Press, 1972.

___. *Current Theories of Folklore*. Printed source (com. Fekade Azeze). 2003, pp. 251.

Finnegan, Ruth. *Oral Literature in Africa*. Oxford: Clarendon Press, 1970.

Goldstein, Kenneth S. *A Guide for Field Workers in Folklore*. Detroite: Gale Research Company, 1974.

Hallpike, C.R. "Some Stories from Konso." Ethiopian Observer, 1966. X(no.3):230-232.

___."The Status of Craftsmen among the Konso of South West Ethiopia." Africa,1968. 38(3): 258-269.

___."The Konso of South Western Ethiopia: A Study of The Values of a Cushitic People." Oxford, Clarendon Press.1972.

Kansite Gellebo." Mora: A study of the People Place and it's multiple purpose among the Konso people of southern Ethiopia." M.A. Thesis, Department of Social Anthropology, Addis Ababa University, 2011.

Lakew Regassa " Settelment and clanship among the Konso" M.A. Thesis, Department of Social Anthropology, Addis Ababa University, 1998.

Mamitu Yilma" Some Aspects of the States of Women among the Konso of Southern Ethiopia." M.A. Thesis, Department of Social Anthropology, Addis Ababa University, 2002.

Melakneh Mengistu. "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Okepwho, Lsidore. African oral Literature. Bloomington and Indianapolis: Indiana University Press, 1992.

Oring, Elliot. *Folk Group and Folklore Genres: An Introduction.* Logan, Utah: Utah University Press, 1986.

Sahilu Kidane. "Borana Oromo Prose Narrative: A Contextual Study." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1996.

Shacko O. "The Nine Cans of the Konso". Sociology Ethnology Bulletin. Vol.1(no.3). 1994. 80-92

Shinohora, T. "The Symbolic Meaning of the Pot on the Roof. A case study of the Konso in Southern Ethiopia". Nilo-Ethiopian Studies. Kyoto. 1993.

Sims, Martha C. and Martine Stefphens.*Living Folklore, An Introduction to the Study of People and their Tradition.* Logan, Utah: Utah State University Press. 2005.

Teferi A. "Resource Use in Konso." Sociology Ethnology Bulletin. 1992, 1: 22-25.

Tesfaye Gebre Mariyam. "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Vansina, Jan. *Oral Tradition as History.* Madison, Wisconsin: University of Wisconsin Press, 1985.

Watson, E.E. "Ground Truths: Land and Power in Konso, Ethiopia." A Dissertation Submitted for the Degree of Philosophy. Cambridge, University of Cambridge, 1998.

Watson,Elizabeth and Lakew Regassa. "Konso" Living on the Edge: Marginalised minorities of craftworkers and Hunters in South Ethiopia. Dena Freeman and Alula Pankkhurst (ed.). Departemment of sociology and social Adminstration, Addis Ababa University, 2001.

Yihenew Jembere. "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1996.

Young, katharin. "The Notion of context." Western states folklore Society. Vol. 44, no. 2 (Apr.,1985) pp.115-122

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፦ የቁርራ እና ቁርታዎች ስብስብ

1. የኹንሶዎች አርክንና እደ ጥበብ

### ቁራ አንድ

የኹንሶ አርክን ስራ

በድሮ ጊዜ የኹንሶ ህዝብ በእሳት አደጋና በጠላት ይጠቃ ነበር። በኋላ ራሱን ከጠላትና ከእሳት አደጋ ለመከላከል በሚኖርባቸውን ቀበሌያትና መንደሮች በሙሉ የካብ አጥር ማጠር ጀመረ። በእነዚህ ካቦች ዙሪያ መግቢያና መውጫ በሮች አሉት። የካቡ መግቢያና መውጫ በሮች ማታ ተዘግተው ጠዋት የሚከፈቱ ናቸው። የማህበረሰቡ አባላት ለስራና ለሌሎች ተግባራት የሚሰማሩት የካቡ በሮች ተከፍተው በአካባቢው የጠላት ኮቴ አለመኖሩን በሚፈትሹ ሰዎች ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ብሄረሰቡ ከሄደበት ተመልሶ ሲገባም በሩ የሚዘጋው አካል ምንም አይነት አደጋ የሚያስከትል ነገር አለመኖሩን ካረጋገጠ በኋላ ነው። እንደ አጋጣሚ ሌላ አካል በሩን ሰብሮም ይሁን የካብ አጥሩን ጥሶ ቢገባ የእሪታ ድምጽ ይሰማል። በዚህን ጊዜ ማንም ድምጹን የሰማ ሰው ከየጎጆው በፍጥነት በመውጣት ቅጥሩን ጥሶ የገባውን ጠላት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያዝ ወይም የሚገደል ይሆናል። የአጥር ካቡ አሰራርም ቀጥ ያለ ሳይሆን በየተወሰነ ርቀት የሚጠማዘዝ በመሆኑ ሮጦ ለማምለጥ የማያመች ነው። የብሄረሰቡ አባላትም በየጥጉ ላይ በመቆም የሚሸሸውን ጠላት እሱ ሳያይ ከፊቱ በቀላሉ ሊያገኙት የሚችል አይነት ነው። የጎጆዎች በሮች አሰራር ጭምር ጠላትን ለመከላከል በሚያስችል ሁኔታ የተሰሩ ናቸው። የአንዱ ቤት በር ከፊት ለፊት ከሆነ ከጎኑ ያለው ቤት በር ደግሞ ከሱ በተቃራኒ አቅጣጫ ነው። በአጥሩ በር አካባቢ የጠላት ዱካ የሚታይ ከሆነ የጥበቃ ስራ የሚሰሩ አካላት በአካባቢው ተሰሚነት ላላቸው የአገር ሽማግሌዎች ያስረዳሉ።

(ከዱራይቱ በዑድን ወይይት የተገኘ መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁራ ሁለት

የኹንሶ ሞራ አሰራር

የኹንሶዎች ቤት ሲሰራ እንደማንኛውም አይነት ነበር። በኋላ ኬኬሻ የሚባል የሞራ አይነት የሳር አከላደን ያለው ጎጆ መስራት ተጀመረ። ይህ የተጀመረው በኮንሶ አልፎ አልፎ ድርቅ የሚከሰት ሲሆን በዚህም ምክንያት ብዙ ከብቶች በምግብ እጥረት ይሞቱ

ነበር። ይህ ኬክሻ የሚባለው ባለሁለት ደረጃ ያለው የሳር ቤት ክዳን በብዙ ሳር የሚከደን ሲሆን በደህና ጊዜ ለቤቱ ውበትና ጥንካሬ በመስጠት ያገለግላል። ድርቅ ሲመጣ ደግሞ ከዚህ የሳር ክዳን ውስጥ ሳር እየተመዘዘ ለከብቶች በመስጠትና በመመገብ ክፉ ጊዜ እንዲያልፍ ይደረጋል። በደህና ጊዜ ደግሞ በሳር መልሶ ይከደናል።

(አቶ ቱሬ ካምብሮ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቱሬ ሶስት

የኾንሶ ዋካ

በኾንሶዎች ዋካ ለጀግኖቻቸውና ለማህበረሰቡ ታላላቅ ስራ ለሰሩ ሰዎች የሚሰራ ነው። ይህ ዋካ የሚሰራው ከእንጨትና አንዳንድ ጊዜም ከሾጣጣ ድንጋይ ነው። ለዋካ የሚሆነው እንጨትም ቶሎ እንዳይበላ የጥድ እንጨት ነው። በዋካውም ላይ የሰውዬው ምስል፣ የገደላቸው የዱር እንስሳት፣ እንዲሁም ያለው ሚስት የሚያሳዩ ትንንሽ ድንጋዮች አብረው ይተከላሉ።

(አቶ መምሩ ካይፊንቶ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም.)

2. የነገሮችና የቦታዎች ስያሜን በሚመለከት የሚተረኩ ቱሬዎች

ቱሬ አራት

ጅብ ለምን ያነክሳል?

በድሮ ጊዜ ጅቦች በጣም ትልልቅ ደኖች ውስጥ ይኖሩ ነበር ይባላል። በጫካው ውስጥ የተለያዩ ምግቦች፣ ጥንብና ቆሻሻ በብዛት ቢኖርም ጅብ በተፈጥሮው ሆዳምና ስግብግብ ስለሆነ ምንም አይበቃቸውም ነበር። እናም በአንድ ሀሳብ ተስማሙ። ይህም በቅርብ ከሚገኘው ትልቅ ተራራ ላይ በየጊዜው ደመና ስለሚታይ ይህንን ደመና ለመብላት መሰነው ሄዱ። ከብዙ ድካም በኋላ ተራራው ላይ ሲደርሱ ቅርብ የመሰለው ደመና ከተራራው ከፍ ማለቱን አስተዋሉ። ከዚያም ጅቦቹ አንዱ በአንዱ ተደራርበው ለመድረስ ሲሞክሩ ከስር ያለው ጅብ ከበላዩ ያሉት እየበሉ መስሎት «እባካችሁ ስጡኝ»» ሲል ጠየቃቸው። አለማግኘታቸውን ቢረዳም ደክሞት ነበርና አዳልጦት ሲወድቅ ከላይ ተንባብረው የነበሩት በጠቅላላ ተንደው እግራቸው ተሰባበረ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጅብ አንካሳ ሆነ ይባላል።

(ወ/ሮ ኩፌ አርሻይታ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁራ አምስት

የዝንጀሮ ለምን እርሻ የለውም?

በድሮ ጊዜ ዝንጀሮ ከሰው ጋር አብሮ ይኖር ነበር። በዚህም ምክንያት ሰው የሚያደርገውን ሁሉ ለማድረግ ይችል ነበር። ከሰው ጋር ብዙ ከተላመደ በኋላ ብቻውን ለመኖር ስለፈለገ ሸፍቶ ወደ ጫካ ገባ። የሰው ልጆችም ዝንጀሮዎችን እያሳደዱ ይገድሉ ስለነበር ከዝንጀሮዎች መሃል አንዱ «እኛ ሞተን እያለቅን ነው። አንተ የሰው ልጆችን ታውቀዋቸዋለህና ወደ እነርሱ በመሄድ ለእኛ የሚሆን የእህል ዘር አምጣልን።» ሲሉ ለመኑት። ዝንጀሮውም በመስማማት ሄዶ ዘሩን አመጣ። ነገር ግን ካሉት የዝንጀሮዎች ቁጥር ጋር ሲተያይ ያመጣው በቂ ሆኖ ስላልተገኘ እንዲጨምር ተነገረው። ዝንጀሮም ተመልሶ ሄዶ አቅሙ የፈቀደውንና በቂ ነው ብሎ የገመተውን ዘር ካመጣ በኋላ «በሉ እንግዲህ ዘሩን የምንዘራበት ቦታ መንጥራችሁ አስተካክሉ!» ሲል አዘዛቸው። ዝንጀሮዎቹም ቦታውን መንጥረውና ደልድለው ሲጨርሱ ዘሩን ዘርተው በእጃቸው የተረፈውን «ሌባ እንዳይወስድብን።» ሲሉ በሉት። የተዘራው ዘርም ሳይበቅል ቀረ። ለዚህም ነው ዝንጀሮ እስከ ዛሬ ድረስ እርሻ የሌለው የሚባለው።

(ወ/ሮ ከቴ አርሻዶታ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁራ ስድስት

በደንገሌቱ

የዥንጎ ህዝቦች ብዙ ጊዜ ወደ አደን ይሄዳሉ። በዚህን ጊዜ ዱራይቱ በደንገሌቱ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች በአደን ማንም አይችላቸውም ነበር። ሁል ጊዜ አድነው ግዳያቸውን ተሸክመው ነበር ወደ ሰፈራቸው የሚሄዱት። በዚህን ጊዜ እነዚህን ነዋሪዎች ሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎች በደንገሌቱ አሏቸው። ይህም በኩንስኛ ሳይገዝ አይገባ ማለት ነው።

(አቶ ዲዶ ገለቦ መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁራ ሰባት

ጨለቅሌ

በዥንጎ አውን ሚሽን አካባቢ ያለው ቦታ በጣም ደን ነበር፤ እህል አይዘራበትም፤ እንጨትም አይለቀምበትም ነበር። ይህ ቦታ ለካላ ቤተሰቦች ለመቃብር ብቻ የተሰጠ ነበር። ቦታው የሚባለው ጨለቅሌ ሲሆን በኩንስኛ የመጤዎች ቦታ ማለት ነው።

(አቶ ጊዶና ባደናመስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቁራ ስምንት

በቃውሌ አስያየም

ከሰፈት በፊት የኾንሶ ዋና ከተማ በመሆን ለረዥም አመታት ያገለገለችው በቃውሌ ነበረች። ይቺ ከተማ ስያሜዋን ያገኘችው በአጼ ሚኒሊክ እንደነበር ይነገራል። የሚኒሊክ ጦር ለማዕከላዊ መንግስት ለማስገበር ኾንሶ ድረስ ከመጣ በኋላ ሚኒሊክ «ከዚህ በኋላ ሌላ ግዛት አልፈልግም፤ በቃ ውሌ።» በማለታቸው ከተማዋን በቃውሌ ተባለች ይባላል።

(አቶ ቱራ ካምብር መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.)

3. ጋብቻን በሚመለከት የሚተረኩ

ቁራ ዘጠኝ

የኾንሶና ጋብቻ

በኾንሶ ባህል ወንዶች ሴቶችን አይደፍሩም። ሴቶችም ወንዶችን አይደፍሩም። አንድ ወንድ ከሚስቱ ውጪ ሌላ ሴት ቤት ሄዶ ሌላ ሰው በተኛበት ቁርበት ላይ ሴት ከተገናኘ ለሰውየው የሚመች ነገር አይኖርም። ይከሳል፤ በመጨረሻም ይሞታል። ሴትም እንዲሁ። በማህበረሰቡ ውስጥ ሙሉ ሲጋዊ ስሜት የለም ማለት ሳይሆን አንድ ሚስቱ የሞተችበት ሰው ሲጋዊ ፍላጎት ቢኖረው ይህን ስሜቱን የሚፈጽመው በተመሳሳይ መልኩ ባሏ የሞተባትን ሴት በማግባት ብቻ ይሆናል። በባልና በሚስት በኩል በትዳራቸው መካከል ማመንዘር እንዳይኖር በብሄረሰቡ በኩል ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣ መተዳደሪያ ደንብ የሚቆጠር ነገር አለ። ይህን ድርጊት መፈጸም በብሄረሰቡ «ኦሌማሌማ» ይባላል። ፍቺውም ማመንዘር የሚል ነው። ይህንን ፈጽሞ የሚገኝ ሰው ከፍተኛ ውግዘትና ቅጣት ይደርስበታል። የኾንሶዎች የቤቶች አሰራርም አንዱ ወደ ሌላው ቤት በመሄድ ለማመንዘር አመቺ እንዳይሆን የአንዱ ቤት በር በሌላው ቤት በር ፊት ለፊት ተደርጎ ነው።

(ፋኛ በዑድጎ ውይይት የተገኘ መስከረም 18 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁራ አስር

ባልና ሁለት ሚስቶች

በድሮ ጊዜ ሁለት ሚስት ያገባ አንድ ሰው የመጀመሪያ ሚስቱ ልጆች ሲኖሯት ሁለተኛዋ ግን አንድም አልወለደችም ነበር። ሰውዬው የሚበላውና የሚያድረው ከሁለተኛ ሚስቱ ቤት ነበር። ወደ መጀመሪያዋ ሚስቱ ቤት ግን መሄድም ሆነ ልጇን ማየት አቁሞ ነበር። አንድ ቀን ወደ መጀመሪያ ሚስቱ ቤት ሲሄድ የመጨረሻ ልጇ ወደ እርሱ በመቅረብ ተደገፈው። አባቱም ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ሲያቅፈው ልጁ ጥርስ የሌለው ባዶ ድድ መሆኑን ስለተመለከተ ከት ብሎ ሳቀ። ልጁን እንዳቀፈም ወደ መጀመሪያ ሚስቱ ሄደ። ሚስትም ወደ ቤቷ መምጣቱ አስደንቋት «አባታችሁ ዛሬ ምን ቢያገኝ ነው ወደዚህ ቤት በፈገግታ ተሞልቶ የመጣው?» በማለት የመጀመሪያ ልጇን ጠየቀችው። እርሱም የታናሽ ወንድሙን ጥርስ ያለመኖር ተመልክቶ መሆኑን ነገራት። እናት ይህንን ስትሰማ የራሷን ጥርስ ሙሉ በሙሉ አራገፈች። ልጇም ሲመለከታት ከጥቂት ሰዓታት በፊት ጥርሷ ጤናማ መሆኑን ስለሚያውቅ አሁን ምን ሆና እንደረገፈ ጠየቃት። እርሷም «አባታችሁ እኛ ቤት የማይመጣው የሚያስቅ ነገር ስለሌለ ይሆናል ብዬ ነው።» አለችው ይባላል።

(አቶ ገለሲሞ ዱንቴ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁራ አስራ አንድ

ሸለምጥማጥና ልጅ (ያላቻ ጋብቻ)

በድሮ ጊዜ ሸለምጥማጥ ሚስቱ ሞታበት ከአንድ ልጁ ጋር አብሮ ይኖር ነበር። ልጁም አድጎ ለአቅመ አዳም ሲደርስ አባቱ እንዲያገባ ይጠይቀዋል። ልጁም ለአባቱ «አባቴ በእኔ ምርጫ እንጂ በአንተ ምርጫ አላገባም።» ሲል ይመልስለታል። ከጊዜ በኋላ ለአባቱ «አግብቻለሁ።» ለማለት ሚስቱን አስከትሎ ይመጣል። አባት «ሚስትህ የት አለች?» ሲል ጠየቀው። ልጅም «በመሬት እየተሳበች የምትመጣው ሚስቴ ናት።» በማለት በአቅራቢያው ያለችውን እባብ አመለከተ። አባትም «ምነው ልጄ! ዘራችንን ከጨረሱትና እናትህንም ከገደሉት መካከል ታገባለህ? በል ይልቅ ቶሎ ብለህ አባራት፤ ወይም ቅቤ እንዳለው ብለህ ጥለሃት ጥፋ።» ብሎ እንደመከረው ጥሏት ጠፋ ይባላል።

(አቶ ካሌቴማ ቀገኘ መስከረም 18 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁራ አስራ ሁለት

ኽውዳዎች

ብዙ ጊዜ ኽውዳዎች ብሊማብሊጥና ከቦታ ቦታ ሄደው የሚሰሩና ቋሚ መኖሪያ የሌላቸው ናቸው። በዚህም ምክንያት ብዙም እምነት የሚጣልባቸው አይደለም። አንድ ቀበሌ ከሌላ ቀበሌ ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ሚስጢርም የሚያባክኑ ናቸው። አንድ ቀበሌና ሌላ ቀበሌ እርስ በርስ በሚጋጩበት ጊዜ ከህዝብ ጋር ለጦርነት ይወጣሉ፤ ነገር ግን በጦርነቱ የአንድ ቀበሌ ሽማኔ ከሚዋጋው ቀበሌ ካለው ሽማኔ ጋር ድንጋይ የሚወረውሩ ይመስሉና ርህብን ለመከላከል ቂጣ ይወረውራሉ፤ ወይም ለልብስ ማንነትን የሚወል ኖራ ቢጤ ነገር ልክ ኑዋ ባልጩት አስመስሎ እዚያ ላለው ኽውዳ ይወረውርሊታል።

ኽውዳዎች በውሸት «እኔ ልሙት! ልጄ ይሙት!» ብለው የሚምሉ ቢሆንብም ማላው ምንም ስለማያደርጋቸው «ፊራ ኽውዳ ሊክሺ» ማላ የሀውዳ ሰዎችን ከመግደል ይልቅ ያበጣቸዋል። ይባላል።

(ሊ/ር ገዋዶ አይላዶ እና አቶ ኮራ ካራ መስከረም 26 እና 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

4. ግብረ ገብ ነክ የኾንሶ ቁራዎች

ስለ ሌቦች የሚተረክ

### ቁራ አስራ ሶስት

አሁን በቅርቡ በኾንሶ የተከሰተ ተጨባጭ የሌቦች ታሪክ አለ። ለጀግኖች የሚተከሉ ዋካዎች በየእርሻውና በየአደባባዩ ነበሩ። እነዚህን ዋካዎች ሌቦች በየሊሊቱ እየተሰማሩ ይሰርቁ ጀመር። ሌቦቹ በየመንደሩ ለመስረቅ ሲሄዱ ተገኝተው ሲጠየቁ የሚሰጡት ምክንያት የተለያየ ነበር። አንዳንዱ «በጣም ብዙ ሚሊየን ብር ስለሚያወጣ የቁራ እንቁላል ነው የምንፈልገው።» ይላሉ። ቁራ እንቁላሉን የሚጥለው ገደል ላይ በመሆኑ የሚያገኝ የለም። እውነት መስሏቸው እንቁላሉን በገደል ለመፈለግ ብለው ሰዎች ሞተዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ «ዘንዶ ወርቅ አለው። ውሀ ሲጠጣ ወርቁን አስቀመጦ ነው። ስለዚህ ይህንን ተከታትለህ ብታመጣ ብዙ ሚሊየን ብር ታገኛለህ።» ይላሉ። ሌሎቹ ደግሞ «ዘንዶውን አነደህ ብትገደለው ወርቁን ጥፍሩ ላይ ታገኘዋለህ።» ይላሉ። ዘንዶን ለመግደልም በጣም ከባድ ነው። ሌቦቹ ግን ይህንን ስልት ተጠቅመው ሰዎቹ በከንቱ ሲለፉ እነሱ ዋካዎቹ የት የት ቦታ እንዳሉ በመሰለል አንድ በአንድ ይለቅሙት ነበር። በኋላ ዋካዎቹ እየተመናመኑ ሲመጡ የኮንሶ ሰው ነቃባቸው። ከዚያ በኋላ

በሌሊትም ሆነ በቀን መኪና ሲመጣ ንቅቶ በመጠበቅና የሌቦችን ኮቴ በመከታተል ብዙ ዋካዎች ከሌቦች እጅ ሊያዩ ችሏል።

(አቶ ካሴ ቱማ ተገኘ መስከረም 18 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁራ አስራ አራት

### ሸለምጥማጥና ሚስቱ ቆቅ

በድሮ ጊዜ ቆቅና ሸለምጥማጥ ትዳር መስርተው አንድ ላይ ይኖሩ ነበር። ሸለምጥማጥ «የእኔ» የሚለው እርሻ ሳይኖረው «አለኝ» እያለ ሚስቱ ቆቅን ይዋሻት ነበር። አንድ ቀን «ከእርሻችን ሂደሽ እሸት አምጪልኝ።» ብሎ እርሻውን ከርቀት አሳያት። ቆቅ ወደ አሳያት እርሻ ሄዳ እየዘፈነች እሸት ስትለቅም የእርሻው ባለቤት ተመልክቷት «ደኸች የማን ናት የሰው እርሻ ውስጥ የምትዘፍን?» ብሎ አባረራት። ቆቅም ወደ ሸለምጥማጥ ሄዳ ወዳሳያት እርሻ ሄዳ እሸት ስትለቅም ባለቤቱ እንዳባረራት ነገረችው። ሸለምጥማጥም «እኔ መች እዚያ ሂጂ አልኩሽ!? የእኔ እርሻ እኮ ግራር ያለበት ነው።» በማለት አታለላት። ለካ ሸለምጥማጥ ሚስቱ የምታስርለትን ስንቅ በሌሎች እርሻ ውስጥ እየተዘዋወረ ሲበላ ውሎ ቀኑ ሲመሽ ሲሰራ እንደዋለ ለማስመሰል ኩይሳ አፈር ላይ እየተንከባለለ ውሎ ይመጣ ነበር።

(አቶ ገለሲሞ ፋንቱ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁራ አስራ አምስት

### ቃሉን የማጠፍ መዘዝ

አንድ ሰውዬ ከብቶች ነበሩት። ከብቶቹን «በሮራ» እንዲጠብቅለት አንድ ደሀ ልጅ ይቀጥርና «በደንብ ከጠበቅህ አንድ ከብት እሰጥሀለው።» ይለዋል። ልጁም እጅግ በጣም ጎበዝ ነበርና ከብቶቹን እየተንከባከበ ስለያዛቸው ከብቶቹ እጅግ በጣም በዙ። አንድ ቀን የከብቶቹ ባለቤት ኮብ ላይ ወጥቶ ሲያይ ከብቶቹ በጣም በዝተውና አምርባቸው ይመለከታል። ከዚያም ወደ እረኛው ይመጣና «አንተ ልጅ በጣም ጎበዝ ስለሆንክ ከዛሬ ጀምሮ ያዊ የምትመለከታት ጊደር ያንተ ትሁን።» ይልና ቃል ኪዳን ይገባለታል። ልጁም የሱን ጊደርና ከብቶችን በሚገባ እየጠበቀ ሁሉም በዙለት። አንድ ቀን እረኛው የከብቶቹን ባለቤት «ሚስት አግብቼ የራሴን ከብቶች እየጠበቅሁ መኖር እፈልጋለሁ።» ይለዋል። የከብቶቹ ባለቤትም ከብቶቹ ቢበዙለትም «እነዚህን ሁሉ ከብቶች ከእኔ አግኝተህ እያዳለው ትላለህ? አትሄድም!» ይለዋል። ልጁ «እሄዳለሁ!»

ይላል። በዚህ ጊዜ የከብቶቹ ባለቤት «እንግዲህ አንድም ላንተ ልሰጥህ ቃል የገባሁት ከብት የለም። ከብቶቹ በሙሉ የኔ ናቸው፤ ከሄድክ ባዶህን መሄድ ትችላለህ።» ይለዋል። ልጁም «እንዴ ጊደር ያንተናት ብለህ ሰጥተኸኝ የለም? ስለዚህ ጊደሯና ከሷ የተገኙት ከብቶች በሙሉ የኔ ናቸው።» ይለዋል። ሰውየውም «አይደሉም!» ሲል ይመልስለታል።

በዚህን ጊዜ ልጁ ሽማግሌዎችን ይሰበስብና «ቃል ኪዳን የገባልኝን ቃል አጥፏል።» ሲል ይነግራቸዋል። ሽማግሌዎችም ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው ለማግባባት ሞከሩ ሰውዬው ግን «የሰጠሁት ምንም ከብት የለም!» በማለት ካደ። ለማግባባት ቢሞክሩም ሊሳካ አልቻለም። ሽማግሌዎችም «እንግዲህ እዚህ አለት ላይ ሆናችሁ ቃል ኪዳን ስትገቡ በመሀላችሁ ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነውና እሱ ይፍረደው!» በማለት ትተው ይሄዳሉ።

ልጁም እዚያው ባለበት እያለቀሰ ሳለ የከብቶቹ ባለቤት የተቀመጠበት አለት ተሰንጥቆ እስከ ወገቡ ድረስ ይውጠዋል። በዚህን ጊዜ ሰውዬው መላቀቂያ ሲያጣ «እረ አባካችሁ! አድኑኝ!» በማለት ይጮሀል። ሽማግሌዎቹ ተመልሰው ይመጡና «የሆነውን ነገር ሁሉ ካልነገርከን አናላቅቅህም።» ይሉታል። እሱም «ከብቶቹን እሰጥሀለሁ። ብዬ ቃል ገብቼ ነበር፤ ነገር ግን ቃል ኪዳኔን አጥፌአለሁ፤ ልጁ ያለው እውነት ነው፤ እንዲውም ከእኔ ይልቅ ከብቶቹን ያበዛው እሱ ነውና ከእኔ ተጨምሮ ይሰጠው። ከእግዚአብሔር ጋርም አስታርቁኝና ከዚህ አጣብቂኝ ገላግሉኝ።» አለ። በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች እንደተባለው ለልጁ ከብቶቹን ሰጥተው አስናበቱት። ሰውዬውንም ከአጣብቂኙ አዳኑት ይባላል።

(አቶ ከራ ጋራ ጥቅምት 02 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ተራ አስራ ስድስት

ከንቱ ምኞት በዱሮ ጊዜ እጅግ የሚዋደዱ የደሀና የሀብታም ልጆች ነበሩ። የሀብታሟ ልጅ የምትለብሳቸው ልብሶችና የምታጌጣቸው ጌጦች በጣም ውድ ነበሩ። የደሀዋ ልጅ ግን የምትለብሰው ልብስ በጣም ያረጀና የተበጣጠሰ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ውሀ ለመቅዳት ከራ ሄደው እንዳለ የደሀዋ ልጅ የሀብታሟን ልጅ ልብሳቸውን ተቀያይረው በኩሬ ውስጥ መልካቸውን እንዲመለከቱ ለመነቻት። የሀብታሟም ልጅ ጓደኛዋን ላለማስከፋት ብላ «እሺ» አለቻት። በኋላ የሀብታሟ ልጅ ጥላዋን ለማየት ወደ ኩሬው ጎንበስ ስትል የደሀዋ ልጅ ገፍትራ ኩሬ ውስጥ ጨመረቻት። ከዚያ ቤቷ ሄዳ ትተራ ውስጥ ተደብቃ ትኖር ጀመር። ከእለታት አንድ ቀን የሃብታሟ ልጅ ቤተሰቦች ውሀ

ለመትዳት ወደ ኩሬው ሲሄዱ የልጃቸውን ድምጽ ስለሰሙ ጠንቋይ ቤት ሄደው ሁኔታውን በዝርዝር ያስረዳሉ። ጠንቋዩም ጥቁር በሬ ገዝተው ጭራው ላይ እምቧይ አስረው ወደ ኩሬው እንዲጨምሩ አዘዛቸው። የልጅቷ ቤተሰቦችም እንደታዘዙት ፈጽመው ልጃቸውን አገኙዋት። በኋላ ለዚህ ያበቃቻችትን የደሀዋን ልጅ ካለችበት አፈላልገው ገደሏት ይባላል።

(አቶ መምሩ ካደፈንቶ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቁራ አስራ ሰባት

ብልጥ ለብልጥ

በድሮ ጊዜ አንድ ብልጥ ሰው ነበር። ይህ ሰው የመንደሩን ሰዎች «ሂዱና ዛሬ የተወለደች ጥጃ ወተት አምጡልኝ።» አላቸው። የሰፈሩም ሰዎች ተገርመው ለጥያቄው መልስ ለመፈለግ ወደ አንድ አማካሪ በመሄድ የተባሉትን ሁሉ በዝርዝር አስረዱት። አማካሪው በጥሞና ካዳመጠ በኋላ «እርሱ በሚያልፍበት መንገድ ሂዱችሁ ትልቅ ድንጋይ ከባችሁ ቆሙ። እርሱም ምን እንደምታደርጉ ቢጠይቃችሁ ድንጋይ እያጥለላችሁ መሆኑን ንገሩት።» ብሎ መከራቸው። የመንደሩ ሰዎችም ብልጡ ሰው ወደሚያልፍበት መንገድ በመሄድ ድንጋይ ከበው ቆሙ። ብልጡም ሰው ሲያልፍ ሰዎቹን አስተውሏቸው ነበርና «ምን እያደረጋችሁ ነው?» ሲል ጠየቃቸው። እነሱም ድንጋይ እያጥለሉ መሆኑን ነገሩት። ብልጡም ሰው ፈገግ በተቀላቀለበት ድምጽ «የት አገር ነው ድንጋይ የሚወለደው?» ቢላቸው የመንደሩ ሰዎችም «የት አገር ነው ዛሬወኑ የተወለደች ጥጃ ወተት የምትሰጠው?» አሉት ይባላል።

(ወ/ሮ ከፉ አርጃደታ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም.)

(ለ)ቶርታ

1. የብሄረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥና ስያሜን በሚመለከት የሚተርኩ

ቶርታ አስራ ስምንት

የኹንሶ ብሄረሰብ ጥንተ አፈጣጠር (ሀ)

እምላክ በአንድ ወቅት ኹንሶ ይመጣል። እሱ ሲመጣ አንድ ቅል ነበር ይከፈትና በውስጡ «ኢታንታ» የሚባል እርሶ አደር ከነእርሻ መሳሪያው ተፈጠረ፤ ቀጥሎም «ኻውላ» የሚባል የእደጥበብ ባለሙያ ከነሸመና መሳሪያዎቹ በመፈጠሩ የኹንሶ ምድር በእነዚህ ሁለት ሰዎች ዘር እንደተሞላ በአፈታሪክ ይነገራል።

(ዶ/ር ገዋዶ እይላዶ መስከረም 26 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁርታ አስራ ዘጠኝ (ለ)

ከዚህ በፊት በኹንሶ ባደሞ የሚባል ቤተሰብ ነበር። ይህ ቤተሰብ ኪቶሌ የሚባል ጫካ ውስጥ ትል የሚያፈራ ተክል ተክሎ ትሉ እያደገና እየወፈረ እየወፈረ ሄደ። በአካባቢው የሚገኘው ሰው «ይህ ተክል ለምን ከእትም በላይ እየወፈረ ሄደ?» በማለት እየተከታተሉት ነበር። አንድ ቀን ትሏ ፈንድታ ለሁለት ተከፈለች። ከዚያ ውስጥም ሁለት ህጻናት ወጡ። በሁለቱ ህጻናት እጅ ላይም የአምባር ምልዕክት ነበር። በአንዱ ህጻን ልጅ ላይ ያለው የአምባር ምልክት የአርሶ አደር ባህላዊ መሪ (ፖቾላ) ምልክት ሲሆን፣ ሁለተኛው የብርቻ ባህላዊ መሪ (ፖቾላ) ምልክት ያለው ነበር። የአርሶ አደር ባህላዊ መሪ ምልክት ያለው «ባደሞ» ሲባል አሁን ያለው ፋሻ ነው። የብርቻ መሪን የሚወክለው ደግሞ «አባ ኩሜ» ሲባል ያለው ሰውጌሜ ነው።

(መምሩ ቆራይንቱ መስከረም 17 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁርታ ሀያ

ስያሜ

የኹንሶ ህዝብም ሆነ መሬቱ «ካራታ» ቋንቋውም አፉ «ካራት» ይባል ነበር። «ኹንሶ» የተባለው የሰፈረበት ቦታ ለሰው ልጅ መኖሪያ ተስማሚ፣ ተራራማ፣ ደጋማና ነፋሻማ አየር ያለበት ቦታ ስለሆነ ቦታው «ኹንሲታ» ስለሚባል ከዚያው ማህበረሰቡም ኹንሶ፣ ቋንቋውም አፋ ኹንሶ መባል ጀመረ።

(ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት መስከረም 20 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁርታ ሀያ አንድ

የማህበረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥ (ሀ)

የኹንሶ ብሄረሰብ ከቦረና ዞን ሊበን ወረዳ እንደመጣ በአፈ ታሪክ ይነገራል። ብሄረሰቡ አሁን ወዳለበት ኹንሶ ወረዳ ሲመጣ በ 3 አቅጣጫ ነበር። አንደኛው ካራት አካባቢ የሰፈረው ነው። እነዚህ ሰፋሪ ህዝቦች አብሮ በመኖር ሂደት ውስጥ መጣላት እንዳይኖርና እርስ በርስ ተከባብረው እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያስችል «ቲምባ» የሚባል ከበሮ አላቸው ይህን ከበሮ የአካባቢው ማህበረሰብ እንደ ማስተዳደሪያ ስልጣን የሚቀጥረው ሲሆን ከበሮውም በየተራ የሚሽከረከር ነው። ሁለተኛው ወደ ፋሻ አካባቢ

ጊዶ የሰፈረው የኙንስ ህዝብ ነው። እነዚህም ህዝቦች ክበር ያላቸው ሲሆን መጠሪያው «ኪሁ» ነው። አገልግሎቱም ተመሳሳይ ነው። ማህበረሰቡ አሁን ወዳለበት የኙንሶ ወረዳ ሲመጣ ዘጠኝ ጎሳዎች ነበሩት። እያንዳንዱ ጎሳ የየራሱ ባህላዊ የጎሳ መሪዎች አሉት። እነዚህ የጎሳ መሪዎች በኙንስ ቋንቋ «ፖችላ» ይባላሉ። የጎሳ መሪው በቀኝ እጁ ላይ የሚያስረው «ቱማ» የሚባል ከንጹህ ብር የሚሰራ ጠፍጣፋ የእጅ አምባር አለው። ሌሎች ምክትል የጎሳ መሪዎች ደግሞ በግራ እጃቸው ላይ የሚያስሩት ከጥቁር ብረት የሚሰራ «መከላ» የሚባል የእጅ አምባር አላቸው። ከዘጠኙ ጎሳዎች ውስጥ አንዱ ጎሳ የሚያገባው ከቀሩት 8 ጎሳዎች ውስጥ እንጂ ከራሱ ጎሳ ጋር አይደለም።

(አቶ ኮራ ጋራ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቁርታ ሀያ ሁለት (ለ)

የኙንስ ብሄረሰብ ዘጠኝ ጎሳዎች ያሉት ሲሆን አብዛኛውን ህዝብ የመጣው ከምስራቅ በኩል ከቦረና ዞን ሊበን ወረዳ፣ ከቡርጂ፣ የካላ ጎሳ ደግሞ በአሌ በኩል ወደ ተልተሌ አልፎ በደቡብ አቅጣጫ አድርጎ ወደ ኙንስ ካራት ገባ። በመጀመሪያ የመጡት የጎሳ መሪዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ህዝቦች ከእነዚሁ ጎሳዎች ተቀልደው ሊበዙ ችለዋል።

(አቶ ኩሲያ በየን መስከረም 17 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቁርታ ሀያ ሶስት (ሐ)

ኙንሶዎች ኙንስ ምድር መጥተው ከመስፈራቸው በፊት በዚህ ቦታ ላይ የሚኖሩት «ኙደራ» የሚባሉ ሰዎች ነበሩ። በኋላ ኙንሶዎች ተዋግተው ቦታውን አስለቅቀው መኖር ጀመሩ። ኙንሶዎች ወደ ቦታው ሲመጡ ቦታው ደን የለበሰ ነበር።

(ሊ/ር ገዋዶ አደላዶ መስከረም 26 ቀን 2005 ዓ.ም.)

2. ትውፊታዊ አስተዳደርን በሚመለከት የሚተረኩ

ቁርታ ሀያ አራት

«ፖችላ» ቱማ

በድሮ ጊዜ የኙንስ «ፖችላ» ወንድ ልጆች ከ«ቱማ» ጋር ይወለዱ ነበር ይባላል። ከረጅም አመታት በፊት የኙንስ ብሄረሰብ «ፖችላ»ዎችን ጨምሮ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ባለመፈጸማቸው ምክንያት የባህላዊ መሪ ልጆች ያለ «ቱማ» ይወለዱ ጀመር።

ይህንን ምልክት ለመተካት ሲባል በኸንሶ ብሄረሰብ ዘንድ የእጅ አምባር ማድረግ አስፈላጊ እየሆነ መጣ።

(አቶ ጊሊዶ ባደና መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሀያ አምስት

የ«ፖቾላዎች» መንፈሳዊ ኃይል (ሀ)

የካላ ቤተሰብ ከዚሶ ተነስቶ ወደ ኸንሶ ሲገባ ጌራ አካባቢ ይሰፍራል። በዚያ አካባቢ ስሙን አላስታወሰውም አንድ ቤተሰብ ነበር። የካላ ቤተሰብ ሀይለኛ መንፈስ፣ ብዙ ከብቶችና ቤተቦች ነበሩት። ያ ቀድሞ የሰፈረው ቤተሰብ «እነዚህ ቤተሰቦች እዚህ አካባቢ ከሰፈሩ ወደ እኔ ወደ እነሱ መልቀቅ አለባቸው።» በማለት ዘዴ ይፈልጋል። ሌሊት አንካሴ በመያዝ የጋያ ትንባሆ እያፈሰሰ፣ መሬቱን በእንካሴ እየወጋና ብዙ ፌካዎችን በራሱና በካላው ቤተሰብ ቤት አካባቢ ሲሰራ ያድራል። በጠዋት ተነስቶም ካላን ይቀሰቅስና «እኛ ሳናውቀው ጠላት መጥቷል። መሰለኝ ይኸው ተመልከት ብዙ ኮቴ ይታያል።» ይለዋል። ካላም የእሱንና የሰውዬውን ቤት አካባቢ ሲመለከት እውነትም ብዙ የእግር ኮቴዎችን ያያል። በዚህን ጊዜ «ምን እናድርግ?» ብሎ ቢጠይቀው ሰውየው «አካባቢውን ለቀን መሄድ አለብን።» ብሎ ይመልስለታል። ካላውም «እውነትም ይህ ያልታወቀ ጠላት ሊያጠፋን ስለሚችል እንዳልከው መውጣት አለብን።» በማለት በሁለቱ ይስማማሙና ለመሄድ ይዘጋጃሉ። በኋላ ካላ ቀድሞ ወንዙን ሲሻገር ሰውዬው ግን ሳይሻገር ይቀራል። ካላ ዞር ብሎ «ተሻገር እንጂ! ቢለው በቃ! ይሆና ሁን፤ እኔ እዚሁ እቀራለሁ።» ይለዋል። ካላው «እታለኸኛልና መሬቱ አለት ይሁንብህ።» ብሎ ይረግመዋል። በዚህን ጊዜ መሬቱ እንዳለ ቀልጦ አካባቢው ድንጋያማ ሆኖ ቀረ። ቦታው አሁንም አለ።

(ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት መስከረም 20ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሀያ ስድስት

የካላ ታናሽ (ለ)

ኬና ከቬሌ በሚባል አካባቢ ካላ ከታናሽ ወንድሙ ጋር ሆኖ በሚሄዱበት ጊዜ የሆነች እርጊት ትሞትባቸዋለች አሉ። ታናሽየው በጣም ትንሽ በመሆኑ እርጊቷን ማንሳት አልቻለም። ታዲያ ወንድሙን «ምን እናደርጋለን? ሜዳ ላይ ጥለን እንሄዳለን? ትበራት።» ይለዋል። ታናሽየው «እኔማ ትንሽ ነኝ፤ አትሚ አይችልም።» ይለዋል።

ታላቅየው «ታዲያ ምን እናድርግ?» ሲለው «የአንተን ልብስ ልያዝልህ እና አንተ ቅበራት።» ይለዋል። ታላቅየውም «እሺ!» በማለት ቱማውንና የአወራረሱን ቀንድ ሊታናሽ ወንድሙ እንዲይዝለት ይሰጠዋል። ከዚያም አሮጊቷን ቀብሮ ይመጣና «እቃዬን ስጠኝ።» ይለዋል። ታናሽየውም «አንተማ የሞተ ርኩስ ነገር ነክተሃልና እንዴት ይህንን እቃ ትይዛለህ?» ይለዋል። ታላቅየውም «እሃ!» ይልና «እንግዲህ ካሌ ሆንህ ካሻሌን ይዘህ እዚህ ቅር።» ብሎ መርቆ የአውራረስ ቀንዱን ትቶለት ቱማውን ግን በዘዴ ተቀበለው። ካሌ ሆንህ ነው ያለው ካላ አላለውም ካሌ ማለት ታናሽ ማለት ነው። ስለዚህም ካሌ ባለቱማ ሳይሆን ባለሙሌጋ ነው። አሁን የሚኖረው ኙንሶ ቱበና ቀበሌ ነው።

(ካላ ገላዬን ወ/ላዊት ጥቅምት 02 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቀሮታ ሀያ ሰባት

የ«ፖ ችላዎች» መንፈሳዊ ኃይል (ሌ)

የኬሮቲታ ጉሳ ባህላዊ መሪ ከቦረና ወደ ኮንሶ ለመስፋፋት ሲመጡ በቀንዳም ላም ላይ ተቀምጠው ነበር። የጉሳው መሪ ላሚቱ ላይ ተቀምጠው ሲጓዙ ላሚቱ አመለኛ ነበረችና ትወጋ ስውፉውንም ትጥለዋለች። አሁንም ሲቀመጡባት ትወጋና ትጥለዋለች። በዚህ ሁኔታ ሶስት ጊዜ ይሞክራሉ። በመጨረሻም አልሳካ ሲል ቀንድ በሌላት ላም ሲቀመጡ ያለምንም ችግር ወደ ኮንሶ አደረሰቻቸው። ከዚያ በኋላ ባህላዊ መሪው ቀንድ የሌላትን ላም «እሁቴ ነች።» አሉ። ከዚያ በኋላ ቀንድ የሌላት ላም ስጋ «አልበላም!» ብለው እስካሁን ድረስ አይበሉም። የጉሳ መሪው ዱሮ ወደሚባል ቀበሌ ከመሄዳቸው በፊት ያረፉት ኙንሶ ካራት ጨና ማዚያ አካባቢ የቶክመሊታ ጎሳ መሪን ቤተሰብ ተጠግተው ነበር። አንድ ቀን የእነዚህ ጉሳ ቤተሰብ የሆነ ልጅ ከብት ሲጠብቅ ቆይቶ ጸጉሩን ሲላጭ ከወንዱ ወተት መፍሰስ ጀመረ። በዚህን ጊዜ አስጠጊው ቤተሰብ ይህ የተጠጋው ቤተሰብ የጉሳ መሪ መሆኑን አወቁ። ሁለት የጉሳ መሪ አንድ ላይ መኖር ስለማይችል የኬሮቲታው የጉሳ መሪ ወደ ዱሮ ቀበሌ ሄደ። አሁንም የኬሮቲታ መሪ ጋስሮቶ ሂክታ ሲባል የሚኖረውም ዱሮ ቀበሌ ነው።

(አቶ ጊዱና ባደና መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቶርታ ሀያ ስምንት

### የ«ፖቻላዎች» መንፈሳዊ ኃይል (መ)

ካላ ጥሩ ነገር እንጂ መጥፎ ነገር የሚያመጣ ድግምት አይወድም ነበር። አንድ ቀን ካላና ከተከታይ ልጁ ከሆነው ሆሌ ጋር ከቡሶ ወደ መሎሎ በሚሄዱበት ጊዜ ሰዎች ለመሻገር የሚሆነውን ውሀ በድንጋይ ስለከበቡት ከብቶችን ይዘው መሻገር አልቻሉም። ካላ መሻገር ፈልጎ በትሩን በውሀው ላይ በመጣል ውሀውን ለማቆም ቢሞክርም አልሆነለትም። በኋላ ለሆሌ በትሩን ይሰጥና «ውሀው ላይ ጣልበት።» ይለዋል። በዚህን ጊዜ ሆሌ በትሩን ውሃው ላይ ሲጥልበት ውሀው ለሁለት ይከፈላል። ይሻገሩና ካላ ሆሌን «አሁን ደግሞ በትሩን በተከፈለው ውሀ ላይ ጣለው።» ይለዋል። ሆሌም በትሩን ሲጥል ውሀው በቦታው ይመለሳል። በዚህን ጊዜ ካላ ሆሌን የሰራው ጥሩ ነገር በመሆኑ «ሆሌ ሆነህ ይህን ውሀ ገድበህ እየተጠቀምክ የፖሳንታ ጎሳ አባል ሆነህ ኑር።» ብሎ መረቀው።

(ካላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት መስከረም 20ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቶርታ ሀያ ዘጠኝ

### የ«ፖቻላ» ቀብር መጀመር

በኾንሶ ማህበረሰብ ባህላዊ መሪ «ፖቻላ» ሲሞት አይቀበርም ነበር። ባህላዊ መሪው ሲሞት አስከሬኑ ድንጋይ ላይ ይቀመጥና ደመና መጥቶ ይወስደዋል። ይህ የቀረው በሁለተኛ ሚስት ምክንያት ነው። ባህላዊ መሪው ህዝቡን በጥሩ መንፈስ እንዲያስተዳድር ማታ ማታ መላእክት መጥተው ያነጋግሩት ነበር። ይህ የሚሆነው ብቻውን ሲሆን ብቻ ስለሆነ ሚስቱ መኝታ ክፍሉ አትገባም ነበር። እንደተለመደው አንድ ቀን ባህላዊ መሪው ከመልአኩ ጋር ሲነጋገር ድምጽ ሲያሰማ ሚስት ከሁለተኛዋ ሚስት ጋር የሚነጋገርና ባህላዊ መሪው ያታለላት ይመስላትና ገረዷን ከማን ጋር እንደሚነጋገር እንድትነግራት ገቡቱ ውስጥ ትደብቃታለች።

እንደተለመደው ባህላዊ መሪውን መልአክ ሊያነጋግረው ሲመጣ መልአኩ አንድ ባእድ ነገር እንዳለ ለባህላዊ መሪው ይነግረዋል። መሪው ግን ምንም ስለማያውቅ ምንም ነገር እንደሌለ ይመልስለታል። መልአኩም «ከእንግዲህ ወዲህ በአካል መጥቼ አላነጋግርህም፤ የሚገለጽልህ ነገር በሙሉ በህልም ይሆናል። አንተን ግን መሬት ይጨምርሃል» አለው። «ለዚህም ምልክት ከዚህ ገቡቱ ስር ነገ ሬሳ እንሳ።» ብሎት ጥሎት ሄደ። ጠዋት ገረዷ ስትፈለግ ትጠፋለች። በኋላ ንጉሱ ትዝ ሲለው ገቡቱው እንዲከፈት ሲያደርግ ሞታ ተገኘች።

ከዚያ በኋላ ባህላዊ መሪው ሲሞት እንደተለመደው እሬሳውን ድንጋይ ላይ አስቀመጡ። ከሶስት ቀን በኋላ ትንሽ ዳመና የሚመስል ነገር መጥቶ አካባቢውን ጋረደውና ሬሳው ተሰወረ። ከ9 ቀን በኋላ እረኞች በሬ ደም ሲያይ የሚጨኸውን አይነት ድምጽ ሰምተው ወደ ቦታው ሲሄዱ የባህላዊ መሪውን ጣት ከንቀለበቱ አገኙ። ይህንን ለአካባቢው ሽማግሌዎች ወስደው ሰጡ። ከዚያ በኋላ ባህላዊ መሪው መቀበር ጀመረ።

(ካላ ገብሬን ወ/ዳዊት መስከረም 20 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሰላሳ

የ«ፖኞላዎች» የግዛት ጥያቄ (ሀ)

ካላና ቲቲባ የሚባሉ ባህላዊ የጎሳ መሪዎች በኙንሶ ይኖሩ ነበር። በኋላ ካላና ቲቲባ መሬቱ «የኔ ነው» «የኔ ነው» በማለት እርስ በርስ መከራከር ይጀምራሉ። በዚህን ጊዜ ሽማግሌዎች ይሰበሰቡና «እስቲ ሀይልን ሳትጠቀሙ በጥበብ መሬቷ የማን እንደሆነች አሳዩን» በማለት ይወስኑና ሶስት ሳምንት የጊዜ ገደብ ይሰጣሉ።

በዚህን ጊዜ ካላ አንድ በጣም ያረጀ አሮጊት መሬት ውስጥ ያስቀብርና በላዩ ላይ (እንቦቅ) የቅርጫት ክዳን አድርገው አፈር ያለብሱና ያስቀምጣሉ። ካላ ቲቲባን «በል ይቺን መሬት እንጠራልን፤ አቤት ያለችው የሱ መሬት ይሆናል፤ አቤት ያላለችው ደግሞ መሬቱ የሱ አይደለም፤ ማለት ነው።» ይለዋል። በኋላ ካላ ቲቲባን «አንተ በቅድሚያ መሬትን ጥራት!» አለው። ቲቲባም «ቲቲባያ! ቲቲባያ! ቲቲባያ!» ብሎ ቢጣራም መልስ የለም። ካላ በተራው ደግሞ «ካላይቲያ! ካላይቲያ! ካላይቲያ!» ሲል ከስር ያለችው አሮጊት አቤት አለች።

ካላ በስራው ጥበብ አሸንፎ መሬት የሱ ሆነች። ቲቲባ ደግሞ ስለተሸነፈ ወደ ዲራሼ ሄዶ ሰፈረ።

(ካላ ገብሬን ወ/ዳዊት መስከረም 20 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሰላሳ አንድ

የ«ፖኞላዎች» የግዛት ጥያቄ (ለ)

የካላ ጎሳ ወደ ኙንሶ ሲመጣ በየቦታው እያረፈ ኙንሶ ካራት አካባቢ ኩተሌ በሚባል ስፍራ ተቀምጦ እያለ ካላ በአካባቢው በ(ፖኞላንት) የተቀመጠውን ቲቲባን ሄዶ «እባክህ እኔ እንግዳ ስለሆንኩ እንወዳጅ።» ብሎ ይጠይቀዋል። ቲቲባም ይቀበለውና አብረው ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ ካላ ዘዴ ይፈልግና «አንተ ትልቅ መሪ ነህ እኛ እዚህ ስንተኛ ጠላት

መጥቶ አንድ ነገር ቢያደርገንስ? ስለዚህ አንድ ነገር ማድረግ አለብን።» ይለዋል። ቲቲባም «እሺ!» ይላል። ካላ «በአንተ ቤት ዙሪያ መሬቱ ላይ አመድ ነስንሰን እንደርና ሌሊት ጠላት መጥቶ የሚሰልለን ከሆነ እናውቃለን።» አለው። ከዚያም ካላ የተነሰነሰውን አመድ ሌሊት የሚረግጡ ሰዎች አዘጋጀ። ጠዋት ሲፈተሽ አመድ የተነሰነሰበት መሬት በእግር ተረግጧል። ካላም «ይኸው አላልኩህም እንዴ? ጠላት እየፈተሸን ነው።» አለው። ቲቲባም «እውነትም ይህ ሰውዬ አዋቂ ነው፤ በቃ አኖረዋለሁ።» ይላል። ቆይቶ ካላ «መሬቱ የኔ ነው።» ይላል። ቲቲባም «እኔ በእንግድነት ስቀበልህ እንዴት መሬት የኔ ነው ለማለት ቻልህ?» በማለት ሲከራከሩ ካላ «መሬቷ ራሷ ትመስክር!» ብሎ ቃል አስገባው። ቲቲባም «ትመስክር፤ መሬቱ የኔ ነው፤ እንጂ ያንተ አይደለም።» ይላል። ካላ «እንግዲህ ነገ ሄደን መሬት ትናገራለች።» ይላል። ቲቲባም «አትናገርም፤ ከተናገረችም ጥሩ ነው።» ብለው ይወጣሉ።

ካላ ሄዶ ጉድጓድ ቆፍሮ ውስጡ ሰው አኖረ። ከዚያ በኋላም ካላ ቲቲባን «በል ራስህ መሬትን ጠይቅ።» ይለዋል። ቲቲባም «ቲቲባያ!» «ቲቲባያ!» «ቲቲባያ!» እያለ ሲጠራ «አቤት!» አላለችም። «ይኸው ያንተ መሬት አይደለችም፤ መልስ አልሰጠችም፤ በል አሁን ደግሞ እኔ ልናገር።» ይላል። ቲቲባም «ተናገር መቼ መሬት ትናገራለች?» ይላል። ከዚያ ካላ «ካላይዲያ» «ካላይዲያ» «ካላይዲያ» ሲል «እ!» በማለት መሬት ድምጽ አሰማች። ካላ «መሬቱ የራሴ ነው። አላልኩህም?» ሲል እንግዲህ «መሬት ያለመሰከረለት መሬቱን ይለቃል።» ስለተባባሉ ቲቲባ መሬቱን ለመልቀቅ ግድ ስለሆነበት ወደ ዲራሼ ሄዶ ሰፈረ። እዚያ ሄዶ ቲቲባ የዴራሼ ጎሳ መሪ ሆነ።

(አቶ ካራ ኩራ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ተረት ሰላሳ ሁለት

የ«ፖቾላዎች» የስልጣን ፍትጊያ (ሀ)

ካላ የመሪነት አምባር (ቀማ) አልነበረውም ነበር። ባህላዊ መሪ ለመሆን ቴማ የግድ ማግኘት ነበረበትና አንድ ጊዜ ወደ ቡሶ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ይሄዳል። እዚያ አንድ የቡሶ የጎሳ መሪ ያገኛል። ያ የጎሳ መሪ ቱርመሌ ነው የሚባለው። ቱርመሌን አግኝቶ «ገበጣ እንጫወት።» ብሎ አብሮ ይጫወታል። እነሱ ገበጣ ሲጫወቱ፤ ሲጫወቱ በአጋጣሚ የቡሶ ሰዎችና የአባርባ የቦርመሌ ሰዎች ይዋጉ ነበርና ለቱርመሌ ።«አንተ ቱርመሌ ዝም ብለህ እኮ ከእኔ ጋ ገበጣ ትጫወታለህ። ህዝብህ ከሌላ ጋር እየተዋጋ ነው፤ በመርጌቱ ይልቅ እየለቅ ሳታውቅ ዝም ብለህ ትጫወታለህ እንዴ? ሄደህ ብታይና

ውኔታውን ብትረዳ ጥሩ ነው።» ይለዋል። እናም «ስትሄድ አንተ የህዝብ (ጐችላ) መሪ ነህ። እና አንተን እያዩ ሲገድሉ ለህብረተሰቡ ጉዳት ነው። ስለዚህ ያንተን ቱማ እዚህ እኔ ጋ አስቀምጥ ሊጠብቀው። አንተ ሂድና ህዝብህን አይተህ ና።» ይለዋል። እውነትም ቱርመሌ «እሺ» አለው። ቱማውን እሱ ጋ አስቀመጠ ጠሩን ይዞ ሄደ። ህዝቡ እያሸነፈ ስለነበር እሱም ንብቶብት የተወሰነ ሰው ገድሎ መጣ። ከዚያም ለካላ «የእኔ ህዝብ እያሸነፈ ነው፤ እኔም ብዙን አንድ ሁለት ሰው ገድያለሁ።» ይለዋል። «እ!!! አንተ ትልቅ ንጉስ ሰውን ከገደልክ ደም አፍስሰህል፤ ተበክለሀል። ስለዚህ ወደፊት ጥቂር ፍየሎች ታርደው የእርቅ ስነ ስርአት ተደርጎ እስክትታጠብ ድረስ ይህን ቱማ ማድረግ አትችልም፤ ስለዚህ እኔ በእጄ ላይ አድርጌ ስነስርአቱ ሲደረግ እሰጥሀለሁ።» ይለዋል። ካላ ቱማውን በዚህ አይነት መንገድ አገኘ።

(አቶ ኮራ ካሉ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሰላሳ ሶስት

የ«ፖችላዎች» የስልጣን ፍትጊያ (ለ)

ዳህሾና ካልማሌ የሚባሉ የቶክመሌታ የአንድ ጎሳ አባላት ነበሩ። ዳህሾ ቱማ ነበረው። ካልማሌ ግን ቱማ አልነበረውም። ሁለቱም ለመታጠብ ወንዝ ሲሄዱ ካልማሌ ዳህሾን «ቱማህን አስቀምጥና እንታጠብ።» ይለዋል። ዳህሾ ያወልቅና ይታጠባል። ከዚያም ካልማሌ ቀደም ብሎ ከውሃው ይወጣና ቱናማውን ይወስድና አጥልቆ ወደ ጃርሶ ቀበሌ ይሄዳል። ካልማሌ ጃርሶ ሲደርስ ኸርቶ የሚባል የኬርቲታ የጎሳ መሪ ቤት ይገባል። በዚህን ጊዜ ኸርቶ ቱማ ስለነበረው እና ሁለት የጎሳ መሪ በአንድ ቦታ ላይ መኖር ስለማይችሉ ወደ ጸራ ቀበሌ ሄዶ የጎሳ መሪ ሆኖ በዚያ መኖር ጀመር። ካልማሌም በጃርሶ መኖር ጀመረ።

(አቶ ጊዲና ባደና መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሰላሳ አራት

ቲምባ

ከብዙ አመታት በፊት የኾንሶ መኖሪያ ቤቶች ተበታትነው ይሰሩ ነበር። በኋላ ህዝቦች ተሰብስበውና «አንድ ላይ ተሰባስበን ብንኖር ጥሩ ነው።» ተባባሉ። ከዚያም ዛፍ ቆረጡና ቲምባ (ከበሮ) ሰርተው እንዲህ ተባባሉ «የከበሮው ባለቤት (አባ ቲምባ) የማስተዳደር ስልጣን አለው፤ ጥሞት የፈጠረ ቀበሌም ሆነ ግለሰብ ለአባ ቲምባው ግብር ይከፍላል።»

በማለት ከበርውንም ለክ እንደሰው የሚሰማና የሚናገር እንደሆነ ህዝቡ ተስማምቶ ነበር ይባላል።

በዚህ ሁኔታ ጉዳት ሲፈጠር ሁሉም ወደ ከበሮው ዘንድ ሄዶ ሀሳቡን በክርክር ይገልጽ ነበር። በአንድ ወቅት አንድ ሰው ጉዳት ፈጠረና አባ ቲምባው «ይህ ሰው ለከተማው ቅጣት ይከፈል አለ።» የአካባቢው ሰዎች ቅጣቱን እንዲከፍል ጠየቁት። ይሁን እንጂ ሰውዬው ቅጣቱን ሳይከፍል ተቃወመ። በዚህን ጊዜ ኹንሶዎች ይህንን ሰው ለማባረር ወሰኑ። ስለዚህም ሁሉም «እሳት አናስጭርህም፤ ውሀ አናስቀዳህም፤ ከአንተ ጋርም አብረን አንሰራም።» በማለት ሁሉም አገለሉት። ከዚያ በኋላ ሰውዬው ከተማውን ለቆ በመሄድ ከሌሎች ህዝቦች ጋር አብሮ መኖር ጀመረ።

ቁርጥ ሰላሳ አምስት

(አቶ ቱሉ ካምባር መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ባህላዊ አስተዳደር (ሀ)

የኾንሶ ህዝብ ከሚኒሊክ II መንግስት በፊት በማዕከላዊ መንግስት ዘንድ እምብዛም የማይታወቅ ህዝብ አልነበረም። የሚመራውም «ቲምባ» በሚባል ከበሮ ውክልና ነበር። ይህ «ቲምባ» በእያንዳንዱ ቀበሌ ውስጥ ያለና እንደ ማስተዳደሪያ ደንብ ሆኖ የሚያገለግል መሳሪያ ነው። ህዝቡም ለዚህ ቲምባ የሚታዘዝና ግብርም የሚከፍል ነበር። ከሚኒሊክ መንግስት በኋላ ግን በየቀበሌው ኃላፊዎችን በማስቀመጥ ማስገበር እንደተጀመረ ይነገራል፤ ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ቲምባው እንደዱሮው ባይሰራም አባ ቲምባዎቹ ግን በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና የሚከበሩ ናቸው።

(ዶ/ር ገዋለ አይላሌ መስከረም 26 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቁርጥ ሰላሳ ስድስት

ባህላዊ አስተዳደር (ለ)

ከዚህ በፊት በኾንሶ አካባቢ ሥርዓቶች እንደሌሉ ይወራ ነበረ። ሚኒሊክ ለማዕከላዊ መንግስት ለማስገበር ሲሉ ካደረጉትና ከጣሊያን ወረራ በኋላ ግን ህዝቡ ሾሮኪታ የሚባሉ ሰዎችን አዘጋጀ። እነዚህ ሰዎች በየዘጠኝ ዓመት የሚመረጡና ሁሉንም ጎሳ በእኩልነት የሚያስተዳድሩ ናቸው። ለዚህ ስርአት «እምቢ!» የሚል ሰው ሲገኝ እነዚሁ ሰዎች ህዝቡን በሞራ ላይ ሰብስበው አጥፊው ጥፋቱን አምኖ እንዲቀጣ፣ «አላምንም!»

ካለ ደግሞ እንዲያምል ያደርጉ ነበር። ከዚያ በኋላ በኮንሶ ዘመናዊ መንግስት ሲስፋፋ ጥፋተኛ የሆነ ሰው ሲኖር ጉዳዩ በህግ እየታየ መጣ።

(አቶ መምሩ ካይፌንቶ መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቶርታ ሰላሳ ሰባት

ላውራ

በፊት ጊዜ ኮንሶ ውስጥ ሁለት ቀበሌዎች ከፍተኛ ውጊያ ሲያደረጉ ሳራና የቲምባ ባለቤቶች መርጉቱ እንዲቆም ሰዎች መለምለው ነበር። ነገር ግን በሁለቱ ተዋጊ ወገኖች ሰላም እንዲሰፍን ማስገደድ አልተቻለም። በኋላ ሊሂታ ከምትባል ትንሽ መንደር «ናማ ላውራ» የሚባሉ አስታራቂዎች በሁለቱ ተዋጊ ወገኖች በኩል ማዕተብ በመጣል በረቀቀ ዘዴ መርገቱ እንዲቆም በማደረጋቸው ሁለቱ ተዋጊ ወገኖች በሰላምና በክብር ከጦርነት እንዲወጡ አደረጉ።

(አቶ ቶሬ ካምባር መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.)

የአነ፡ ሽማግሌዎች

### ቶርታ ሰላሳ ስምንት

ክፉዋ ንግስትና ብልሁ ሽማግሌ

በፊት ጊዜ አንዲት ሴት በኮንሶ ምድር ላይ ነግሳ ነበር። ይህቺ ንግስት ባሎችን የመግደል ስልጣን ተሰጥቷት ስለነበር በአገሪቱ ላይ ያሉትን ባሎች ባጠቃላይ ማጥፋት ጀመረች። አንድ ልጅ ይህንን ሰምቶ ኖሮ ወደ አባቱ በመሄድ ንግሲቲቱ ባሎችን በመትላላ እየገደለች መሆኑን ነገረው። አባትየውም እርሱ ከደበቀው እንደሚተርፍ አስረዳው። ልጁም አባቱን ደብቆ ከሞት አዳነው።

በአንድ ወቅት ንግስቲቱ በከር ጨርቅ ሰርተው ተራራውን እንዲያለብሱ የአገሩን ልጆች አዘዘቻቸው። ልጁም ተደብቆ ወደነበረው አባቱ በመሄድ የታዘዙትን ነገረው። አባትየውም «ተራራው ላይ ሄዳ ነው? ወይስ ከቤት ሆና ነው የምትመከተው?» ሲል ጠየቀው። ልጁም ከቤት ሆና እንደምትመለከት መለሰለት። አባትም «ተራራውን በሙሉ አቃጥልና ለነጋ ሲል አጥፋው።» ሲል መከረው። ልጁም እንደመከረው አደረገ። በማግስቱ ንግስቲቱ ከቤት ሆና ተራራውን ስትመለከት የተቃጠለውን ቁጥቋጦ ተመልክታ ጥቁር ጨርቅ ስለመሰላት ልጁን አመሰገነች። በሁለተኛው ቀን በሁለት ጎኑ ፀጉር ባለው ቆዳ የተሰራ ጫማ እንዲያመጡ አዘዘቻቸው። ልጁም ሄዶ የታዘዙትን

ለአባቱ ነገረው። አባትየውም «ሁለቱን የአህያ ጆሮ ቆርጠህ ይዘህላት ሂድ።» አለው። ልጁም አባቱ እንዳለው በማድረጉ ተመሰገነ። በሌላ ቀን ደግሞ ንግስቲቱ «ቁንጫ በማሳበሪያ ሞልታችሁ አምጡልኝ።» ስትል አዘዘቻቸው። ልጁም ወደ አባቱ ሄዶ ምክር ጠየቀ። አባትም «የፍየል ፍግ በማሳበሪያ ሞልተህ አስቀምጥ። ቁንጫም ቀስ በቀስ እየገባ ይሞላዋል።» አለው። ልጁም በማሳበሪያ ቁንጫውን ሞልቶ ወደ ንግስቲቱ ሄደ። እርሷም «ጥሩ ነው!» ብላ ካመሰገነችው በኋላ ቀጣይ ትዕዛዟን ገለጸች። ትዕዛዟም «ጎጆ ቤት ትሰራላችሁ፤ ቤቱ ግን ምሰሶውን ጨምሮ ሙሉ በሙሉ የሳር መሆን አለበት።» የሚል ነበር።

የአገሩ ልጆች በሙሉ በትዕዛዙ ክብደት ይጨነቁ ነበርና ልጁ ወደ አባቱ ሄዶ መፍትሄ እንዲጠይቅላቸው ጠየቁት። ልጁም ለአባቱ ትዕዛዙን ሲነግረው «ዛሬ የንግስቲቱ ሞት ይሆናል።» በማለት እንዲህ ሲል መከራቸው። «አንድ በቅሎ መርጣችሁ በደንብ ከገረፋችሁት በኋላ ለንግስቲቱ ስጧት። እሷም በቅሎዋን በምትጋልብበት ጊዜም ትግሬውን ይዛችሁ ከበቅሎዋ ፊት ቁሙ።» አላቸው። ልጆቹም እንደተባሉት ሲያደርጉ በቅሎዋ አለንጋውን ስታይ ፈርታ እየተደናበረች ንግስቲቱን ይዛ ገደል ገባች። በዚህን ጊዜ ንግስቲቱ «ባሎችን ገድዬና ህዝቤን አስጨንቄ በራሴ ላይ ሰበብ አመጣሁ። ከእንግዲህ እኛ ሴቶች ለወንዶች እንገዛ።» አለች ይባላል።

(አቶ ጊሊሳ ባደሳ፣ መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሰላሳ ዘጠኝ

ብልሁ ሽማግሌ

በድሮ ጊዜ አንድ ብልጥ ሽማግሌ ነበር። ይህ ሽማግሌ አንዲት የደሀ ልጅ ከልጁ ጋር ሊያጋባት ስለፈለገ ብልጥ መሆኗን ለማረጋገጥ ወደ ቤቷ ሊያድር እንደሚፈልግ ነገራት። ልጅቱም ትንሽ የበግ ቆርበት አነጠፈችለት። ሽማግሌውም «ይኼ አያበቃኝም!» አለ። በስራዋ የተበሳጨ በመምሰል። ልጅቷ ግን እርጋታ በተሞላበት አነጋገር «መጀመሪያ ይህንን ጨርስና ሌላ ይጨመርልሀል።» አለችው። ሽማግሌውም በመልሷ በአርቆ አሳቢነቷ እየተደነቀ በጠዋት ተነስቶ ወደ ቤቱ በመሄድ ልጆቹን «በአህያ ላይ ጤፍ ጭናችሁ ልጅቷ ቤት በመሄድ ጤፉን ቆጥረሽ ስንት እንደሆነ ንገሪኝ በሏት።» ሲል አዘዛቸው። ልጆቹም ሄደው የታዘዙትን ነገሯት። ልጅቱም ጤፉን በእጇ ከነካች በኋላ መልሳ ወደ አህያው በማስጫን «አባታችሁን ሂዱና የአህያዋን ፀጉር ቆጥረህ የጤፉን ብዛት ማወቅ ትችላለህ፤ ምክንያቱም የጤፉና የአህያዋ ፀጉር ብዛት

አንድ ነውና።» ብሌት በማለት ለጆቹን መልሳ ላከቻቸው። ሽማግሌውም በሰማው መልስ ስለረካና ብልጥ መሆኗን ስለተረዳ ለመጀመሪያ ልጁ ሊድራት ወሰነ።

ሰርጉ ተዘጋጅቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊፈትሻት በማሰብ ወደ ቤተሰቦቿ ሄዶ «የእናንተ ልጅ ዛሬ አርግዛ፣ ዛሬ ወልዳ፣ ህጻኑ ዛሬውኑ ከብት የሚጠብቅ ከሆነ ልጃችሁን ልጃችን ያገቢታል።» አላቸው። ቤተሰቦቿ በቀረበው ሀሳብ ላይ በመጨነቅ ላይ እንዳሉ ወሬው ከልጅቷ ጆሮ ደረሰ። ምንም ችግር እንደማይኖር ለቤተሰቦቿ አስረዳች። ልጅቱም የተጠሩ እንግዶች ቦታ ቦታቸውን ሲይዙ ጠብቃ በደንቡ መሰረት ለሰርጉ የተዘጋጀውን እህል ከሁሉ ቀድማ እንድትቀምስ ስትጠየቅ አለማመነታት እንቢታዋን ገለፀች። ሽማግሌውም የልጁ ሰርግ እንዳይበላሽ ስላልፈለገ ተጨንቆ የማትቀምስበትን ምክንያት ቢጠይቃት «እኔ የምቀምሰው እህል ዛሬ ተዘርቶ፣ ዛሬውን ተቆርጦ፣ ዛሬውን ተለቅሞ፣ ዛሬውኑ ተፈጭቶና ዛሬውኑ ከበሰለ ነው።» ስትል መለሰችለት። ሽማግሌውም «የት አገር ነው እንዲህ የሚደረገው?» ሲል ጠየቃት። ልጅቱም ፈገግ ብላ «እንግዲያውስ የት አገር ነው ሴት ልጅ ይህንን ሁሉ ነገር በአንድ ቀን የምታደርሰው?» አለችው ይባላል።

(ከሊያ በየነ መስከረም 18 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### 3. የኾንሶ እርከንና እደ ጥበብ

ቀርታ አርባ

ኾንሶና የእርከን ስራ

ኾንሶዎች ወደ ኾንሶ ምድር ሲመጡ በየደረሱበት ቦታ እርከን እየሰሩ ነበር። ኾንሶዎች በመጡበት በስተምስራቅ ከሊበንና ሌሎች በመጡባቸው ቦታዎች ሁሉ በበሬ እየታረሰ እርከኑ እየጠፋ ቢሆንም የእርከን ፈለጎች ግን አሁንም አሉ። ስለዚህም ኾንሶዎች እርከን የመስራት ጥበቡን ቀድመው ይዘው የመጡ ናቸው። ኾንሶዎች «መሬት እናታችን ሆና ምግብ ትሰጠናለች፤ ስንሞትም እንቀበርባታለን፤ ስለዚህ በአግባቡ መያዝ አለብን።» የሚል ጠንካራ እምነት ስላላቸው ነው። መሬት እንዳይጎዳ እርከን የሚሰሩት።

(አቶ ኩራ ኳሪ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### 4. ኾንሶዎችና ምንጮቻቸውን በሚመለከት የሚተረኩ

ቀርታ አርባ አንድ

የሂምፓራ ምንጭ አፈጣጠር (ሀ)

ከብዙ አመታት በፊት የማያታ ቤተሰብ ትጥር ግቢ አሁን የሂምባራ ምንጭ ያለበት ነው። በአንድ ወቅት በድንገት በማያታ ትጥር ግቢ ኤላ የሚባል በጣም የደለበ በግ ቤሔኙት በየቀኑ ግቢውን ይበጠብጥ ነበር። የማያታ ቤተሰብም በበጉ ድርጊት ፍርሃት ስላደረባቸው በአካባቢያቸው ወደሚገኘው ጠንቋይ ዘንድ በመሄድ ስለበጉ ሁኔታ ነገሩት። ጠንቋዩም በጉን አርደው ምንም ነገር ሳያስቀሩ እንዲበሉ ምክር የሰጣቸው ሲሆን ምንም አይነት የበጉ ሲጋም ሆነ አጥንት መሬት ላይ መውደቅ እንደሌለበት አስጠንቀቃቸው። በዚህ መሰረት የማያታ ቤተሰብ በጉን አርደው በሉ።

ከጥቂት ቀን በኋላ አንዲት ሴት ከቤት ውጭ እርሻ ላይ ለተሰማሩ የቤተሰቡ አባላት በኡንሶ ብሄረሰብ ባህል መሰረት ምሳ ስታዘጋጅ በምታዘጋጀው ምግብ ላይ ስብ (ቅባት) ለትቀባቅል ስትል ስቡ ከእጇ ላይ አምልጦ መሬት ላይ ወደቀ። በዚህን ጊዜ ጠንቋዩ የመከረት ምክር ትዝ አላትና ስጋት አድሮባት ከመሬት ላይ በእጇ ለመጥረግ ስትሞክር ስቡ ከመሬት ላይ ከመነሳት ይልቅ በመሬት ላይ ሆኖ መጠኑ እየጨመረ፣ እየጨመረ መጣ። ሴትየዋ ስቡን ባገኘችው ነገር ሁሉ በመጠቀም ደጋግማ ከመሬት ላይ ለማስወገድ ሞከረች። ነገር ግን ስቡ ይበልጥ እየሰፋና እያደገ ሄዶ ወደ ውሀነት በመቀየር የማያታ ቤተሰብ ትጥር ግቢና ንብረትን በመጥለቅለቅ ዛሬ በአካባቢው የሚገኘውን የሂምፓራን ኩሬን እንደፈጠረ በአፈ ታሪክ ይነገራል።

(አቶ መሙሬ ካይራንቶ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቁርታ እርባ ሁለት

(ለ)

አንድ አይኑ የታወረና በእግሮቹ ላይ በወጣ አስቸጋሪ ቁስል ይሰቃይ የነበረ ሰው ለጃገረድ አጥብቆ ይኖር ነበር። በአካባቢያቸው የቤተሰብ ንብረት አስተዳደር መሰረት ሚስት የእርሻ ስራውን የምታከናውን ሲሆን ባለየው በህመም ምክንያት ቤት ይውል ነበር። ዘውትር ሚስት እርሻ ወላ ወደቤት በምትመለስበት ጊዜ ባልዋን «ቁስልህ የበለጠ እየቆሰለ ነው። ይህንንም የምታደርገው እራስህ ቁስልህን በእጅህ በማቁሰልህ ነው። ስለዚህ እኔም ቁስልህን የበለጠ ባቆስለው የሰውነትህ ስጋ የበለጠ ይለሰልስ ነበር።» በማለት ጠዋት ማታ ትጨቀጭቀው ስለነበር እሱም በሚስቱ ጸባይ ተናደደና አንገቷን በሰላ ቢላዋ በጥሶ ገደላት። አንገቷም መሬት ላይ ከተንከባለለ በኋላ ከአካባቢው ተሰወረ።

ይህ በደም የተጨማለቀ ድርጊት በአካባቢው ማህበረሰቡ ዘንድ ፍርሀት ፈጠረ። በአካባቢው ያለ ማንኛውም ሰው አንድ ቃል በተናገረ ቁጥር ያ ቃል እንደገደል ማሚቱ ያስተጋባ ነበር። ይህ ያልተለመደ ሁኔታ በማህበረሰቡ ዘንድ ፍርሀት በመፍጠሩ ምክር ለማግኘት ወደ ጠንቋይ ዘንድ ሄዱ። ጠንቋዩም ለአካባቢው ማህበረሰብ «በጋራ ሆናችሁ ድርጊቱ የሚፈጸምበት ቦታ ሂዱና አካባቢውን ቃኙI አንድ ቀይ ቆዳ ያላት ሴት ፍየል ታገኛላችሁ። ፍየሏንም ወደ ቤታችሁ ወስዳችሁ እሰሯት በዚህን ጊዜ የሚያስተጋባው ድምጽ ከአካባቢው ይጠፋል።» ብሎ ምክሩን ለገሳቸው። የአካባቢውም ማህበረሰብ ጠንቋዩ የሰጣቸውን ትዕዛዝ በመፈጸም ፍየሏን ካገኙ በኋላ ለሂንባራያ ቤተሰበ አስረከቢት።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአካባቢው የሚገኙ ወጣቶች በሙሉ ለረጅም ጊዜ በህይወት ሳይቆዩ መሞት ጀመሩ። የሂንባራያ ቤተሰብም ተጨማሪ ምክር ለማግኘት ቀደም ሲል ምክር ወደሰጣቸው ጠንቋይ ዘንድ ሄዱ። ጠንቋዩም ፍየሏን አርደው እንዲበሉ በማዘዝ ምንም ጎደኑት ሲጋም ሆነ አጥንት በመሬት ላይ እንዳይወድቅ አስጠነቀቃቸው። ሆኖም ከሂንባራያ ቤተሰብ መካከል አንዲት አሮጊት የፍየሏን ስጋ በምትመገብበት ጊዜ ትንሽ ስጋ ጥርሷ ውስጥ በመሰንቀሩ ስትተፋው ስጋው መሬት ላይ ወደቀ። ይህም ስጋ ወዲያውን እራሱን ወደ ውሀነት በመቀየር ቀስ በቀስ ወደ ትልቅ ሀይቅነት ተቀይሮ የሂንባራያ ቤተሰብ ቅጥር ግቢና የአካባቢውን ማህበረሰብ እና እንሰሳትን አጠፋ።

(አቶ ኮሬ ካሬ ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቁርታ አርባ ሶስት

የሾነሶ ምንጭ ወደ ደምንትና ትልንት መቀየር

በውሀ አካባቢ ያሉ መናፍስት ይከበራሉ። ሰዎች ደግሞ ህጉን ካላከበሩ ደግሞ ይቀጣሉ። እነዚህ መናፍስት ከፕላስቲክ የሚሰሩ ጫማዎችና እቃዎች ወደ ውሀው አካባቢ መጣልን፣ ከብረት የሚሰሩ እንስራዎችን፣ የወር አበባ ላይ ሆነው ውሀ የሚቀዱ ሴቶችን ይጠላሉ። እርምጃም ስለሚወስዱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በሶርቦ ቀበሌ ገበሬ ማህበር በደባናና ሰገሌ መካከል ያለ ሸነሶ የሚባል ቆንጆ የውሀ ምንጭ አለI ነገር ግን እነዚህ ደንቦች ደንቦቹ በሚጣሱበት ጊዜ በተደጋጋሚ ወደ ደምንትና ትል በትል ወደመሆንነት ተቀይሯል። እሁንም ደንቦቹ ሳይከበሩ ከቀሩ ወደ ደምንት ይለወጣል። ውሀውም ትል በትል ይሆናል። ውሀው ወደነበረበት ቦታ የሚመለሰው ፍየል ታርዶ ልመና ተደርጎ ነው።

(አቶ መምሩ ካይሬንቶ መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁርታ አርባ አራት

የኩቶ ምንጭ መድረቅ

በአሁኑ ጊዜ የኩቶ ምንጭ አገልግሎት አይሰጥም። ለዚህም ምክንያቱ ከሸክላ የተሰራ አዲስ እንስራ በመወርወር የምንጩን መንፈስ ቦታውን እዲለቅ ስላደረጉትና በምንጩ አካባቢ የሚገኙ የወንድ ሀጻናት አባቶች ተገርዘው በመወለዳቸው ምክንያት እንደሆነ በአፈ ታሪክ ይነገራል።

(አቶ ኮራ ካራ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁርታ አርባ አምስት

ካይታዖ ምንጭ ለምን ደረቀ?

ካይታዖ ምንጭ ረጅም ዘመንን ያስቆጠረ ቢሆንም አሁን አገልግሎት የሚሰጥ ምንጭ አይደለም። አንዲት አሮጊት እንስራ በመወርወሯ ምክንያት መናፍስቶቹ በድርጊቷ ስመቅጣት ባደረሱባት ብቶላ ከቤቷ እንድትወጣ አድርገዋታል። ሱናታ የሚባለውን ባህላዊ መሬ (ፖችላ) ሚስት የምንጩ መናፍስት በፈጸመችው ድርጊት በብቶላ እሷንም አሙር እንዳደረጓት በአፈ ታሪክ ይነገራል።

(ሶ/ር ገየዶ አይላዶ መስከረም 26 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁርታ አርባ ስድስት

የዱባሌ ቤተሰብና መናፍስት

በቅርብ አመታት ውስጥ ከዱባሌ ቤተሰብ መካከል አንዲት ሴት ከጭቃ የተሰራ እንስራ ወደ ሄምፖሬ ምንጭ በመወርወሯ የምንጩን መናፍስት አስቆጣች። በዚህም ምክንያት የምንጩ ውሀ ወደ ቀይነት ተቀየረ። ሀይለኛ ንፋስ በሚነፍስበት ወቅት ውሀው የተስተደመሩ መልክ በመያዙ የአካባቢው ማህበረሰብ ውሀውን መጠቀም በማቆም ምክር ስመቀበል ወደ ጠንቋይ ዘንድ በመሄድ ሁኔታውን አስረዱ። ጠንቋዩም የአካባቢውን ህዝብ «ጥቁር ሴት በግ መስዋዕት አረዱለትና እባክህ ከዚህ በፊት ላጠፋትና እኛም ላጠፋነው ጥፋት ሁሉ ይቅር በለን።» በሉ ብሎ የምንጩን ውሀ መናፍስት ይቅርታ እንዲጠይቁ መከራቸው። ማህበረሰቡም የታዘዘውን ጸሎት መፈጸም በመጀመሩ

የሚጠይቀው ነገር በሙሉ ይፈፀምለት ጀመር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የዱባሌ ቤተሰቦችም ያለእንከን መወለድ ጀመሩ።

(አቶ ኮራ ካራ ጥቅምት 02 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### 5. የኾንሶ ርኩስ መናፍስት

#### ቶርታ አርባ ሰባት

አሬታ

በኮንሶ ማኅበረሰብ ዘንድ የተለያዩ ስያሜዎች ያላቸው እርኩሳን መናፍስት እንደነበሩ በአፈ ታሪክ ይታመናል። በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚታወቀው እርኩስ መንፈስ መካከል «አሬታ» በመባል የሚታወቀው አንዱ ነው። ይህ ርኩስ መንፈስ በየውሀማና በየዱሩ የሚገኝ ሲሆን ሰዎች ለእርሻ፣ ለእንጨት ለቀማ፣ ከብቶች ለማሰማራትና ቀፎ ለመስቀል በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ እንደሚለክፋቸው በአፈ ታሪክ ይነገራል። መንፈሱም የሚፈልገውን ግለሰብ በመለከፍ ሊያቋርጥ በማይችል ነስር እንደሚገድል ይወራል። በዚህም የሚጠቁት አብዛኛዎቹ ወጣቶች እንደሆኑ ይነገራል። ይህ መንፈስ ቆንጆ የሆኑ ለጃገረዶችን በመለከፍ በማይታወቅ መንገድ ወሲባዊ ጥቃት የሚፈጽምና በመጨረሻም ይገድላቸዋል። ወንዶችንም በመለከፍ ግብረ ሰዶምን እንደሚፈጽምባቸውና ራሳቸውን እንዲያጠፉ የሚያደርግ መሆኑ ይታመናል።

ማኅበረሰቡም እንደዚህ አይነቶቹን ርኩስ መናፍስት እንደሚፈራ፣ ወደ በረሀ በሚሄድበት ጊዜም በእነዚህ መናፍስት አማካኝነት ክፉ ድርጊት እንዳይደርስበት መናፍስቱ የሚጠሉትን ነገሮች በመጠቀም እንደሚከላከል በአፈ ታሪክ ይነገራል። ለምሳሌ የአሬታ ርኩስ መንፈስ ውሻን ይጠላል ተብሎ ስለሚታመን ሰዎች ወደ ቦታው በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ውሻን እንደሚያስከትሉ ወይም ከውሻ ቆዳ የተሰራ ክታብ በአንገታቸው ያስራሉ። ከዚህም ሌላ ርኩስ መንፈሱ እንዳይለክፏቸው ፊታቸውንና ልብስ የማያርፍበትን የሰውነት ክፍሎች በጭቃና በጥላሸት እንደሚቀቡ ይነገራል።

(አቶ ኮራ ጋራ ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁርታ አርባ ስምንት

ኤላ

«ኤላ» የሚባል ምትሀታዊ ርኩስ መንፈስ እንዳለ ሲታመን መንፈሱ ሰዎችን በመልከፍ ለአእምሮ ህመም ወይም ለእብደት የሚዳርግ ነው። ይህ መንፈስ በውሀማ አካባቢዎችና በባህል በተከለከሉ ደናማ ቦታዎች እንዲሁም በረሀማ አካበቢ እንደሚገኝ ይወራል። ከእነዚህ ሌላ አያና የሚባል ርኩስ መንፈስ እንዳለ፣ መንፈሱም በሰዎች ላይ በማደር እሱን ካመለኩት ተለክፈውን ሰው እንደ ፈረስ በማድረግ እራሱንና ቤተሰቡን እንደሚያድን፣ ከክፉ አደጋ ሁሉ እንደሚጠብቅ ራሱ የሚናገር መንፈስ ነው። ይህ መንፈስ በተለይ ኦሮምኛና የኸንሰን ቋንቋ የሚናገርና መንፈሱ ያረፈባቸው ሰዎችም መንፈሱ ከለቀቃቸው በኋላ ምን እንደተናገሩ ሌላ ሰው ካልነገራቸው በስተቀር እንደማያውቁ ይነገራል።

(ፋኛ በቡድን ውይይት የተገኘ መስከረም 18 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቁርታ አርባ ዘጠኝ

አለባይቴታ

በሌት ጸታ የምትጠራና እንደሌት ድምጽ ያላት «አለባይቴታ» የምትባል መንፈስ ነበረች። ይህቺ መንፈስ ወደፊት የሚመጣውን መጥፎ ክስተት በሙሉ እየጮኸች ወይም እያለቀሰች ትተነብያለች። እኔ በህይወቴ ከአንድም አራት ጊዜ ያጋጠመኝ ነገር አለ። ጤነኛ የሆኑ ሰዎች አለባይቴታ ቀድማ አልቅሳላቸው በኋላ ሰዎቹ ሞተዋል።

ዱሮ በሚኒሊክ ጊዜ የሉልሰገድ ጦር ወደ ኮንሶ ገብቶ የዱካቶን መንደር ከማቃጠሉ በፊት ይህቺው አለባይቴታ ሌሊት እየዞረች «ወይኔ! ወይኔ! ይህቺ ውብ ቀበሌያችን ወዬውላት ተቃጠለች። ወይኔ! ወይኔ! ይህቺ ውብ ቀበሌያችን ወዬውላት ተቃጠለች።» እያለች ትጮህ ነበር። በኋላ በሉልሰገድ የሚመራው የሚኒሊክ ጦር መጥቶ እንደተባለው ዱካቶን አቃጠላት።

(አቶ ኮራ ጋሬ መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሀምሳ

እያና

በዱሮ ጊዜ በኮንሶ ርኩስ መንፈስ የለም ነበር፤ ርኩስ መንፈስ መምጣት የጀመረው በቅርብ ነው። እያና የሚባለው ርኩስ መንፈስ ነው። ሰዎችን በመለከፍ የሚያሰቃይ ሲሆን የመጣውም ከሩቅ ቦታ ነው። የሚናገረው ኦሮምኛ ቋንቋ ሲሆን በመንፈሱ የሚጠሩት ቦታዎችም ከኮንሶ ውጪ ያሉትን ነው።

(ኑላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት መስከረም 20 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሀምሳ አንድ

የሙሴሎ መንፈስ

ኾንሶ መሬሙሎ ውስጥ አንድ ሰው ዋሪ ውስጥ ተኝቶ እያንኮራፋ እያለ ሌሊት ላይ መንፈሶች እየጨፈሩ ወደ ዋሪው ውስጥ ገቡ ይባላሉ። ከእነሱ ውስጥ የልጃገረድ አለባበስ የለበሰች መንፈስ የተኛውን ሰው «አፉን ከፍቶ እኮ ነው የተኛው አፉ ውስጥ ሌው.ነው?» ትላለች አሉ። ሌሎቹ መንፈሶች «ተይ የሰውን ሰው ዝም ብለሽ አትውጊ። ዝም ብሎ ነው የተኛው።» ይሏታል። ሰውዬው ይህን በሰመመን ውስጥ ሆኖ ይሰማ ነበር። መንፈሷ እንደማለፍ ብላ ጣቷን አፉ ውስጥ ክትት ስታደርግ ይነክሳታል። መንፈሷም ጩኸቷን ትለቀዋለች። ይህን ጊዜ ሌሎች መንፈሶች «ተይ እያልንሽ አየነገርንሽ አይደለም?» ብለው እየጨፈሩ ይሄዳሉ። እሷም ተከትላ ትሄዳለች። ሌላ ጊዜ ይህን የሰማ አንድ የኾንሶ ሰው «ዝም ብላችሁ ነው፤ ያልሆነ ነገር ነው የምታወሩት።» ይላቸዋል። ሰዎቹም «ናና አንተም እቦታው ላይ ተኛና ታያለህ።» ይሉታል። «እሺ!» ብሎ ቦታው ላይ ሄዶ ይተኛል። ሌሊት ላይ መንፈሶቹ እየጨፈሩ ወደ «ዋሪው» ይገባሉ። እሱም መንፈሶቹን ይረጋግጣቸዋል፤ እየረጋገጧቸው ሄዶ ሄዶ መጨረሻ ላይ ሲደርስ ይወድቃል፤ እግሩ በጣም አብጦ በመጨረሻ ሞተ። እየተባለ ይነገራል።

(ኑላ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም.)

6. ኾንሶ ቦታዎች፣ አካባቢያዊ ስያሜዎችና ከነገሮች አመጣጥ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ታሪኮች

### ቁርታ ሀምሳ ሁለት

(የኒዮርክ አፈጣጠር) (ሀ)

ጋሰርጊዮ አካባቢ ወይም በአሁኑ አጠራሩ ኒዮርክ ተብሎ የሚጠራው ቦታ የአልሞጊ ቤተሰብ ታናሽ ሸሁታ የሚባለው ሰው ከቤቱ ተናዶ እቃ ይዞ ይወጣል። የወሰደው እቃ ቱማ (የእጅ አምባር) እና የአውራሪስ ቀንድ ነበር። እቃውን ይዞ ከቤቱ ወጥቶ ሲሄድ አሁን ኒዮርክ የሚባለው ቦታ ላይ ሲደርስ የእጅ አምባሩ ወደቀበት። ፈልጎ ፈለጎ ሲያጣው ተናዶ ጥሎት ሄደ። ካራቴ የሚባል ተራራ ላይ ደርሶ ወደ ኋላ ዞሮ ሲያይ ቱማው ሲያብረቀርቅ ያያል። ተመልሶ እንደገና ቢፈልገው ሊያገኘው አልቻለም። እንደገናም ጉዞውን ወደ ፊት በመቀጠል እዚያ ቦታ ሲደርስ እንደገና ዞሮ ቢመለከት ቱማው አሁንም ሲያብረቀርቅ ይመለከተዋል። አሁንም ተመልሶ ቢፈልገው ሊያገኘው አልቻለም። በጣም ተናዶ በያዘው የአውራሪስ ቀንድ መሬቱን መቶ «አንቺ መሬት ገደል ይውጣብሽ።» ብሎ ረግሞ ኩይሌ ወደሚባል ሰፈር ሲያመራ ከፊት ለፊቱ ወንዝ ያገኛል። ወንዙንም በበትሩ በመምታት አቋርጦ ሄደ። ከዚያ በኋላ ያ አካባቢ በውሀ ተበልቶ አሁን ያለውን መልክ ሊይዝ ቻለ። ይህ ግለሰብ ይህን ነገር በማድረጉ ሰው ተደንቆ የሄደበት አካባቢ ነገሶ ኖሬ ዘሩም እስከ አሁን ድረስ በዚያ አካባቢ ይገኛል።

(አቶ መምሩ ቀደራንቶ መስከረም 17 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቀርታ ሀምሳ ሶስት

(ለ)

ሊቦች ባህላዊ መሪው ሲሞት ለለቅሶና ለጭፈራ ብቻ የሚውለውን ከበሮ ሰርቀው ሲሄዱ አሁን ኒዮርክ በሚባለው ቦታ ሲደረሱ ይንጋባቸውና እዚህ ቦታ ከበሮውን ቀብረው ይሰወራሉ። የሊቦቹን ኮቴ እየተከተሉ የመጡ ሰዎች ቦታው ላይ ሲደርሱ ዱካው ይጠፋባቸዋል። በዚህን ጊዜ ባህላዊ መሪውም አብሮ ነበርና «አንቺ ከበሮ እዚህ ቦታ ካለሽ ውጪ!» ብሎ መሬቱን ሲመታ ከበሮዋ ወጣች። ከበሮዋ የወጣችበት ቦታም እንደዚሁ ጉድጓዶ ቀረ።

(ኑሳ ዝናቤኝ ወ/ዳዊት መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ቀርታ ሀምሳ አራት

(ሀ)

ሊቦች ባህላዊ መሪው ሲሞት ለለቅሶና ለጭፈራ ብቻ የሚውለውን ከበሮ ከባህላዊ መሪው ቤት ሰርቀው ይጠፋሉ። የአገሬው ሰውና ንጉሱ ፍለጋቸውን ይቀጥላሉ። የንጉሱ ፈረስ

ጋሰርን (ጊዮርጊስ) እየተባለ በሚጠራው ሰፍራ ላይ ሲደርስ አልሄድም ትልና ቦታውን በሀይል ረገጠችው። በዚህ ጊዜ ቦታው ጎደጎደ፤ ከጉድጓዱም ከበሮው ወጣ። ቦታው ግን እስካሁን ድረስ እንደጎደጎደ ቀረ።

(ካሳ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሀምሳ አምስት

የሽውራራነት አመጣጥ

በድሮ ጊዜ አንድ ሰው እየሰራ እየለፋ ነገር ግን ምንም ሊያልፍለት አልቻለም። በዚህን ጊዜ ሰውዬው «እንዲህ እየለፋሁ የማያልፍልኝ እግዚአብሄር ቢጠላኝ ነው። ሄጄ እገድለዋለሁ።» ይልና ጋሻና ጦር ይዞ ይሄዳል። እመንገድ ላይ እግዚአብሄር በሰው ተመስሎ ያገኘውና «አንተ ሰው ወዴት ትሄዳለህ?» ይለዋል። እሱም «እኔ እየለፋሁ እግዚአብሄር ምንም ሊያሳልፍልኝ ስላልቻለ ልገድለው መሄዴ ነው።» በማለት ይመልስለታል። እሱም «ለመሆን እግዚአብሄርን መግደል ይቻላል? ይቅርብህ።» ይለዋል። ሰውዬው ግን «እሞክራለሁ።» ይልና ወደፊት ይቀጥላል። አሁንም እግዚአብሄር ከፊቱ በሰው ተመስሎ ያገኘውና ይህንኑ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ሰውዬውም «እግዚአብሄርን ልገድል ነው።» በማለት አሁንም ይመልስና ወደፊት ይሄዳል። በዚህን ጊዜ አደገኛ ነጎድጓድ ከተሰማ በኋላ አሁንም እግዚአብሄር ይመጣና «አንተ ሰውዬ ምን አይነት አስተሳሰብ ያለህ ነህ? እኔን ነው የምትገድለው? አጠፋህ ነበር፤ ግን ሚስኪን ሰው ነህ። በል አሁን ወደ ቤትህ ሂድ። ለምልክቱ ግን አይንህ ሸውራራ ይሆናል።» አለው። ሸውራራነት በኩንስ የመጣው ከዚያ በኋላ ነው።

(አቶ ኮሩ ጋሪ ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሀምሳ ስድስት

የእለት ዋዩ ማጠርና የሴቶች የወር አባባ ማየት መጀመር

ሰማይና ምድር ቅርብ ለቅርብ ነበሩ። ሰማይም በጣም ዝቅ ብሎ እስከ እጽዋት አናት ድረስ ይደርስ ነበር። የእለት (ሽፈራ) ዋዩ ቁመቱ ከሌሎች ዛፎች የበለጠ በጣም ረጅም ነበር። ዋዩ ላይ ወጥቶ ለምግብነት የእለትን ቅጠል የመልቀም ግዴታ የሴቶች ብቻ ነበር። ወንዶች ስራቸው የተሰራውን እለት መብላት ብቻ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሴትዮ ለቤተሰብ እራት ለመስራት የእለት መልቀሚያ «ሸንቃራ» (የብረት መንጠቆ) ይዛ የእለት ዋዩ ላይ ትወጣለች። እለትውን በብረት መንጠቆው ስትለቅም

ሰማይ ቅርብ ነበርና በመንጠቆው ስለት አቆሰለች። በዚህ ጊዜ ሰማይ መድማት ጀመሮ እንደ ዝናብ ይወርድ ነበር፤ የሚደማው ግን በሷ ላይ ብቻ ነበር። በልብስ ውስጥ ብትደበቅም ልብሶቹን አልፎ ደሙ በሷ ላይ ይወርድ ጀመር። ህዝቡ ሁኔታውን አይቶ መፍትሄ ለመፈለግ ይነጋገርና መፍትሄው እግዚአብሄርን መለመን ብቻ መሆኑን ይስማሙና ሽማግሌዎች ተመርጠው እግዚአብሄርን ለማነጋገር ይሄዳሉ። በኋላም «እግዚአብሄር ሆይ! ይህቺ ሴት አጥፍታለችና ይቅር በላትና የደም ዝናብህን በሷ ላይ ማውረድህ ቢቀር፣ ቅጣትም ከሆነ እንቀበላለን። የኛ ውሳኔ ዛፍ ላይ መውጣቱ የሴቶች ብቻ ሳይሆን የወንዶችም እንዲሆን፣ አንተም ሰማይ ቤትህ ነውና ሰው በመንጠቆው እንዳይነካብህ በጣም ከፍ እንዲል ብታደርግ፣ ሌላው ይህ በጣም ከፍ ያለው የአለኮ ዛፍ ዝቅ እንዲል ወስነናል። ሌላው ሴቶች ከዚህ በፊት እንደ ሌሎች እንስሳ የነበረው የወር አበባ ቀርቶ በየወሩ እንዲሆንና እሷም እንድትታገስ እናደርጋለንና በዚህ እሺ ብትለን?» ብለው ይማፀናሉ። እግዚአብሄርም የአለኮ ዛፍ ዝቅ እንዲል፣ አለኮ መልቀም የወንዶችም ተግባር ሆኖ ዛፍ ላይ ወጥተው መልቀም እንዲጀምሩ፣ ሴቶችም በየወሩ የወር አበባ እንዲያዩ በመስማሙ በሴትየዋ ላይ ይዘንብ የነበረው ደም ቆመ። ይባላል።

(አቶ ኮራ ጋሪ ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርታ ሆምሳ ሰባት

ጃላ ሼኬራ

በድሮ ጊዜ አንድ እርጉዝ ሴት በኾንሶ ምድር ነበረች ። ይህች ሴት ልጇ በሆዷ ውስጥ እንዳለ «እናቴ እወለዳለሁ!» ሲል ሰማች። እናትየውም ተገርማ «ልጄ እንዴት ትወለዳለህ? እኔ እንደሁ ጎመን አልቀቀልኩም።» አለችው። ልጁም ጎመኑን ቀቅላ እስክትጨርስ ጠብቆ «እወለዳለሁ!» እያለ መጨትጨቱን ገፋበት። እናትየዋ ግን እቤት ለመጡት እንግዶች ከርኩፋ ቀቅላ እስክታበላ ድረስ እንዲታገሳት ለመነችው። በኋላም እንግዶቹን አስተናግዳ ከሸኘቻቸው በኋላ «ልጄ አሁን መወለድ ትችላለህ።» ስትል ፈቀደችለት። ልጁም እንደተወለደ «እማዬ እኔ አባትና እናቴ የሚያውቁትን በሙሉ አውቃለሁ።» አላት። እናትየውም «ልጄ እናትና አባትህ የሚያውቁትን እንዴት ታውቃለህ?» ስትል ጠየቀችው። እሱም «አባቴ ከእግዚአብሄር በላይ አያውቅም፤ እናቴም ያው እንደዚያው።» በማለት መለሰላት። እናቱም ስሙን «ጃላ ሼኬራ» ብላ ጠራችው። ይህ ማለት በናቱ ሆድ ውስጥ እንዳለ ሁሉን የሚያውቅና አፉን የፈታ ማለት ነው።

(እቶ መምሩ ቀራደንቶ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### 7. ሁለተኛ ሚስትን የሚከለክሉ ታሪኮች

#### ቆሮታ ሀምሳ ስምንት

ካዳና ሁለተኛ ሚስቱ

የካዳ ቤተሰብ ኽንሶ ኩተሌ በሚባለው አካባቢ ነበር የሚኖረው። ቦታውን ለቆ አሁን ወዳለበት ፋራህ ተራራ እንዲመጣ ያደረገው በሁለተኛ ሚስት ምክንያት ነው። ባህላዊ መሪው በሚስቱ ከሚዘጋጀው ምግብ በስተቀር በሌሎች የሚዘጋጀውን ምግብ አይቀምስም። በዚህን ጊዜ ዋንኛ ሚስቱ ለባህላዊ መሪው በቅል «ጨ.ቃ» ትሞላለትና ትሄዳለች፤ ባህላዊ መሪውም የአካባቢው ሰው ቤት ሲያሰራ ይቆይና መጥቶ ጨ.ቃውን ይጠጣል። ሁለተኛ ሚስትም «እኔ የምሰራውን ለምን አይመገብም?» ትልና ቅሉን «በጨ.ቃ» ትሞላለች። ዋና ሚስት ለምሳው ቅሉን ልትሞላ ስትል እንደተሞላ በማየቷ «እሊጠጣውም ማለት ነው።» በማለት ትመለሳለች። ባህላዊ መሪው ቆይቶ «ጨ.ቃውን» ለመጠጣት ቅሉን ሊያነሳ ሲል ቅሉ ወደ ኋላ ይሸሻል። እጁን ሲሰበስብ ደግሞ ቅሉ ወደ እሱ ይመለሳል። መልሶ ሊጨብጠው ሲል ይሸሻል። ደጋግሞ ሞክሮ ሳይችል ሲቀር ቤቱን የሚያድሱትን ሰዎች ይጠራና ሁኔታውን ይነገራቸውና ቅሉን ለመያዝ እጁን ሲዘረጋ ቅሉ ይሸሻል፤ እጁን ሲሰበስብ ቅሉ ወደ ቦታው ይመለሳል። በዚህን ጊዜ ሰዎቹ እንደምንም ብለው ከበው ቅሉን ይይዙና በውስጡ ምን እንዳለ በገበቴ ላይ «ጨ.ቃውን» ይገለብጣሉ። በዚህን ጊዜ በቅሉ ስር የገብስ ገለባ ይታያል። ሁለቱንም ሚስቶች ይጠሩና ምን እንዳደረጉ ይጠይቃሉ። የመጀመሪያዋ ሚስት «ጠዋት በቅሉ ውስጥ <ጨ.ቃ> የጨመርኩት እኔ ነኝ። ለምሳው ለመጨመር ስመጣ ቅሉ እንደተሞላ ነው። <ጨ.ቃው> ምንም ያልተጠጣ ከሆነ ተጠያቂ እኔ ነኝ።» ትላለች። ሁለተኛዋ ሚስት ስትጠየቅ «እኔ <ጨ.ቃ> የምጨምረው ዛሬ ነው? መቼ ነው ለመሆኑ? እኔ ምንም ነገር አላየሁም።» ትላለች።

በዚህን ጊዜ ለቤት ክዳን የሚሰሩትን ሰዎች በክዳኑ ውስጥ ሆነው ስራቸውን እንዲያከናውኑና ስራው እስኪያልቅ ድረስ የሚያስፈልጋቸውን ምግብ ውስጥ በማድረግ ከደኑባቸው። ሰዎቹም «ስራችንን ስንጨርስ እንዴት እንወጣለን?» በማለት ሲጠይቁ «ስትጨረሱ እንዲህ አድርገን እናወጣችኋለን።» በማለት መልሰው የቤቱን ክዳን በላያቸው ላይ ደፍተው የካዳ ቤተሰብ ቦታውን ትተው አሁን ወዳሉበት ቦታ ሄደው ሰፈሩ።

(ካሳ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት መስከረም 20 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርጥ ሀምሳ ዘጠኝ

የሁለተኛ ሚስት መዘዝ

በሁለተኛ ሚስት ምክንያት ትልቅ መቅሰፍት የደረሰባቸው በርካታ ሰዎች ያሉ ቢሆንም ስም መጥቀስ ተገቢ አይሆንም። ነገር ግን ከእኛ አቻ የሆነ ሰው ስለሆነ ሊጠልፈኝ ስለማይችል አንድ ታሪክ ልንገርህ አንድ ሰው ሁለት ሚስት ያገባል። ከሁለተኛው ሚስት የሚወለደው ልጅ ለሚታ ይባላል። የመጀመሪያዋ ታላቅ ሚስት ከሁለተኛ ሚስት የሚወለደውን ልጅ ለመደች። በዚህን ጊዜ ያ ወንድ ልጅ ሞተ። ሊሎቹ ሴቶች ናቸው፤ ሁሉም አግብተው ሄዱ፤ ቤቱ ወናቀረ በመጨረሻም በድህነት መኖር ጀመሩ።

(ኩሲያ በየነ መስከረም 18 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርጥ ስድሳ

ከጋብቻ ውጪ ልጅ መውለድ

በዱሮ ጊዜ ነው አሉ አንዲት የኙንሶ ልጅ ከጋብቻ ውጪ ታረግዛለች። ከዚያ በኋላ በአካባቢው የተዘራው እህል ሙሉ በሙሉ በቁጫጭ ተሞላ፤ ሰብሉም ጠወለገ፤ መኖሪያ አካባቢም በቁንጫጭ ተወረረ። ከዚያ በኋላ ከጋብቻ ወጪ የምታረግዝ ልጃገረድ በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ አትወልድም። የምትወልደው ከመኖሪያ ቤቷ አካባቢ በመራቅ ነው።

(ከዱራይቴ በቡድን ውይይት የተገኘ መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## 8. ከጦርነት እና ከጀግንነት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ የኙንሶ ታሪኮች

### ቁርጥ ስድሳ አንድ

ከሚኒሊክ ጦር ጋር የተደረገ

በአፄ ሚኒሊክ ዘመን የኙንሶ ማህበረሰብ ራሱን በራሱ በባህላዊ መንገድ ያስተዳድር ነበር። በኋላ የሚኒሊክ ጦር የኙንሶን ህዝብ ለማዕከላዊ መንግስት ለማስገበር በፈታውራሪ ሉልሰገድ የሚመራ ጦር በቡርጂ ወረዳ በኩል ወደ ኮንሶ ይገባል። በዶካቶ ቀበሌ የሚገኘው የኮንሶ ማህበረሰብ ወደ ጦርነቱ ላለመግባት አንድ በግ የባንዲራ ቀለም ያለው ልብስ በማልበስ ወደ ሉልሰገር ጦር ይልካል። በጃርሶ ቀበሌ የሚገኘው የኙንሶ

ማህበረሰብ ደግሞ «እኛ ጀግኖች ነን፤ ለምን እንደ ሰነፍ ህዝብ በባህላዊ መንገድ እርቅ ይላካል?» በሚል ወደ ጦርነቱ ለመግባት ተዘጋጁ። ከዚያም ኩሲያ ሳሊቶ የሚባል በጃርሶ የሚገኝ አንድ ሰው ህዝቡን የሉልሰገድ ጦር ወደ መጣበት ጉማይዴ አካባቢ በመውሰድ እሱ ከፊት ህዝቡን ደግሞ ከኋላው አድርጎ ጭንቅላታቸውን ወደ መሬት፣ እግራቸውን ወደ ላይ በማድረግ ለጠላት ምልክት ያሳያሉ። ጦሩም አዲስ አይነት የውጊያ ስልት መስሎት በመፍራት ወደ ዶራሼና ሌሎች አካባቢዎች በመሄድ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ። ህዝቡም በዚህ ስልቱ ኩሲያ ሳሊቶን በወቀቱ በቅኔ ያወድሱትና ያከብሩት ነበር።

በኋላም የፊተኛው የሉልሰገድ ጦር ወደ ዶራሼ አካባቢ ሲያመራ ቀሪው ጦር ተጠናክሮ ወደ ኮንሶ ጃርሶ ቀበሌ በመምጣት ህዝቡን አጠቁት። የጃርሶ ቀበሌ ህዝብ ቢጎዳም ከፍተኛ ትንቅንቅ በማድረጉ የተጎዳ ተጎድቶ ጦሩ ከአካባቢው ያባርራል። የሉልሰገድ ጦርም ወደ ዱካቶ ቀበሌ ያመራል። የዱካቶ ቀበሌ ህዝብም የጦሩን አመጣጥ በማየት በየጎጆው ተሸሽጎ ጦሩን ለመዉጋት ስልት ይቀይሳል። የጎጆውም አሰራር በዙሪያው ዝቅ ያሉ በሮች ያለት ነበር። የዱካቶ ህዝብም በየበሩ ትይዩ ጦር ይዞ ከላይ በቤቱ ጣራና ግድግዳ ላይ ተደብቆ ጦሩን ይጠብቅ ነበር። ውጭ ምንም ሰው ያላገኘው የሉልሰገድ ጦርም በየቤቱ የሚገኘውን የዱካቱ ህዝብ ለመውጋትና ለመማረክ ከነታጠቀው ዘመናዊ መሳሪያ በየጎጆዎቹ በሮች ሲገባ አድፍጦ የነበረው በዱካቶ አካባቢ የሚገኘው የኮንሶ ማህበረሰብ ጦሩን ከላይ ሆኖ በጦሩ እየወጋ ይገድለው ጀመር። ከውጭ የሚገኘው የሉልሰገድ ጦር ከጎጆው የሚወጣ አንድም የራሱን የጦር አባል ሲያጣና ይብሱንም የራሱን የጦር አባል ደም ከጎጆዎቹ እንደጎርፍ ሲወርድ ይመለከታል። በዚህን ጊዜ ይህ አይነቱ የውጊያ ስልት እንደማያዋጣ የተረዳውና በወገኖቹ ማለቅ በጣም የተናደደው የሉልሰገድ ጦር የዱካቶን ህዝብ ለመፍጀት በማሰብ በየጎጆዎቹ ላይ እሳት ለቀቀባቸው። ህዝቡም ከየጎጆው በመውጣት ዙሪያውን ከከበበው ጦር ጋር መፋለም ጀመረ። በዚህም የዱካቶ ቀበሌ በእሳት ብትጠፋም ያለቀው አልቆ የሉልሰገድ ጦርን እንዲዳከምና ከአካባቢው እንዲለቅ አድርጓል።

(አቶ ጊሊዶ ባደና መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቆሮታ ስድሳ ሁለት

የውጊያ ስልት

በዱሮ ጊዜ በተለይ የሚኒሊክ ጦር ወደ ኾንሶ በሚገባበት ወቅት የኮንሶ ህዝብ ከጋሻና ጦር በስተቀር ሌላ የጦር መሳሪያ አያውቅም ነበር። በእንፃሩ ደግሞ የሉልሰገድ ጦር ደግሞ መሳሪያ የታጠቀ በመሆኑ በመሳሪያው ተኩሶ ኮንሶዎችን ሲገድል ኾንሶዎች ድምፅ በመስማቱ ብቻ ሰው እንዴት እንደሚሞትና እንደሚወድቅ አያውቁም ነበር። ከዚያ በማየት ኮንሶዎች በበኩላቸው ከጋሻና ጦር ውጪ አመድ በቅል በመሙላት ከፍተኛ ድምጽ እንዲያሰማና አመዱን በማቡነን እይታ እንዲከልል በማድረግ የውጊያ ስልት ቀይሰው ነበር። ይሁን እንጂ ስልቱ የማያዋጣ ሆኖ በማግኘታቸው በጋሻና ጦር እንዲሁም በድንጋይ እያሳደዱ በመውጋር ተዋግተዋል።

(አቶ ጊሌዶ ባደና መስከረም 4 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቆሮታ ስድሳ ሶስት

አደን (1)

በኾንሶ ብሄረሰብ ሰው ሰውን ገድሎ ጀግና ሊባል አይችልም። ጀግና የሚባለው አንበሳና ሌሎች ትልልቅ እንስሳትን ሲገድል ብቻ ነው። እንዚህምን ትልልቅ እንስሳ የሚገድለው የኾንሶ ህዝብ ከሚተዳደርበት የእርሻ ስራ ባሻገር በበረሀ ከብቶችን ጭምር የሚያረባ በመሆኑ አንበሳና ነብር ከብቶቹን እየበላ ስለሚያስቸግሩት ነው።

(ከፋሻ በቡድን ውይይት የተገኘ መስከረም 17 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ቆሮታ ስድሳ አራት

አደን (2)

ትልልቅ አውሬዎችን የገደሉ በርካታ የኾንሶ ሰዎች በመሆናቸው ብዙዎቹን ለማስታወስ አይቻልም። ነገር ግን አላንቶ የሚባል የኾንሶ ጀግና አንበሳን በጦርና በጋሻ ገድሎ በመንደር ውስጥ በሚገኘው ሞራ አካባቢ (መሰብሰቢያ ስፍራ) ከጓደኞቹ ጋር ሲፎክሩና ሲሸልሉ አይቶናል። በኾንሶ ብሄረሰብ አንድ ሰው ጀግና የሚባለው ትልልቅ የዱር እንስሳትን በመግደሉ ብቻ ሳይሆን በመጀመሪያ አንበሳውን በጦር ወግቶ ያቆሰለም ጀግና ይባላል።

(ከፋሻ በቡድን ውይይት የተገኘ መስከረም 17 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርጥ ስድሳ አምስት

ጀግና (1)

ኙንሰዎች በመሰረቱ ሰው የመግደል ባህል የላቸውም ሆኖም በድንበር አካባቢ ድንበር ጥሶ ለጥቃት የሚመጣ በሚያጋጥምበት ጊዜ እርስ በርስም ሆነ ከሌሎች አጎራባቾች ጋር ይዋጋል። በውጊያው ላይም ከኋላው የሚወጋ ካለ ሲሸሽ ነው የተወጋው በማለት ፈሪ ይባላል።

(ዶ/ር ገዋዶ እይላዶ መስከረም 26 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርጥ ስድሳ ስድስት

ጀግና (2)

አንድ ቀን በዮ ፈርታ የሚባል በጣም ጨካኝ የሆነ የኙንሶ ሰው ነበረ። በዮ አንበሳ ካልገደልኩ ብሎ ጫካ ለጫካ ሄዶ አንበሳ ሲፈልግ ውሎ በመጨረሻም አንበሳውን አግኝቶ በእጁ ይዞ ተናንቀ፤ ነገር ግን በዚህን ጊዜ አንበሳው ተወርውሮ ይዞ ሰውዬውን ገደለው። ይሁን እንጂ በዮ ፈርዳ ቢሞትም ጀግና ነው። ጀግና በመሆኑ «ዋካ» ተሰርቶለታል።

(አቶ ገለሲዋ ዱንቴ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርጥ ስድሳ ሰባት

ጀግና (3)

በኙንሶ ሀሉኬ የሚባለው የጉዬታ ልጅ አውራሪስ ገደለ። በዚህም ምክንያት የጉዬታ ልጅ ሀሉኬ የገደለውን አውራሪስ የአደን ሰዎች በሙሉ በሁለት እጃቸው በአየር ላይ ተሸክመውት አርደው ወደ እኛ ሞራ ይዘውት መጡ። እየተባለ እስካሁን ድረስ በልጃገረዶች ይዘፈናል።

(አቶ ኮራ ካራ ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርጥ ስድሳ ስምንት

ልጃገረዶና የኤላ መንፈስ

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ህዝባዊ በአል በታችኛው ዱካቶ ይከበር ነበር። ህዝቡ ተሰብስቦ ባህላዊ ጭፈራውን ሲጨፍር ግማሹ ሲጨፍር ግማሹ ደግሞ አካባቢውን ይቃኝ ነበር። ከዚያ ውስጥ የዋዮ ቤተሰብ ሴት ልጅ ባህላዊ ጭፈራውን ስትመለከት አንድ ወጣት በጥሩ ሁኔታ ሲጨፍር ተመለከተችና በእጨፋፈሩ ተማረከች። ከዚያም ሊታገባው ወሰነች። ያ ሰው ለሌሎች ሰዎች የማይታይና እውነተኛ ሰው ያልሆነ የኤላ መንፈስ ነበር።

ጭፈራው ሲያልቅ ልጅቷ ልጁ ጋ ሄዳ «በጣም ወድጄሀለሁ፤ እባክህ ውሰድና ሚስትህ አድርገኝ።» አለችው። እሱም ተስማምቶ ወደቤቱ አብረው ሄዱ። ነገር ግን የልጁ ቤት የውሀ ምንጭ ውስጥ ሆኖ አገኘችው። ልጁ ለልጅቷ ምቾት ለመፍጠር ሲል «ለሚትሳችን የሚሆን ምን አይነት ምግብ ብንበላ ይሻላል?» በማለት ጠየቃት። እሷም «በሚትሳችን ጊዜማ ቂቤ ብንበላ ጥሩ ነው።» በማለት መለሰችለት። ስውዬውም ትኩስ ጭቃ በማምጣት እንድትበላ ጠየቃት። እሷ ግን እንደማትበላ ነገረችው። ሰውዬው የምትበላው ምን አይነት ነገር ይዞላት እንደሚመጣ ጠየቃት። እሷም «የጠበደለች ፍየል ይዘኽልኝ ከመጣህ እሷን እበላለሁ» በማለት መለሰችለት። ከዚያም ይሄድና ትልቅ ኤሊ ይዞ መጥቶ እንድትበላ ይጠይቃታል። እሷም የቀረበላት ፍየል ባለመሆኑ እንደማትበላው ትመልስለታለች። በመጨረሻም «በጣም ስለደከመኝ ማረፍ እፈልጋለሁና መኝታውን አሳየኝ።» አለችው። እሱም በድንጋይና በጭቃው ላይ እንድታርፍ ነገራት። ነገር ግን እሷ በዚያ ላይ ለማረፍ እንደማትፈልግ ነገረችው።

በንጋታው ስለ ሁሉም ነገር ለማንም ምንም እንዳትናገር አስጠንቅቆ ወደ ቤቷ ላካት። ይኸው መንፈስ ወደ ልጅቷ ቤት በሚወስደው መንገድ ከፊት ለፊቷ መንገደኛ መስሎ «ከየት ነው የምትመጪው?» በማለት ጠየቃት። እሷም «ቂቤ፤ ማርና የሰባ ፍየል ከሚበላበት አገር ነው የምመጣው» በማለት መለሰችለት። ከትንሽ መንገድ ጉዞ በኋላም ተመልሶ በመምጣት ከየት እንደምትመጣ ጠየቃት። እሷም መልሳ ያንኑ መልስ መለሰችለት። በመጨረሻም ወደቤቷ ልትቃረብ አካባቢ መንፈሱ ራሱን ለውጦ ልክ ጓደኛዋን መስሎ «ውይ የኔ ጓደኛ ለመሆኑ ከየት ነው የምትመጪው?» በማለት ጠየቃት። እሷም እውነትም ጓዋደኛዋ መስላት ሀዘን ተሰምቷት ያየችውን ሁሉ ዘክዝካ ነገረቻት።

በኋላም መንፈሱ መልኩን ወደራሱ ለውጦ «ያየሽውን ሁሉ ለማንም ሰው እንዳትናገሪ ብዬ አስጠንቅቄሽ አልነበር?!» አለና በጭካኔ ገደላት። የሷም ፍቅር መጨረሻው ሆነ።

(አቶ ኩራ ካራ ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## 9. ግብረ ገብነትን የሚሰብኩ የኾንሶ ታሪኮች

### ቁርጥራጭ ስድሳ ዘጠኝ

የኾንሶ የሊቦች ታሪክ

ኮንሶዎች በመሰረቱ ማንኛውም እምነት አልነበራቸውም። የሚያምኑት «ሰው ከሞተ በኋላ መንፈሱ ይኖራል።» በሚል ነው። ይህ መንፈስ «ከራያ» በዱሮ አካባቢ ደግሞ «ካራዋ» ይባላል። መንፈሱ በህዝብ ዘንድም ሆነ በአስተዳደሩ ላይ ስህተት የሚፈጽም ከሆነ «እርምጃ ይወስዳል።» ስለሚባል ይፈራል።

ከዚህ ቀደም ኮንሶ ውስጥ ዱሮ በሚባል አካባቢ የተወሰኑ ሰዎች ስርቆት በመፈፀም የሰውን አውራ ፍየሎች እየሰረቁ በመቃብር ውስጥ እያረዱ ይበሉና ይመለሱ ነበር። ሊቦቹ መቃብር ቦታ ውስጥ ፍየሎችን ሰርቀው እያረዱ የሚበሉት ሰዎች «በመቃብር ውስጥ እሳት የሚያነዱት መናፍስ ይሆናሉ። ብለው ያስባሉ።» በሚል ነበር። በኋላ ህዝቡ አወቀባቸው። አንድ ቀን ፍየል ሰርቀው እሳት ሲያነዱ ሰዎችን መርጠው በአራቱም አቅጣጫ አስቀመጡ።

አንድ ሰው ከሩቅ ሆኖ «አንተ እነዚህ እነማናቸው በሰው መካነ መቃብር ውስጥ ሆነው እሳት የሚያነዱ? ከሙታን መናፍስት ውስጥ አንዱ ጨካን መጥቶ አንዱን በጥፊ አይወለውለውም እንዴ?!» ብሎ ድምፅ ሲያሰማ ሌሎች የተደበቁ ሰዎች ደግሞ በየተራ «አዎ በቅርቡ ነው ያለነው፤ በቅርቡ ነው ያለነው፤ እረሳንም! እረሳንም! እረሳንም!» ሲሉ እነዚያ ሰዎች በርግገው እየወደቁ እየተነሱ ሸሹ። በመጨረሻም በተቅማጥ አለቁ ይባላል።

(አቶ ኮራ ካራ መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)

### ቁርጥራጭ ሰባ

ሊቦችና መንፈስ (1)

ዱሮ በሚባል አካባቢ የሚገኙ ኾንሶዎች ከዷራሺ በሬ ይሰርቃሉ። በሬውን በረሀ ላይ አርደው ይበላሉ። ከዷራሺ መንፈስ ትመጣና «ሰዎች በሬ ጠፍቷልና ፈልጉ እያለች በየመንደሩ እየዞረች ትጮህ ነበር።» በኋላ በሬውን የሰረቁት ብቻ ሳይሆኑ ስጋውን የበሉ ሰዎች በሙሉ አልቀዋል። ይባላል።

(ዶ/ር ገዋዶ እይላዶ መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም.)

ሲሉ እነዚያ ሰዎች በርግገው እየወደቁ እየተነሱ ሸሹ። በመጨረሻም በተቅማጥ አለቁ ይባላል።

(አቶ ኮራ ካራ መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## አባሪ ሁለት፡- የመረጃ አቀባዮች

### 2.1 ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች

| ተራ ቁጥር | የመረጃ አቀባዩ ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የመኖሪያ አድራሻ | ስራ ( መተዳደሪያ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ኮራ ጋራ | 64 | ወ | ዱካቶ | ጡረታ እና መጽሃፍትን በመጻፍ እና በማሳተም። |
| 2 | ካሳ ገዛኸኝ ወ/ዳዊት | 44 | ወ | ፋራህ ተራራ (ካሳ ጫካ) | የኬርቲታ ጎሳ ባህላዊ መሪ |
| 3 | ዶ/ር ገዋዶ አይላዶ | 40 | ወ | ካራት ከተማ | በኢፌዴሪ የህ/ተ/ም/ቤት የብሄረሰቡ ተወካይ |
| 4 | አቶ መምሩ ቆይራንቶ | 60 | ወ | ፋሻ | አርሶ አደር |
| 5 | አቶ ጊሊዶ ባደና | 56 | ወ | ዱራይቴ | አርሶ አደር |
| 6 | አቶ ቱሬ ካምብሮ | 70 | ወ | ዱራይቴ | አርሶ አደር |
| 7 | አቶ ጉዲሺ ኩታማ | 74 | ወ | ፋሻ | ጡረተኛ |
| 8 | አቶ ካሌቱማ ተገኘ | 60 | ወ | ፋሻ (ቡርጂ) | አርሶ አደር |

### 2.2. ቁልፍ ያልሆኑ የመረጃ አቀባዮች

| ተራ ቁጥር | የመረጃ አቀባዩ ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የመኖሪያ አድራሻ | ስራ ( መተዳደሪያ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ኩዪ አርኻይታ | 48 | ሴ | ፋሻ | ነጋዴ |
| 2. | አቶ ካቱሳ ካታሌ | 74 | ወ | ኮልሜ | ጡረተኛ |
| 3. | አቶ ቁታ ደሲታ | 66 | ወ | ኮልሜ | አርሶ አደር |
| 4. | አቶ ዲዶ ገለቦ | 74 | ወ | ዱራይቴ | ግብርና እና ጡረታ |
| 5. | አቶ ኩሲያ በየነ | 72 | ወ | ፋሻ(ተራዳ) | ግብርና |
| 6. | አቶ ገለሲዋ ዱኖቴ | 65 | ወ | ዱካቱ | ንግድና ግብርና |

## 2.3. በፋሻና  በዱራይቴ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች

| ተራ ቁጥር | የመረጃ አቀባዩ ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የመኖሪያ አድራሻ | ስራ ( መተዳደሪያ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ገልሲሞ ዱኖቴ | 65 | ወ | ዱካቴ | ንግድና ግብርና |
| 2. | አቶ ጉዲሺ ኩታማ | 74 | ወ | ፋሻ | ጡረተኛ |
| 3. | አቶ ጊሊዶ ባደና | 56 | ወ | ዱራይቴ | አርሶ አደር |
| 4. | አቶ ዲዶ ገለቦ | 74 | ወ | ዱራይቴ | ግብርና እና ጡረታ |
| 5. | አቶ ኩሲያ በየነ | 72 | ወ | ፋሻ(ተራዳ) | ግብርና |
| 6. | ዶ/ር ገዋዶ አይላዶ | 40 | ወ | ካራት ከተማ | የህዝበ ተወካይ |
| 7. | አቶ ካሌቴማ ተገኘ | 60 | ወ | ፋሻ | አርሶ አደር |
| 8. | አቶ ቱሬ ካምብሮ | 70 | ወ | ዱራይቴ | አርሶ አደር |
| 9. | አቶ ቴታ ደሲታ | 66 | ወ | ኩልሜ | ጡረተኛ |

### 2.3.1. የፋሻ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች

| ተራ ቁጥር | የመረጃ አቀባዩ ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የመኖሪያ አድራሻ | ስራ ( መተዳደሪያ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ካሌቴማ ተገኘ | 60 | ወ | ፋሻ | አርሶ አደር |
| 2. | አቶ ጉዲሺ ኩታማ | 74 | ወ | ፋሻ | ጡረተኛ |
| 3. | አቶ ኩሲያ በየነ | 72 | ወ | ፋሻ(ተራዳ) | አርሶ አደር |
| 4. | አቶ መምሩ ቆይራንቶ | 60 | ወ | ፋሻ | አርሶ አደር |

### 2.3.2. የዱራይቴ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች

| ተራ ቁጥር | የመረጃ አቀባዩ ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የመኖሪያ አድራሻ | ስራ ( መተዳደሪያ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ቱሬ ካምብሮ | 70 | ወ | ዱራይቴ | አርሶ አደር |
| 2. | አቶ ቱታ ደስታ | 66 | ወ | ኮልሜ | ጡረተኛ |
| 3. | አቶ ጊሊዶ ባደና | 56 | ወ | ዱራይቴ | አርሶ አደር |
| 4. | አቶ ዲዶ ገለቦ | 74 | ወ | ዱራይቴ | ግብርና እና ጡረታ |
| 5. | ዶ/ር ገዋዶ አይላዶ | 40 | ወ | ካራት ከተማ | የህዝበ ተወካይ |



አቶ ጊሌዴ ባደና በዱራይቱ መረጃ ሲያቀብሉ፣ ዶ/ር ገዋዶ አይላዶ ሲያስተረጉሙ (የዱራይቱ የቀበሌ ጽ/ቤት) ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ዲዶ ገለቦ እና ቁሬ ካምብሮ ናቸው።



ኾንሶዎች በአካባቢያቸው በፋሺስት እቅውና በማግኘታቸው

ለመታወቂያነት የተሰራ ሀውልት



ጋሰርጊዮ (ኒዮርክ)



የኬርቲታ ጎሳ ባህላዊ መሪ የማዕረግ ልብሳቸውን ለብሰው



ለኾውላዎች የሚለበስ የኾንሶ ባህላዊ ልብስ



የኾንሶ መቃብር (ዋካ)

# አባሪ ሶስት

## 3. ከመስክ የተወሰዱ የፎቶግራፍ ስብስቦች



ካላ ገዛኸኝ ወ/ሳዊት በትረካ ላይ

(በእንግዳ ማረፊያ ጎጆአቸው ውስጥ)



አቶ መምሩ ቀይራንቶ በፋሻ መረጃዎችን ሲያቀብሉ



አቶ ኦርጋሌ ሙወሌ በፋሻ የቡድን ውይይት መረጃዎችን ሲያስተረጉሙ

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ኃ/ሚካኤል አረጋኸኝ

ፊርማ